# የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ

◦ ፪ኛ መጽሐፍ ◦



ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

ያለ አሳታሚው ፈቃድ በሙሉም በከፊልም ማሳተም ክልክል ነው ።
የመንበረ ጸባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።
የፖ. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፲፱፻፷፬ ዓ.ም.

በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍትን አክብራ የተቀበለችበት ጊዜ በጣም ረዘም ያለ ነው ፤ ይኸውም ከክርስትና በፊትና ከክርስትና በኋላ እንደሆነ ሊቃውንቱ ይተርካሉ ። የመጻሕፍትም ኃይል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያናዊ እምነቷን ጠብቃ ለመኖር ረድቷታል ። የክርስቲያንም ደሴት ሊያሰኛት የቻለው ቅሉ ፤ ሕዝባችን በቅዱሳት መጻሕፍት መሪነት ትልቁም ትንሹም በአንድ ክርስቲያናዊ መንፈስ ተሳሥሮ ከመኖሩ ጋር ቅዱሳት መጻሕፍትን አተኩሮ በመመልከቱና ክርስቲያናዊ ተግባሩን በመፈጸሙ ነው ። አባቶቻችን ነገሥታት ስለቅዱሳት መጻሕፍት አጠባበቅ ለሕዝቡም እንዴት እንደሚዳረስ በጠቅላላም ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት አጠባበቅ በብዛት ሠርተዋል ፤ ለትውልድም እንዲተላለፍ ለማድረጋቸው ሕያው ታሪካቸው ይመሰክራል ።

እንደዛሬው ሁሉ የማተሚያ መኪና ባይኖርም እንኳ ቅዱሳት መጻሕፍትና የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በእጅ ጽሑፍ ተባዝተው ለሁሉም እንዲደርሱ ስላደረጉ ገዳማትና አድባራት በጠቅላላም አብያተ ክርስቲያናታችን በቅዱሳት መጻሕፍት በልጽገው ይገኛሉ ። እንዲሁም ከልዩ ልዩ ቋንቋ ወደ ግዕዝ እንዲተረጐሙ ወዲያውም በቋሚ መጻሕፍትነት እንዲጻፉ ያደረጓቸው መጻሕፍት ፤ ለዘመናቸው አገልግሎት በቂ ጥቅምን ከመስጠታቸው ጋር ለአሁኑም ዘመን እንዲሁ ከፍ ያለ ጥቅምን በመስጠት ላይ ይገኛሉ ። የሰው ሕይወት በቅዱስ መጽሐፍ ደጋፊነት ተወስኖ እንዲኖር በግድ ያስፈልጋል ። አንድ ሰው በቅዱስ መጽሐፍ መሪነት ካልተመራና ጊዜውን ሳያባክን ካልሠራ በነፋስ ኃይል እንደሚወዛወዝ ሸንበቆ ምንም የያዘው ቁም ነገር ሳይኖር እንዲሁ ያልፋል ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በየጊዜው መመልከት ግን የሰው ልጅ ራሱን ገዝቶ ፈቃደ ብርቱነቱን አፅንቶ እንዲኖር ይረዳዋል ። ቅዱስ መጽሐፍን ቤተ ክርስቲያናችን በምትቀበለው መልክ ጠቅላላውን በአንድ ጥራዝ እንዲገኝ ከማድረጋችን ጋር እርሱንም ወደ አማርኛ አስተርጕመን አሳትመነዋል ። ዋናው ዓላማችንም በጠቅላላ ወገናችንን ስለ ቅዱስ መጽሐፍ ያለውን ፍላጎት ለማርካት ነው ።

አሁንም ክርስቲያኑ ሕዝባችን በተለይም አዲሱ ትውልድ በሚስማማውና በሚገባው ዕቅድ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲማር አስበን በቀላሉ መንገድ እንዲዘጋጅ ያዘዝነው ተምሮ ተመራምሮ በእውነቱ ጸንቶ ለመኖር ይረዳዋል በማለት ነው ። ለሕዝባችን እንደፍላጎቱ ለማርካት በዐቀድነው መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ጊዜያችንን መስሎ የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት ተከትሎ የተዘጋጀ እንደሆነ ዳር እስከ ዳር ያለው ተቀባይነት ሊሟላ እንደሚችል የታወቀ ነው ፡ በተምሮ ማስተማርም ፡ ሁሉ እንዲጠቀምበት ያለን እምነት ፍጹም ነው ።

ቀ. ኃ. ሥ.



www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

ዱስ መጽሐፍ የሰው ልጅ መመሪያ የሕይወቱም መምሪያ በመሆኑ ፣ የሰው ልጅ ራባት እንደጀመረ ወዲያውኑ አምላክ በቅዱሳን ነቢያት አድሮ ፡ ብሉያት መጻሕ ት እንዲጻፉ አድርጓል ። በኋላም ራሱ ሥጋን ለብሶ በምድር ተመላልሶ እንደ አምላ ነቱ ቅዱስ ወንጌልን አስተምሯል ። ቀጥሎም ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝ ው ፡ የረቀቀውን አጕልተው ፡ ትንቢቱን አማናዊ አድርገው አስተምረዋል ፡ ቅዱስ ጽሐፍንም ጽፈው ሰጥተዋል ። ቅዱስ መጽሐፍ የሰው ልጅ የልቡናው ፋና ነው ፣ ነርሱ ሕይወቱ በጨለማ ይዋጣል ፤ ያለርሱ ቢራመድ ይሰነካከላል ።

በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድና በርሱም ገላጭነት የተጻፈ ቅዱስ መጽሐፍ ሰው ልጅ ለትምህርት ፣ ለተግሣጽ ይጠቅማል ፤ የዚህንም እውነተኛ አስረጂነት ዱስ ጳውሎስ በመረዳት ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን ሲመክር ይገኛል (፪ ጢሞ. ፤ ፲፮ - ፲፯) ።

ቤተ ክርስቲያን የጸጋ መዝገብ ስትሆን ምእመናን ደግሞ ጸጋውን እንዴት ሊካ ሉት የሚችሉ በቅዱስ መጽሐፍ መመሪያነት መሆኑ የታመነ ነው ። ስለዚህ ቤተ ርስቲያን ዘመኑን ተከትላ ረጅሙን በማሳጠርና በመጠቅለል በየጊዜውም ቋንቋ ን ከከባድ ወደ ቀላል በማሻሻል ተስማሚ የሆነ ዝግጅት በማድረግ ስታስተምር ይታለች ፤ አሁንም ታስተምራለች ።

ከዚህ ቀደም በሀገራችን በዚህ መልክ እየተዘጋጁ የቀረቡ ብዙ የመጽሐፍ ዱስ ታሪኮች እንደነበሩ ይታወቃል ። በተጨማሪም አሁን በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ርስቲያን ኃላፊነት የተዘጋጀ ሆኖ ቀርቧል ። ይሁን እንጂ ማንኛውም አማኒ ዳር ስከዳር እንዲጠቀምበት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል ። ኽንም የተቀደሰ ተግባር ለመጀመር የቻልነው የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ፤ ክርስቲያን ሃይማኖት ደጋፊ በሆኑ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልካም ፈቃድና ትእዛዝ ነው ። የዚህንም ዝግጅት ኃላፊነት የመንበረ ጸባዖት ቅድ ት ሥላሴ ካቴድራል የወሰደና ያሳተመው ሲሆን ፣ በመላ ክርስቲያኑ ሕዝባችን እን ጠቀምበት እምነታችን ከፍ ያለ ነው ።

በሥጋዊ ጥበብ የተራቀቀው ትውልድ መንፈሳዊው ጥበብ እንዳይነሣው ቅዱስ መጽሐፍን በማንበብ እንዲጠቀም ትንሽ ትልቅም ሳይል ሁሉም እንደፍላጎቱ እንዲ ርሰው ከፍ ያለ ጥንቅቄ በማድረግ ቀላል መስሎ በታየን መንገድ አዘጋጅተን አቅር ናል ።

መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ለማጥናት የሚያስችለውን «የመጽሐፍ ቅዱስ መማ ያ» ብለን የሰየምነውን ፪ኛውን ክፍል በዚህ መልክ ስናቀርብ ሁላችሁም በመ ባር ልዩም ምርምር በማድረግ እንድትጠቀሙበት በእግዚአብሔር መንፈስ እንታ ዎናለን ።

የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።



# መግቢያ

የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ ብለን የሰየምነው ይኽ መጽሐፍ ፩ኛ በትምህርት ቤት ፣ ፪ኛ በእሑድ ትምህርት ቤት ፤ ፫ኛ በግልም በየቤቱ ሁሉም እንዲማርበትና እንዲያስ ተምርበት ታስቦ አማካይ መንገድን በመከተል የተዘጋጀ ነው ። መጽሐፉም ፫ት ክፍል ይኖረዋል ፡ ይኸውም በ፩ኛ ደረጃና በ፪ኛ ደረጃ ፡ እንዲሁም ከፍተኛ ዕውቀት ላላቸው ሰዎች እንዲመች ሆኖ ተመጥኖ የተሠራ ሲሆን ፡ ፩ኛውም ሆነ ፡ ፪ኛው ክፍል ፡ ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ተወጣጥቶ ክፍለ ዘመናትን በመከተል ለትምህርት ተስ ማሚ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ ነው ፤ ለምሳሌ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ መግቢያ የመዘጋጃ ጊዜ እንደመሆኑ ፤ ብሉያትንና መጻሕፍተ ነቢያትን በመማር እንዲጠቀሙ በት ተዘጋጅቷል ። ከታኅሣሥ እስከ ጰራቅሊጦስ ማለት እስከ ግንቦት ድረስ የመድኃ ኒት ዘመን እንደመሆኑ መጻሕፍተ ሐዲሳትን በመከተል ተዘጋጅቿል ። ከሰኔ እስከ ነሐሴ መጨረሻ ባለው ጊዜ እንደገና ብሉይ ኪዳንን በመከተል ተዘጋጅቷል ።

ተማሪዎችም በዚህ መሠረት ሊማሩ እንደሚገባ ስናስገነዝብ ፤ አስተማሪዎችም በዚሁ መልክ እንዲያስተምሩ ፡ የግል ሰዎችም ቢሆኑ በዚህ መሠረት እንዲማሩ እም ነታችን ፍጹም ነው ።

ከ፫ቱ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ ፪ኛው ይኽ ሲሆን ፩ኛው ክፍል ከዚህ ቀደም ታትሞ በሥራ ላይ ውሏል ። ፫ተኛው ክፍል ደግሞ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል ። እያን ዳንዱ ምዕራፍ ተመሳሳይ ከሆነበት ቦታ ላይ ምዕራፍና ቊጥሩን በማያያዝ እየጠቀ ስን አሳይተናል ። ከጥናቱ ቀጥሎ ለትምህርት ተስማሚ የሆኑ ጥቅሶች እንደማጠቃ ለያ ትምህርት ሆነው ገብተዋል ፤ እንዲሁም በያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የት ምህርቱን ጠቅላላ ስሜት የሚገልጡ ጥያቄዎች ስለሚገኙ ፤ አስተማሪው እርሱንና በርሱ መልክ ጥያቄ እንዲያቀርብ የሚገልጥ ሆኖ ተዘጋጅቷል ። አስተማሪውና ተማ ሪው በረጋ መንፈስ እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል ። የተማሩትንም ሁሉ የሚገልጥ ቅዱስ መንፈስን መጥራት ስለሚያስፈልግ ፡ በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ በጸሎት መልክ ተዘጋጅቶ ይገኛል ። የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል ፤ ቀና ጎዳናን ያገኛልና ። ቤተ ክርስቲያናችን ይኽን ዝግጅት ለማድረግ የወሰነችበት እያንዳንዱ ወጣት ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ ኃላፊነት ስላለበት ለመንፈሳዊ ሕይወቱ መመሪያ እን ዲሆነው ሰፋ ያለ ጥናት ካደረገች በኋላ ነው ።

የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

የድርሰት ክፍል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ

## ከብሉይ ኪዳን


| ምዕራፍ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | የጥጃ ምስል | ፲፯ |
| ፪ | የቃል ኪዳን ድንኳን | ፳ |
| ፫ | የአሮንና የልጆቹ ክህነት | ፳፫ |
| ፬ | የእስራኤል ሠፈርና ጉዞ | ፳፮ |
| ፭ | የእስራኤል አለማመን | ፳፱ |
| ፮ | ከቃዴስ ወደ ዮርዳኖስ | ፴፪ |
| ፯ | ባላቅና በለዓም | ፴፭ |
| ፰ | የሙሴ ስንብትና የኢያሱ መሾም | ፴፰ |
| ፱ | የእስራኤል ዮርዳኖስን መሻገር | ፵፩ |
| ፲ | የኢያሪኮ ቅጥር መውደቅ | ፵፬ |
| ፲፩ | የድል ዕንቅፋት | ፵፮ |
| ፲፪ | ታላቅ ድል | ፵፱ |
| ፲፫ | የርስት ድልድልና የኢያሱ ስንብት | ፶፪ |
| ፲፬ | የሐዲስ ኪዳን ተስፋ | ፶፭ |


## ከሐዲስ ኪዳን


| | | |
|---|---|---|
| ፲፭ | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ | ፶፱ |
| ፲፮ | የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ | ፷፪ |
| ፲፯ | የሰማርያ ሴት | ፷፭ |
| ፲፰ | የኢየሱስ የቃሉ ኃይል | ፷፰ |
| ፲፱ | የፈሪሳውያን ክርክር | ፸፩ |
| ፳ | ጌታችን በጌርጌሴኖን አገር | ፸፬ |
| ፳፩ | የመጥምቁ ዮሐንስ ሞት | ፸፯ |
| ፳፪ | ጌታችን አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አበረከተ ። | ፸፱ |
| ፳፫ | ጌታችን ከእስራኤል አገር ውጭ | ፹፪ |
| ፳፬ | የጌታችን ክብር መገለጥ | ፹፭ |
| ፳፭ | ጌታችን ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ | ፹፰ |
| ፳፮ | ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው | ፺፩ |
| ፳፯ | የእግዚአብሔር መንጋና እረኛው | ፺፬ |
| ፳፰ | አልዓዛርና እኅቶቹ | ፺፯ |
| ፳፱ | የአይሁድ ፋሲካ እንደ ቀረበ | ፻ |





| ምዕራፍ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፴ | ካህናት ላቀረቡት ጥያቄ የጌታችን መልስ | ፻፫ |
| ፴፩ | ኢየሱስ የሚፈታተኑትን መልስ አሳጣቸው | ፻፮ |
| ፴፪ | ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አዲስ ሥርዓት ሰጠ | ፻፱ |
| ፴፫ | ጌታችን የተያዘባት ሌሊት | ፻፲፫ |
| ፴፬ | የጌታችን ስቅለትና ትንሣኤ | ፻፲፮ |
| ፴፭ | በገሊላ ባሕር ዳር | ፻፲፱ |
| ፴፮ | የቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና አጠባበቅ | ፻፳፩ |
| ፴፯ | የእስጢፋኖስ ምስክርነትና ሞት | ፻፳፬ |
| ፴፰ | የወንጌል ትምህርት በአረማውያን | ፻፳፯ |
| ፴፱ | የአንጾኪያና የኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናት | ፻፴ |


## ከብሉይ ኪዳን


| | | |
|---|---|---|
| ፵ | ጀግናው ጌዴዎን | ፻፴፫ |
| ፵፩ | ኃያሉ ሶምሶን | ፻፴፯ |
| ፵፪ | ሞዓባዊት ሩት | ፻፵ |
| ፵፫ | የሳሙኤል ልደትና መጠራት | ፻፵፫ |
| ፵፬ | የእግዚአብሔር ታቦት መማረክና መመለስ | ፻፵፮ |
| ፵፭ | ሳኦል ተቀብቶ ነገሠ | ፻፵፱ |
| ፵፮ | የዳዊት መመረጥ | ፻፶፪ |
| ፵፯ | ዳዊትና ጎልያድ | ፻፶፭ |
| ፵፰ | የዳዊት መሳደድ | ፻፶፰ |
| ፵፱ | የዳዊት መንግሥት | ፻፷፪ |
| ፶ | የዳዊት ኃጢአትና ንስሐ | ፻፷፭ |
| ፶፩ | የአቤሴሎም ዓመፅ | ፻፷፰ |
| ፶፪ | የሰሎሞን መንግሥት | ፻፸፩ |


## ካርታዎች


| | |
|---|---|
| ቅድስት አገር በክርስቶስ ዘመን | በመጽሐፍ መጀመሪያ |
| ከሲና ወደ ግብፅ | ፲፪ |
| የእስራኤል ነገዶች ምድረ ርስት | ፲፫ |
| እስራኤል በሳሙኤልና በሳኦል ዘመን | ፲፬ |
| የዳዊትና የሰሎሞን መንግሥት | ፲፭ |


www.ethiopianorthodox.org

# ማሳሰቢያ

የዚህ መጽሐፍ አገላለጥና የጥቅሶች አገባብ ትንሽ ለየት ያለ ስለሚመስል ለአንባቢዎች እንዲመች ከዚህ በሚቀጥለው መንገድ እንገልጣለን ።

ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩ - ፪ ፥ ፫ ። ይህ ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፩ እስከ ምዕራፍ ፪ ቍጥር ፫ ማለት ነው ።

ይህ ንዑስ ሠረዝ «፥» የሚገኘው ከምዕራፍና ከቍጥር መካከል ብቻ ሲገኝ ነው ።

« — » ሂድ የሚለው ምልክት ደግሞ «እስከ» ማለት ነው ።

በአንድ ቦታ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ ክፍሎች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ክፍል መካከል ድርብ ሠረዝ «፤» ይታተማል ። ለምሳሌ ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፯ - ፴፩ ፤ ፫ ፥ ፪ ፤ አሞጽ ፬ ፥ ፲፫ ። ይህ ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ ቍ. ፳፯ - ፴፩ ፤ ም. ፫ ቍ. ፪ ፤ አሞጽ ም. ፬ ቍ. ፲፫ ማለት ነው ።

፪ ጴጥ. ፪ ፥ ፫ ፡ ፱ ፡ ፲ ማለት ፪ኛ ጴጥሮስ ም. ፪ ቍ. ፫ ቍ. ፱ ቍ. ፲ ማለት ነው ። ዘፍጥ. ፬ ፡ ፫ ። ይህ ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፬ና ምዕራፍ ፫ ማለት ነው ። ሌላውም በዚህ መልክ ስለሚሄድ አንባቢዎች ሁሉ በጥንቃቄ እንድትረዱልን እናሳስባለን ።

በአንድ ቃል አጠገብ * ሲገኝ ፡ በምዕራፉ ሥር መግለጫ መስጠቱን ያመለክታል ።



ምዕራፍ ፩ ።

## የጥጃ ምስል ።

ዘጸ. ፳፬ ፡ ፲፪ - ፴፬ ፡ ፴፭ ።



፩ ፡ ሙሴ በተራራ ላይ ።

ዘጸ. ፳፬ ፡ ፲፪ - ፳፭ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ፡ ፲፰ ።

በሲና ተራራ ራስ ላይ የእግዚአብሔር የክብሩ መታየት እንደሚያቃጥል እሳት ነበረ ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «ና ፡ ወደ እኔ ውጣ ፤ የጻፍሁትንም ሕግ እሰጥሃለሁ» አለው ። ሙሴም የሕዝቡን ሽማግሌዎች ፡ «እስክመለስ ድረስ ቈዩኝ ፤ ነገረተኛም ቢኖር ወደ አሮንና ወደ ሖር ይሂድ» ብሎ ኢያሱ ከተባለ ሎሌው ጋር ተራራውን ወደ ሸፈነው ደመና ገባ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «እኔ በመካከላቸው ለማደር ወድጃለሁና መቅደስ እንዲሠሩልኝ ወርቅ ብር ነሐስም ፡ የሚያስፈልገውንም ሁሉ እንዲያመጡልኝ ለእስራኤል ሁሉ ተናገር» ብሎ ለጕዞ የሚመች የድንኳን መቅደስ እንዴት እንደሚሠራ አሳየው ። በመቅደስ ስለሚያገለግሉትም ሲያዝዝ ፡ «አሮንንና ልጆቹን ካህናት እንዲሆኑልኝ ለያቸው» ብሎ ተናገረ ።

ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ሲነግረውና ሲያሳየው ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት በተራራው ላይ ቈየ ። እግዚአብሔርም ሕጉን የጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑትን ሁለት ጽላቶች ሰጠው ።

፪ ፡ የሕዝብ ኃጢአት ።

ዘጸ. ፴፪ ፡ ፩ - ፳፱ ፡ ፴፫ ።

እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ስለሚሠሩለት መቅደስ ከሙሴ ጋር በተራራው ላይ ሲነጋገር ሳለ ፡ እነርሱ በተራራው ግርጌ ወደ አሮን ተሰብስበው ፡ «ይህ ከግብፅ ያወጣን ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅም ፤ ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱትን አማልክት ሥራልን» አሉት ።

አሮንም ፡ «በሚስቶቻችሁና በልጆቻችሁ ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች አምጡልኝ» አላቸው ። ከእጃቸውም የወርቅ

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

ባቶችን ተቀበለ ፤ አቅልጦም የወርቅ
ሠራ ፤ ሕዝቡንም ፡ «እስራኤል ሆይ ፡
.ሀ ከግብፅ ያወጡአችሁ አማልክት
ው» አላቸው ። በወርቁ ጥጃም ፊት
ዊያን ሠርቶ ፡ «ነገ የእግዚአብሔር
ነው» ብሎ አወጀ ። በነጋውም
ቡ ማልደው ተነሡ ፤ መሥዋዕትንም
፤ በጣዖቱም ፊት ሊበሉና ሊጠጡ
መጡ ፡ ሊዘፍኑም ጀመሩ ።
ግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «ከግብፅ ያወ
ው ሕዝብህ ኃጢአት ሠርተዋልና
ውረድ ። ከዘዝኋቸው መንገድ ፈጥ
ወጡ ፤ ቀልጦ የተሠራም የጥጃ ምስል
ላቸው አደረጉ ። እኔም ይህን አንገተ
ና ሕዝብ አየሁት ፡ እንዳጠፋቸውም
፤ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግ
» አለው ።
ሙሴም ፡ «አቤቱ ፡ ቍጣህ ከግብፅ ባወ
ው ሕዝብህ ላይ ስለምን ተቃጠለ ?
ውያንስ ፡ ሊገድላቸው አወጣቸው
ው ስለምን ይናገሩ ? ከቍጣህ ተመ
ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን
ራኤልንም አስበህ ለሕዝብህ ራራ»
ጸለየ ። እግዚአብሔርም የሙሴን
ት ተቀበለ ፤ ለሕዝቡም ራራ ።
ሙሴም ሁለቱን ጽላቶች በእጁ ይዞ
ራራው ራስ ተመለሰ ፤ ይጠባበቀው
ረ ሎሌውም ጋር ተገናኘ ። ሁለቱም
ጹ ሳሉ ኢያሱ ፡ «የሰልፍ ድምፅ
ሩ ውስጥ አለ» አለው ። ሙሴም ፡
የድል ነሺዎች ወይም የድል ተነሺ
ድምፅ አይደለም ፤ ነገር ግን የዘፈን
ዕ እሰማለሁ» አለው ። ወደ ሠፈሩ
ቡም በጣዖቱ ፊት የሚዘፍኑ ሕዝብ
ዜ የሙሴ ቍጣ ተቃጠለ ፤ ጽላቶቹ
ከእጁ ጥሎ ሰበራቸው ። የሠሩትንም
ወስዶ በእሳት አቀለጠው ፤ እንደ ትቢ
እስኪሆን ድረስ ፈጨው ፡ በውኃ
ውም በጥብጦ ለሕዝቡ አጠጣ ። የወርቅ ጥጃን ስለ ሠሩም እግዚአብሔር ሕዝቡን ቀሠፈ ።

፫ ፤ የሙሴ ጸሎትና የኪዳኑ መታደስ ።

ዘጸ. ፴፪ ፡ ፴ - ፴፬ ፡ ፴፭ ፤ ፪ ቆሮ. ፫ ፡ ፯ - ፲፰ ።

በነጋውም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ፡ «ወዮ ! እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል ፤ አሁን ፡ አቤቱ ፡ ይቅር በላቸው ፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እኔን ደምስሰኝ» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «የበደለኝን እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ ። አሁንም ሂድ ፤ ይህንም ሕዝብ ወደ ነገርሁህ ፡ ወተትና ማርም ወደምታፈስሰው ምድር ምራ ። አንገተ ደንዳና ሕዝብ ስለ ሆናችሁ በመንገድ ላይ እንዳላጠፋችሁ በፊታችሁ መልአክ እሰዳለሁ እንጂ እኔ በመካከላችሁ አልወጣምና ጌጣችሁን አውጡ» አለ ። ሕዝቡም ይህን ክፉ ወሬ ሲሰሙ አዘኑ ፤ ከእነርሱም ማንም ጌጡን አላደረገም ።

ሙሴም ከሠፈሩ ውጭ ለጸሎት ተተክሎ ወደ ነበረው ድንኳን ወጥቶ ፡ «እነሆ አንተ ፡ ይህን ሕዝብ አውጣ ትለኛለህ ፤ ከእኔም ጋር የምትልከውን አላስታወቅኸኝም ። አሁንም በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ መንገድህን እባክህ አሳየኝ ፤ ይህም ሕዝብ ሕዝብህ እንደሆነ ተመልከት» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ ፤ አሳርፍሃለሁ» አለው ።

ሙሴም ፡ «እባክህ ክብርህን አሳየኝ» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «ቸርነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፌ ስሜን አውጃለሁ ። ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደ ፊተኞች አድርገህ ጥረብ ፤ በሰበርኻቸው ጽላቶች የነበሩትንም ቃላት እጽፍባቸዋለሁ ። ነገም የተዘጋጀህ ሁን ፤ በማለዳም ወደ ሲና ተራራ ወጥተህ በፊቴ ቁም» አለው ።

ሙሴም ሁለት ጽላቶችን ጠረበ ፤ በነጋውም ማልዶ ወደ ተራራው ወጣ ። እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ወረደ ፡ በሙሴም ፊት አልፎ ፡ «እግዚአብሔር ፡ እግዚአብሔር መሐሪ ፡ ሞገስ ያለው ፡ ታጋሽም ፡ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት ፡ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ ፡ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል ፡ በደለኛውንም እንዳልበደለ የማይቈጥር ፡ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው» ሲል ስሙን አወጀ ። ሙሴም ጐንበስ ብሎ ሰገደ ። ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊትም ሳይበላና ሳይጠጣ ከእግዚአብሔር ጋር ቈየ ። እግዚአብሔርም ፡ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር ። በጽላቶቹም ላይ አሥሩን የቃል ኪዳን ቃላት ጻፈ ፤ የሕዝቡንም ኃጢአት ይቅር ብሎ ቃል ኪዳኑን አጸና ።

ሙሴ ከተራራው በወረደ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ ፊቱ ያንጸባርቅ ነበር ፤ እርሱ ግን ፊቱ እንዳንጸባረቀ አላወቀም ። አሮንና ሕዝቡም ሙሴን ባዩ ጊዜ ወደ እርሱ ለመቅረብ ፈሩ ። ሙሴም በፊቱ መሸፈኛ አድርጎ ተናገራቸው ፤ ወደ እግዚአብሔር ገብቶ ከእርሱ ጋር ሲነጋገር ግን መሸፈኛውን ከፊቱ አነሣ ።

* * *

እግዚአብሔር ፡ እግዚአብሔር መሐሪ ፡ ሞገስ ያለው ፡ ታጋሽም ፡ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት ፡ . . . ኃጢአትንም ይቅር የሚል ፡ በደለኛውንም እንዳልበደለ የማይቈጥር . . . . አምላክ ነው ።

ዘጸ. ፴፬ ፡ ፮ - ፯ ።

እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤ ስሜ ይህ ነው ፤ ክብሬን ለሌላ ፡ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም ። ኢሳ. ፵፪ ፡ ፰ ።


* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሕዝቡ ከዐሠርቱ ቃላት የትኛውን በመተላለፍ በደሉ ?
፪ ፤ ሙሴስ ከፋታቸውን ባየ ጊዜ ምን አደረገ ?
፫ ፤ ሙሴ ከራሱ ይልቅ የእግዚአብሔርን ክብር የሕዝቡንም ደኅንነት እንደ ፈለገ ምንና ምን በማለቱ አሳየ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ክብርህን አሳየኝ ።

ዘጸ. ፴፫ ፡ ፲፰ ።


www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፪ ።

# የቃል ኪዳን ድንኳን ።

ዘጸ. ፴፭ - ፵ ።

## ፡ የሕዝቡ ገጸ በረከት ።

ዘጸ. ፴፭ ፡ ፬ - ፱ ፡ ፳ - ጽ፱ ።

ግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ መካከላቸው ለማደር ፡ ከእነርሱም ጋር መሄድ እንደወደደ በሰሙ ጊዜ ሕዝቡ ስ አላቸው ። ሙሴም ፡ «እግዚአብሔር ምላካችን መቅደስ እንድንሠራለት አዝ ል ። አሁንም ከእናንተ ፈቃደኛ የሆነ ሉ ፡ ይህ መቅደስ የሚሠራበትን ወርቅ ርም ነሐስም ፡ ሰማያዊና ሐምራዊ ይም ግምጃ ፡ ጥሩ በፍታም ፡ የፍየል ጉርም ፡ ቁርበትም ፡ እንጨትም ለእግዚ በሔር ይስጥ» አላቸው ።

ከሕዝቡም ፈቃደኞች የሆኑት ሁሉ ሚያስፈልገውን በየዓይነቱ ለእግዚአብ ር ስጦታ አመጡ ። ወንዶችና ሴቶችም ለዳ ማለዳ እየመጡ የወርቅ ጌጦችን ን ሌላ ነገርንም በደስታ ያቀርቡ ነበር ። በበኞች የሆኑ ሴቶችም በእጃቸው የፈተ ትን ግምጃ ጥሩውንም በፍታ አመጡ ። ሕዝብ አለቆችም ስጦታቸውን አቀረቡ።

## ፪ ፡ የድንኳን መቅደስ ሠሪዎች ።

ዘጸ. ፴፭ ፡ ፴ - ፴፮ ፡ ፯ ።


ሙሴም ለሕዝቡ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፡ « እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ የሆነ ውን ባስልኤልን በስሙ ጠርቶ ፡ በወር ቅና በብር በነሐስም እንዲሠራ ፡ እንጨቱ ንም እንዲጠርብ ፡ የብልሃት ሥራውንም ሁሉ እንዲያደርግ የእግዚአብሔርን መን ፈስ ሞላበት ። እንደዚሁም ከዳን ነገድ የሆነውን ኤልያብን ጠራ ። ማናቸውንም የብልሃት ሥራ ሁሉ እንዲያደርጉ ፡ እንዲ ያስተምሩም በልባቸው ጥበብን አሳደረባ ቸው ። ከእናንተም ጥበብና ማስተዋል የተሰጠው ሁሉ ከእነርሱ ጋር ይሥራ ።»

በዚያን ጊዜ ባስልኤልና ኤልያብ ፡ እግ ዚአብሔርም በልቡ ጥበብን አሳድሮበት ልቡ ለሥራ ያነሣሣው ሁሉ ፡ ሕዝቡ ያመ ጡትን ስጦታ ከሙሴ እጅ ተቀብለው መቅደስን መሥራት ጀመሩ ። ከሕዝቡ የተሰጠውም ነገር ሥራውን ለማስፈጸም በቅቶ ስለ ተረፈ ወደ ሙሴ መጥተው ፡






የምስክር ታቦት



የማዕድ ገበታ



መቅረዝ



የዕጣን መሠዊያ.


«ሕዝቡ ያመጡት ስጦታ ከሚያስፈልግ በላይ እጅግ ብዙ ነው» ብለው ነገሩት ። ሙሴም ፡ «ወንድ ወይም ሴት ከዚህ የበ ለጠ የሚያመጣ አይኑር» ብሎ በሠፈሩ ውስጥ አሳወጀ ።

## ፫ ፡ የድንኳን መቅደስ አሠራር ።

ዘጸ. ፴፮ ፡ ፳ - ፴፱ ፡ ፵፫ ።

በምድረ በዳ ሳሉ እስራኤላውያን የሚሠ ሩት መቅደስ ለመንገድ የሚመች ፡ ድን ኳን መሳይ መሆን ነበረበት ። ይህም መቅ ደስ «ማደሪያ» ሲባል ፡ እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለሚገናኝ በት «የመገናኛ ድንኳን» ተባለ ። አንዳ ንድ ጊዜ ደግሞ ሕግ የተጻፈባቸው የምስ ክር ጽላቶች ስለ ነበሩበት «የምስክር ድን ኳን» ይባል ነበር ።

ባስልኤልና ኤልያብ ፡ ከእነርሱ ጋር የነ በሩም አንጥረኞች ፡ ሸማኔዎችና ጠላፊ ዎች ፡ የእንጨት ጠራቢዎችም እጅግ እየ ተጉ መጋረጃዎችንና ሳንቃዎችን ዓምዶች ንም ሠሩ ። ለማደሪያውም ዐርባ ሁለት ሳንቃዎችና ዘጠኝ ዓምዶች በወርቅ ከተ ለበደ እንጨት ተሠሩ ። በሰማያዊና በሐ ምራዊ በቀይም የተጠለፉት መጋረጃዎች በእነርሱ ላይ እንደ አጎበር ሆነው እንዲዘ ረጉ ተሠሩ ። ከፍየል ጠጉርና ከቁርበት



የነሐስ መሠዊያ

የተዘጋጁ ሌሎች መጋረጃዎችም ከሁሉ በላይ እንደ ጣራ ሆነው እንዲዘረጉ ተሠሩ ። የተጠለፉ ሁለት መጋረጃዎችም፡ አንዱ ቅድስተ ቅዱሳን የተባለውን ክፍል ቅድስት ከተባለው እንዲለይ ፡ ሁለተኛ ውም በቅድስቱ ደጃፍ እንዲንጠለጠል በብልሃት ተሠሩ ።

ይህም ሁሉ በሚሠራበት ጊዜ ባስል ኤል ፡ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈባቸው የምስ ክር ጽላቶች እንዲቀመጡበት ፡ በወርቅ ከተለበደው እንጨት የምስክር ታቦትን ሠራ ። ይህም ታቦት ፡ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ፡ ስፋቱና ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ሳጥን ሲሆን ፡ በሁለት ኪሩቤል ክንፎች የሚሸፈን ሁለንተናው ከወርቅ የተሠራ መክደኛ ተደረገለት ። ይህም መክደኛ «የሥርየት መክደኛ» ተባለ ። እግዚአብሔርም ፡ «በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካ ከል በሥርየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋ ግርሃለሁ» ሲል ለሙሴ ተናግሮ ነበር ።

ቅድስት በተባለው የማደሪያው ክፍል የሚቆሙትንም ፡ በወርቅ የተለበደውን ገበታና የዕጣን መሠዊያን ፡ ሁለንተናው ከወርቅ የተደረገውንም መቅረዝ ባስል ኤል ሠራ ። እንደዚሁም በማደሪያው አደ ባባይ የሚቆሙትን የነሐስ መሠዊያና



የመታጠቢያ ሰን

www.ethiopianorthodox.org

የመታጠቢያ ሰንን ሠራ ። መታጠቢያ
ውም የተሠራው ፤ በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ የሚያገለግሉ ሴቶች ከሰጡት ከነ
ሐስ መስተዋታቸው ነበረ ።

በአደባባዩም ዙሪያ የሚንጠለጠሉ መጋ
ረጃዎች ከጥሩ በፍታ ፤ እነርሱ የሚንጠለ
ጠሉባቸው ዓምዶችም ከነሐስ ተሠሩ ።
በምሥራቅ በኩል በነበረው ደጃፍም የሚ
ንጠለጠል የተጠለፈ መጋረጃ ተዘጋጀ ።
እግዚአብሔርም ካህናት ለሚሆኑ ለአሮ
ንና ለልጆቹ ያዘዛቸው ልብሶች በየዓይነቱ
ተሠሩ ። እንዲሁም የሥራው ተካፋይ የሆ
[illegible] እያዘጋጁ ፤
እግዚአብሔር በተራራው ላይ ለሙሴ እን
ዳሳየው ምሳሌ አድርገው ሠሩ ። ሙሴም
ባረካቸው ።

፥ የቃል ኪዳን ድንኳን አተካከል ።

ዘጸ. ፵ ፥ ፩ - ዘሌዋ. ፩ ፥ ፩ ፥ ፲፯ ፥ ፩ - ፲፩ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፤ «በመጀመሪ
ያው ወር በፊተኛው ቀን የመገናኛውን
ድንኳን ትተክላለህ» በማለት ስለ አተካ
ከሉ አዘዘው ። እንደዚሁም ከግብፅ በወጡ
በሁለተኛው ዓመት በመጀመሪያው ቀን
ሙሴ የማደሪያውን ድንኳን ተከለ ። ሥራ
ውንም ሁሉ በፈጸመ ጊዜ ደመና መጥቶ
ማደሪያውን ሸፈነው ፤ የእግዚአብሔርም
ክብር ማደሪያውን ሞላ ፤ ሙሴም ሊገባ
በት አልቻለም ።

እግዚአብሔርም [illegible] ድንኳን ውስጥ
ሙሴን ጠርቶ ፤ «ከእስራኤል [illegible] ማናቸ
ውም ሰው መሥዋዕት ቢያቀርብ ፤ ለእግ
ዚአብሔር እንዲሠዋ ወደ መገናኛው ድን
ኳን ደጃፍ ሳያመጣ ለሰይጣናት በሜዳ
ቢሠዋው [illegible] ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ
ይጥፋ ። የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ
[illegible]ውና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስ
ተሥረያ እንዲሆን እኔ ለእናንተ ሰጠሁት»
ሲል የእስራኤል ሰዎች ወደ እርሱ የሚቀርቡበት በመሥዋዕት እንደሆነ ተናገረ ።

* * *

እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ
በልቡ እንዳሰበ ይስጥ ፤ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም ።

፪ ቆሮ. ፱ ፥ ፯ ።

እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱ
ሳን ሁኑ ።

ዘሌዋ. ፲፱ ፥ ፪ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ መቅደስን ለመሥራት መውደዳቸውን ሕዝቡ እንዴት አሳዩ ?
፪ ፤ ያቀረቡትስ የስጦታ ዓይነት ምንና ምን ነበረ ?
፫ ፤ ልዩ ጥበብና ችሎታ የተሰጣቸው የሥራ መሪዎችስ እነማን ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አምላካችን ሆይ እንገዛልሃለን ፤ ለክቡር ስምህም
ምስጋና እናቀርባለን ። ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና ፤
ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና ይህን ያህል
ችለን ልናቀርብልህ እኛ ማን ነን ? ፩ ዜና. ፳፱ ፥ ፲፫ - ፲፬ ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፫ ።

## የአሮንና የልጆቹ ክህነት ።

ዘሌዋ. ፰ - ፲ ።



### ፩ ፤ የካህናት መቀደስ ።

ዘሌዋ. ፰ ፥ ፩ - ፱ ፥ ፳፬ ፤ ዘጸ. ፳፰ ፥ ፩ - ፳፱ ፥ ፴፯ ።

ለአሮን ናዳብና አብዩድ ፤ አልዓዛርና ኢታምር የተባሉ ወንዶች ልጆች ነበሩት ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፤ «አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ወስደህ ማኅበሩን ሁሉ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሰብስባቸው» አለ ። ሙሴም እንደ ታዘዘ አደረገ ፤ ማኅበሩም ሁሉ በደጃፍ ተሰብስበው ሳሉ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝና ሥርዓት አሮንን ከነልጆቹ ቀደሰ ። እነርሱም እስከ ሰባት ቀን ድረስ ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አል ወጡም ።

በስምንተኛውም ቀን ማኅበሩ ሁሉ ቀር በው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆሙ ፤ አሮን እንደ ታዘዘ ሁሉ መሥዋዕቶችን በነሐስ መሠዊያው ላይ ሠዋ ፤ ከሙሴም ጋር ወደ ማደሪያው ገባ ፤ ሁለቱም ወጥተው ሕዝ ቡን ባረኩ ። የእግዚአብሔርም ክብር ለሕ ዝቡ ሁሉ ተገለጠ ፤ እሳትም ከእግዚአብ ሔር ዘንድ ወጥቶ ከመሠዊያው ላይ መሥ ዋዕቱን ስቡንም በላ ። ሕዝቡም ሁሉ አይ ተው እልል አሉ ፤ በግምባራቸውም ወደቁ ።

### ፪ ፤ የናዳብና የአብዩድ ድፍረት ።

ዘሌዋ. ፲ ፥ ፩ - ፲፩ ።

ነገር ግን በዚህ በታላቁ የደስታ ቀን የሚያ ስደነግጥና አሳዛኝ የሆነ ነገር ተደረገ ። ናዳ ብና አብዩድ የተባሉት የአሮን ታላላቅ ልጆች እየራሳቸው ጥናውን ወስደው እሳት አደረጉበት ፤ በላዩም ዕጣን ጨመሩ በት ፤ በእግዚአብሔር ፊት እርሱ ያላዘዛ ቸውንም ሌላ እሳት አቀረቡ ። እንዲሁ ደፍረው የገዛ ራሳቸውን አሳብ በመከተል እግዚአብሔር ያላዘዘውን ነገር ሲያደርጉ ከእግዚአብሔር ፊት እሳት ወጥቶ በላ ቸው ፤ ሞቱም ። ሙሴም አሮንን ፤ «ወደ እኔ በሚቀርቡ እቀደሳለሁ ፤ በሕዝቡም ሁሉ ፊት እከብራለሁ ብሎ እግዚአብሔር

ናገረው ይህ ነው» አለው ። አሮንም
ም አለ ።
ሙሴም ለአሮንና ለቀሩት ልጆቹ ፡ «እን
ሞቱ ራሳችሁን አትንጩ ፡ ልብሳችሁ
አትቅደዱ ፤ ወንድሞቻችሁ ግን የእስ
ል ቤት ሁሉ ያልቅሱ» አላቸው ።
ደ ቃሉም አደረጉ ። እግዚአብሔርም
ንን ፡ «እንዳትሞቱ ወደ መገናኛው
ኳን ስትገቡ አንተና ልጆችህ የወይን
ና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ»
ው ።

## የአሮንና የልጆቹ አገልግሎት ።

ንና ልጆቹ ምን ሲሠሩ ተቀደሱ ብለን
ጠይቅ ፡ ሙሉ የሆነ መልስ በኦሪት
ሕፍት ተጽፎ እናገኛለን ። እዚህ ላይ
፡ በየዕለቱና በሰንበት በሰንበት ፡ በየ
ቱም በሚከበረው በማስተሥረያ ቀን
ጽሙአቸው የነበሩትን አንዳንድ ድር
ችን በአጭሩ እናያለን ።

ዕለታዊ አገልግሎት ። ዘጸ. ፳፱ ፡ ፴፰ - ፵፮ ፡
ሌዋ. ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ፤ ዘጸ. ፴ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፲፯ - ፳፩ ።

ዳ ማለዳ አሮንና ልጆቹ በነሐስ መታ
ያ እግራቸውንና እጃቸውን ይታጠቡ
፤ ለጥቀውም የአንድ ዓመት ጠቦት
ተው ከነሐሱ መሠዊያ ላይ ዘወትር
ገኘውና ከቶ በማይጠፋው እሳት ያቃ
ት ነበር ። አሮንም ቅድስት ወደ ተባ
ክፍል ይገባና በመቅረዙ የሚገኙትን
ት መብራቶች እያዘጋጀ በወርቁ መሠ
ላይ ዕጣን ያጤስ ነበር ። ማታ ማታም
የአንድ ዓመት ጠቦት ሲያቀርቡ አሮን
ራቶቹን እያበራ ዕጣንን ያጤስ ነበር።
ትር የሚቃጠለው ይህ የዕለት ዕለት
ዋዕት በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ሠዋ ባዘዘ ጊዜ እግዚአብሔር ፡
ስራኤል ልጆች ጋር በዚያ እገናኛ
ለሁ ፤ በመካከላቸውም እኖራለሁ» አለ ።

## ለ) ሳምንታዊ አገልግሎት ።

ዘሌዋ. ፳፬ ፡ ፭ - ፱ ፤ ዘጸ. ፳፭ ፡ ፴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ፡ «መልካሙን ዱቄት ወስደህ አሥራ ሁለት ኅብስት ጋግር ፤ እነዚህንም ስድስት ስድስቱን በሁለት ተርታ አድርገህ በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ በየሰንበቱ አኑራቸው» አለ ። አሮንና ልጆቹም ይህን ትእዛዝ ተቀብለው በሰንበት በሰንበት ትኩስ የሆነ ኅብስትን በጥሩው ገበታ ላይ ያኖሩ ነበር ። ከገበታውም የሚያነሡትን የሰነበተውን የገጽ ኅብስት ሁሉ በተቀደሰ ሥፍራ ይበሉ ነበር ። የገጽ ኅብስት ተብሎ የተጠራውም በእግዚአብሔር ፊት ስለ ተደረገ ነው ።

## ሐ) ዓመታዊ አገልግሎት ።

ዘሌዋ. ፲፯ ፡ ፩ - ፴፬ ፤ ፳፫ ፡ ፳፯ - ፴፪ ፤ ዕብ. ፱ ፡ ፯ - ፲፪ ፤
ዕብራ. ፲ ፡ ፩ - ፬ ፡ ፲፩ - ፳፪ ፤ ማቴ. ፳፯ ፡ ፶፩ ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «እኔ በሥርየቱ መክደኛ ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ሥርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ሥፍራ ሁልጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው» ብሎ አንድ ጊዜ በዓመት ሲገባ የሚያደርገውን ሥርዓት ሁሉ ሰጠ ።

አሮንም ይህን ትእዛዝ ሁሉ ተቀብሎ በየዓመቱ በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን ፡ የማስተሥረያው ቀን በሚከበርበት ጊዜ ፡ የበፍታ ልብሱን ለብሶ ይህን ልዩ የሆነ ሥርዓትን ለመፈጸም ይዘጋጅ ነበር ። ይህም የማስተሥረያ ቀን ለእስራኤል ሁሉ የዕረፍት ሰንበት ነበረ ፤ በዚህም ዕለት ሰው ሁሉ ሰውነቱን አዋርዶ እንዲያስጨንቅ ታዘዘ ። አሮንም አስቀድሞ ለራሱና ለቤተሰቡ ኃጢአት ወይፈንን ይሠዋና ፡



ጥናውን በመሠዊያው ላይ ካለው ፍም ሞልቶ ዕጣንንና ከወይፈኑ ደም ይዞ በመጋረጃው ውስጥ ይገባ ነበር ፤ በታቦቱ ላይ ባለው በሥርየቱ መክደኛም ላይ ደሙን በጣቱ ሲረጭ ፡ በጥናው ያደረገው የዕጣኑ ጢስ መክደኛውን ይሸፍን ነበር ።

ወጥቶም ፍየልን ለሕዝቡ ኃጢአት ይሠዋና ፡ በፊተኛው ጊዜ እንዳደረገ ሁሉ እንደዚሁ ሁለተኛ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ከፍየሉ ደም ይረጭ ነበር ። እንደዚሁም ስለ ራሱና ስለ ቤተሰቡ ስለ እስራኤል ጉባዔም ሁሉ ያስተሠርይ ነበር ፡ ከእስራኤል ልጆች ርኵስነትና ኃጢአት የተነሣም ለመቅደሱና ለመገናኛው ድንኳን ያስተሠርይ ነበር ። እንደገናም ወጥቶ ከወይፈኑና ከፍየሉ ደም ይወስድና የመሠዊያውን ቀንዶች አስነክቶ በመሠዊያው ላይ በጣቱ በመርጨት ከእስራኤል ልጆች ርኵስነት አንጽቶ ይቀድሰው ነበር ።

የኮርማዎችና የፍየሎችም የበጎችም ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልምና ከአሮን ዘመን ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ በየትውልዱ የሚነሣ የእስራኤል ሊቀ ካህናት ሁሉ ፡ እነዚህን መሥዋዕቶች እየደጋገመ ሲያቀርብ ይቆም ነበር ። ክርስቶስ ግን ለሚሻለው ለሐዲስ ኪዳን መካከለኛና ሊቀ ካህናት ሆኖ ስለ ኃጢአት አንድ ጊዜ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ለሚታመኑበት ሁሉ የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ። እርሱ በመስቀል ላይ ነፍሱን በሰጠ ጊዜ ፡ የእርሱ ሥጋ ምሳሌ የነበረ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ ። በራሱ መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበትን አዲስና ሕያው መንገድ መርቆልን ስለነበር ፡ የእርሱና የሥራው ምሳሌ የሆነው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ተፈጸመ ።

* * *

በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ ፤ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና ። ዕብራ. ፲፪ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ።

ሊቀ ካህናት ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል ፤ ክርስቶስ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት . . . . አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል ። ዕብራ. ፲ ፡ ፲፩ - ፲፬ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፤ ካህናት እንዲሆኑ የተቀደሱ እነማን ነበሩ ?
፪ ፡ አሮን አገልግሎቱን ሲጀምር ሕዝቡ ምን አይተው እልል አሉ ?
፫ ፡ የእልልታውስ ድምፅ ወደ ልቅሶ የተለወጠ በምን ምክንያት ነበረ ?
፬ ፡ በየዓመቱ በሚሆን በማስተሥረያ ቀን አሮን ምን ያደርግ ነበር ?

ጸሎት ፤ እግዚአብሔር ይባርክህ ፡ ይጠብቅህም ፤
እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ፡ ይራራልህም ፤
እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ፡ ሰላምንም
ይስጥህ ። ዘኍ. ፮ ፡ ፳፬ - ፳፮ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፩ ።

# የእስራኤል ሠፈርና ጕዞ ።

ዘኍ. ፩ - ፲ ።

## ፩ ፡ የእስራኤል ቍጥርና ሠፈር ።

ዘኍ. ፩ ፡ ፩ - ፬ ፡ ፵፱ ።

መገናኛው ድንኳን ከተተከለ ከአንድ ር በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ፡ «የእስ ኤልን ማኅበር ሁሉ ቍጠር ። ከሃያ መት ጀምሮ ወደ ሰልፍ የሚወጡትን ሉ ቍጠራቸው ፡ የሌዊ ወገን ግን ማደሪ ውንና ዕቃዎቹን እንዲሸከሙ ካህናት ም ለማገልገል ስለ ተለዩ ወደ ሰልፍ ከሚ ጡት ጋር አይቈጠሩ» አለው ። ሙሴም ሲና ምድረ በዳ ሕዝቡን ቈጠረ ።

እግዚአብሔርም ለሙሴና ለአሮን እን ህ ብሎ ተናገረ ፡ «የእስራኤል ልጆች ያንዳንዱ በየዓላማው በየአባቶቻቸው ቶች ምልክት በመገናኛው ድንኳን ዙሪያ ሥፈሩ ። በምሥራቅ በኩል ወደ ፀሐይ ውጫ የሚሠፍሩት የይሁዳ ፡ የይሳኮር ፡ ብሎን ነገዶች ይሆናሉ ። በደቡብ በኩ ም በየሠራዊታቸው የሮቤል ፡ የስም ን ፡ የጋድ ነገዶች ይሥፈሩ ። በምዕራብ ኩልም እንደ ሠራዊታቸው የኤፍሬም ፡ ምናሴ ፡ የብንያም ነገዶች ይሥፈሩ ። በሰ ን በኩልም እንደ ሠራዊታቸው የዳን ፡ ሴር ፡ የንፍታሌም ነገዶች ይሥፈሩ ።» ስራኤል ነገዶችም እንዲሁ በየዓላማዎ ቸው አጠገብ ሠፈሩ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «የሌዊን ድ በየአባቶቻቸው ቤቶች በየወገናቸው ጠር» አለው ። የያዕቆብ ልጅ ሌዊ ፡ ድሶን ፡ ቀዓት ፡ ሜራሪ የተባሉ ሦስት ጆች ስለ ነበሩት ሌዋውያን በሦስት ን ተከፍለው ተቈጠሩ ። የጌድሶን ን ሠፈርም ከማደሪያው በስተኋላ ነበረ፡ የቀዓት ወገን ሠፈርም በማደሪያው አጠ ገብ በደቡብ ፡ የሜራሪ ወገን ሠፈርም በሰ ሜን በኩል ነበረ ። በማደሪያውም ፊት በምሥራቅ በኩል በስተ ፀሐይ መውጫ የሚሠፍሩት ፡ ከቀዓት ወገን የሆኑት ሙሴና አሮን የአሮንም ልጆች ነበሩ ።


## ፪ ፡ ሰረገሎችና የብር መለከቶች ።

ዘኍ. ፯ ፡ ፩ - ፱ ፡ ፲ ፡ ፩ - ፲ ።

ማደሪያው ከተተከለ በኋላ የነገዶች አለ ቆች ለእግዚአብሔር ስጦታ አድርገው ስድስት የተከደኑ ሰረገሎች ፡ አሥራ ሁለ ትም በሬዎች አቀረቡ ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «ለመገናኛው ድንኳን ማገልገያ እንዲሆኑ ከእነርሱ ተቀብለህ ለሌዋውያን ለእያንዳንዱ እንደ አገልግሎታቸው ስጣ ቸው» አለው ። ሙሴም ሰረገሎችን ተቀ ብሎ ለጌድሶን ወገን ሁለት ሰረገሎችንና አራት በሬዎችን ሰጣቸው ፤ ለሜራሪ ወገ ንም አራት ሰረገሎችንና ስምንት በሬዎ ችን ሰጣቸው ። ምክንያቱም ፡ ጌድሶናው ያን ለሚሸከሙአቸው ለማደሪያው መጋረ ጃዎች ሁለት ሰረገሎች ይበቋቸው ነበር ። የሜራሪ ወገን ግን ሳንቃዎቹንና ዓምዶ ቹን ስለሚሸከሙ ፡ ለእነርሱ አራት ሰረገ ሎች ያስፈልጓቸው ነበር ። ለቀዓት ልጆች አንድ ሰረገላ ስንኳ አልተሰጠም ፡ ምክን ያቱም ፡ የተቀደሱትን ዕቃዎች መሸከም የእነርሱ አገልግሎት ነበረና በትከሻቸው ይሸከሙአቸው ነበር ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ሁለት የብር መለከቶች ጠፍጥፌህ ለአንተ አድ





እስራኤል በየነገዶቻቸው ሲሠፍሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ርግ» ብሎ በምንና በምን ጊዜ እንደሚነፉ
አዘዘ ። ማኅበሩ በሞላ እንዲሰበሰቡ ሲፈ
ለግ ሁለቱ መለከቶች ይነፉ ነበር ። የሕ
ዝቡ አለቆች እንዲሰበሰቡ ሲፈለግ ግን ፤
አንድ መለከት ብቻ ይነፋ ነበር ። እንዲ
ሁም ደመናው ከማደሪያው ላይ በሚነሣ
በት ጊዜ ፤ የእስራኤል ነገዶች በየተራቸው
እንዲጓዙ መለከት በከፍታ ድምፅ መነ
ፋት ያስፈልግ ነበር ።

፫ ፡ የእስራኤል ጒዞ ።

ዘዳግ. ፩ ፥ ፮ - ፰ ፤ ዘኍ. ፲ ፥ ፲፩ - ፴፮ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «በዚህ ተራራ
ተቀመጣችሁት በቃ ፡ ወደ ከነዓናውያን
ምድር ፤ ወደ ሊባኖስም እስከ ታላቁ ወን
ዝም እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ሂዱ ። እነሆ
ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጌአለሁ ፤
ቡ ፡ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም
ግልሁላቸውን ምድር ውረሱ» አለው ።
ደመናውም ከምስክሩ ማደሪያ ተነሣ ፤
መለከቶቹም ከፍ ባለ ድምፅ ተነፉ ፤ ሠፈ
ራቸው በምሥራቅ የነበሩት የይሁዳና የይ
ኮር የዛብሎንም ነገዶች በየሠራዊታ
ቸው ተጓዙ ።

በዚህ ጊዜም ካህናት ወደ ማደሪያው
ገብተው የተቀደሱትን ዕቃዎች ሸፋፈኑ ።
ሌዋውያንም እንደ አገልግሎታቸው አድ
ርገው ለጒዞ ካሰናዱ በኋላ የጌድሶንና የሜ
ራሪ ሰዎች ሰረገሎቻቸውን ይዘው ተጓዙ ።

ከእነርሱም በኋላ የሮቤል ፡ የስምዖንና
የጋድ ነገዶች ተጓዙ ። ከእነርሱም በኋላ
የቀዓት ሰዎች የተቀደሱትን ዕቃዎች በት
ከሻቸው እየተሸከሙ ተጓዙ ። ወደሚሠፍ
ሩበትም ሥፍራ እስኪደርሱ ቀድመው የተ
ጓዙት የጌድሶንና የሜራሪ ሰዎች ማደሪያ
ውን ተክለው ይቈዩአቸው ነበር ።

ከቀዓት ሰዎች በኋላም የኤፍሬም የምና
ሴና የብንያም ነገዶች ተጓዙ ። በመጨረ
ሻም የዳን ፡ የአሴርና የንፍታሌም ነገዶች
ተጓዙ ። እንደዚሁም ከሲና ተራራ ግርጌ
የተነሡት ፤ ከግብፅ በወጡ በሁለተኛው
ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በሃያ
ኛው ቀን ነበረ ። ደመናውም በእስራኤል
ፊት ይሄድ ነበር ። ታቦቱም በተጓዘ ጊዜ
ሙሴ ፤ «አቤቱ ተነሣ ፤ ጠላቶችህም ይበ
ተኑ ፤ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሽሹ» ይል
ነበር ። ባረፈም ጊዜ ፤ «አቤቱ ፤ ወደ እስራ
ኤል እልፍ አእላፋት ተመለስ» ይል ነበር።

*   *   *

እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አም
ላክ አይደለምና . . . . ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን ።

፩ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፴፫ ፥ ፵ ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይሠፍሩ ነበር ፤ በእግዚአብሔ
ርም ትእዛዝ ይጓዙ ነበር ። ዘኍ. ፱ ፥ ፳፫ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ካህናትን ለማገልገል የተለየ ነገድ የትኛው ነበረ ?
፪ ፤ የነገዶች አለቆች ለእግዚአብሔር ምን ስጦታ ሰጡ ?
፫ ፤ እስራኤል በሲና ተራራ ሥር የሠፈሩ ምን ያህል ጊዜ ነበረ ?
(ዘጸ. ፲፱ ፥ ፩ ፤ ዘኍ. ፲ ፥ ፲፩ ።) በዚያም ሳሉ የተደረጉት ነገሮች
ምንና ምን ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ . . . . በጽድቅህ ምራኝ ፤
መንገዴንም በፊትህ አቅና ። መዝ. ፭ ፥ ፰ ።





ምዕራፍ ፫ ።

## የእስራኤል አለማመን ።

ዘኍ. ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፩ ፡ የሰላዮች መላክ ።

ዘኍ. ፲፫ ፥ ፩ - ፳፩ ፤ ዘዳግ. ፩ ፥ ፪ ፥ ፲፱ - ፳፬ ።

ሕዝቡ እጅግ በሚያስፈራው ምድረ በዳ
ሲጓዙ ፡ እየመገበ የመራቸውን አምላክ
ከማውሳት ይልቅ ውለታ ቢሶችና አንጐ
ራጓሪዎች ስለሆኑ ፡ በከነዓን ዳርቻ ወዳ
ለው ቃዴስ በርኔ ወደሚባለው ሥፍራ የደ
ረሱ ከብዙ መዘግየትና መከራ በኋላ ነበረ።

በቃዴስም ሲሠፍሩ ሙሴ ፡ «አምላካ
ችን እግዚአብሔር ወደሚሰጠን ምድር
መጣን ፤ እነሆ ውጡ ፡ ውረሱአት ፤ አት
ፍሩ» አላቸው ። ሕዝቡም ፡ «ምድሪቱን
እንዲጐበኙልን ሰዎች እንስደድ» አሉ ።
እግዚአብሔርም ፡ «ከየነገዱ አለቃ የሆነ
ውን ትልካላችሁ» አለ ። ሙሴም እንዲሁ
አድርጎ አሥራ ሁለት አለቆችን ላከ ፤ እነ
ርሱም በኬብሮን በኩል አልፈው እስከ
ሐማት ዳር ድረስ ሰለሉ ። ወይኑ አስቀ
ድሞ ፍሬ የሚያፈራበት ወራት ስለነበረ
ከኤሽኮል ሸለቆ አንድ ዘለላ ወይን ቈር
ጠው በመሎጊያ ለሁለት ተሸከሙት ፤ ደግ
ሞም ከሮማኑና ከበለሱ ይዘው ከዐርባ ቀን
በኋላ ወደ ቃዴስ ተመለሱ ።

፪ ፡ የሰላዮች ወሬ ።

ዘኍ. ፲፫ ፥ ፳፮ - ፴፫ ።

አሥራ ሁለቱ ሰላዮች ወደ ሠፈሩ ሲደርሱ
የያዙትን ፍሬ ለሙሴና ለሕዝቡ አሳይ



www.ethiopianorthodox.org

ው ፤ «ወደ ላክኸን ምድር ደረስን ፤ እር
ዋም ወተትና ማር ታፈስሳለች ፤ ፍሬ
ም ይህ ነው ። ነገር ግን በምድሪቱ የሚ
ሩ ሰዎች ኃያላን ናቸው ፤ ከተሞቻቸ
ም የተመሸጉ እጅግም የጸኑ ናቸው»
ለው አወሩ ።

ሕዝቡም ደንግጠው ሲፈሩ ካሌብ የተ
ለ ከይሁዳ ነገድ የሆነው ሰላይ ፤ «ማሸ
ፍ እንችላለንና እንውጣ ፤ ምድሪቱንም
ንውረስ» ብሎ አበረታታቸው ። የሚበ
ጡት ሰላዮች ግን ፤ «እኛ ዞረን የሰለል
ት ምድር ፤ የሚኖሩባትን ሰዎች የምት
ናት ። ያየናቸውም ሰዎች ሁሉ ረጃ
ም ናቸው ፤ በዚያም የዔናቅን ልጆች
ን ፤ እኛም በራሳችን አገማመትና በእነ
ቱም ዓይኖች ፊት እንደ አንበጣ ያነስን
ርን» ብለው ክፉ ወሬ አወሩ ።

የሕዝቡ ዓመፅ ።

ዘኍ. ፲፬ ፤ ፩ - ፲ ፤ ዘዳግ. ፩ ፤ ፳፮ - ፴፫ ።

ው የእስራኤል ማኅበርም ድምፃቸውን
አድርገው አለቀሱ ፤ በሙሴና በአሮ
አጕረምርመው ፤ «በግብፅ ሳለን
ው በሞትን ኖሮ ! ወይም በዚህ ምድረ
ምነው በሞትን ኖሮ ! እግዚአብሔርስ
ይፍ እንድንሞት ወደዚች ምድር ለምን
ባናል ? ሴቶቻችንና ልጆቻችንም ምርኮ
ናሉ ፤ ወደ ግብፅ መመለስ አይሻለን
?» አሉአቸው ። እርስ በርሳቸውም
መካከረው ፤ «ኑ ፤ አለቃ ሾመን ወደ
ፅ እንመለስ» ተባባሉ ።

ዚያን ጊዜ ግን ሙሴና አሮን በግምባ
ው ወደቁ ። ምድሪቱንም ከሰለሉት
ች ሁለቱ ፤ እነርሱም ኢያሱና ካሌብ
ሳቸውን ቀድደው ፤ «ዞረን የሰለልናት
ር እጅግ መልካም ናት ። እግዚአብሔ
ከወደደን ወደዚያች ምድር ያገባናል ፤
ዋንም ይሰጠናል ። ተው ፤ በእግዚአ

ብሔር ላይ አታምፁ ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩአቸው» አሉ ። ማኅበሩ ግን ኢያሱንና ካሌብን በድንጋይ ለመውገር ተማከሩ እንጂ አልሰሙአቸውም ።

፬ ፤ የእግዚአብሔር ውሳኔ ።

ዘኍ. ፲፬ ፤ ፲ - ፴፭ ፤ ዘዳግ. ፩ ፤ ፴፬ - ፴፭ ።

በዚያን ጊዜም የእግዚአብሔር ክብር ለእስራኤል ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ተገለጠ ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፤ «ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ድረስ ይንቀኛል ? በፊታቸውስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከ መቼ አያምኑብኝም ? በቸነፈር እመታቸዋለሁ ፤ ከአንተም ከእነርሱ የሚበዛና የሚጠነክር ሕዝብ አደርጋለሁ» አለው ። ሙሴም መልሶ ፤ «ግብፃውያን ሰምተው ለዚች ምድር ሰዎች ፤ እግዚአብሔር ወደ ማለላቸው ምድር ሊያገባቸው አልቻለምና በምድረ በዳ አጠፋቸው ብለው ይናገራሉ ። አሁንም እባክህ ፤ እግዚአብሔር ታጋሽና ምሕረቱ የበዛ ነው ብለህ እንደ ተናገርህ ፤ የጌታ ኃይል ታላቅ ይሁን ። ይህን ሕዝብ ከግብፅ ካወጣህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይቅር እንዳልሃቸው ፤ እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት ኃጢአታቸውን ይቅር በል» ብሎ ጸለየ ።

እግዚአብሔርም ፤ «እንደ ቃልህ ይቅር አልሁ ፤ ነገር ግን እኔ ሕያው ነኝና በእውነት ክብሬ ምድርን ሁሉ ይሞላል ። በግብፅና በምድረ በዳ ያደረግሁትን ተአምራቴን ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ ነገሬን ስላልሰሙ ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን ምድር አያዩም ። ባሪያዬ ካሌብ ግን ፈጽሞ ስለ ተከተለኝ እርሱ ወደ ገባበት አገር አገባዋለሁ ፤ እርሱና ኢያሱም ይገቡበታል ። በነጋውም ተመልሳችሁ ወደ ምድረ በዳ ሂዱ ። ምድሪቱንም በሰለላችሁበት ቀን



ቍጥር ፤ ዐርባ ቀን ፤ ስለ አንድ ቀንም አንድ ዓመት ፤ ኃጢአታችሁን ዐርባ ዓመት ትሸከማላችሁ» አለው ። ክፉ ወሬ በማውራታቸው ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ እንዲያጕረመርሙ ያደረጉ አሥሩ ሰላዮችም በዚያኑ ጊዜ ተቀሥፈው ሞቱ ።

ሙሴም ሕዝቡን ፤ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ እኔ ሕያው ነኝና በጆሮዬ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ አደርግባችኋለሁ ፤ በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ ። ምርኮኛ ይሆናሉ ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን ወደ ከነዓን አገባቸዋለሁ ፤ እናንተ ግን አትገቡም ። በድኖቻችሁ በምድረ በዳ እስኪጠፉ ድረስ ልጆቻችሁ ዐርባ ዓመት እየተቅበዘበዙ ኃጢአታችሁን ይሸከማሉ» ብሎ ነገራቸው ። ሕዝቡም እጅግ አዘኑ ።

በነጋውም ማልደው ተነሡና ሙሴን ፤ «እኛ በድለናል ፤ አሁን ግን እግዚአብሔር ወዳለው ምድር እንወጣለን» አሉ ። ሙሴም ፤ «እግዚአብሔር በመካከላችሁ አይደለም ፤ በጠላቶቻችሁ ፊት እንዳትወድቁ አትውጡ» አላቸው ። እነርሱ ግን ወደ ተራራው ሊወጡ ደፈሩ ፤ በዚያም የተቀመጡ ሰዎች ተነሡባቸው ፤ ንብ እንደ ምታሳድድም አሳደዱአቸው ።

* * *

በምድረ በዳ እንደ ተፈታተኑት እንዳስቈጡት ጊዜ ፤
ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ ።

መዝ. ፺፬ (፺፭) ፤ ፰ ።

ወንድሞች ሆይ ፤ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፋና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ ፤ ነገር ግን . . . . ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ፤ በማስመረር እንደሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ ።

ዕብራ. ፫ ፤ ፲፪ - ፲፭ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሰላዮች ስለ ከነዓን የተናገሩት መልካምና ክፉ ወሬ ምንድር ነው ?
፪ ፤ ሕዝቡ ፤ ተስፋ ወደ ተደረገላቸው አገር እንዳይወጡ መፍራት ይገባቸው ነበርን ?
፫ ፤ ከሰላዮቹስ በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ያመኑ እነማን ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፤ የዓመፅን መንገድ ከእኔ አርቅ ፤
በሕግህም ማረኝ ፤
የእውነትህን መንገድ መረጥሁ ፤
ፍርድህንም አልረሳሁም ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፤ ፳፱ ፡ ፴ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፮ ።

## ቃዴስ ወደ ዮርዳኖስ ።

ዘኍ. ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፴፪ ።



፡ የዐርባ ዓመት መቅበዝበዝ ።

ዘዳግ. ፪ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ፡ ፪ - ፰ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ፡ ፪ - ፭ ፡ ዘኍ. ፳ ፡ ፩ ።

ስራኤል ተመልሰው እስከ ብዙ ዓመት ረስ በሴይር ተራራ እየዞሩ በምድረ በዳ ቅበዘበዙ ከሠፈሩ መካከል ተቈርጠው ስኪጠፉ ድረስ የእግዚአብሔር እጅ በሰ ፈኞች ትውልድ ላይ ነበረ ። እግዚአብ ሔር አምላክ ግን ከሕዝቡ ሳይለይ ፡ ሰው ጁን እንደሚገሥጽ እየገሠጸ ፡ በሚሄዱ ት መንገድ ሁሉ ሲመራቸው ልብስን ማርጀት ፡ እግርን ከማበጥ እየጠበቀ ላት ዕለት መናን ይመግባቸው ነበር ።

ከብዙ ቀንም በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ፡ «ይህን ተራራ መዞር ይበቃች ል ፤ ተመልሳችሁ ወደ ሰሜን ሂዱ ። በሴይር በተቀመጡት በወንድሞቻችሁ በዔሳው ልጆች አገር ታልፋላችሁ ። ነገር ግን ተጠንቀቁ ፤ ሴይርን ለዔሳው ርስት አድርጌ ስለ ሰጠሁ ከምድራቸው የጫማ መርገጫ ታህል አልሰጣችሁምና አትጣሉአቸው ። እንደዚሁም ለሎጥ ልጆች ለሞዓብና ለአሞን የሚኖሩባቸውን አገሮች ርስት አድርጌ ስለ ሰጠሁ አትጣሉአቸው» አለው ። ማኅበሩም ሁሉ ወደ ቃዴስ ተመልሰው ሠፈሩ ፤ የሙሴም እኅት ማርያም በዚያ ሞተች ፡ ተቀበረችም ።

፪ ፡ የመሪባ ውኃ ።

ዘኍ. ፳ ፡ ፪ - ፲፫ ፡ መዝ. ፩፻፭ (፩፻፮) ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።

ማኅበሩም ውኃ አላገኙም ፤ በሙሴና በአሮንም ላይ ተሰብስበው ፡ «ወደዚህ ክፉ ሥፍራ እንድታመጡን ከግብፅ ለምን አወጣችሁን ? የእህል ዘርና በለስ ወይንም ሮማንም የሌለበት ሥፍራ ነው ፤ የሚጠጣም ውኃ የለበትም» እያሉ እንደገና በእግዚአብሔር ላይ አንጐራጐሩ ። ሙሴም ገና በእግዚአብሔር ባለመተማመናቸው ተበሳጨ ፡ ከአሮንም ጋር ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሄደ ። በግምባራቸውም ወደቁ ፡ የእግዚአብሔርም ክብር ተገለጠላቸው ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «በትርህን ውሰድ ፤ አንተና አሮንም ማኅበሩን ሰብስቡ ፡ እነርሱም እያዩ ውኃ እንዲሰጥ ድንጋዩን ተናገሩት» አለው ።

ሙሴና አሮንም ጉባዔውን በድንጋዩ ፊት ሰብስበው ፡ «እናንተ ዓመፀኞች ስሙ ፤ በውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃ እናወጣላችኋለን ? » አሏቸው ። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው ፤ ብዙም ውኃ ወጣ ፡ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ ።

ነገር ግን ሙሴና አሮን የተናገሩት ነገር እግዚአብሔርን ደስ አላሰኘም ፤ እግዚአብሔርም ፡ «በእስራኤል ሕዝብ ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ አላመናችሁምና ወደ ሰጠኋቸው ምድር ይህን ሕዝብ ይዛችሁ አትገቡም» አላቸው ። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ጠብ ያደረጉበት ፡ እርሱም ቅዱስ መሆኑን የገለጠበት ፡ ይህ በቃዴስ ያለው የመሪባ* ውኃ ነው ።

፫ ፡ የነሐስ እባብ ።

ዘኍ. ፳ ፡ ፲፬ - ፳፱ ፡ ፳፩ ፡ ፬ - ፱ ።

ሙሴም ከቃዴስ ወደ ኤዶምያስ ንጉሥ መልእክተኞችን እንዲህ ብሎ ላከ ፤ «ወንድምህ እስራኤል እንዲህ ይላል ፤ ያገኘንን መከራ ሁሉ አንተ ታውቃለህ ። እባክህ በምድርህ ላይ እንለፍ ፡ ወደ እርሻም ወደ ወይንም አንገባም ፡ ከውኃህ ብንጠጣ ዋጋውን እንከፍላለን ፤ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ሳንልም በንጉሥ ጐዳና እንሄዳለን ።» የኤዶም ንጉሥም ፡ «አታልፍም» ብሎ ተቃወመው ። ስለዚህ እስራኤል ከእርሱ ተመልሰው ወደ ሖር ተራራ መጡ ። አሮንም በዚያ ሞተ ፤ ልጁ አልዓዛርም የካህናት አለቃ ሆነ ።

ከሖርም ተራራ ተነሥተው ከኤዶምያስ አገር ርቀው ሲጓዙ ከመንገዱ የተነሣ የሕዝቡ ሰውነት ደከመ ። በእግዚአብሔርና በሙሴም ላይ አጕረምርመው ፡ «በምድረ በዳ እንድንሞት ለምን አወጣችሁን ? እንጀራና ውኃ በዚህ የለም ፤ ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ» አሉ ። እግዚአብሔርም እባቦችን ሰደደባቸው ፡ ሕዝቡንም ነደፉ ፤ ከእስራኤልም ብዙዎች ሞቱ ። ሕዝቡም ወደ ሙሴ መጥተው ፡ «በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ስለ ተናገርን በድለናል ፤ እባቦችን ከእኛ እንዲያርቅ ጸልይልን» አሉት ። ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «እባብን ሠርተህ በምሰሶ ላይ ስቀል ፡ የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል» አለው ። ሙሴም ከነሐስ እባብን ሠርቶ በምሰሶ ላይ ሰቀለ ፤ እባቡም የነደፈችው ሰው ሁሉ የነሐሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ ።

፬ ፡ የሴዎንንና የአግን ምድር መውረስ ።

ዘኍ. ፳፩ ፡ ፲ - ፳፪ ፡ ፩ ፡ ፴፪ ፡ ፩ - ፵፪ ።

እስራኤላውያን ጕዞአቸውን በመቀጠል ከጨው ባሕር ወደ ምሥራቅ በሞዓብ በረሀ ወዳለው ሸለቆ ደረሱ ። ከሠፈሩበት ሥፍራና ከዮርዳኖስ መካከል ባለው አገርም አሞራውያን ተቀምጠው ስለነበር ሙሴ ፡ «በምድርህ ላይ እንለፍ» የሚሉ መልእክተኞችን ወደ አሞራውያን ንጉሥ ወደ ሴዎን ላከ ። ሴዎንም ከእስራኤል ጋር



www.ethiopianorthodox.org

ሊዋጋ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ሁለቱን የአሞራውያንን ነገሥታት ፡ ሴዎንንና አግን በእስራኤል እጅ ጣላቸው ። እስራኤልም ሰፊ የሆነውን የአሞራውያንን አገር ይዘው ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ከኢያሪኮ ፊት ለፊት ሠፈሩ ።

የሮቤልና የጋድ ልጆችም ሙሴንና የማኅበሩን አለቆች ፡ «ይህ ምድር ለእኛና ለእንስሶቻችን የተመቸ ነውና ርስት አድርገህ ስጠን ፤ ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን» አሉ ። ሙሴም መልሶ ፡ «ወንድሞቻችሁ ወደ ጦርነት ሲሄዱ እናንተ በዚህ ትቀመጣላችሁን ? ከቃዴስ የሰደድኋቸው ሰላዮች እንዳደረጉ ወደ ምድሪቱ እንዳይሻገሩ የወንድሞቻችሁን ልብ ለምን ታደክማላችሁ ? » ብሎ ገሠጻቸው ።

የሮቤልና የጋድ ልጆችም ፡ «በዚህ ለእንስሶቻችን በረቶች ለልጆቻችንም ከተሞች እንሠራለን ፤ እኛ ግን ለጦርነት ተዘጋጅተን ወደ ሥፍራቸው እስክናገባቸው ድረስ በእስራኤል ልጆች ፊት እንሄዳለን» አሉት ። ሙሴም ፡ «ይህንስ ነገር ካደረጋችሁ ንጹሐን ትሆናላችሁ ፤ ይህችም ምድር ርስት ትሆንላችኋለች» ብሎ በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በገቡባት ምድር ለሮቤልና ለጋድ ነገዶች ፤ እንደዚሁም ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስትን አካፈላቸው ።

* * *

ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳንጐራጐሩ በሚያጠፋውም እንደ ጠፉ አታንጐራጕሩ ። ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው ፤ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ ።
፩ ቆሮ. ፲ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።

ሰው ልጁን እንደሚገሥጽ እንዲሁም አምላክህ እግዚአብሔር አንተን እንዲገሥጽ በልብህ አስተውል ። ዘዳግ. ፰ ፡ ፭ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፡ ሙሴና አሮን ወደ ከነዓን እንዳይገቡ ለምን ተከለከሉ ?
፪ ፡ በሕዝቡ መካከል እባቦች የተሰደዱ በምን ምክንያት ነው ?
፫ ፡ በእባብ የተነደፈው ሰው እንዲድን ምን ማድረግ ነበረበት ?
፬ ፡ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ርስትን የተቀበሉ እነማን ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ፍርድህ ጽድቅ እንደሆነች ፡
በእውነትህም እንዳስቸገርኸኝ ዐወቅሁ ።
ምሕረትህ ለመጽናናቴ ትሁነኝ ፡
እንደ ቃልህም ለባሪያህ ይሁነው ።
መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፸፭ ፡ ፸፮ ።

* መሪባ ማለት ክርክር ማለት ነው ፤ ከዘጸ. ፲፯ ፡ ፯ ጋር ይነጻጸር ።





ምዕራፍ ፯ ።

## ባላቅና በለዓም ።

ዘኍ. ፳፪ - ፳፯ ፡ ፴፩ ።

### ፩ ፤ ባላቅ በለዓምን አስጠራው ።

ዘኍ. ፳፪ ፡ ፩ - ፳ ።

ባላቅ የተባለ የሞዓብ ንጉሥ የአሞራውያን ነገሥታት እንደ ተሸነፉ ባየ ጊዜ እስራኤልን እጅግ ፈራ ። ከምድያም ሽማግሌዎች ጋር ተባብሮ ስለ ሟርት የሚከፈል ዋጋን አስይዞ መልእክተኞችን በኤፍራጥስ ወንዝ አቅራቢያ ወደሚኖረው በለዓም ወደ ተባለው ነቢይ ልኮ ፡ «እነሆ ከግብፅ የወጣ ሕዝብ የምድሩን ፊት ሁሉ ሸፈነ ፤ አሁንም እንዳሸንፋቸው ና ርገምልኝ» ብሎ አስጠራ ። በለዓምም ፡ እግዚአብሔር የሚነግረውን እስኪያውቅ ድረስ መልእክተኞቹን በእርሱ ዘንድ አሳደራቸው ። እግዚአብሔርም ፡ «አትሂድ ፤ የተባረከ ነውና ሕዝቡን አትረግምም» ብሎ በዚያ ሌሊት ነገረው ። በለዓምም ለሰዎቹ፡ «እግዚአብሔር አልፈቀደልኝምና ሂዱ» ብሎ አሰናበታቸው ።

ባላቅም ከፊተኞች የበዙና የከበሩ ሌሎች አለቆችን ሰደደ ። እነርሱም ወደ በለዓም መጥተው ፡ «ንጉሡ ፡- ክብርህን እጅግ ታላቅ አደርገዋለሁ ፡ የተናገርኸውንም ሁሉ አደርግልሃለሁ ፤ እባክህ ና ፡ ይህን ሕዝብ ርገምልኝ ብሎሃል» አሉት ። በለዓምም ገንዘብን ስለ ወደደ የተረዳውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይከተል ፡ «እግዚአብሔር የሚነግረኝን እንዳውቅ በዚህ እደሩ» ብሎ መለሰላቸው ። እግዚአብሔርም የበለዓምን አሳብ ዐውቆ ፡ «ከእነርሱ ጋር ሂድ ፡ ነገር ግን የምነግርህን ብቻ ታደርጋለህ» ብሎ አስጠነቀቀው ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ በለዓም በአህያ ተዘለፈ ።

ዘኍ. ፳፪ ፡ ፳፩ - ፴፭ ፡ ፪ ጴጥ. ፪ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።

ቀኑ ሲነጋም በለዓም በአህያዪቱ ላይ ተቀ
ምጦ ከሰዎቹ ጋር ሄደ ፤ የእግዚአብሔር
መልአክ ግን የተመዘዘ ሰይፍ ይዞ ሊቋቋ
መው በመንገድ ላይ ቆመ ። አህያዪቱም
የእግዚአብሔርን መልአክ አይታ ፈቀቅ
ኣለች ፤ በለዓምም መታት ። የእግዚአብሔ
ርም መልአክ በግንቦች መካከል በሚያ
ልፍ ጠባብ መንገድ ላይ ቆመ ፤ አህያዪ
ቱም ወደ ግንቡ ተጠግታ የጌታዋ እግር
እንዲጣበቅ አደረገች ። እርሱም ደግሞ
መታት ። የእግዚአብሔርም መልአክ ወደ
ፊት ሄዶ መተላለፊያ በሌለበት እጅግ
ጠባብ በሆነ ሥፍራ ቆመ ። አህያዪቱም
ጌታዋ እንደ ተቀመጠባት ተኛች ፤ በለዓ
ምም እጅግ ተቈጥቶ ደበደባት ።

እግዚአብሔር ግን የአህያዪቱን አፍ
ከፈተ ፤ በለዓምንም ፡ «ሦስት ጊዜ የመታ
ሽኝ ምን አድርጌብህ ነው ? » አለችው ።
እርሱም ፡ «ስላላገጥሽብኝ ነው ፤ በእጄስ
ሰይፍ ቢኖር አሁን በገደልሁሽ ነበር»
አላት ። እርስዋም ፤ «ከብዙ ዘመን ጀምሮ
የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን ?
እንዲህስ ለማድረግ ልማዴ ነበረን ?» አለ
ችው ። «እንዲህ አላደረግሽም» አላት ።

እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች
ከፈተ ፤ እርሱም የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ የእ
ግዚአብሔርን መልአክ አየ ፤ በግምባሩም
ወደቀ ። የእግዚአብሔርም መልአክ ፡
«መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና ልቋቋ
ምህ ወጥቼአለሁ ። አህያዪቱ አይታኝ
ከፊቴ ፈቀቅ ባትል ኑሮ አንተን ገድዬ እር
ስዋን ባዳንኳት ነበር» አለው ። በለዓምም፡
«በድያለሁ ፤ አሁንም አትወድ እንደሆነ
እመለሳለሁ» አለው ። የእግዚአብሔርም
መልአክ ፡ «ሂድ ፡ ነገር ግን የምናገርህን
ቃል ብቻ ትናገራለህ » አለው ። በለዓምም
ሄደ ።



፫ ፡ በለዓም እስራኤልን ባረከ ።

ዘኍ. ፳፪ ፡ ፴፮ - ፳፬ ፡ ፳፭ ።

ባላቅም በለዓምን ሊገናኝ ወጥቶ ፡ «ለምን አልመጣህም ? በውኑ ላከብርህ አልችል ምን ? » አለው ። በለዓምም መልሶ ፡ «እነሆ መጥቼአለሁ ፤ በውኑ አንዳችን ነገር እንድናገር እችላለሁን ? እግዚአብሔር በአፌ የሚያደርገውን ቃል እርሱን እናገራለሁ» አለው ።

በነጋውም ባላቅ በለዓምን ይዞ የእስራኤል ሠፈር ወደሚታይበት ወደ አንድ ኮረብታ አወጣው ። በለዓምም እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ሲናገር እንዲህ አለ :-

« ባላቅ ከአራም አመጣኝ ፤ . . . .
ና ፡ ያዕቆብን ርገምልኝ . . . ብሎ ። . . .
እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ ? . . . .
እነሆ ብቻውን የሚቀመጥ ሕዝብ ነው ፤
በአሕዛብም መካከል አይቈጠርም ።
የእስራኤልን እርቦ ማን ይቈጥራል ?
የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት ፤
ፍጻሜዬም እንደ እርሱ ፍጻሜ ትሁን ። »

ባላቅም ፡ «ያደረግህብኝ ምንድር ነው ? ጠላቶቼን ፈጽመህ ባረክሃቸው» አለው ። በለዓምም መልሶ ፡ «በውኑ እግዚአብሔር በአፌ ያደረገውን እንድናገር አልጠነቀቅምን ?.» አለ ። ባላቅም በለዓምን ወደ ሌላ ቦታ ፡ እንደገናም ወደ ሦስተኛ ቦታ ቢወስደው እንዲሁ እስራኤልን ባረከ ፡ ሲባርካቸውም እንዲህ አለ :-

« ባላቅ ሆይ ፡ ተነሣ ፡ ስማ ፤ . . .
ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም ፤
ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም ።
እርሱ ያለውን አያደርገውምን ?
የተናገረውንስ አይፈጽመውምን ?
እነሆ ለመባረክ ትእዛዝን ተቀብያለሁ ፤
እርሱ ባርኮአል ፡ እመልሰውም ዘንድ አልችልም ። . . .
በያዕቆብ ላይ አስማት የለም ፤
በእስራኤልም ላይ ሟርት የለም ፤
በጊዜው ስለ ያዕቆብና ስለ እስራኤል ፤
እግዚአብሔር ምን አደረገ ! ይባላል ።»

ባላቅም በለዓምን ተቈጣ ፡ እጁንም አጨብጭቦ ፡ «ሦስት ጊዜ ጠላቶቼን ፈጽመህ ባረክሃቸው ፡ አሁንም ወደ ሥፍራህ ሽሽ ፡ እኔ ላከብርህ ወድጄ ነበር ፡ እግዚአብሔር ግን ክብርህን ከለከለ» አለው ። በለዓምም እንደገና ስለ እስራኤል የትንቢትን ቃል ተናግሮ መንገዱን ሄደ ።

፬ ፡ የበለዓም ክፉ ምክር ። ዘኍ. ፳፭ ፡ ፩ - ፱ ፡ ፳፮ ፡ ፩ - ፳፭ ፡ ፴፩ ፡ ፩ - ፲፱ ፡ (ራእይ ፪ ፡ ፲፬ ።)

በለዓም እስራኤልን የባረከው ፈቅዶ ሳይሆን በግድ እንደ ነበረ ለባላቅ በሰጠው ምክር ይታያል ። እርሱም ባላቅን ፡ እስራኤልን ለማሰናከል ብትወድ የሞዓብና የምድያም ሴቶች እስራኤላውያንን ወደ አምላኮቻቸው መሥዋዕት በመጥራት የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲተላለፉ ይፈትኑአቸው ብሎ መከረው ። ብዙዎች እስራኤላውያን በዚህ ፈተና ተጸምደው ከሞዓባውያን ጋር እየበሉና እየጠጡ ብዔልፌጎር ለተባለው ጣዖት ሰገዱ ፡ ከሞዓባውያን ሴቶችም ጋር ያመነዝሩ ጀመር ። እግዚአብሔርም እስራኤልን ቀሠፈ ፤ በመቅሠፍቱም የሞቱ ሃያ አራት ሺህ ነበሩ ። ከዚህም በኋላ እስራኤል ከምድያማውያን ጋር ተዋግተው አሸነፉአቸው ። በሰይፍ ከተገደሉትም መካከል ፡ በክፉ ምክሩ ያሰናከላቸው ነቢዩ በለዓም ነበረ ።

ብዔልፌጎርን የተከተሉት በመቅሠፍት ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ፤ «ከእስራኤል ወደ ሰልፍ ሊወጣ የሚቻለውን ሁሉ ቍጠር» አለው ። ሙሴና አልዓዛርም ሕዝቡን ቈጠሩአቸው ፤ እነሆም በሲና ምድረ በዳ ከተቈጠሩ ሰዎች ፤ ከካሌብና ከኢያሱ በቀር የቀረ ሰው አልነበረም ። «ወደ ከነዓን ልንገባ አንችልም» ብለው ያመፁት ሁሉ ሞተው ነበር ።

* * *

ጠማማ ልብ ያለው መልካምን አያገኝም ፤
ምላሱንም የሚገለብጥ በክፉ ላይ ይወድቃል ።

ምሳሌ ፲፯ ፡ ፳ ።

አምላካችን እርግማኑን ወደ በረከት መለሰው ።

ነሀ. ፲፫ ፡ ፪ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ባላቅ በለዓምን ያስጠራው ምን እንዲያደርግለት ነበረ ?
፪ ፡ እግዚአብሔር እንዳይሄድ ከከለከለው በኋላ በለዓም ለምን ሁለተኛ ጊዜ ጠየቀ ?
፫ ፡ እግዚአብሔርን አለማክበሩ ወደ ጥቅም አደረሰው ወይስ ወደ ጉዳት ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ልቤን ወደ ምስክርህ አዘንብል ፡
ወደ ስስትም አይሁን ።
ከንቱ ነገርን እንዳያዩ ዓይኖቼን መልስ ፤
በመንገድህም ሕያው አድርገኝ ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፰ ።

# የሙሴ ስንብትና የኢያሱ መሾም ።

ዘዳግ. ፯ - ፱ ፡ ፳፯ - ፴፩ ።

የሙሴ ኑዛዜ ።

ዘዳግ. ፰ ፡ ፩ - ፳ ፡ ፯ ፡ ፩ - ፯ ፡ ፱ ፡ ፩ - ፯ ።

ርዳኖስ ማዶ ሳሉ ሙሴ ጊዜ ሞቱ እንደ
በ ዐውቆ ለእስራኤል ሁሉ እንዲህ ብሎ
ገረ ፤ «በሕይወት እንድትኖሩ ፡ እንድ
ዙም ፡ እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ
ማለላችሁ ምድር ገብታችሁ እንድት
ርሱአት ፡ ዛሬ የማዝዘውን ትእዛዝ ሁሉ
በቁ ። አምላክህ እግዚአብሔር በልብህ
ውን ትእዛዝ ትጠብቅ ወይም አትጠ
እንደሆነ ያውቅ ዘንድ በእነዚህ ዐርባ
ዓታት በምድረ በዳ እንዴት እንደ
ራህ አስብ ። ሰውም ከእግዚአብሔር
በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲ
እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳ
ይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ ፡ አስራበህም ፡ ያላወቅኸውንም መና አበላህ ።

«አምላክህ እግዚአብሔር አንዳች ወደ ማታጣባት ወደ መልካም ምድር ያገባሃል ። ነገር ግን በልተህ ስትጠግብ ፡ መልካምም ቤት ሠርተህ ስትቀመጥበት ፡ ላምና በግ ፡ ብርና ወርቅም ሲበዛልህ ልብህ አይኩራ ፤ ከግብፅም ባርነት ያወጣህን ፡ እባብና ጊንጥ ጥማትም ባለበት በታላቂቱና በምታስፈራው ምድረ በዳ የመራህን አምላክህን አትርሳ ፤ በልብህም ፡ ጉልበቴ ይህን ሀብት አመጣልኝ አትበል ። ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ ።



እርሱን ብትረሳ ፡ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል ከምትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ ፡ ትጠፋላችሁም ።

«አምላክህ እግዚአብሔር ልትወርሳት ወደምትገባባት ምድር ባመጣህ ጊዜ ፡ በእጅህ አሳልፎ ከሰጣቸው ጣዖታትን ከሚያመልኩ ሕዝቦች ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ ፡ አትማራቸውም ፤ ከእነርሱም ጋር አትጋባ ። እንዳይከተለኝ ፡ ሌሎችንም አማልክት እንዲያመልክ ልጅህን እንዳያስት ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ ፡ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ ። መሠዊያቸውንም አፍርስ ፡ ጣዖታታቸውንም ሰባብረህ አቃጥል ።

«እስራኤል ሆይ ፡ ከአንተ የበረቱትን ታላላቅና ረጃጅም ሕዝቦች ለማሸነፍ ዮርዳኖስን ትሻገራለህ ። አምላክህም እግዚአብሔር እንደሚበላ እሳት ሆኖ በፊትህ አልፎ ያዋርዳቸዋልና አንተ ፦ ስለ ጽድቄ እወርሳት ዘንድ ወደዚች ምድር አገባኝ ብለህ በልብህ አትናገር ። ምድራቸውን የምትወርሰው ስለ ጽድቅህና ስለ ልብህ ቅንነት አይደለም ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ ሕዝቦች ኃጢአት ምክንያትና ለአባቶችህ የማለላቸውን ቃል እንዲፈጽም ነው ። እንግዲህ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነህና አምላክህ እግዚአብሔር ይህችን መልካም ርስት የሰጠህ ስለ ጽድቅህ እንዳይደለ ዕወቅ ።»

፪ ፡ በረከትና መርገም ።

ዘዳግ. ፳፯ ፡ ፩ - ፴ ፡ ፳ ።

ሙሴም እንዲህ ብሎ ሕዝቡን አዘዘ ፤ «ዮርዳኖስን በተሻገርህ ጊዜ የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ በታላላቅ ድንጋዮች ጽፈህ በጌባል ተራራ አቁም ፡ በኖራም ምረጋቸው ። በዚያም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርተህ መሥዋዕትህን አቅርብበት ፤ በዚያም ብላ ፡ በአምላክህ በእግዚአብሔርም ፊት ደስ ይበልህ ። በዚያን ጊዜም ሕዝቡን ይባርኩ ዘንድ ስምዖንና ሌዊ ይሁዳና ይሳኮር ዮሴፍና ብንያም በገሪዛን ተራራ ላይ ይቁሙ ። ይረግሙም ዘንድ ሮቤልና ጋድ አሴርና ዛብሎን ዳንና ንፍታሌም በጌባል ተራራ ላይ ይቁሙ ። ሌዋውያንም የሕጉን ቃሎች ሁሉ በረከቱንና እርግማኑን ያንብቡ ፤ ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይበል ።»

ሙሴም ፤ መታዘዝ በረከትን ፡ አለመታዘዝ ግን እርግማንን እንደሚያስከትሉ በግልጥ ካሳየ በኋላ ፤ «በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት እንድትኖሩ ሕይወትን ምረጥ ። እርሱ ሕይወትህ ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወደው ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ» አላቸው ።

፫ ፤ የሙሴ ቡራኬና ሞት ። ዘኍ. ፳፯ ፡ ፲፪ - ፳፫ ፤ ዘዳግ. ፴፩ ፡ ፩ - ፲፫ ፡ ፴፪ ፡ ፵፰ - ፴፬ ፡ ፲፪ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «ወደዚህ በኢያሪኮ አንጻር ወዳለው በዓባሪም ተራራ ውስጥ ወዳለው ወደ ናባው ተራራ ውጣ ፡ ለእስራኤልም ርስት አድርጌ የምሰጣቸውን የከነዓንን ምድር እይ ፡ በወጣህበትም ተራራ ትሞታለህ ፡ ወደ ወገኖችህም ትከማቻለህ» አለው ።

ሙሴም እግዚአብሔርን ፡ «የእግዚአብሔር ማኅበር እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን በፊታቸው የሚወጣውን የሚገባውንም ሰው የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአብሔር በማኅበሩ ላይ ይሹመው» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «መንፈስ ያለበትን ሰው የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን በላዩ ጫንበት ፤ በካህኑ በአልዓዛርና በማኅበሩ ሁሉ ፊት አቁመው ፡ እነር

www.ethiopianorthodox.org

ሱም እያዩ እዘዘው ። ማኅበሩም ሁሉ እንዲታዘዙት ከክብርህ አኑርበት» አለው ።

ሙሴም ሄዶ ለእስራኤል ሁሉ እንዲህ አላቸው ፤ «እኔ ዛሬ መቶ ሃያ ዓመት ሆኖኛል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ዮርዳኖስን አትሻገርም ብሎኛል ። አምላካችሁ እግዚአብሔር እርሱ በፊታችሁ ያልፋል ፤ እርሱም እንደ ተናገረ ኢያሱ በፊታችሁ ይሻገራል ። ጽኑ ፡ አይዞአችሁ ፡ አትፍሩ ፡ አትደንግጡም ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር እርሱ ከእናንተ ጋር ይሄዳል ። አይጥልህም ፡ አይተውህምም ።» ኢያሱንም ጠርቶ ፡ «አንተ ከዚህ ሕዝብ ጋር እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ትገባለህ ለእርሱ ታወርሳታለህና ጽና ፡ አይዞህ ። እግዚአብሔር በፊትህ ይሄዳል ፡ ከአንተም ጋር ይሆናል ፡ አይጥልህም ፡ አይተውህምም ፡ አትፍራ ፡ አትደንግጥ» አለው ።

ሙሴም የተሰጠውን ሕግ ጻፈ ፤ የቃል ኪዳኑንም ታቦት ይሸከሙ ለነበሩት ሌዋውያን ለእስራኤልም ካህናትና ሽማግሌዎች ሁሉ ሰጥቶ ፡ «በየሰባት ዓመት መጨረሻ ፡ በዳስ በዓል ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ወንዶችንና ሴቶችን ሕፃናቶችንም በአገራችሁ ያለውንም መጻተኛ ሰብስባችሁ ይህን ሕግ በእስራኤል ሁሉ ፊት በጆሮው አንብቡት ። ሕግን የማያውቁ ልጆቻቸውም እግዚአብሔርን መፍራት ይማሩ» አላቸው ።

ሙሴም የእስራኤልን ነገዶች ሁሉ እያንዳንዳቸውን ባረከ ፤ ከባረካቸውም በኋላ ወደ ናባው ተራራ ወደ ፈስጋ ራስ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ምድሪቱን አሳይቶ ፡ «ለዘርህ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማልሁላቸው ምድር ይህች ናት» አለው ። የእግዚአብሔርም ባሪያ ሙሴ በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ ። ዕድሜውም መቶ ሃያ ዓመት ነበረ ፤ ዓይኑ አልፈዘዘም ፡ ጕልበቱም አልደከመም ። እስራኤልም ሁሉ ሠላሳ ቀን አለቀሱለት ።

* * *

እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሣም ።

ዘዳግ. ፴፬ ፡ ፲ ።

እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ ።

ዘዳግ. ፴ ፡ ፳ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ እግዚአብሔር ከነዓንን ለእስራኤል ያወረሰ ስለምን ነበረ ?
፪ ፡ ሕዝቡ ሲበለጽግ እንዳይኰራ ሙሴ ምን ተናገረ ?
፫ ፡ ሙሴ በሕዝብ ፊት ያቀረበው ምርጫ ምን ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ትእዛዛትህን መርጫለሁና
እጅህ የሚያድነኝ ይሁን ።

መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፡ ፻፸፫ ።





ምዕራፍ ፱ ።

## የእስራኤል ዮርዳኖስን መሻገር ።

ኢያሱ. ፩ - ፫ ።

### ፩ ፡ ለኢያሱ የተሰጠ መመሪያ ።

ኢያሱ ፩ ፡ ፩ - ፱ ።

እግዚአብሔር ለሙሴ አገልጋይ ለኢያሱ ወልደ ነዌ እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ «ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል ፤ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ ይህን ዮርዳኖስን ተሻገሩ ። በዕድሜህ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ፤ ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፤ አልጥልህም ፡ አልተውህምም ፡ ጽና ፡ አይዞህ ። ነገር ግን ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ ፡ አድርገውም ። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው ፤ ያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ፡ ይከናወንልሃልም ። ጽና ፡ አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን ?»

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ ፡ የኢያሪኮ መሰለል ።

ኢያሱ ፪ ፡ ፩ - ፳፬ ።

ኢያሱ ሁለት ሰዎችን መርጦ ፡ «ሂዳችሁ ኢያሪኮን እዩ» ብሎ በስውር ላካቸው ። እነርሱም ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ኢያ ሪኮ ደረሱ ፤ ከተማዪቱም በትልቅ ቅጥር የተመሸገች መሆንዋን አዩ ። በከተማዪ ቱም በር ገብተው በቅጥሩ ላይ ወደ ተሠ ራው ረዓብ የምትባል ጋለሞታ ወደምትኖ ርበት ቤት ገቡ ።

የኢያሪኮም ንጉሥ ፡ የእስራኤል ሰዎች አገሩን ሊሰልሉ ገቡ ሲባል ወሬ ሰማ ፤ ይዘ ውም እንዲያመጡለት መልእክተኞችን ወደ ረዓብ ላከ ። እርስዋ ግን ወደ ሰገ ነት አውጥታ በረበረበችው የተልባ እግር ውስጥ እንዲሸሸጉ አደረገች ። የንጉሡን መልእክተኞችም ፡ «ወደ እኔ የመጡ ሰዎች ፡ የከተማዪቱ በር በተዘጋበት ሰዓት በምሽት ወጡ ፤ ፈጥናችሁ ተከተሉአ ቸው» ብላ ከሰደደቻቸው በኋላ ወደ ሰላ ዮቹ ተመልሳ ፡ «እግዚአብሔር ይህችን ምድር እንደ ሰጣችሁ ዐወቅሁ ። ከግ ብፅ በወጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ባሕርን በፊታችሁ እንዳደረቀ ፡ በዮርዳኖስም ማዶ በነበሩት ነገሥታት በሴዎንና በአግ ያደረጋችሁትን ሁሉ ሰምተናል ፤ ይህንን ሁሉ በሰማን ጊዜ ልባችን ቀለጠ ፡ እናንተ ንም መፍራት ወደቀብን ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ፡ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና ከዚያ ወዲያ ማንም ነፍስ አልቀረለትም ። አሁንም በአምላካችሁ እኔ ቸርነት እንዳደረግሁላችሁ እናንተ ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት አድ ርጉ ፡ ከተማዪቱንም በምትይዙበት ቀን ከሞት እንድታድኑን ምልክት ስጡኝ» አለቻቸው ። እነርሱም ፡ «እንደልመናሽ እናደርጋለን» ብለው መለሱላት ።

በዚያ ሌሊትም በመስኮት በኩል በገ መድ ከቅጥሩ ውጭ አወጣቻቸው ። እነር ሱም ፡ «እኛ ወደ አገሩ በምንገባ ጊዜ ይህን ቀይ ፈትል በዚህ መስኮት በኩል እሠሪው ፤ ቤተ ዘመዶችሽንም ሁሉ ወደ ቤትሽ ሰብስቢ ፤ በቤትሽ ውስጥ የሚገኙ ትም ሁሉ ይድናሉ» ብለው ሄዱ ። ረዓ ብም ቀዩን ፈትል በመስኮቱ በኩል አንጠ ለጠለች ። ሁለቱ ሰላዮችም ወደ ኢያሱ ተመልሰው ፡ «በእውነት እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ ሰጥቶናል ፤ የአገሩም ሰዎች ሁሉ በፊታችን ይቀልጣሉ» ብለው ያዩት ንና የሰሙትን ሁሉ አወሩለት ።

## ፫ ፡ የዮርዳኖስ መቆም ።

ኢያሱ ፫ ፡ ፩ - ፲፯ ።

ኢያሱም ማልዶ ተነሣ ፡ እርሱና ሕዝቡ ሁሉ ከሠፈሩበት ከሰጢም ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ መጡ ፤ በዚያም አደሩ ። ከሦስት ቀንም በኋላ የሕዝቡ አለቆች በሠ ፈሩ መካከል አልፈው ፡ «የእግዚአብሔ ርን ቃል ኪዳን ታቦትና የሚሸከሙትን ካህናት ስታዩ ፡ ተነሥታችሁ የሁለት ሺህ ክንድ ርቀት ያህል ወደ ኋላ ሆናችሁ ተከ ተሉ» አሉአቸው ። ኢያሱም ካህናቱን ፡ «የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕ ዝቡ ፊት እለፉ ፡ በዮርዳኖስ ዳር ስትደር ሱም በውኃው ውስጥ ቁሙ» ብሎ አዘዛ ቸው ።

ዮርዳኖስም በመከር ወራት በየዓመቱ እንደሚሞላ እጅግ ሞልቶ ነበር ፤ ታቦት ተሸካሚዎቹም ወደ ውኃው ዳር ደርሰው እግሮቻቸው መጥለቅ ሲጀምሩ ፡ ከላይ የሚወርደው ውኃ ራቅ ብሎ ቆመ ፡ እንደ ክምርም ሆነ ፤ ሕዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት በደረቅ መሬት ተሻገሩ ። የቃል ኪዳ ኑንም ታቦት የተሸከሙ ካህናት ፡ ሕዝቡ እስኪሻገሩ ድረስ በዮርዳኖስ መካከል በደ ረቅ መሬት ጸንተው ቆሙ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፬ ፡ የመታሰቢያ ድንጋዮች ።

ኢያሱ ፬ ፡ ፩ - ፳፬ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ፡ «ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ምረጥ ፤ የካህናት እግ ሮች ከቆሙበት ሥፍራም አሥራ ሁለት ድንጋዮች ያንሡ ፡ በምታድሩበትም ሥፍራ ያኑሩአቸው» ብሎ አዘዘው ። ኢያሱም አሥራ ሁለት ሰዎችን መርጦ ፡ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ከዮርዳኖስ መካከል እንዲያነሡ አዘዛቸው ፡ በዮርዳኖስም መካ ከል ሌሎች አሥራ ሁለት ድንጋዮች እንዲ ተከሉ አደረገ ።

ሕዝቡም ሁሉ ከተሻገሩ በኋላ እንደ እግ ዚአብሔር ትእዛዝ ኢያሱ ካህናቱን ፡ «ከዮ ርዳኖስ ውጡ» ብሎ አዘዛቸው ። እነርሱም ከዮርዳኖስ መካከል ወጡ ፤ ደረቅ መሬት መርገጥ በጀመሩ ጊዜም የዮርዳኖስ ውኃ ወደ ሥፍራው ተመለሰ ፤ ቀድሞም እንደ ነበረ በዳሩ ሁሉ ተንሠራፍቶ ሄደ ።

ሕዝቡም በመጀመሪያው ወር በአሥረ ኛው ቀን ዮርዳኖስን ተሻግረው ከኢያሪኮ በስተ ምሥራቅ በጌልገላ ሠፈሩ ። ከዮርዳ ኖስ ውስጥ የወሰዱአቸውንም ድንጋዮች ኢያሱ መታሰቢያ እንዲሆኑ በጌልገላ አቆ ማቸው ። እስራኤልንም ሁሉ ፡ «በሚመ ጣው ዘመን ልጆቻችሁ አባቶቻቸውን :- እነዚህ ድንጋዮች ምንድር ናቸው ? ብለው ሲጠይቁ ፡ ልጆቻችሁን :- እስራኤል ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻገሩ ብላችሁ እግዚ አብሔርን ለዘላለሙ እንድትፈሩት በጠን ካራ እጁ ያደረገላችሁን ነገር ታስታውቃ ላችሁ» አላቸው ።

* * *

የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ፡ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው ፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ፡ ይከናወንልሃልም ።

ኢያሱ ፩ ፡ ፰ ።

ለተአምራቱ መታሰቢያን አደረገ ፤
እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው ። . . .
የአሕዛብን ርስት ይሰጣቸው ዘንድ
ለሕዝቡ የሥራውን ብርታት አሳየ ።

መዝ. ፩፻፲ (፩፻፲፩) ፡ ፬ ፡ ፮ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ረዓብ ሰላዮችን አሳልፋ ያልሰጠችበት ምክንያት ምንድር ነው ?
፪ ፡ ሰላዮቹ ወደ ኢያሱ በተመለሱ ጊዜ ምን አሉት ?
፫ ፡ አሥራ ሁለት ድንጋዮች ከዮርዳኖስ መካከል የተወሰዱት ስለ ምንድር ነው ?

ጸሎት ፤ አምላክ ሆይ ፡ እንደ ስምህ
እንዲሁም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስጋናህ ነው፤
ቀኝህ ጽድቅን የተሞላች ናት ። መዝ. ፵፯ (፵፰) ፡ ፲ ።



ምዕራፍ ፲ ።

# የኢያሪኮ ቅጥር መውደቅ ።

ኢያሱ ፭ ፡ ፮ ።

## ፩ ፡ ለኢያሱ የተሰጠ ትእዛዝ ።

ኢያሱ ፭ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፲፫ - ፮ ፡ ፭ ።

የከነዓን ነገሥታት ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ፊት የዮርዳኖስን ውኃ እንዳደ ረቀ በሰሙ ጊዜ ፈሩ ፡ ልባቸውም ቀለጠ ። ከሁሉ ቅርብ የነበረችው የኢያሪኮ ከተ ማም ከፍርሃት የተነሣ ተዘግታ ነበር ፡ ወደ እርስዋም የሚገባና የሚወጣ አልነበረም ።

ኢያሱም በኢያሪኮ አጠገብ ሆኖ ዓይኑን አንሥቶ ሲመለከት ፡ እነሆ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር ። ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ፡ «ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ ?» አለው ። እርሱም ፡ «አይደለሁም ፤ እኔ የእግዚአብ ሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ » አለ ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደ ፍቶ ፡ «ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምን ድር ነው ? » አለው ። የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ ኢያሱን ፡ «አንተ የቆምህ በት ሥፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን አው ልቅ» አለው ። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው ፤ «ተመልከት ፤ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ፡ ጽኑ ዓን ኃያላንዋንም በእጅህ ሰጥቻለሁ ። እስከ ስድስት ቀን ድረስ አንድ ጊዜ በየቀኑ ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማዪቱን ይዙሩ አት ። ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለ ከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ ። በሰባተኛ ውም ቀን ከተማዪቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ ፤ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ይንፉ ። ቀንደ መለከቱንም ባለማቋረጥ ሲነፉ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ ፤ የከተማዪ ቱም ቅጥር ይወድቃል ፤ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ይገባባታል ።»

## ፪ ፡ የኢያሪኮ መከበብ ።

ኢያሱ ፮ ፡ ፮ - ፲፬ ።

ኢያሱም ለካህናትና ለሕዝቡ ይህን ትእ ዛዝ ከሰጠ በኋላ ሰባት ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት እየነፉ ከእግዚአብሔር ታቦት ፊት ሲሄዱ ፡ ሰልፈኞቹ ደግሞ በሰባቱ ካህ ናት ፊት ይሄዱ ነበር ፤ የቀረውም ሕዝብ ከታቦቱ በኋላ ይከተል ነበር ። ኢያሱም ሕዝቡን ፡ «ጩኹ እስከምልበት ቀን ድረስ አትጩኹ ፡ ከአፋችሁም አንድ ቃል አይውጣ» አለ ። እንደ ትእዛዙም አንድ ጊዜ ከተማዪቱን ዞሩ ፤ ወደ ሠፈሩም ተመ ልሰው አደሩ ። እንዲሁ ማለዳ ማለዳ እየተ ነሡ ከተማዪቱን በመዞር ስድስቱን ቀን ፈጸሙ ።

## ፫ ፡ የኢያሪኮ መውደቅ ።

ኢያሱ ፮ ፡ ፲፭ - ፳፭ ።

በሰባተኛውም ቀን ማልደው ተነሡ ፡ እንደ ሥርዓቱም ሰባት ጊዜ ከተማዪቱን ዞሩ ። ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ሲነፉ ፡ ኢያሱ ለሕዝቡ እንዲህ አለ ፤ «እግዚአብ ሔር ከተማዪቱን ሰጥቶአችኋልና ጩኹ ፤ ከተማዪቱም በእርስዋም ውስጥ ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም ይሆናል ። ረዓብ የላክናቸውን መልእክተኞች ስለ ሸሸገች እርስዋና በቤትዋ ውስጥ ያሉት ብቻ በሕይወት ይኖራሉ ። ከእነርሱም በቀር ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም ነውና እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ ፤ አንዳች የወሰዳችሁ እንደሆነ የእስራኤ ልን ሠፈር የተረገመ ታደርጉታላችሁ ። ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ ፡ የነሐስና የብ ረትም ዕቃ ፡ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ግምጃ ቤት ይግባ ።»

ይህን እንደ ሰሙም ፡ ካህናቱ ባለማቋ ረጥ ቀንደ መለከቱን ሲነፉ ሕዝቡ ታላቅ ጩኸት ጮኹ ። ቅጥሩም ወደቀ ፤ እያንዳ ንዱ እስራኤላዊም እንዳሰላለፉ ተራ በቀ ጥታ ወደ ከተማዪቱ ገባ ። የኢያሪኮንም ሰዎች ሁሉ በሰይፍ አጠፉ ፤ ከተማዪቱንና በእርስዋ የነበረውንም ሁሉ አቃጠሉ ። ነገር ግን ብሩንና ወርቁን ፡ የነሐሱንና የብ ረቱንም ዕቃ ፡ ወደ እግዚአብሔር ግምጃ ቤት አገቡ ።

ሰላዮቹም ጋለሞታዪቱን ረዓብን ፡ ወላ ጆችዋንና ወንድሞችዋን ዘመዶችዋንና ያላትንም ሁሉ አወጡ ፤ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በእስራኤል መካከል ኖረች ።

* * *

የኢያሪኮ ቅጥር ሰባት ቀን ከዞሩበት በኋላ በእምነት ወደቀ ።

ዕብራ. ፲፩ ፡ ፴ ።

ጋለሞታዪቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም ስለተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር ያልጠፋችው በእምነት ነው ።

ዕብራ. ፲፩ ፡ ፴፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እስራኤላውያን ከአንድ እስከ ስድስት ቀን ድረስ ምን እንዲያደ ርጉ ታዘዙ ?
፪ ፤ በሰባተኛውስ ቀን ምን ሆነ ?
፫ ፤ ከኢያሪኮ ሰዎች የዳኑት እነማን ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ እንደ ቃልህ
ምሕረትህና መድኃኒትህ ይምጡልኝ ። . . .
ስምህን ለሚወዱ እንደምታደርገው ፍርድ
ወደ እኔ ተመልከት ማረኝም ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፵፩ ፡ ፩፻፴፪ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፩ ።

## የድል ዕንቅፋት ።

ኢያሱ ፯ ፡ ፰ ።

፩ ፡ የእስራኤል ድል መነሣት ።

ኢያሱ ፯ ፡ ፳፯ - ፯ ፡ ፲፩ ።

የኢያሪኮ ቅጥር በወደቀ ጊዜ የኢያሱ ዝና በአገሩ ሁሉ ወጣ ። ነገር ግን ከይሁዳ ነገድ የሆነ አካን የተባለ ሰው እርም ከሆነው ነገር በመውሰዱ መላ እስራኤል እንደ በደለና የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው እንደ ወረደ ለኢያሱና ለእስራኤል ሕዝብ ገና አልታወቀም ነበር ።

ኢያሱም ጋይ የተባለችውን ከተማ እን ዲሰልሉ ሰዎችን ላከ ። እነርሱም ሄደው በተመለሱ ጊዜ ፡ «ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ሰልፈኞች ወጥተው ጋይን ይምቱ እንጂ ሕዝቡ ሁሉ ወደዚያ ለመሄድ አይ ድከም ፤ የጋይ ሰዎች ጥቂቶች ናቸውና» አሉት ። ኢያሱም ሦስት ሺህ ሰዎች ወደ ዚያ ላከ ፤ እነርሱ ግን ከጋይ ሰዎች ፊት ሸሹ ፡ ተሸነፉም ።

ኢያሱም ልብሱን ቀደደ ፤ እርሱና የእስ ራኤል ሽማግሌዎችም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግምባራቸው ተደፉ ፤ በራሳ ቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ ። ኢያሱም ፡ «ዋይ ! ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! እስራ ኤል በጠላቶቻቸው ፊት ከሸሹ ምን እላ ለሁ ? ጠላቶቻችንም ሰምተው ስማችንን ከምድር ያጠፉሉ ፤ ለታላቁ ስምህስ የምታ ደርገው ምንድር ነው ?» አለ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ፡ «ለምን በግ ምባርህ ተደፍተሃል ? ቁም ፤ እስራኤል በድሎአል ፤ እርም የሆነውን ነገር ወሰዱ ፡ ሰረቁም ፡ ዋሹም ፡ በዕቃቸውም ውስጥ ሸሸጉት ። ስለዚህም በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም ። እርም የሆነውንም ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ ከእናንተ ጋር አልሆንም ። ተነሣ ፡ ለሕዝቡም ፡- እስራኤል ሆይ ፡ እርም የሆነ ነገር በመካከ ልህ አለ ። ነገም በየነገዳችሁ ትቀርባላ ችሁ ፤ እግዚአብሔርም የሚለየው ነገድ በየወገኖቹ ይቀርባል ፤ እግዚአብሔርም የሚለየው ወገን በየቤተ ሰቦቹ ይቀርባል ፤ እግዚአብሔርም የሚለየው ቤተሰብ በየ ሰዉ ይቀርባል ። በደል የተገኘበት ሰውና ያለውም ሁሉ በእሳት ይቃጠላሉ ብለህ ንገራቸው» አለው ።

፪ ፡ የአካን መቀጣት ።

ኢያሱ ፯ ፡ ፲፮ - ፳፮ ።

ኢያሱም ማልዶ ተነሣ ፡ እስራኤልንም በየ ነገዶቻቸው አቀረበ ፤ የይሁዳም ነገድ ተለየ ። የይሁዳንም ወገን አቀረበ ፤ የዛ ራም ወገን ተለየ ። የዛራንም ወገን ሰዎች አቀረበ ፤ ዘንበሪም ተለየ ። የቤቱንም ሰዎች አቀረበ ፤ የከርሚ ልጅ አካን ተለየ ።

ኢያሱም አካንን ፡ «ልጄ ሆይ ፡ ለእግዚ አብሔር ክብር ስጥ ለእርሱም ተናዘዝ ፤ ያደረግኸውንም ንገረኝ ፡ አትሸሽገኝም» አለው ። አካንም መልሶ ፡ «በእውነት እግ ዚአብሔርን በድያለሁ ። በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ ፡ ሁለት መቶም ሰቅል ብር ፡ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው ፡ ወሰድኋቸ ውም ፤ እነሆም በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል ፡ ብሩም ከሁሉ በታች ነው» አለ ።

ኢያሱም ሰዎችን ሰደደ ፡ ወደ ድንኳ ኑም ሮጡ ፤ እነሆም እንደ ተባለ ተሸሽገው ነበር ፤ ይዘውም ወደ ኢያሱና ወደ ሕዝቡ አመጡአቸው ፤ በእግዚአብሔርም ፊት አኖሩአቸው ። ኢያሱና እስራኤልም ሁሉ አካንን ፡ ብሩንም ካባውንም ወርቁንም ልጆቹንም ፡ ለእርሱ የሆነውንም ሁሉ ወደ አንድ ሸለቆ ወሰዱ ፤ ኢያሱም አካንን ፡ «ለምን አስጨነቅኸን ? እግዚአብሔር ዛሬ ያስጨንቅሃል» አለው ። እስራኤልም ሁሉ በድንጋይ ወገሩአቸው ፡ በእሳትም አቃጠሉአቸው ። በላዩም ታላቅ የድንጋይ ክምር ከመሩ ። የዚያም ሥፍራ ስም የአ ኮር ሸለቆ ተብሎ ተጠራ ። አኮር ማለትም ማስጨነቅ ማለት ነው ።

፫ ፡ የእስራኤል ድል መነሣት ።

ኢያሱ ፰ ፡ ፩ - ፳፱ ።

እግዚአብሔር ኢያሱን ፡ «አትፍራ ፡ ሰል ፈኞችን ሁሉ ወስደህ ወደ ጋይ ውጣ ፤ ንጉ ሥዋንና ከተማዪቱንም በእጅህ ሰጥቼሃ ለሁ ። ከከተማዪቱም በስተኋላ ድብቅ ጦር አስቀምጥ» አለው ።

ኢያሱም ሰልፈኞቹም ሁሉ ወደ ጋይ ሊወጡ ተነሡ ፤ ኢያሱም ኃያላን የሆኑትን መርጦ ፡ የሚያደርጉትን አዝዞ ከጋይ በስተ ኋላ በምዕራብ በኩል እንዲደበቁ በሌሊት ሰደዳቸው ። በማግሥቱም ማልዶ ተነሣ ፡ ሕዝቡንም አሰለፈ ፡ ከጋይም በስተ ሰሜን በኩል እንዲሠፍሩ አደረገ ፤ ኢያሱም በዚያች ሌሊት በእነርሱና በከተ ማዪቱ መካከል ወዳለው ሸለቆ ሄደ ። የጋይ ንጉሥና ሕዝቡም የኢያሱን መቅ ረብ ባዩ ጊዜ ፈጥነው በማለዳ ተነሡ ፡ ሊዋጉአቸውም ወጡ ፡ ከከተማዪቱም በስ


www.ethiopianorthodox.org

ተኋላ ድብቅ ጦር እንዳለ አላወቁም ። ኢያሱና ሰልፈኞቹም ድል የተነሡ መስለው ከጋይ ሰዎች ፊት ወደ ኋላ ሸሹ ። በከተማዪቱም የነበሩ ሁሉ እንዲያሳድዱአቸው ተጠሩ ፤ ከከተማዪቱ እስኪርቁ ድረስም ኢያሱን አሳደዱት ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ፤ «ጋይን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁና በእጅህ ያለውን ጦር በሳይዋ ዘርጋ» አለው ። ኢያሱም ጦሩን በከተማዪቱ ላይ ዘረጋ ። የተደበቁትም ፈጥነው ተነሡ ፤ ሮጡም ፤ ወደ ከተማዪቱም ገብተው ያዙአት ፤ በእሳትም አቃጠሉአት ። የጋይ ሰዎችም ወደ ኋላቸው ዘወር ቢሉ የከተማዪቱ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ ፤ የሚያደርጉትም ጨነቃቸው ፤ እንደ ሸሹ የመሰሉትም እስራኤላውያን መለስ ብለው ገጠሙአቸው ፤ ከተማዪቱን ያቃጠሉትም በስተ ጀርባ ደረሱባቸው ። የጋይም ሰዎች በእስራኤል መካከል ሆኑ ፤ ከእነርሱ አንድ ስንኳ ሳያመልጥ ሁሉም ተገደሉ ። ኢያሱም ፈጽሞ እስኪጠፉ ድረስ ጦር የዘረጋባትን እጁን አላጠፈም ።

## ፬ ፤ ኢያሱ በሕዝቡ ፊት ሕግን አነበበ ።

ኢያሱ ፰ ፥ ፴ - ፴፭ ፤ ዘዳግ. ፳፯ ፥ ፪ - ፳፮ ።

ከዚያም በኋላ ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዳዘዘ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠርቶ መሥዋዕትን አቀረበ ፤ የእስራኤልም ልጆች ሲያዩ በዚያ ሥፍራ በድንጋዮች ላይ ሕጉን ጻፈ ። ከእስራኤል ነገዶች እኩሌቶቹ በገሪዛን ተራራ ፊት ፤ እኩሌቶቹም በጌባል ተራራ ፊት ቆመው ሳሉ የሕጉን ቃሎች ሁሉ በረከቱንና እርግማኑን አነበበ ። ኢያሱም በእስራኤል ጉባዔ ሁሉ ፤ በሴቶቹም በሕፃናቱም በመካከላቸውም በሚኖሩት መጻተኞች ፊት ሁሉን አነበበ እንጂ ሙሴ ካዘዘው አንዲት ቃል አላስቀረም ።

* * *

ኃጢአታችሁ እንዲያገኛችሁ ዕወቁ ። ዘኊ. ፴፪ ፥ ፳፫ ።

እኛን በሚቈጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም ።

ዕብራ. ፬ ፥ ፲፫ ።

* * *

ጥያቄ ፥ ፩ ፥ እስራኤል በጋይ ሰዎች ድል የተነሡ በምን ምክንያት ነው ?
፪ ፥ አካን የተላለፈው ምንድር ነው ? ምንስ ወስዶ ነበር ?
፫ ፥ በአካን ላይ ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ለኢያሱ ምን ትእዛዝና ተስፋ ሰጠው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ እነሆ እውነትን ወደድህ ፤
የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ ። . . .
ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ ፥
በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ ። መዝ. ፶ (፶፩) ፥ ፮ ፥ ፱ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፪ ።

# ታላቅ ድል ።

ኢያሱ ፱ - ፲፬ ።

## ፩ ፤ የገባዖን ሰዎች ተንኰል ።

ኢያሱ ፱ ፥ ፩ - ፳፯ ።

በከነዓን ሁሉ በተራራማውና በቈላው በባሕር ዳርም የነበሩ ነገሥታት ሁሉ ጋይ እንደ ተሸነፈች በሰሙ ጊዜ እስራኤልን ሊወጉ አንድ ሆነው ተሰበሰቡ ። የገባዖን ሰዎች ግን ከእነዚህ ነገሥታት ጋር ሳይማከሩ በተንኰል ከእስራኤል ጋር ለመስማማት አስበው በአህዮቻቸው ላይ አርጅቶ የተቀደደ የተጠቀመም አቁማዳ ጫኑ ። ያረጁ ጫማዎችም በእግራቸው አደረጉ ፤ አሮጌ ልብስም ለበሱ ፤ ለስንቅም የደረቀና

የሻገተ እንጀራ ይዘው ኢያሱ ወደ ሠፈረበት ወደ ጌልገላ መጥተው ፡ «ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ስም የተነሣ እጅግ ከራቀ አገር መጥተናል ፤ ዝናውንም ሰምተናል ። በአገራችንም የሚኖሩት ሁሉ ፦ ሂዱ ፡ ከእነርሱም ጋር ኪዳን አድርጉ አሉን» አሉት ።

ኢያሱና የሕዝቡ አለቆችም ደርቆ የሻገተ ስንቃቸውን ባዩ ጊዜ የገባዖንን ሰዎች ተቀበሉ ፤ የእግዚአብሔርንም ምክር ሳይጠይቁ በሕይወት እንዲተዉአቸው ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ ፤ ማሉላቸውም ። ከሦስት ቀን በኋላም ጐረቤቶች መሆናቸውን ሰሙ ፤ ተጕዘውም በሦስተኛው ቀን ወደ ከተሞቻቸው ደረሱ ። ኢያሱም የገባዖንን ሰዎች ፡ «ለምን አታለላችሁን ? አሁንም የተረገማችሁ ናችሁ» ብሎ እንጨት ቈራጮችና ውኃ ቀጂዎች አድርጎ እንደ መሐላው በሕይወት ተዋቸው ።

## ፪ ፤ የደቡብ ነገሥታት መሸነፍ ።

ኢያሱ ፲ ፡ ፩ - ፵፫ ።

የኢየሩሳሌም ንጉሥ የገባዖን ሰዎች ከእስራኤል ጋር ሰላም እንዳደረጉ በሰማ ጊዜ በዙሪያው ወደ ነበሩ ወደ ሌሎች አራት ነገሥታት ልኮ ፡ «ወደ እኔ ውጡ ፤ ገባዖንን ለመምታት አግዙኝ» አለ ። እነርሱም ሠራዊቶቻቸውን ሰብስበው ወጡ ፤ ገባዖንንም ከበቡአት ።

የገባዖንም ሰዎች ወደ ጌልገላ ልከው ኢያሱን ፡ «ባሪያዎችህን ለመርዳት ፈጥነህ ውጣ» አሉት ። ኢያሱና ሰልፈኞቹም ሁሉ ተነሥተው ወጡ ። እግዚአብሔርም ኢያሱን ፡ «በእጅህ አሳልፌ ሰጥቻቸዋለሁና አትፍራቸው ፤ ከእነርሱም አንድ ሰው የሚቋቋምህ የለም» አለው ።

ኢያሱም ሌሊቱን ሁሉ ገሥግሦ አምስቱ ነገሥታትና ሠራዊቶቻቸው ካሉበት በድንገት ደረሰ ። እግዚአብሔርም በእስራኤል ፊት አስደነገጣቸው ፤ ታላቅ መምታትም መታቸው ። አምስቱም ነገሥታት ከነሠራዊቶቻቸው ሲሸሹ እግዚአብሔር ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ ከሰማይ አወረደባቸውና ሞቱ ፤ በሰይፍ ከተገደሉትም ይልቅ በበረዶ የሞቱት በለጡ ።

በዚያን ቀን ኢያሱ በእስራኤል ፊት እንዲህ ብሎ ለእግዚአብሔር ተናገረ ፤ «በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም ፤ በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ ።» ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ ፤ ጨረቃም ዘገየ ። እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበርና እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ አልነበረም ። እግዚአብሔርም ለእስራኤል ስለ ተዋጋላቸው ኢያሱ እነዚህን ነገሥታት ሁሉ ምድራቸውንም በአንድ ጊዜ ያዘ ። ኢያሱም ከነሠራዊቱ ወደ ጌልገላ ተመለሰ ።

## ፫ ፤ የሰሜን ነገሥታት መሸነፍ ።

ኢያሱ ፲፩ ፡ ፩ - ፳ ፡ ፳፫ ።

በከነዓን ሰሜን ክፍል ከነበሩት ነገሥታት አንዱ የአሶር ንጉሥ ፡ ወደ ሌሎች ነገሥታት ላከ ። እነርሱም ሠራዊቶቻቸውን አስከትተው ከብዙ ፈረሰኞችና ሰረገሎች ጋር ወጡ ፤ ብዛታቸውም በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ነበረ ። በማሮን ውኃ አጠገብም አንድ ሆነው ሠፈሩ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ፡ «ነገ በዚህ ጊዜ በእስራኤል እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና አትፍራቸው» አለው ። ኢያሱም ከሰልፈኞቹ ሁሉ ጋር ወደ ማሮን ውኃ መጣ ፤ ወደቀባቸውም ። እግዚአብሔርም በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣቸው ፤ መትተውም አሳደዱአቸው ፡ ገደሉአቸውም ። ኢያሱም ወደየአንዳንዱ ከተማ ደርሶ አጠፋቸው ። ብዙ ዘመንም ከከነዓን ነገሥታት ጋር ይዋጋ ነበር ። ከገባዖን ሰዎችም በቀር ከእስራኤል ጋር ዕርቅ ያደረገች አንዲት ከተማ አልነበረችም ፤ ሁሉንም በሰልፍ ያዙ ። ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች ።

## ፬ ፤ እስራኤል ምድረ ርስትን መውረስ ።

ኢያሱ ፲፫ ፡ ፩ - ፯ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን ፡ «አንተ ሸመገልህ ፤ በዕድሜህም አረጀህ ፤ ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች ። በቀረችውም ምድር ያሉትን ከእስራኤል ልጆች ፊት አባርራቸዋለሁ ። አሁንም እንዳዘዝሁ ይህን ምድር ለዘጠኙ ነገድ ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገህ ክፈለው» አለው ። ኢያሱና አልዓዛር የእስራኤል አለቆችም ምድሪቱን አካፈሉ ።

* * *

በሰይፋቸው ምድርን አልወረሱም
ክንዳቸውም አላዳናቸውም ፤
ቀኝህና ክንድህ የፊትህም ብርሃን ነው እንጂ ፤
ወደሃቸዋልና ።
መዝ. ፵፫ (፵፬) ፡ ፫ ።

ኃጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል ፤
ጻድቃንንም የሚጠሉ ይጸጸታሉ ።
መዝ. ፴፫ (፴፬) ፡ ፳፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የገባዖን ሰዎች እስራኤልን እንዴት አድርገው አታለሉአቸው ?
፪ ፤ የእግዚአብሔርን ምክር ባለመጠየቃቸው ኢያሱና የእስራኤል አለቆች ምን ስሕተት አደረጉ ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መሆኑን በምን አሳየ ?

ጸሎት ፤ ለእኛ አይደለም አቤቱ ፡ ለእኛ አይደለም ፡
ነገር ግን ለስምህ
ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ ።
መዝ. ፩፻፲፫ ፡ ፱ ። (መዝ. ፩፻፲፭ ፡ ፩ ።)


www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፫ ።

## የርስት ድልድልና የኢያሱ ስንብት ።

ኢያሱ ፲፬ - ፳፬ ።

### ፩ ፡ የካሌብ ርስት ።

ኢያሱ ፲፬ ፡ ፮ - ፲፭ ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ዘፍጥ. ፳፫ ፡ ፪ ፡ ፲፱።

ካህኑ አልዓዛርና ኢያሱ የእስራኤልም አለቆች አገሩን ለማካፈል በጀመሩ ጊዜ የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ወደ ኢያሱ ቀርቦ እንዲህ አለው ፤ «ለእግዚአብሔር ሰው ለሙሴ ስለ እኔና ስለ አንተ እግዚአብሔር በቃዴስ በርኔ የተናገረውን ነገር ታውቃለህ ። ሙሴ ከነዓንን እንድሰልል በላከኝ ጊዜ የዐርባ ዓመት ሰው ነበርሁ ። ከእኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼም የሕዝቡን ልብ አቀለጡ ፤ እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልሁ ። ሙሴም ፡ እግርህ የረገጠው ሥፍራ ለአንተና ለልጆችህ በእርግጥ ርስት ይሆናል ብሎ ማለ ። አሁንም እነሆ እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከተናገረ በኋላ እስራኤል በምድረ በዳ ሲዞሩ ፡ እንደ ተናገረኝ እነዚህን ዐርባ አምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ ። እነሆ አሁን ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ ።



ይሁን እንጂ ሙሴ በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርሁ ዛሬም ጒልበታም ነኝ ። አሁን እንግዲህ በዚያን ቀን እግዚአብሔር የተናገረውን ይህን ተራራማ ሥፍራ ስጠኝ ። ዔናቃውያን ፡ ታላላቆችና የተመሸጉ ከተማዎችም በዚያ እንዳሉ ሰምተሃል ፤ ምናልባት እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ይሆናል ፡ እንደ ተናገረኝም አሳድዳቸዋለሁ ።»

ኢያሱም ካሌብን ባረከው ፤ ኬብሮንም ርስት አድርጎ ሰጠው ። ኬብሮንም አስቀድሞ ቂርያትአርባቅ ትባል ነበር ፤ በዚያም አብርሃም ለመቃብር የገዛው ዋሻ ነበረ ። ካሌብም ሦስቱን የዔናቅ ልጆች ከዚያ አሳድዶ ኬብሮንን ወረሰ ፡ ኖረባትም ።

### ፪ ፡ የርስት አያያዝ ውሳኔ ።

ኢያሱ ፲፭ ፡ ፩ - ፳፩ ፡ ፵፭ ።

የይሁዳ ነገድ እንደዚሁም የዮሴፍ ልጆች የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች ፡ ድርሻ ርስታቸውን ከተቀበሉ በኋላ እስራኤል ሁሉ በሴሎ ተሰበሰቡ ፤ በዚያም የመገናኛውን ድንኳን ተከሉ ። (ኢያሱ ፲፰ ፡ ፩ ።)

ከዚህም በኋላ ርስት ገና ላልተቀበሉት ነገዶች የርስት ድርሻ በዕጣ ታደላቸው ። ለሌዊ ነገድ ግን ከሌሎቹ ነገዶች መካከል የሚኖሩባቸው ዐርባ ስምንት ከተሞች እንጂ የርስት ድርሻ አልተሰጣቸውም ። ምክንያቱም እግዚአብሔር አሮንን ፡ «በእስራኤል ልጆች መካከል ድርሻህና ርስትህ እኔ ነኝ ። ለሌዊም ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን ስለሚያገለግሉ የእስራኤልን ልጆች አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ ፤ ስለዚህ በእስራኤል ልጆች መካከል ርስት አይወርሱም አልኋቸው» ብሎ ነበርና ። (ዘኍ. ፲፰ ፡ ፳ - ፳፬ ፡ ፴፭ ፡ ፩ - ፰ ፡ ኢያሱ ፳፩ ፡ ፩ - ፵፪ ።)

እንዲሁም የእስራኤል ነገድና ቤተሰብ ሁሉ በየርስቱ ላይ በሰላምና በደስታ እንዲኖር እግዚአብሔር ወዶ ፡ «ምድር ለእኔ ናት ፤ እናንተም ከእኔ ጋር እንግዶችና መጻተኞች ናችሁና ምድርን አትሽጡ ። ወንድምህ ቢደኸይ ከርስቱም ቢሸጥ ፡ ለእርሱ የቀረበ ዘመዱ መጥቶ ወንድሙ የሸጠውን ይግዛለት ፤ ኢዮቤልዩ እስከሚባለው እስከ አምሳኛው ዓመት ድረስ የተሸጠው መሬት በገዛው ዘመድ እጅ ይሁን ፤ በዚያ ዓመት ግን ይውጣ ፡ ባለቤቱም ወደ ርስቱ ይመለስ» አለ ። (ዘሌዋ. ፳፭ ፡ ፳፫ - ፳፰ ።)

ኢያሱንም ደግሞ ፡ «ሳይወድ ሳያውቅም ሰውን በስሕተት የገደለ ገዳይ እንዲሸሽባቸው በሙሴ የነገርኋችሁን መማፀኛ ከተሞችን ለዩ ፤ ከደም ተበቃዩም መማፀኛ ይሆኑላችኋል ። ሳይወድ ሰውን የገደለ ገዳይም ፡ ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ ይሸሻል ፤ የከተማዪቱ ሽማግሌዎችም ይቀበሉታል» አለው ። የእስራኤልም ነገዶች ሰውን በስሕተት ለገደለ ገዳይ መማፀኛ የሚሆኑ ስድስት ከተሞች ለዩ ፤ በጥላቻ የገደለ ነፍሰ ገዳይ ግን እንዲሞት እንጂ በመማፀኛ ከተሞች እንዲሸሸግ አልተፈቀደለትም ። (ዘኍ. ፴፭ ፡ ፱ - ፴፬ ፡ ኢያሱ ፳ ፡ ፩ - ፱ ።)

### ፫ ፡ የኢያሱ ኑዛዜና ሞት ።

ኢያሱ ፳፫ ፡ ፩ - ፳፬ ፡ ፴፫ ።

ኢያሱም እስራኤልን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፤ «እኔ ሸምግያለሁ ፤ እናንተም ፡ እግዚአብሔር ስለ እናንተ ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል ። እነሆ ባካፈልኋችሁ ርስት ገና የሚገኙትን አሕዛብ ፡ እርሱ ከፊታችሁ በብርቱ ያሳድዳቸዋል ። ስለዚህም በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ ለማድረግ በጣም በርቱ ፤ በመካከላችሁ ወደ ቀሩት አሕዛብም አትግቡ ፡ የአማል



www.ethiopianorthodox.org

ክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ ፡ አታምልኩ አቸውም ።

«እነሆ ዛሬ የምድርን ሁሉ መንገድ እሄ ዳለሁ ፤ እናንተም ፡ እግዚአብሔር ስለ እና ንተ ከተናገረው ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ በልባችሁ ሁሉ ነወቁ ፤ ሁሉም ደርሶላችኋል ፤ ከእርሱም አንድ ነገር አልቀረም ። ተመልሳችሁ ለሌ ሎች አማልክት ብትሰግዱ ግን ከዚች መል ካም ምድር ትጠፋላችሁ ።

«እንግዲህ እግዚአብሔርን ፍሩ ፡ በፍጹ ምም በእውነተኛም ልብ አምልኩት ። እግ ዚአብሔርን ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያ ችሁ ፡ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመ ለኩአቸውን አማልክት ወይም በመካከላ ችሁ የቀሩትን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደሆነ ፡ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔ ርን እናመልካለን ።»

ሕዝቡም መልሰው ፡ «አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን ፡ ድምፁ ንም እንሰማለን» አሉት ። በዚያም ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ፤ ታላቅ ድንጋይንም ወስዶ በእግዚአብሔር መቅደስ አጠገብ አቆመው ። ለሕዝቡም ፡ «እነሆ የተናገረንን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ሰምቶአልና ይህ ድንጋይ ይመሰክር ብናል ፤ እንግዲህ አምላካችሁን እንዳት ክዱ ይህ ድንጋይ ምስክር ይሆንባችኋል» ብሎ ወደየርስታቸው ሕዝቡን ሰደደ ።

ይህንም ሁሉ ከፈጸመ በኋላ በመቶ አሥር ዓመቱ ሞተ ፤ የኤፍሬምም ድርሻ በሆነ በርስቱ ዳርቻ ቀበሩት ።

* * *

እግዚአብሔር ስለ እናንተ ከተናገረው ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ በልባችሁ ሁሉ በነፍሳችሁም ሁሉ ዕወቁ ።

ኢያሱ ፳፫ ፡ ፲፬ ።

እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን ።

ኢያሱ ፳፬ ፡ ፲፭ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ካሌብ ኢያሱን ምን ብሎ ጠየቀ ?
፪ ፡ የርስት ድርሻ ያልተሰጠ ለየትኛው ነገድ ነው ? ምክንያቱስ ምን ነበረ ?
፫ ፡ ኢያሱ ከመሞቱ በፊት ሕዝቡ ከምን እንዲጠነቀቁ አሳሰባቸው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ በአንተ ታምኛለሁና ጠብቀኝ ።
እግዚአብሔርን ፡ አንተ ጌታዬ ነህ አልሁ ፤
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም ። . . .
እግዚአብሔር የርስቴ እድል ፈንታና ጽዋዬ ነው ፤
ዕጣዬንም የምታጠና አንተ ነህ ።

መዝ. ፲፭ (፲፮) ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፭ ።





ምዕራፍ ፲፬ ።

# የሐዲስ ኪዳን ተስፋ ።

ዘዳግ. ፴፪ ፤ ኤር. ፴፪ ።

፩ ፤ በኪዳን ያልጸና ሕዝብ ።

ዘዳግ. ፴፩ ፡ ፲፬ - ፴፪ ፡ ፵፯ ፤ ፪ ዜና. ፴፮ ፡ ፲፩ - ፳፩ ።

ሙሴና ኢያሱ የእስራኤላውያንን ዐመፀኛ ነትና ደንዳናነት ዐውቀው በየተራ ፡ «አም ላካችሁን እግዚአብሔርን ብትረሱ ፡ ሌሎ ችንም አማልክት ብትከተሉ ከተሰጠቻ ችሁ ከመልካሚቱ ምድር ትነቀላላችሁ ፤ ትጠፋማላችሁ» እያሉ በብርቱ ያስጠነቅ ቋቸው ነበር ። በተለይም ሙሴ ፡ ጊዜ ሞቱ ሲቀርብ ፡ ምን ጊዜም ሳይረሳ ለልጅ ልጆ ቻቸው ምስክር የሚሆንባቸውን መዝሙር ጽፎ አስተማራቸው ። ከዚህም በታች አልፎ አልፎ በተጠቀሱት በመዝሙሩ ክፍሎች እንደሚታይ ፡ ሙሴ የእግዚአብ ሔርን ታማኝነት ሲያወድስ የሕዝቡን አለ መታመንና ክፋት ተናገረ ። ከዚህም በኋላ ሕዝቡ በራሳቸው ላይ መከራንና መማረ ክን እንደሚያመጡ ሲናገር ፡ የማዳኑን አሳብ ወደ ፍጻሜ የሚያደርሰው እግዚአብ ሔር አምላክ የሕዝቡን ቅሬታ ከምርኮ መልሶ እንደሚባርክ ፡ የምድር አሕዛብም ሁሉ ከሕዝቡ ጋር የበረከትና የደስታ ተካ



www.ethiopianorthodox.org

ፋዮች እንደሚሆኑ በትንቢት ተናገረ ፡-

« ሰማያት ሆይ ፤ አድምጡ ፤ እኔም እናገራለሁ ፤
ምድርም የአፌን ቃሎች ትስማ ። . . . .
የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁና ፤
ለአምላካችን ታላቅነትን ስጡ ። . . .
የእግዚአብሔር እድል ፈንታ ሕዝቡ ነው ፤
ያዕቆብም የርስቱ ገመድ ነው ።
በምድረ በዳ በጥማት ፤
የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው ፤
ከበበው ተጠነቀቀለትም ፤
እንደ ዓይን ብሌን ጠበቀው ። . . .
እግዚአብሔር ብቻውን መራው ፤ . . .
በምድርም ከፍታ ላይ አወጣው ፤
የእርሻውን ፍሬ በላ ፤ . . . .
ከወይኑም ደም ያለውን ጠጅ ጠጣህ ።

ዘዳግ. ፴፪ ፤ ፩ - ፲፬ ።

« ይሹሩን (ያዕቆብ) ወፈረ ፤ ተራገጠ ፤
ወፈረ ፤ ደነደነ ፤ ሰባ ፤
የፈጠረውንም እግዚአብሔርን ተወ ፤
የመድኃኒቱንም አምላክ ናቀ ። . . .
እግዚአብሔር ላልሆኑ አጋንንት ፤
ለማያውቋቸውም አማልክት ፤
በቅርብ ጊዜ ለተነሡ ለአዲሶች
አባቶቻቸውም ላልፈሩአቸው አማልክት ሠዉ ። . . .
እርሱም አለ ፡- ፊቴን እሰውርባቸዋለሁ ፤ . . .
በራብ በንዳድ ይጠፋሉ ፤ . . . .
በሜዳ ሰይፍ ፤ በቤትም ውስጥ ድንጋጤ ያጠፋቸዋል ።
እበትናቸዋለሁ አልሁ ። ቍ. ፲፩ - ፳፮ ።

« ኃይላቸውም እንደ ደከመ ፤
የተዘጋ የተለቀቀም እንደሌለ ባየ ጊዜ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳል ፤
ስለ ባሪያዎቹም ያዝናል ። . . .
ምድሪቱንና ሕዝቡን ይከሳልና ፤
እናንተ አሕዛብ ሆይ ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ።» ቍ. ፴፮ - ፵፫ ።

...ይህ ማሳሰቢያ የሆነ መዝሙር ምንም ቢሰ...ባቸው ሕዝቡ ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ ...ጊዜ ወደ ጊዜ እንደ አሕዛብ ያለ ርኵሰ...ትን በማድረግ በብዙ ተላለፉ ፤ ምድሪቱንም የእግዚአብሔርንም መቅደስ አረከሱ ። እግዚአብሔርም ለሕዝቡና ለማደሪያው ስላዘነ በየጊዜው ሁሉ መልእክተኞቹን እየላከ በእነርሱ ይናገር ነበር ። ነገር ግን ፤ ፈውስ እስከማይገኝላቸው ድረስ በእግዚአብሔር መልእክተኞች ላይ ሲያፌዙ ቃሉን ያቃልሉ ነበር ። በዚህም ምክንያት የተነገረባቸው ፍርድ ተፈጸመ ። በመጨረሻም ፤ ከኢያሱ ዘመን ከስድስት መቶ ዓመት ያህል በኋላ ፤ የባቢሎን ንጉሥ ጦር ሠራዊት በምድሪቱ ተጥለቅልቆ ኢየሩሳሌምን ከበበ ። ሕዝቡም በሰይፍና በፍርሃት ፤ በራብና በቸነፈርም እየደከመ ሄደ ፤ ከተማዪቱም ተይዛ ተቃጠለች ፤ ከሰይፍ የተረፉትም ሕዝብ ተማረኩ ።

፪ ፤ በነቢዩ ኤርምያስ የተሰጠ ተስፋ ።

ኤር. ፴፪ ፤ ፩ - ፵፬ ፤ ፴፩ ፤ ፴፩ - ፴፬ ፤ ፴፫ ፤ ፲፬ - ፲፮ ።

በዚህ አሳዛኝ ዘመን ነቢዩ ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገር ነበር ። ኢየሩሳሌም በጠላት ተከብባ ሳለች ኤርምያስ የሕዝቡን ማለቅ እየተጨነቀ ከመመልከቱ በላይ ፤ የሚናገረውን የእግዚአብሔርን ቃል ሳይቀበሉ ሲንቁት በማየቱ በጣም አዘነ ። ሴዴቅያስ የተባለ ፤ በኢየሩሳሌም ከነገሡት ከዳዊት ቤት ነገሥታት መጨረሻው ንጉሥ ፤ የእግዚአብሔርን ቃልና ምክር ጥሎ ኤርምያስን አሳሠረ ፤ በንጉሥም ግቢ በነበረው ግዞት ቤት እንዲጠበቅ አዘዘ ።

በዚህም አስቸጋሪና ተስፋ ቢስ በሆነው ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ መጥቶ ፤ «እነሆ የአጐትህ ልጅ አናምኤል ወደ አንተ መጥቶ ፤ በዓናቶት ያለውን እርሻዬን ግዛ ይልሃል» አለው ። እንደ እግዚአብሔርም ቃል አናምኤል መጣና ፤ «እባክህ ፤ እርሻዬን ግዛ» አለው ። ኤርምያስም ይህ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ዐውቆ ፤ ምስክሮችን አቆመና የእርሻውን ዋጋ ከፈለ ፤ በውሉም ወረቀቶች ላይ ፈርሞ አተመ ፤ በምስክሮቹም ፊት ለጸሐፊው ለባሮክ ፤ «የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡- ብዙ ቀን እንዲጠበቁ እነዚህን የውል ወረቀቶች ወስደህ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኑራቸው ። የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፡- ሰዎች በዚህች ምድር ቤትንና እርሻን የወይን ቦታንም እንደገና ይገዛሉ ይላልና» ሲል የውል ወረቀቶቹን በአደራ ሰጠው ።

ባሮክም ውሉን ተቀብሎ ሲሄድ ፤ ኤርምያስ እንዲህ ብሎ ጸለየ ፤ «አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፤ እነሆ አንተ ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃል ፤ ለአንተም የሚሳንህ ነገር የለም ። በምልክትና በድንቅ ነገር ፤ በብርቱ እጅና በተዘረጋች ክንድ በታላቅም ግርማ ሕዝብህን ከግብፅ አወጣህ ። ትሰጣቸውም ዘንድ ለአባቶቻቸው የማልህላቸውን ምድር ሰጠሃቸው ፤ እነርሱም ገብተው ወረሱአት ። ነገር ግን በሕግህ አልሄዱም ፤ ስለዚህ ይህን ክፉ ነገር ሁሉ አመጣህባቸው ። እነሆ ከሰይፍና ከራብ ከቸነፈርም የተነሣ ከተማዪቱ ለጠላት እጅ ተሰጥታለች ። አንተም ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፤ እርሻውን ግዛ አልኸኝ ፤ ከተማዪቱ ግን ለጠላት እጅ ተሰጥታለች ።»

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ ፤ «እነሆ ፤ እኔ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ ፤ በውኑ እኔን የሚሳነኝ ነገር አለን ? እነሆ ይህችን ከተማ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣታለሁ ፤ ያስቈጡኝም ዘንድ በሰገነታቸው ላይ ለበአል ካጠኑባቸው ፤ ለሌሎችም አማልክት የመጠጥን ቍርባን ካፈሰሱባቸው ቤቶች ጋር ያቃጥሉአታል ። አሁን እንግዲህ በሰይፍና በራብ በቸነፈርም ለባቢሎን ንጉሥ እጅ ተሰጥታለች ስለምትላት ከተማ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ እነሆ በቍጣዬ እነርሱን ካሳደድሁባት አገር ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ፤ ወደዚህም ሥፍራ እመልሳቸዋለሁ ፤ ተዘልለውም እንዲኖሩ አደርጋለሁ ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ ። ለእነርሱም ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ለዘላለም እንዲፈሩኝ አንድ ልብና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ ። ለእነርሱም ከማደርገው በጎነት አልመለስም ስል ከእነርሱ ጋር የዘላለምን ቃል ኪዳን እገባለሁ ፤ ከእኔም ዘንድ ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ ። ለጠላት እጅ ተሰጥታለች በምትሉአት ምድር እርሻን ይገዛሉ ፤ በውሉም ወረቀት ፈርመው ያትማሉ ፤ ምስክሮችንም ይጠራሉ ።»

እግዚአብሔርም ሁለተኛ ጊዜ ተናግሮ እንዲህ አለው ፤ «እነሆ የተናገርሁትን መልካም ቃል የምፈጽምበት ዘመን ይመጣል ፤ በዚያም ዘመን ለዳዊት የጽድቅን ቍጥቋጥ አበቅልለታለሁ ፤ እርሱም ፍርድንና ጽድቅን በምድር ያደርጋል ። ኢየሩሳሌምም ተዘልላ ትቀመጣለች ፤ የምትጠራበትም ስም ፤ እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው ።»

፫ ፤ የተስፋው መፈጸም ።

ዕብራ. ፰ ፤ ፮ - ፲፫ ፤ ፱ ፤ ፲፭ ።

እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም መታደስና ስለ አዲስ ኪዳን መመሥረት ያረጋገጠለት የተስፋ ቃል ሳይፈጸም ኤርምያስ ሞተ ። በተወሰነው ዘመን ግን ፤ ከምርኮ የተመለሰ የሕዝብ ቅሬታ ኢየሩሳሌምን አድሶ ሠራ ። ከኤርምያስም ዘመን ከስድስት


www.ethiopianorthodox.org

መቶ ዓመት ያህል በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ቤት ተወለደ ። በሙሴ በኩል ከተሰጠው ከብሉይ ኪዳን ለሚሻል ለአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነ እርሱ ነው ። በነቢያት የተናገሩትም መልካም ትንቢቶች ሁሉ በእርሱ ይፈጸማሉ ።

* * *

ለእነርሱ ከማደርገው በጎነት አልመለስም ስል ፡ ከእነርሱ ጋር የዘላለምን ቃል ኪዳን እገባለሁ ፤ ከእኔም ዘንድ ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ ።

ኤር. ፴፪ ፡ ፵ ።

ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ ፤ ስሙ ፤ በውነታችሁም በሕይወት ትኖራላችሁ ፤ የታመነችዪቱን የዳዊትን ምሕረት ፡ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ ። እነሆ ፡ ለአሕዛብ ምስክር ፡ ለወገኖችም አለቃና አዛዥ እንዲሆን ሰጥቼዋለሁ ።

ኢሳ. ፶፭ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ የሙሴ መዝሙር ስለምን ተጻፈ ? በመዝሙሩ መጨረሻስ ምን ተስፋ ተሰጠ ?
፪ ፡ ኢየሩሳሌም በመውደቅ ላይ ሳለች ኤርምያስ ምን እንዲያደርግ ታዘዘ ?
፫ ፤ ስለዚህስ ድርጊት ኤርምያስ ሲጸልይ እግዚአብሔር ምን ተስፋ ሰጠው ?

ጸሎት ፤ የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ ፡
ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና ፤
ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ
እንደ ተናገረ ፡
በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል ።
ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ ።
ይሁን ይሁን ። ሉቃ. ፩ ፡ ፷፰ - ፸ ፤ መዝ. ፸፩ (፸፪) ፡ ፲፱ ።





ምዕራፍ ፲፫ ።

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ።

ሉቃ. ፪ ፡ ፳፭ - ፴፰ ።

፩ ፤ ለስምዖን የተሰጠ ተስፋ ።

ሉቃ. ፪ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ።

የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ በነቢያት ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ በዳዊት ከተማ በቤተልሔም ተወልዶ ሲመጣ ፡ ሊቀበሉት ተዘጋጅተው የሚጠባበቁ አንዳንድ ሰዎች ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች መካከል ነበሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

ከእነርሱም ፡ መንፈስ ቅዱስ የነበረበት
ድቅና ትጉህ የሆነ ስምዖን የሚባል ሰው
በረ ። እርሱም ፡ የተቀባውን መድኅን
ያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ ገል
ለት ነበርና የሚያይበትን ቀን በትጋትና
ናፍቆት ይጠባበቅ ነበር ።

፤ ለሕፃኑ የተፈጸመ ሥርዓት ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፳፩ - ፳፬ ፤ ዘጸ. ፲፫ ፥ ፩ ፥ ፲፩ - ፲፮ ፤
ዘሌዋ. ፲፪ ፥ ፩ - ፰ ።

ምዖን እንዲሁ ሲጠባበቅ ሳለ ፡ ለኢየሩሳ
ም ቅርብ በነበረች በቤተልሔም ከተማ
ተወለደው ሕፃን እናቱና ዮሴፍ የተገባ
ገርን ሁሉ ሊፈጽሙ ይዘጋጁ ነበር ።
ሁሉ አስቀድሞም ፡ እግዚአብሔር ለአብ
ሃምና ለዘሮቹ ያቆመውን ኪዳን አስበው
ሕፃኑን በተወለደ በስምንተኛ ቀኑ አስገረ
ት ፤ በመልአኩ እንደ ተነገረለትም ስሙ
የሱስ ተብሎ ተጠራ ።
እንዲሁም ከሕግ በታች በሆነ ሕዝብ
መካከል ከሕግ በታች ሆኖ ተወልዶ ስለ
በር ፡ በሙሴ ሕግ ፡ ማኅፀን የሚከፍት
ኵር ልጅ ለጌታ የተቀደሰ ይሁን በተባ
ው አኳኋን ፡ ሕፃኑን በእግዚአብሔር
ት ለማቆምና ለወላድ ሴት የታዘዘውን
መሥዋዕት ለማቅረብ ፡ ዐርባ ቀን ሲሞ
ው ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሊወስ
ት ተነሡ ። ነገር ግን የሚቀርበው መሥ
ዕት ፡ የታዘዘው ጠቦትና ርግብ ሳይሆን
ድኆች የተፈቀደ ሁለት ዋሊያ ወይም
ለት የርግብ ጫጩቶች ነበረ ።

፤ የስምዖን ምስጋናና ትንቢት ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፳፭ - ፴፭ ።

ወደ ኢየሩሳሌም ደርሰው ሕፃኑን ኢየሱ
ን ወደ ቤተ መቅደስ ባስገቡት ጊዜ ፡
ንም ከድኆች ልጆች እንደ አንዱ ሆኖ
ሊታይ እንኳ ፡ ክብሩን የሚገልጥ ልዩ
የሆነ አቀባበል ተዘጋጅቶለት ነበር ።
እነሆ ፡ ከመሞቱ በፊት የተቀባውን መድ
ኅን በዓይኖቹ እንዲያየው ተስፋ የተሰ
ጠው ያ ስምዖን የተባለው ጻድቅ ፡ በመን
ፈስ ቅዱስ በመመራት ወደ ቤተ መቅደስ
ወጥቶ ኖሮ ፡ ሕፃኑን ኢየሱስን ተቀብሎ
አቀፈው ፤ እግዚአብሔርንም እየባረከ እን
ዲህ አለ ፦

« ጌታ ሆይ ፡ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን
በሰላም ታሰናብተዋለህ ፤ ዓይኖቼ በሰ
ዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን
አይተዋልና ፤ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን
የሚገልጥ ብርሃን ፡ ለሕዝብህም ለእስ
ራኤል ክብር ነው ። »

ዮሴፍና እናቱም ስለ ሕፃኑ በተባለው ነገር
ሲደነቁ ሳሉ ስምዖን ባረካቸው ። እናቱ
ንም ፡ «እነሆ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገ
ለጥ ዘንድ ፡ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙ
ዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው
ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል ።
በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል»
አላት ።

፬ ፤ የሐና ምስጋናና ምስክርነት ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፴፮ - ፴፰ ።

በዚያ ጊዜም ከአሴር ነገድ የሆነች ሐና
የምትባል አንዲት ነቢይት ወደ እነርሱ
ቀርባ ፡ ስምዖን የታቀፈው ሕፃን ማን እን
ደሆነ በማስተዋል እግዚአብሔርን አመሰ
ገነች ። እርስዋ ከድንግልናዋ በኋላ ባል
አግብታ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት የኖረች
የሰማንያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና
በጣም አርጅታ ነበር ። በጾምና በጸሎትም
ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለ
ይም ነበር ። በዚህም ዕለት ሕፃኑን ኢየሱ
ስን በማየት ተደስታ ከኢየሩሳሌም ነዋ
ሪዎች መካከል ለሚጠባበቁት ሁሉ ስለ
እርሱ ትናገር ነበር ።



በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ
ብርሃን ወጣላቸው ። . . . ሕፃን ተወልዶልናልና ፡ ወንድ
ልጅም ተሰጥቶናልና ፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆ
ናል ፤ ስሙም ድንቅ መካር ፡ ኃያል አምላክ ፡ የዘላለም
አባት ፡ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ። ኢሳ. ፱ ፥ ፪ ፥ ፮ ።

እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ
ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ። ኢሳ. ፵፱ ፥ ፮ ።

ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው ፤ ለማያምኑ ግን . . .
የዕንቅፋት ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ ።

፩ ጴጥ. ፪ ፥ ፯ ፥ ፰ ።

የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደ
ውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ ፤ እንደ ልጆች
እንሆን ዘንድ ፡ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ ።

ገላ. ፬ ፥ ፬ ፥ ፭ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ሕፃኑ ኢየሱስ ዐርባ ቀን በሆነው ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ ለምን ተወሰደ ?
፪ ፡ ስምዖን ለተባለ ሰው ምን ተስፋ ተሰጥቶት ነበር ?
፫ ፡ ስምዖን ሕፃኑን በደስታ ተቀብሎ ምን ተናገረ ?
፬ ፡ ገና ሲናገር ሳለስ የቀረበች ማን ናት ? ምንና ምንስ አደረገች ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ ፡ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰ
ናብተዋለህ ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸ
ውን ማዳንህን አይተዋልና ። ሉቃ. ፪ ፥ ፳፱ - ፴፩ ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፮ ።

## የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ ።

ዮሐ. ፪ ፡ ፲፫ - ፫ ፡ ፲፮ ።

### ፩ ፡ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ምልክቶችን አደረገ ።

ዮሐ. ፪ ፡ ፲፫ - ፳፭ ።

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዓመት ያህል ሲሆነው በሕዝብ መካከል አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ የአይሁድ ፋሲካ ሲቀርብ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከቅፍርናሆም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ ። በቤተ መቅደስም ፡ ለመሥዋዕት የሚሆኑትን በሬዎችና በጎች ርግቦችም የሚሸጡትን ፡ ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ ፡ የገመድ ጅራፍም አበጅቶ ሁሉን ከመቅደስ አወጣ ፡ የለዋጮችንም ገበታዎች ገለበጠ ፡ ገንዘባቸውንም በተነ ፡ ርግብ ሻጪዎችንም ፡ «ይህን ከዚህ ውሰዱ ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት» አላቸው ።

በኢየሩሳሌምም ሳለ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ ። ኢየሱስ ግን በሰው ያለውን ያውቅ ስለ ነበር አይተማመናቸውም ነበር ።



### ፪ ፡ ፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጣ ።

ዮሐ. ፫ ፡ ፩ - ፲፭ ።

በዚያን ጊዜም ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል ሰው በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ ፡ «መምህር ሆይ ፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን» አለው ።

ኢየሱስም መልሶ ፡ «እውነት እውነት እልሃለሁ ፡ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው ። ኒቆዲሞስም ኢየሱስ የሚናገረው ስለ መንፈሳዊ ልደት መሆኑን ሳያስተውል እጅግ ተደንቆ ፡ «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል ? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን ? » አለው ። ኢየሱስም መልሶ ፡ «እውነት እውነት እልሃለሁ ፡ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ፡ ድምፁንም ትሰማለህ ፡ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ፡ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» አለው ።

ኒቆዲሞስም መልሶ ፡ «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ? » አለው ። ኢየሱስም ፡ «አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን ? » ብሎ ፡ ሙሴ የሰቀለውን የነሐስ እባብ ምሳሌ በማድረግ ሰው የሚድንበት በተሰቀለው የሰው ልጅ ፡ በራሱ በክርስቶስ በማመን እንደሆነ እንዲህ ሲል አስረዳው ፤ «ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ ፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል ።»

### ፫ ፡ ኒቆዲሞስ በጓደኞቹ ፈሪሳውያን መካከል ኢየሱስን ደገፈ ።

ዮሐ. ፯ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ፡ ፳፭ - ፴፪ ፡ ፵ - ፶፫ ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በአይሁድ የዳስ በዓል ጊዜ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ሳለ ፡ ስለ እርሱ ብዙ ክርክርና መለያየት ሆነ ። ቃሉን ከሰሙት ሕዝብ አንዳንዶች ፡ «ይህ ክርስቶስ ነው» ሲሉ ፡ ሌሎች ደግሞ ፡ «ክርስቶስ በውኑ ከገሊላ ይመጣልን ? ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ፡ ዳዊትም ከነበረበት መንደር ከቤተልሔም እንደሚመጣ መጽሐፍ አላለምን ?» እያሉ የተወለደበትን ሥፍራ ሳያረጋግጡ አላመኑበትም ። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሕዝቡ ስለ እርሱ እንደሚያንጐራጕሩ ሰምተው እንዲይዙት ሎሌዎችን ላኩ ። እነርሱም ሳይዙት ቢመለሱ ፡ «ያላመጣችሁት ስለምን ነው ?» ሲሉ የላኩአቸውን ጠየቋቸው ። ሎሌዎቹም ፡ «እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም» ብለው መለሱ ። ፈሪሳውያንም ፡ «እናንተ ደግሞ ሳታችሁን ? ከአለቆች በእርሱ ያመነ አለን ? ነገር ግን ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም ነው» ብለው መለሱላቸው ።

በዚያን ጊዜም ከእነርሱ አንዱ ፡ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ ፡ «ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ፡ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን ?» አላቸው ። እነርሱም መለሱና ፡ «አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን ? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ መርምርና እይ» ካሉት በኋላ ወደየቤታቸው ሄዱ ።



www.ethiopianorthodox.org

፩ ፡ ኒቆዲሞስ በዕለተ ስቅለት ለኢየሱስ
ያለውን ፍቅር ገለጠ ። ዮሐ. ፲፱ ፡ ፴፰ - ፵፪ ።

በዚህ ከዳስ በዓል በኋላ መንፈቅ ቈይቶ
በሆነው የአይሁድ ፋሲካ ፡ የካህናት አለ
ቆችና ፈሪሳውያን ፡ እጅግ እየጠነከረ
በሚሄድ መቃወማቸው የተነሣ ኢየሱስን
ለሞት አሳልፈው ሰጡት ። በዚያም የስቅ
ለት ዕለት እንደ ኒቆዲሞስ ወገኖቹን ከመ
ፍራት የተነሣ የኢየሱስ ደቀ መዘምር
መሆኑን ሰውሮ የነበረ አማካሪ ፡ የአርማት
ያስ ዮሴፍ ፡ ወደ ጲላጦስ ደፍሮ በመቅረብ
የጌታን ሥጋ ለመውሰድ አስፈቀደ ። እር
ሱም ገና ማንም ባልተቀበረበት ከዓለት
በተወቀረ መቃብር ሊያኖረው ሲያዘጋጅ ፡
ኒቆዲሞስ ደግሞ ዋጋው ውድ የሆነ መቶ
ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል
ሽቱ ይዞ መጣ ፡ እንደ አይሁድ አገናነዝ
... ሥጋውን ከሽቱ ጋር በተልባ
እግር ልብስ በመከፈን ዮሴፍ ... ። 

* * *

እውነት እውነት እልሃለሁ ፡ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር
የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ። ዮሐ. ፫ ፡ ፫ ።

ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚ
ያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ
የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል ። ዮሐ. ፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኒቆዲሞስ ከምን ወገን ነበረ ? በሌሊትስ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ምን አለው ?
፪ ፡ ጌታችን ምን ብሎ መለሰለት ?
፫ ፡ ኒቆዲሞስ ጌታችንን አክብሮ እንደ ወደደው በምን አሳየ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ ፡
የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ ።
መዝ. ፶ (፶፩) ፡ ፲ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፯ ።

## የሰማርያ ሴት ።

ዮሐ. ፬ ፡ ፩ - ፵፪ ።

፩ ፡ ኢየሱስ በሰማርያ አለፈ ።
ዮሐ. ፬ ፡ ፩ - ፯ ።

ደቀ መዛሙርቱ እየበረከቱ መሄዳቸውን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ጌታ ባወቀ ጊዜ ፡ ይሁዳን ትቶ በሰማርያ በኩል በሚያልፈው መንገድ ወደ ገሊላ ለመመለስ ፡ ከገሊላ የተከተሉትን ደቀ መዛሙርት ይዞ ተነሣ ። ሰማርያንም ሲያቋርጥ ለስድስት ሰዓት አቅራቢያ ሲካር ወደሚባል ፡ ጥንታዊ የሆነ የያዕቆብ ውኃ ጕድጓድ ወደ ነበረበት ደረሰ ። መንገድ ከመሄድም ደክሞ በጕድጓዱ አጠገብ ተቀመጠ ፡ ደቀ

 መዛሙርቱም ምግብ ለመግዛት ወደ ከተ
ሄዱቱ ገቡ ። በዚያም ተቀምጦ ሳለ ከአይ
ዶች ጋር ግንኙነት ካልነበራቸው ወገን
ነበረች አንዲት ሳምራዊት ሴት ውኃ
ትቀዳ መጣች ።

፤ የሳምራዊት ሴትን አነጋገረ ።

ዮሐ. ፬ ፥ ፯ - ፳፮ ።

ኢየሱስ የሳምራዊቲቱን ሴት ከውኃው
ጉድጓድ ስትደርስ ባያት ጊዜ ፤ «ውኃ
ጠጪኝ» አላት ። ሴቲቱም ተደንቃ ፤
አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት
ት ከምሆን ከእኔ ውኃን እንዴት ትለም
ለህ ?» አለችው ። እርሱም መልሶ ፤ «የእ
ግዚአብሔርን ስጦታና ውኃ አጠጪኝ
ሚልሽ ማን እንደሆነ ብታውቂስ ፤ አንቺ
ለምኚው ነበርሽ ፤ የሕይወትም ውኃ
ይሰጥሽ ነበር» አላት ። ሴቲቱም ፤ የሕይ
ወት ውኃ ምን መሆኑን ባለማስተዋልዋ ፤
ጌታ ሆይ መቅጃ የለህም ፤ ጕድጓዱም
ጥልቅ ነው ፤ እንግዲህ የሕይወት ውኃ
ወዴት ታገኛለህ ? በውኑ አንተ ይህን
ጉድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ
ትበልጣለህን ?» አለችው ።

ኢየሱስም መልሶ ፤ «ከዚህ ውኃ የሚ
ጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል ፤ እኔ ከምሰ
ጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም
አይጠማም ፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ
ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ
ምንጭ ይሆናል እንጂ» አላት ። ሴቲቱም፤
«ጌታ ሆይ ፤ እንዳልጠማ ፤ ውኃም ልቀዳ
ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ»
አለችው ።

ኢየሱስም ፤ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ
ወደዚህ ነዪ» አላት ። እርስዋም ፤ «ባል
የለኝም» አለችው ። ኢየሱስም ፤ «በዚህስ
እውነት ተናገርሽ ፤ አምስት ባሎች ነበ
ሩሽ ፤ አሁን ከአንቺ ጋር ያለውም ባልሽ
አይደለም» አላት ። ሴቲቱም ይህን ሁሉ
በማወቁ ተገርማ ፤ «ጌታ ሆይ ፤ ነቢይ እን
ደሆንህ አያለሁ» አለችና ወገኖችዋ ይሰግ
ዱበት የነበረውን ገሪዛን የተባለውን
ተራራ እያመለከተች ፤ «አባቶቻችን በዚህ
ተራራ ሰገዱ ፤ እናንተም ፤ ሰው ሊሰግድ
በት የሚገባው ሥፍራ በኢየሩሳሌም ነው
ትላላችሁ» አለች ። ኢየሱስም ፤ «አንቺ
ሴት እመኚኝ ፤ በዚህ ተራራ ወይም በኢየ
ሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመ
ጣል ። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ
ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱ
በት ጊዜ ይመጣል ፤ አሁንም ሆኖአል ፤
አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻ
ልና ። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፤ የሚሰ
ግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱ
ለት ያስፈልጋቸዋል» ብሎ መለሰላት ።

ሴቲቱም ፤ «ክርስቶስ የሚባል መሢሕ
እንዲመጣ ዐውቃለሁ ፤ እርሱ ሲመጣ
ሁሉን ይነግረናል» አለችው ። ኢየሱስም ፤
«የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ» አላት ።

፫ ፤ ሴቲቱ ስለ እርሱ መሰከረች ።

ዮሐ. ፬ ፥ ፳፯ - ፵፪ ።

በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡና
ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ ። እርስዋም
እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ፤ ለሰዎ
ችም ፤ «ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው
ኑና እዩ ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን ? »
አለች ። ከከተማም ወጥተው ወደ እርሱ
ይመጡ ነበር ።

ይህም ሲሆን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ፤
«መምህር ሆይ ፤ እህል ብላ» ብለው ለመ
ኑት ። እርሱ ግን ፤ «እናንተ የማታውቁት
የምበላው መብል ለእኔ አለኝ» አላቸው ።
እነርሱም ፤ «የሚበላው አንድ ሰው አምጥ
ቶለት ይሆንን ?» ተባባሉ ። ኢየሱስም ፤
«የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ
ዘንድ ፤ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው»
አላቸው ።

ከሴቲቱ ከሰሙት የሰማርያ ሰዎች ወደ
እርሱ መጡ ፤ በእነርሱም ዘንድ እንዲኖር
ለመኑት ፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ቈየ ።
ስለ ቃሉም ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች
አመኑ ፤ ሴቲቱንም ፤ «አሁን የምናምን
ስለ ቃልሽ አይደለም ፤ እኛ ራሳችን ሰምተ
ነዋልና ፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓ
ለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን»
ይሉአት ነበር ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፤ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል ፤
እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠ
ማም ፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይ
ወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ ። ዮሐ. ፬ ፥ ፲፬ ።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና
በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል ። ዮሐ. ፬ ፥ ፳፬ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ባነጋገራት ጊዜ ሳምራዊትዋ ስለምን ተደነቀች ?
፪ ፡ «ከያዕቆብ ትበልጣለህን ? » ብላ የጠየቀችው ኢየሱስ ምን ቢላት ነው ?
፫ ፡ «ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ» ያለችው እርሱ ምን ቢላት ነው ?
፬ ፡ ስለ ክርስቶስ መምጣት ያሳሰባት ምን ቢላት ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ መረመርኸኝ ፡ ዐወቅኸኝም ።
አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ዐወቅህ ፤
አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ ።
አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ ፤ . . . .
ወደ እኔ ተመልከት ማረኝም ።

መዝ. ፩፻፴፰ (፩፻፴፱) ፥ ፩ ፡ ፪ ፤ ፹፭ (፹፮) ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።


www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፰ ።

# የኢየሱስ የቃሉ ኃይል ።

ዮሐ. ፬ ፣ ፵፮ - ፶፬ ፤ ሉቃ. ፯ ፣ ፩ - ፲፯ ።

## ፩ ፤ የአንድ ሹም ልጅ ።

ዮሐ. ፬ ፣ ፵፮ - ፶፬ ።

ኢየሱስ መንገዱን በመቀጠል ሰማርያን አልፎ ወደ ገሊላ ቃና ደረሰ ። በቅፍርናሆ ምም ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት የሆነ አንድ ሹም ነበረ ። እርሱም የኢየሱ ስን ወደ ቃና መምጣት ሲሰማ ፣ ወዲያውኑ ተነሥቶ ወደ እርሱ መጣ ። ቀርቦም ፣ «ጌታ ሆይ ፣ ልጄ ሊሞት ነውና ወደ ቅፍር ናሆም ወርደህ ፈውስልኝ» ብሎ ለመ ነው ።

ኢየሱስም ፣ «ምልክትና ድንቅ ካላያ ችሁ ከቶ አታምኑም» አለው ። ሹሙም ፣ «ጌታ ሆይ ፣ ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ»



www.ethiopianorthodox.org

አለው ። ኢየሱስም ፣ «ሂድ ፣ ልጅህ በሕይ ወት አለ» አለው ። ሰውዬውም ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ ። ገናም በመን ገድ ላይ ሳለ አገልጋዮቹ ሊገናኙት መጥ ተው ፣ «ብላቴናህ በሕይወት አለ» ብለው ነገሩት ። አባትዬውም ፣ «የዳነበት በስንት ሰዓት ነበረ ?» ብሎ ቢጠይቃቸው ፣ «ትና ንት በሰባት ሰዓት ንዳዱ ለቀቀው» አሉት። አባትዬውም ኢየሱስ ፣ ልጅህ በሕይወት አለ ባለበት ሰዓት መሆኑን ዐወቀ ፤ ከነ ቤተሰቦቹም በኢየሱስ አመነ ።

## ፪ ፤ የአንድ መቶ አለቃ ባሪያ ።

ሉቃ. ፯ ፣ ፩ - ፲ ፤ ማቴ. ፰ ፣ ፲ - ፲፫ ።

አንድ የሮም ጭፍራ መቶ አለቃ በቅፍርና ሆም ለአይሁዶች ምኵራብ ሠርቶ ከእነ ርሱ ጋር በወዳጅነት ሲኖር ሳለ ፣ የሚወ ደው ባሪያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር ። በዚያን ጊዜም ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም እንደ ገባ ተሰማ ፤ መቶ አለቃውም የአይ ሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከ ። እነር ሱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው የመቶ አለቃ ውን ባሪያ እንዲፈውስለት እየለመኑ ፣ «ይህን እንድታደርግለት መቶ አለቃው ይገባዋል ፤ ሕዝባችንን በመውደድ ምኵ ራብ ራሱ ሠርቶልናል» አሉት ። ኢየሱ ስም ከእነርሱ ጋር ሄደ ።

መቶ አለቃውም በቤት ሆኖ የኢየሱስን መምጣት ሲጠባበቅና ስለ እርሱ የተረዳ ውን ሁሉ ሲያወጣና ሲያወርድ ሳለ ፣ እኔ እንኳ በተሰጠኝ ሥልጣን ከጭፍራዬ አንዱን ፣ ወደዚያ ሂድ ፣ ባሪያዬንም ፣ ይህን አድርግ በማለት ጉዳዬን ካስፈጸ ምሁ ፣ እንዴት ይልቅ እርሱ ካለበት ሆኖ ቃል ቢናገር የሚፈልገውን ሁሉ አያስፈ ጽም ! በማለት ወዳጆች የሆኑትን ሁለተኛ ልኮ ፣ «ጌታ ሆይ ፣ ከቤቴ ጣራ በታች ልት ገባ አይገባኝምና አትድከም ፤ ወደ አን ተም ልመጣ እንዲገባኝ ሰውነቴን አልቈ ጠርሁትም ፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር ፣ ብላቴናዬም ይፈወሳል ። እኔ ደግሞ ለሌ ሎች ተገዥ ነኝና ፣ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ ፤ አንዱንም ፣ ሂድ ብለው ይሄዳል ፣ ሌላውንም ፣ ና ብለው ይመጣል ፤ ባሪያዬ ንም ፣ ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል» አለው ።

ኢየሱስም ይህን ሰምቶ ተደነቀ ፤ ዞወር ብሎም ለተከተሉት ሕዝብ ፣ «እላችኋ ለሁ ፣ በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም ። እላችኋለ ሁም ፣ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆ ብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመ ጣሉ ፤ የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ ፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል» አላቸው ። የተ ላኩትም ወደ ቤት ተመልሰው ባሪያውን ባለ ጤና ሆኖ አገኙት ።

## ፫ ፤ የአንዲት መበለት ልጅ ።

ሉቃ. ፯ ፣ ፲፩ - ፲፯ ።

በማግሥቱም ኢየሱስ ናይን ወደምትባል ከተማ ሄደ ፤ ደቀ መዛሙርቱና ብዙ ሕዝ ብም ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ ። ወደ ከተ ማዪቱም በር በቀረበ ጊዜ እነሆ ፣ የሞተ ሰውን ተሸክመው አወጡ ፤ የሞተውም ለእናቱ አንድ ነበረ ፣ እናቱም መበለት ነበ ረች ፣ ብዙም የከተማ ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ ። ጌታም ባያት ጊዜ አዝኖ ላት ፣ «አታልቅሽ» ሲል ቀርቦ ቃሬዛውን ነካ ፤ የተሸከሙትም ቆሙ ። ኢየሱስም፣ «አንተ ጐበዝ ፣ እልሃለሁ ፣ ተነሣ » አለው ። የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ፣ ሊናገርም ጀመረ ፤ ለእናቱም ሰጣት ።

ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና ፡ «ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ተነሥቶአል» ደግሞም ፡ «እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ» እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ ። ዝናውም በዚያ ዙሪያ ወዳሉት ሁሉ ወጣ ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፡ «አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ይህ የማደርገው ሥራ ፡ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራል ።»
ዮሐ. ፭ ፡ ፴፮ ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ ፡ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው ፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ ። ዮሐ. ፭ ፡ ፳፭ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ሹሙ ከነቤተሰቦቹ በኢየሱስ ሊያምን የቻለው ፡ ምን በመረዳቱ ነው ?
፪ ፡ የመቶ አለቃው ፡ «ቃል ብቻ ተናገር ፡ ብላቴናዬም ይፈወሳል» ያለው ፡ ምን በማስተዋሉ ነው ?
፫ ፡ ኢየሱስ እንዴት አድርጎ የሞተውን ሰው አስነሣ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ልመናዬ ወደ ፊትህ ትድረስ ፡
እንደ ቃልህ አድነኝ ።
መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፩፻፸ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፲፱ ።

## የፈሪሳውያን ክርክር ።

ማቴ. ፲፪ ፡ ፩ - ፲፬ ፡ ማር. ፯ ፡ ፩ - ፳፫ ።

### ፩ ፡ የሰንበት ክርክር ።

ማቴ. ፲፪ ፡ ፩ - ፲፬ ፡ ማር. ፪ ፡ ፳፫ - ፫ ፡ ፮ ፡ ሉቃ. ፮ ፡ ፩ - ፲፩ ።

በአንድ ሰንበት ኢየሱስ በእርሻ መካከል ሲያልፍ ደቀ መዛሙርቱ ተራቡና እሸት እየቈረጡ በእጃቸውም እያሹ ይበሉ ጀመር ። የሚከሱበትንም ምክንያት የሚፈልጉበት ፈሪሳውያን ይህን አይተው ፡ «እነሆ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ» ብለው ወቀሱት ።

«በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን» ሲሉ ከሽማግሌዎቻቸው ከተቀበሉት ወግ ይጠቅሱ ነበር ። የእግዚአብሔር ሕግ ፡ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ ፤ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥራ» የሚል ሲሆን ፤ የሽማግሌዎች ወግ ፡ ሥራ ምንድር ነው ? ለሚል ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ፡ በሰንበት ማድረግ የማይገቡትን ብዙ ነገሮች ከልክሎ ነበር ። ለምሳሌ ፡ ሰው በእርሻ መካከል ቢገባ እሸትን በእጁ ቈርጦ

ያሸ መብላት የተፈቀደ ሲሆን (ዘዳግ. ፳፫ ፡
፭) ማጨድንና ማበራየትን ስለሚመ
ል በሰንበት አልተፈቀደም ይል ነበር ።
ንደዚሁም ወደ ሞት የማያደርስ በሽታ
ሰንበት እንዳይታከም ይከለክል ነበር ።
ፈሪሳውያንም ከወጋቸው እየጠቀሱ ፡
ደቀ መዛሙርትህ ያልተፈቀደውን ያደር
ሉ» ሲሉት ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ቃል
መጥቀስ ፡ «ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበ
ት በተራቡ ጊዜ ፡ ከካህናት በቀር ሌላ
ንዲበላው ያልተፈቀደውን የመሥዋዕት
ንጀራ እንደ በሉ አላነበባችሁምን ? ካህ
ትስ በሰንበት በመቅደስ አገልግሎታቸ
ን ሲፈጽሙ ሰንበትን እንደሚያረክሱ
ጢአትም እንደማይሆንባቸው በሕጉ አላ
ነበባችሁምን ?» በማለት እርሱ ከመቅደስ
ሚበልጥ የሰው ልጅ ፡ የሰንበት ጌታ እን
ሆነ ሲያስረዳ ፡ «ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥ
አል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠ
ም» አላቸው ። ከትንቢተ ሆሴዕም
ቅሶ ፡ «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕት
ም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታ
ቁስ ፡ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኰነና
ሁም ነበር» አለ ። (ሆሴዕ ፮ ፡ ፮ ።)
ከዚያም አልፎ ወደ ምኵራባቸው ገባ ።
ሆም ፡ እጁ የሰለለች ሰው ነበረ ። ፈሪሳ
ያን ፡ ስለ ምሕረት የነገራቸውን ሳያስተ
ሉ በኢየሱስ ላይ የክስ ምክንያት እንዲ
ኙ በመጠባበቅ ፡ «በሰንበት መፈወስ
ፈቅዶአል ? » ብለው ጠየቁት ። እርሱ
ን ፡ «ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰን
ት በጕድጓድ ቢወድቅበት ፡ ይዞ የማያወ
ው ሰው ማን ነው ? እንግዲህ ሰው ከበግ
ልቅ እንደምን አይበልጥም ! ስለዚህ በሰ
ነት መልካም ማድረግ ተፈቅዶአል»
ላቸው ። ስለ ልባቸውም ድንዛዜ አዝኖ
ሪያውን እየተመለከተ በቍጣ አያቸው ፡
ውየውንም ፡ «እጅህን ዘርጋ» አለው ።

ዘረጋትም ፡ እንደ ሁለተኛዪቱም ደኅና
ሆነች ። ፈሪሳውያን ግን በቍጣ ተሞል
ተው ወጡ ፤ እንዴት አድርገው እንዲያጠ
ፉትም ተማከሩ ።

## ፪ ፡ እጅን ስለ መታጠብ ክርክር ።

ማር. ፯ ፡ ፩ - ፳፫ ፤ ማቴ. ፲፭ ፡ ፩ - ፳ ፤
ሉቃ. ፲፩ ፡ ፴፯ - ፶፩ ፤ ማቴ. ፳፫ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ።

በሌላ ጊዜም ከኢየሩሳሌም የመጡ ፈሪሳ
ውያንና ጸሐፍት ወደ ኢየሱስ ተሰብስ
በው ፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንድ እንደ
ሽማግሌዎች ወግ እጃቸውን ሳይታጠቡ
ሲበሉ አዩና ፡ «ደቀ መዛሙርትህ እንደ
ሽማግሌዎች ወግ ስለምን አይሄዱም ? »
ብለው ጠየቁት ።

እርሱም መልሶ ፡ «እናንተስ ስለ ወጋ
ችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን
ትተላለፋላችሁ ? እግዚአብሔር ፡ አባትህ
ንና እናትህን አክብር ብሎአልና ፤ እናንተ
ግን ትላላችሁ ፡ ሰው እናቱን ወይም አባ
ቱን ፦ ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ
ለእግዚአብሔር የሚሰጥ መባ ነው ቢል ፡
ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ
ወደ ፊት አትፈቅዱለትም ። ባስተላለፋች
ሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራ
ላችሁ ፤ እንደዚሁም ይህን የሚመስል
ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ ። እናንተ ግብ
ዞች ፡ ኢሳይያስ ስለ እናንተ ፦ ይህ ሕዝብ
በከንፈሩ ያከብረኛል ፡ ልቡ ግን ከእኔ
በጣም የራቀ ነው ፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ
ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩ
ኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ» አላ
ቸው ።

ደግሞም ሕዝቡን ጠርቶ ፡ «ስሙ ፡ አስ
ተውሉም ፤ ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚ
ያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጭ የሚገባ
ውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም ።
የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ» አላ



ቸው ። ወደ ቤትም ከገባ በኋላ ስለዚህ ነገር
ደቀ መዛሙርቱ ላቀረቡት ጥያቄ መልስ
ሲሰጥ ፡ «ከውጭ ወደ ሰው የሚገባ ሊያረ
ክሰው ምንም እንዳይችል አትመለከቱ
ምን ? ወደ ሆድ እንጂ ወደ ልብ አይገባ
ምና ። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ
አሳብ ፡ ዝሙት ፡ መስረቅ ፡ መግደል ፡
ምንዝርነት ፡ መጐምጀት ፡ ክፋት ፡ ተን
ኰል ፡ መዳራት ፡ ምቀኝነት ፡ ስድብ ፡ ትዕ
ቢት ፡ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከው
ስጥ ይወጣል ፡ ሰውንም ያረክሰዋል» አላ
ቸው ።

በሌላ ቀን ደግሞ ኢየሱስ ሲያስተምር
አንድ ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምሳ ይበላ
ዘንድ ለመነው ፤ እርሱም ገብቶ ተቀመጠ።
ከምሳም በፊት አስቀድሞ እንዳልታጠበ
ባየው ጊዜ ፈሪሳዊው ተደነቀ ። ጌታም ፡

«አሁን እናንተ ፈሪሳውያን የጽዋውንና
የወጭቱን ውጭ ታጠራላችሁ ፡ ውስጣ
ችሁ ግን ቅሚያና ክፋት ሞልቶበታል ።
እናንተ ደንቆሮች ፡ የውጭውን የፈጠረ
የውስጡን ደግሞ አልፈጠረምን ? ነገር
ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋ
ችሁ ስጡ ፡ እነሆም ሁሉ ንጹሕ ይሆንላች
ኋል» አለው ።

በሌላም ጊዜ ኢየሱስ ፡ «እናንተ ግብ
ዞች ፡ ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም
አሥራት ስታወጡ ፡ በሕግ ያለውን ዋና
ነገር ፡ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም
ስለምትተዉ ወዮላችሁ ። ሌላውን ሳት
ተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር ።
እናንተ ዕውሮች መሪዎች ፡ ትንኝን የምታ
ጠሩ ግመልንም የምትውጡ» አላቸው ።

* * *

ጽድቃችሁ ከጸሐፊዎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ
ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም ። ማቴ. ፭ ፡ ፳ ።

ከልብ ክፉ አሳብ ፡ መግደል ፡ ምንዝርነት ፡ ዝሙት ፡
መስረቅ ፡ በውሸት መመስከር ፡ ስድብ ይወጣልና ፡
ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው ። ማቴ. ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ፡ «በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን» ብለው የጠየቁትን
በቍጣ የተመለከታቸው ስለምን አዝኖ ነው ?
፪ ፡ ሰውን የሚያረክሰው ምንድር ነው ?
፫ ፡ የሕግ ዋና ነገሮች ምንድር ናቸው ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለምና
ከባሪያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ ።


መዝ. ፩፻፵፪ (፩፻፵፫) ፡ ፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፳ ።

# ጌታችን በጌርጌሴኖን አገር ።

ማር. ፬ ፡ ፴፭ - ፭ ፡ ፳ ።



የባሕር ጸጥ ማለት ።

ማር. ፬ ፡ ፩ ፡ ፴፫ ፡ ፴፭ - ፵፩ ።

የሱስ በገሊላ ባሕር ዳር ለተሰበሰቡት ሕዝብ ፡ መስማት በሚችሉበት ጠን ቃሉን ሲያስተምራቸው ውሎ ፡ ሻሽ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ፡ «ወደ ማዶ ሻገር» አላቸው ። ሕዝቡንም ትተው ያው በጀልባ እንዳለ ወሰዱት ፡ ሌሎች ባዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ ። እርሱም ጀልባዩቱ በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ፡ አንቀላፋም ።

በባሕሩም ላይ ሳሉ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ጣ ፤ በእርሱም የተነሣው ማዕበል ውኃ ን እያማታ ጀልባዩቱን ይሞላ ነበር ። መዛሙርቱም ቀሰቀሱትና እጅግ ጨንቀው ፡ «መምህር ሆይ ፡ ስንጠፋ ገድህምን ?» አሉት ። ነቅቶም ነፋሱን ጸው ፡ ባሕሩንም ፡ «ዝም በል ፡ ጸጥ » አለው ። ነፋሱም ተወ ፡ ታላቅ ጸጥ ሆነ ። «እንዲህ የምትፈሩ ስለምን ነው ! እንዴትስ እምነት የላችሁም ?» አላቸው ። እጅግም ፈሩና ፡ «እንግዲህ ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው ?» ተባባሉ ።

፪ ፤ የአጋንንት መሰደድ ።

ማር. ፭ ፡ ፩ - ፲፫ ፡ ሉቃ. ፰ ፡ ፳፮ - ፴፫ ።

ወደ ባሕር ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር ደረሱ ። ጌታም ከጀልባዩቱ ሲወርድ ፡ አጋንንት ያደሩበት ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ ። እርሱም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ በመቃብር እንጂ በቤት አይኖርም ነበር ። ሊያሥረውም የሚችል አልነበረም ፤ የሚታሠርበትንም እግር ብረትና ሰንሰለት ይሰባብር ይበጣጥስም ነበር ፤ ሌሊትና ቀንም በመቃብርና በተራራ እየሆነ ሁልጊዜ ይጮኽ ነበር ፤ ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር ።

ይህ ሰው ኢየሱስን ከሩቅ ባየ ጊዜ ሰገደ ፤ በታላቅ ድምፅም ፡ «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ ፡ ከአንተ ጋር ምን አለኝ ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ» አለ ፤ «አንተ ርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ» ብሎት ነበርና።

ኢየሱስም ፡ «ስምህ ማን ነው ? » ብሎ ጠየቀው ፡ «ብዙዎች ነንና ስሜ ሌጌዎን * ነው» አለው ፤ ከአገር ውጭም እንዳይሰዳቸው አጥብቆ ለመነው ። በዚያም ተራራ ጥግ ብዙ የእሪያ መንጋ ይሰማራ ነበርና ፡ «ወደ እሪያዎቹ እንድንገባ ስደደን » ብለው ለመኑት ፤ እርሱም ፈቀደላቸው ። አጋንንትም ከሰውዬው ወጥተው ወደ እሪያዎች ገቡ ፤ መንጋውም ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና ሰጠሙ ።

፫ ፡ የጌርጌሴኖን ሰዎች አለመቀበል ።

ማር. ፭ ፡ ፲፬ - ፳ ፡ ሉቃ. ፰ ፡ ፴፬ - ፴፱ ።

እረኞችም የሆነውን ባዩ ጊዜ ሸሽተው በከተማዪቱና በአገሩ አወሩ ። ብዙዎችም የሆነውን ሊያዩ ሲመጡ ፡ አጋንንት የወጡለትን ሰው ልብሱን ለብሶ ልቡም ተመልሶለት በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ ። በዙሪያውም በጌርጌሴኖን አገር ያሉት ሁሉ ታላቅ ፍርሃት ይዞአቸው ከእነርሱ እንዲሄድ ኢየሱስን ለመኑት ፤ ከዚያም ሊሄድ ተነሣ ።

ወደ ጀልባዩቱም በገባ ጊዜ የዳነው ሰውዬ ከእርሱ ጋር እንዲኖር ለመነው ። ኢየሱስም አልፈቀደለትም ፡ ነገር ግን ፡ «ወደ ቤትህ ተመለስ ፡ ጌታም እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ ፡ እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው» ብሎ አሰናበተው ። ሄዶም ፡ ኢየሱስ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት አሥር ከተማ በሚባል አገር ይሰብክ ጀመር ፤ ሁሉም ተደነቁ ።

* * *

እንዲህ የምትፈሩ ስለምን ነው ? እንዴትስ እምነት የላችሁም ?

ማር. ፬ ፡ ፵ ።

ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ ።

፩ ዮሐ. ፫ ፡ ፰ ።

* * *


ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ምን በማድረግ ባሕሩን ጸጥ አሰኘ ?
፪ ፡ አጋንንት ያደሩበት ሰው እንዴት ባለ ሁኔታ ይኖር ነበር ?
፫ ፡ ከዳነ በኋላስ ምን ልዩነት ታየበት ? ጌታችንስ ምን ብሎ አዘዘው ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ዝማሬን ባቀረብሁልህ ጊዜ ከንፈሮቼ ደስ ይላቸዋል ፡
አንተ ያዳንሃትም ነፍሴ ። . . .
አንደበቴ ደግሞ ሁልጊዜ ጽድቅህን ይናገራል ።

መዝ. ፸ (፸፩) ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ።

* እስከ ፮ ሺህ ወታደር የነበረው የሮም ጦር ሠራዊት ክፍል ሌጌዎን ተባለ ።


www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፩ ።

## የመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ።

ሉቃ. ፯ ፣ ፲፰ - ፴፭ ፤ ማር. ፮ ፣ ፲፬ - ፳፱ ።

### ፩ ፤ ዮሐንስ ለኢየሱስ ጥያቄን አቀረበ ።

ማር. ፩ ፣ ፲፬ ፤ ፲፭ ፤ ፮ ፣ ፲፯ ፤ ፲፰ ፤
ሉቃ. ፯ ፣ ፲፰ - ፳፫ ፤ ማቴ. ፲፩ ፣ ፪ - ፮ ።

ኢየሱስን በሕፃንነቱ ሊያስገድለው የፈለገው የታላቁ ንጉሥ ሄሮድስ መንግሥት ለሦስት ልጆቹ በተከፈለ ጊዜ ፣ በአባቱ ስም ሄሮድስ ተብሎ የተጠራው ልጁ የገሊላ ገዥ ሆነ ። እርሱም የወንድሙን ሚስት ሄሮድያዳን ስላገባና ስለ ሌላ ክፋቱም ሁሉ መጥምቁ ዮሐንስ ይገሥፀው ነበር ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕዝብ መካከል አገልግሎቱን እንደ ጀመረ ፣ ሄሮድስ ክፋትን በክፋት ላይ ጨምሮ የጌታን መንገድ ያዘጋጀውን መጥምቁ ዮሐንስን በግዞት አሳሠረው ።

ዮሐንስም ታሥሮ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ኢየሱስ የሚያደርገውን ሁሉ አወሩት ። ዮሐንስም ከእነርሱ ሁለቱን ጠርቶ ፣ «የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ ?» ብሎ ወደ ኢየሱስ ላከ ። የተላኩትም ወደ ኢየሱስ መጥተው ፣ «መጥምቁ ዮሐንስ ፣ የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ ? ብሎ ወደ አንተ ላከን» አሉት ። በዚያች ሰዓት ከደዌና ከሥቃይ ከክፉዎች መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ ፤ ለብዙ ዕውሮችም ማየትን ሰጠ ። ለተላኩትም ፣ «ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩት ፤ ዕውሮች ያያሉ ፣ አንካሶችም ይሄዳሉ ፣ ለምጻሞችም ይነጻሉ ፣ ደንቆሮችም ይሰ



www.ethiopianorthodox.org

ማሉ ፣ ሙታንም ይነሣሉ ፣ ለድኆችም ወንጌል ይሰበካል ፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው» ሲል በነቢዩ ኢሳይያስ የተሰጠውን ትንቢት በማሳሰብ ወደ ዮሐንስ መለሳቸው ።

(ኢሳ. ፳፯ ፣ ፲፱ ፤ ፴፭ ፣ ፭ ፣ ፮ ፤ ፷፩ ፣ ፩ ።)

### ፪ ፤ ኢየሱስ ለዮሐንስ መሰከረ ።

ሉቃ. ፯ ፣ ፳፬ - ፴፭ ፤ ማቴ. ፲፩ ፣ ፯ - ፲፱ ።

የዮሐንስም መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ ኢየሱስ ለሕዝብ ስለ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፤ «ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ ? ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን ? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ ? ቀጭን ልብስ የለበሰውን ሰውን ? እነሆ ፣ ጌጠኛ ልብስ የሚለብሱ በነገሥታት ቤት አሉ ። ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ ? ነቢይን ? አዎን እላችኋለሁ ፣ ከነቢይም የሚበልጠውን ። እላችኋለሁ ፣ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል ።»

በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁት ሕዝብም ይህን ሁሉ በደስታ ሰሙ ። ፈሪሳውያንና የሕግ አዋቂዎች ግን የእግዚአብሔርን ምክር ጥለው ዮሐንስን ሆነ ጌታን አላከበሩም ። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፤ «እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን እመስላቸዋለሁ ? በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ ፣ እርስ በርሳቸውም እየተጠሩ ፣ እንቢልታ ነፋንላችሁ አልዘፈናችሁም ፤ ሙሾ አወጣንላችሁ አላለቀሳችሁምም ይላሉ ። መጥምቁ ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላ የወይን ጠጅም ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና ፣ ጋኔን አለበት አላችሁት ። የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና ፣ እነሆ በላተኛና የወይን ጠጭ ፣ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ አላችሁት ። ጥበብም በልጆችዋ ሁሉ ጸደቀች ።»

### ፫ ፤ የዮሐንስ ሞት ።

ማር. ፮ ፣ ፲፱ - ፳፱ ፤ ማቴ. ፲፬ ፣ ፫ - ፲

በዚህም ጊዜ ሁሉ ሄሮድያዳ በዮሐንስ ቂ
ይዛ ልታስገድለው ትፈልግ ነበረች ። ሄ
ድስ ግን ዮሐንስ ጻድቅ ሰው እንደሆ
ዐውቆ ይፈራውና ይጠብቀው ነበር ፤ በ
ስታም እየሰማው በብዙ ነገር ያመነ
ነበር ። ነገር ግን የተወለደበትን ቀን ለማ
በር ለገሊላ ሹማምንት ያደረገው ታላ
ግብር ለሄሮድያዳ ፍላጎት ምቹ ጊዜ ሆነ ፤
ለግብር ተቀምጠው ሳሉ የሄሮድያዳ ልጅ
ገብታ ስትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋ
የነበሩትን ደስ አሰኘቻቸው ። ንጉሡም
«የምትወጂውን ሁሉ ለምኚኝ እሰጥሻ
ለሁ ፤ የመንግሥቴን እኩሌታ ስንኳ
ቢሆን እሰጥሻለሁ» ብሎ ማለላት ። ወጥ
ታም ለእናትዋ ፣ «ምን ልለምነው ?»
አለች ። እርስዋም ፣ «የመጥምቁን የዮሐን
ስን ራስ» አለች ።

ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገባችና ፣ «የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ» ብላ ለመነችው ። ንጉሡም እጅግ አዘነ ፤ ነገር ግን ስለ መሐላው ፣ ከእርሱም ጋር ስለ ተቀመጡት ሊነሣት አልወደደም ። ወደ ወኅኒም ልኮ የዮሐንስን አንገት አስቈረጠው ። ራሱንም በወጭት አምጥተው ለብላቴናዪቱ ሰጡአት ፣ ወደ እናትዋም ወሰደችው ። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው መጡ ፤ በድኑንም ወስደው ቀበሩት ፣ መጥተውም ለኢየሱስ አወሩት ።

### ፬ ፤ ሄሮድስና ክርስቶስ ።

ማር. ፮ ፣ ፲፬ ፤ ሉቃ. ፱ ፣ ፱ ፤ ፳፫ ፣ ፰ - ፲፪ ።

የጌታችን ስምና ዝና በገሊላ በተገለጠ ጊዜ ሄሮድስ ፣ ይህ ማን ይሆን ? ይህን ኃይል ሁሉ የሚያደርግ እኔ አንገቱን ያስቈረጥሁት መጥምቁ ዮሐንስ ይሆንን ? ብሎ

በመገረም ሊያየው ይሻ ነበር ። ነገር ግን ኢየሱስን ያየው በግዛቱ በገሊላ ሳይሆን በኢየሩሳሌም ነበረ ።

እንዲህም ሆነ ፤ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች ኢየሱስን አስይዘው ወደ ጲላጦስ አሳልፈው በሰጡበት የፋሲካ በዓል ጊዜ ሄሮድስ በኢየሩሳሌም ተገኝቶ ነበር ። ጲላጦስም በኢየሱስ ሊፈርድ ስላልወደደ ፡ በሄሮድስ ግዛት ከገሊላ መሆኑን በሰማ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው ።

ሄሮድስም ኢየሱስን ባየ ጊዜ ደስ አለው ምልክትንም ሲያደርግ ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበርና በብዙ ቃል ጠየቀው ። እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም ። የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎችም አጽንተው ሲከሱት ዝም አለ ። ሄሮድስም ከነሠራዊቱ ናቀው ፡ ዘበተበትም ፤ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው ። እንዲሁ አስቀድሞ የዮሐንስን ቃል እየሰማ ጻድቅ ሰው ነው ብሎ ይፈራው የነበረው ንጉሥ ፡ ንስሐ ባለመግባቱ ልቡን አደንድኖ ጌታን ራሱን ወደ መናቅና ማላገጥ እንደ ደረሰ እናየዋለን ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፡ በእኔ የማይሰነካከል ሁሉ ብፁዕ ነው ።

ሉቃ. ፯ ፡ ፳፫ ።

ለእናንተ ለወዳጆቼ እላችኋለሁ ፡ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ ።

ሉቃ. ፲፪ ፡ ፬ ።

የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው ።

መዝ. ፩፻፲፭ (፩፻፲፮) ፡ ፮ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ዮሐንስ በምን ምክንያት ታሠረ ?

፪ ፡ ከዮሐንስ ለተላኩ ሰዎች ኢየሱስ ምን መልስ ሰጠ ?

፫ ፡ ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ ሲመሰክር ምን አለ ?

፬ ፡ ንስሐ ባለመግባቱ ሄሮድስ በክፋት እየባሰ መሄዱ በምን ታየ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ዓመፃን ጠላሁ ተጸየፍሁም ፡
ሕግህን ግን ወደድሁ ።
ሕግህን ለሚወዱ ብዙ ሰላም ነው ፡
ዕንቅፋትም የለባቸውም ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፩፻፷፫ ፡ ፩፻፷፭ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፪ ።

## ጌታችን አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አበረከተ ።

ማር. ፮ ፡ ፴ - ፵፪ ፤ ማቴ. ፲፬ ፡ ፲፫ - ፴፫ ።

፩ ፤ ኢየሱስ ለሕዝብ አዘነ ።

ማር. ፮ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፴ - ፴፬ ፤ ሉቃ. ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።

ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ሁለት ሁለት አድርጎ እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ ላካቸው ። ሄደውም በብዙ መንደሮች ሰበኩ ። ተመልሰውም ያደረጉትንና ያስተማሩትን ሁሉ ለኢየሱስ ነገሩት ። ኢየሱስም አሥራ ሁለቱን ፡ «እናንተ ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳኑና ጥቂት ዕረፉ» አላቸው ፤ ከሕዝብ ብዛት የተነሣ ለመብላት እንኳ ጊዜ አጥተው ነበርና ። በጀልባም ገብተው ባሕሩን በመሻገር ቤተ ሳይዳ ከምትባል ከተማ አጠገብ ወዳለው ምድረ በዳ ሄዱ ። ሰዎ

ችም ሲሄዱ አዩአቸው ፤ ብዙዎችም ሰም
ተው ከየከተማቸው በእግር እየሮጡ ቀደ
ሙአቸውና ወደ እርሱ ተሰበሰቡ ። እር
ሱም ከጀልባ ሲወጣ አያቸውና ፤ እረኛ
እንደሌላቸው በጎች ስለ ነበሩ አዘነላቸው ፤
ድውዮቻቸውንም ፈወሰ ፤ ብዙም ነገር ያስ
ተምራቸው ጀመር ።

፪ ፡ በምድረ በዳም መገባቸው ።

ማር. ፮ ፡ ፴፫ - ፵፮ ፤ ሉቃ. ፱ ፡ ፲፪ - ፲፯ ፤
ዮሐ. ፮ ፡ ፩ - ፲፭፤ ማቴ. ፲፬ ፡ ፲፭ - ፳፫ ።

ቀኑም ለመምሸት ሲቃረብ ደቀ መዛሙ
ርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ፡ «ቦታው ምድረ
በዳ ነው ፤ ጊዜውም መሽቶአል ፤ የሚበ
ሉት የላቸውምና በዙሪያችን ወዳሉ መንደ
ሮች ሄደው እንጀራ ለራሳቸው እንዲገዙ
አሰናብታቸው» አሉት ። እርሱ ግን
መልሶ ፡ «እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው
እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም» አላቸው ።
ሄደን እንጀራ በሁለት መቶ ዲናር* እንግ
ዛላቸውን ? እንዲበሉም እንስጣቸውን ? »
አሉት ። እርሱም ፡ «ስንት እንጀራ አላ
ችሁ ? ሂዱና እዩ» አላቸው ። እንድርያ
ስም ፡ «አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት
ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ ፤ ነገር ግን እነ
ዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆ
ናል ? » አለው ። ኢየሱስም ፡ «እነዚያን
ወደዚህ አምጡልኝ» ብሎ ፡ ሁሉንም
ሰዎች በክፍል በክፍል በለመለመ ሣር ላይ
እንዲያስቀምጡ አሥራ ሁለቱን አዘዘ ።
መቶ መቶና አምሳ አምሳም እየሆኑ በተራ
በተራ ተቀመጡ ። ከሴቶችና ከልጆችም
በቀር አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር ።

ኢየሱስም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን
ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ እየተመለከተ አመሰ
ገነ ፤ እንጀራውንም ቈርሶ ለደቀ መዛሙ
ርቱ ሰጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመ
ጡት ሰዎች ሰጡአቸው ። ሁሉም በልተው
ጠገቡ ፤ ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙር
ቱን ፡ «አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈ
ውን ቍርስራሽ አከማቹ» አላቸው ። ቍር
ስራሹንም አከማችተው አሥራ ሁለት
መሶብ ሞሉ ። የተመገቡት ሰዎችም ኢየ
ሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ፡ «ይህ
በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ
ነው ... የሱስን ለማንገሥ መጥ
ተው ሊነጥቁት አሰቡ ። ኢየሱስ ... አሳባ
ቸውን ዐውቆ ደቀ መዛሙርቱን በጀልባ
ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ
አላቸው ። እርሱም ሕዝቡን አሰናብቶ ሊጸ
ልይ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ ።

፫ ፡ ኢየሱስ በባሕር ላይ ተራመደ ።

ማር. ፮ ፡ ፵፯ - ፶፪ ፤ ማቴ. ፲፬ ፡ ፳፬ - ፴፫ ፤
ዮሐ. ፮ ፡ ፲፮ - ፳፩ ።

ደቀ መዛሙርቱም በጀልባዪቱ ገብተው
ወደ ባሕር ማዶ ሲሄዱ ሳለ ፡ በስተ ፊት
በተነሣው ... ርቱ ነፋስ ምክንያት እየተ
ቸገሩ ይቀዝፉ ነበር ። ኢየሱስም ካለበት
ተራራ ሆኖ መጨነቃቸውን አየ ፤ ከሌሊ
ቱም በአራተኛው ክፍል* በባሕር ላይ እየ
ተራመደ ወደ እነርሱ ቀረበ ። እነርሱም
ማን መሆኑን ስላልለዩ ታወኩ ፤ በፍርሃ
ትም ጮኹ ። እርሱ ግን ፡ «አይዞአችሁ ፤
እኔ ነኝ ፤ አትፍሩ» አላቸው ።

ጴጥሮስም መልሶ ፡ «ጌታ ሆይ ፤ አን
ተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እን
ድመጣ እዘዘኝ» አለው ። እርሱም ፡ «ና»
አለው ። ጴጥሮስም ከጀልባዪቱ ወርዶ
ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ ።
ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ ፤ ሊሰ
ጥምም በጀመረ ጊዜ ፡ «ጌታ ሆይ አድ
ነኝ» ብሎ ጮኸ ። ወዲያውም ኢየሱስ
እጁን ዘርግቶ ያዘውና ፡ «አንተ እምነት



የጐደለህ ስለምን ተጠራጠርህ ?» አለው ።
ወደ ጀልባዪቱም በወጡ ጊዜ ነፋሱ ተወ ።
ደቀ መዛሙርቱም ፡ «በእውነት የእግዚአ
ብሔር ልጅ ነህ» ብለው ሰገዱለት ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፡ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ፡ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም ።

ዮሐ. ፮ ፡ ፴፭ ።

ኢየሱስ ተናገራቸውና ፡ አይዞአችሁ ፡ እኔ ነኝ ፤ አትፍሩ አላቸው ።

ማቴ. ፲፬ ፡ ፳፯ ።

* * *


ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ወደ እርሱ የተሰበሰቡትን ሕዝብ ባየ ጊዜ ምን አደረገ ?
፪ ፡ ኢየሱስ ሕዝቡን በምን መገበ ?
፫ ፡ ጴጥሮስ ፡ «በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ» ባለ ጊዜ ጌታ ምን አለው ? ከመስጠምም ሲያድነው ምን አለው ?

ጸሎት ፡ ጌታ ሆይ ፡ አድነኝ ።

ማቴ. ፲፬ ፡ ፴ ።

* አንድ ዲናር ፶ ሳንቲም ያህል ሲሆን ፣ ይህም በዚያ ዘመን የዕለት ደመወዝ ነበረ ።
* ከሌሊቱ አራተኛው ክፍል ማለት ከሌሊቱ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ማለት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፫ ።

## ጌታችን ከእስራኤል አገር ውጭ ።

ማር. ፯ ፥ ፳፬ - ፰ ፥ ፲ ፤ ማቴ. ፲፭ ፥ ፳፩ - ፴፱ ።

### ፩ ፡ ለአሕዛብ ያለው የጌታ ፍቅር ።

ኢየሱስ በገሊላ ያለውን ሥራ እንደ ፈጸመ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደ ፊንቂ አገር ለመሄድ ተነሣ ። እርሱ የዓለም ብርሃንና መድኃኒት ሆኖ ወደ ዓለም የተላከው ፡ ከእስራኤል ቤት የጠፉትን ለመፈለግ ፡ ጠርቶ ያስተማራቸውን ደቀ መዛሙርቱንም ወደ ዓለም ሁሉ ለመላክ ነበረ እንጂ እርሱ ራሱ በሕዝቦች ሁሉ መካከል እየሰበከ ለመዞር አልነበረም ። ይሁን እንጂ ፡ በሰማርያ ባለፈ ጊዜ ለሲካር ሰዎች መድኃኒትነቱን ሲገልጥ ፡ የሮምንም መቶ አለቃ ልመና ሰምቶ ሲፈጽምለት ፡ ለሁሉ ያለውን ፍቅር አሳይቶአል ። አሁን ደግሞ ገሊላን ትቶ ወደ ውጭ አገር የሄደው ፡ ምንም እንኳ ደቀ መዛሙርቱን የሚያስተምርበትን ቦታ ለመፈለግ ቢሆን ፡ ከማንኛውም ሕዝብና ወገን ወደ እርሱ የሚመጣ ቢኖር ከመቀበል የማይመለስ መሆኑን እንደገና አሳየ ።



www.ethiopianorthodox.org

### ፪ ፡ ከነናዊት ሴት ።

ማቴ. ፲፭ ፥ ፳፩ - ፳፰ ፤ ማር. ፯ ፥ ፳፬ - ፴ ፤ የሐዋ. ፲ ፥ ፳፰ ።

ኢየሱስ ከገሊላ ወጥቶ ፡ ጢሮስና ሲዶና የሚባሉት ከተማዎች ወዳሉበት ወደ ፊንቂ አገር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በደረሰ ጊዜ ፡ ከእነርሱ ጋር በአንድ ቤት ሊገባ ወዶአል እንጂ ስለ መምጣቱ ማንም እንዲሰማ አልወደደም ። ነገር ግን ሊሰወር አልተቻለምና አንዲት ከነናዊት ሴት ስለ እርሱ ሰምታ ከችግርዋ ብዛት የተነሣ እጅግ ደፍራ እየተከተለች ፡ «ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ፡ ማረኝ ፤ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል» በማለት ትጮኽ ነበር ።

እስራኤላውያን ያደርጉ እንደነበር የጌታ ደቀ መዛሙርትም ከአሕዛብ ወገን የሆኑትን ሰዎች እንደ ውሾች ርኩሳን ናቸው በማለት ስለማያቀርቡአቸው ወደ ኢየሱስ መጥተው ፡ «ይህች ሴት በኋላችን ትጮኻለችና አሰናብታት» እያሉ ለመኑት ። ኢየሱስም ፡ «ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም» ብሎ መለሰ ።

ሴቲቱም ፡ እስራኤላዊት ባለመሆኔ አይቀበለኝ ይሆናል በማለት ምንም በልብዋ ብትፈራ እንኳ በድፍረት ቀርባ በኢየሱስ እግር ላይ ወድቃ ፡ «ጌታ ሆይ እርዳኝ» እያለች ትለምነው ነበር ። እርሱም አሳብዋን ዐውቆ ፡ «ልጆቹ በፊት እንዲጠግቡ ተዪ ፤ የልጆቹን እንጀራ ይዞ ለውሾች መጣል አይገባምና» አላት ። ከዚህም ቃል ተስፋን አግኝታ ፡ «አዎን ጌታ ሆይ ፡ ውሾችም እኮ ከማዕድ በታች ሆነው የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ» አለችው ። እርሱም፡ «አንቺ ሴት ፡ እምነትሽ ታላቅ ነው ፤ ስለ ዚህ ቃልሽ ሂጂ ፡ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል» አላት ። ወደ ቤትዋም ሄዳ ጋኔኑ ወጥቶ ልጅዋን በአልጋ ላይ ተኝታ አገኘች ።

### ፫ ፡ ደንቆሮና ኰልታፋ የሆነ ሰው ።

ማር. ፯ ፥ ፴፩ - ፴፯ ።

ኢየሱስ ፡ ከገሊላ ባሕር ወደ ምሥራቅ ፡ አሥር ከተማ ወደሚባለው አገር መጣ ። ደንቆሮና ኰልታፋም የሆነ ሰው ወደ እርሱ አመጡ ፡ እጁንም ይጭንበት ዘንድ ለመኑት ። ከሕዝቡም ለይቶ ለብቻው ወሰደው ፡ ጣቶቹንም በጆሮቹ አገባ ፡ እትፍም ብሎ ምላሱን ዳሰሰ ፤ ወደ ሰማይም እየተመለከተ ፡ «ተከፈት» አለው ። ወዲያውም ጆሮቹ ተከፈቱ ፡ የምላሱም እሥራት ተፈታ ፡ አጥርቶም ተናገረ ።

### ፬ ፡ አራት ሺህ ሕዝቦች ።.

ማቴ. ፲፭ ፥ ፳፱ - ፴፱ ፤ ማር. ፰ ፥ ፩ - ፲ ።

ኢየሱስም በዚያ አገር ወዳለው ወደ አንድ ተራራ ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ ። አንካሶችንም ዲዳዎችንም ፡ ጒንድሾችንም ፡ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙትንም ይዘው ቀረቡ ፡ በኢየሱስ እግር አጠገብም ጣሉአቸው ፡ ፈወሳቸውም ። ስለዚህም ሕዝቡ ፡ ዲዳዎች ሲናገሩ ፡ ጒንድሾችም ሲድኑ ፡ አንካሶችም ሲሄዱ ፡ ዕውሮችም ሲያዩ አይተው ተደነቁ ፤ የእስራኤልንም አምላክ አከበሩ ። እስከ ሦስት ቀን ድረስም ከእርሱ ጋር ቈዩ ።

ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ፡ «በዚህ ከእኔ ጋር ከዋሉ ሦስት ቀናቸው ነውና የሚበሉት ስለሌላቸው ለዚህ ሕዝብ እራራለሁ ። በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም » አላቸው ። ደቀ መዛሙርቱም ፡ «ይህን ለሚያህል ሕዝብ የሚያጠግብ እንጀራ ከወዴት እናገኛለን ?» አሉት ። ኢየሱስም ፡ «ስንት እንጀራ አላችሁ ?» አላቸው ። እነርሱም ፡ «ሰባት ፡ ጥቂትም ዓሣ» አሉት ። ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ ። ሰባቱንም እንጀራ ዓሣዎቹንም ይዞ አመሰገነ ፤

ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ አቀረቡ ። ሁሉም በሉ፤ ጠገቡም ፤ የተረፈውንም ቍርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ ። የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ ። ከዚህም በኋላ ሕዝቡን አሰናብቶ በጀልባ ገባና ወደ ገሊላ አገር መጣ ።

*　*　*

በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለም ፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ፤ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው ።

ሮሜ ፲ ፡ ፲፪ ።

ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል ፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም ።

ኤፌ. ፪ ፡ ፰ ፡ ፱ ።


*　*　*

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ጌታ ለከነናዊት ሴት ምን አደረገላት ?
፪ ፡ አሥር ከተማ ወደሚባለው አገር በደረሰ ጊዜ ምን ዓይነት ሰው አመጡለት ?
፫ ፡ ወደ ተራራስ በወጣ ጊዜ ለተከታተሉት ሕዝብ ምን አደረገ ?

ጸሎት ፡ እግዚአብሔር ይማረን ይባርከንም ፡
ፊቱንም በላያችን ያብራ ፡
በአሕዛብ ሁሉ መካከል ማዳንህን ፡
መንገድህንም በምድር እናውቅ ዘንድ ።

መዝ. ፷፯ (፷፮) ፡ ፩ ፡ ፪ ።





ምዕራፍ ፳፬ ።

## የጌታችን ክብር መገለጥ ።

ማቴ. ፲፮ ፡ ፲፫ - ፲፯ ፡ ፳፩ ።

### ፩ ፡ ኢየሱስ ስለ ሕማማቱ ተናገረ ።

ማቴ. ፲፮ ፡ ፲፫ - ፳፰ ፡ ማር. ፰ ፡ ፳፯ - ፱ ፡ ፩ ፤
ሉቃ. ፱ ፡ ፲፰ - ፳፯ ።

ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስለ ተገባው ስለ መስቀል ሞቱ ሊያዘጋጃቸው በማሰብ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ከእስራኤል በስተሰሜን በሄሮድስ ወንድም በፊልጶስ ግዛት ወደ ነበረ ፊልጶስ ቂሣርያ ወደ ተባለው ሥፍራ ሄደ ። በመንገድም ሳሉ ፡ «ሰዎች እኔ ማን እንደሆንሁ ይላሉ ? » ብሎ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፡ «አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ፡ ሌሎችም ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል ይላሉ» አሉት ። «እናንተስ እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ ? » ብሎ ጠየቃቸው ። ጴጥሮስም ፡ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» አለ ። ኢየሱስም መልሶ ፡ «ስምዖን ሆይ ፡ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ» አለው ። ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ፤ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ ፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር ። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ፡ «አይሁንብህ ጌታ ሆይ ፡ ይህ ከቶ አይደርስብህም» ብሎ ገሠፀው ። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ፡ «ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን ፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆንህብኛል» አለው ።

ለሁሉም እንዲህ አላቸው ፤ «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ ። በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ ፡ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል ። እውነት እላችኋለሁ ፡ በዚህ ከቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት በኃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ ፡ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ ። »

፪ ፤ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር በክብር ታዩ ።

ማር. ፱ ፡ ፪ - ፲፫ ፤ ሉቃ. ፱ ፡ ፳፰ - ፴፮ ፤ ማቴ. ፲፯ ፡ ፩ - ፲፫ ።

ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው ። ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለውጦ እንደ ፀሐይ በራ ፤ ልብሱም አንፀባረቀ ፤ አጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ሊያነጣ እስከማይችል ድረስ በጣም ነጭ ሆነ ። እነሆም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር በክብር ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይነጋገሩ ነበር ።

ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ከእንቅልፍ ነቅተው የጌታን ክብር ከእርሱም ጋር የነበሩትን ሰዎች አዩ ። ሙሴና ኤልያስም ከእርሱ ሊለዩ ሲሉ ጴጥሮስ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና አንድ ለአንተ አንድም ለሙሴ አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶች እንሥራ» አለው ። እጅግ ስለ ፈሩ የሚለውን አያውቅም ነበርና ። ገና ሲናገርም ፤ እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው ፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ፈሩ ። እነሆም ከደመናው ፡ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት» የሚል ድምፅ መጣ ። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ እጅግም ፈርተው ነበር ። ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸውና ፡ «ተነሡ ፤ አትፍሩም» አላቸው ። ዓይኖቻቸውንም አቅንተው ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም ።

ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ ፡ «የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ» ብሎ አዘዛቸው ። ቃሉንም ይዘው ፤ «ከሙታን መነሣት ምንድር ነው ? » እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ ።

፫ ፤ ኢየሱስ ጋኔን ያደረበትን ልጅ ፈወሰ ። ማር. ፱ ፡ ፲፬ - ፳፱ ፤ ሉቃ. ፱ ፡ ፴፯ - ፵፭ ፤

ማቴ. ፲፯ ፡ ፲፬ - ፳፩ ።

ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርትም በመጣ ጊዜ በብዙ ሕዝብ ተከብበው ጸሐፎች ሲከራከሩአቸው አየ ። ሕዝቡም ባዩት ጊዜ ደነገጡ ፤ ወደ እርሱም ሩጠው እጅ ነሡት ። ኢየሱስም ጸሐፎችን ፡ «ስለምን ከእነርሱ ጋር ትከራከሩላችሁ ? » ብሎ ጠየቃቸው ። ከሕዝቡም አንዱ መልሶ ፡ «መምህር ሆይ፤ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቻለሁ ፤ በደረሰበትም ሥፍራ ሁሉ ይጥለዋል ፤ ደቀ መዛሙርትህም ሊያወጡለት አልቻሉም» አለው ።



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስም መልሶ ፤ «የማታምን ትውልድ ሆይ ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ ? ወደ እኔ አምጡት» አላቸው ። ወደ እርሱም አመጡት ። እርሱንም ባየ ጊዜ ያ መንፈስ ወዲያው አፈራገጠው ፤ ወደ ምድርም ወድቆ አረፋ እየደፈቀ ተንፈራፈረ ። አባቱንም ፡ «ይህ ከያዘው ስንት ዘመን ነው ? » ብሎ ጠየቀው ። አባቱም ፡ «ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው ፤ ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው ፤ ቢቻልህ ግን እዘንልን ፤ እርዳንም» አለው ። ኢየሱስም ፡ «ቢቻልህ ትላለህ ፡ ለሚያምን ፡ ሁሉ ይቻላል» አለው ። የብላቴናውም አባት ጮኾ ፡ «አምናለሁ ፡ አለማመኔን እርዳው» አለ ። ኢየሱስም ርኵሱን መንፈስ ገሥፀና ፡ «አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ ፡ እኔ አዝሃለሁ ፡ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት» አለው ። ጮኾም እጅግ አፈራግጦት ወጣ ፤ ብዙዎችም ፡ ሞተ እስኪሉ ድረስ እንደ ሙት ሆነ ። ኢየሱስ ግን አስነሣው ፡ ለአባቱም ሰጠው ።

ሁሉም ኢየሱስ ባደረገው ነገር ሲደነቁ፡ ለደቀ መዛሙርቱ ፡ «የሰው ልጅ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለውና እናንተ ይህን ቃል በጆሮአችሁ አኑሩ» አለ ። እነርሱ ግን ይህን ነገር አላስተዋሉም ፡ እንዳይጠይቁትም ፈሩ ። ወደ ቤትም ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ፡ «እኛ ጋኔኑን ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምንድር ነው ? » ብለው ጠየቁት ። እርሱም ፡ «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው ። ይህ ዓይነት ግን በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም» አላቸው ።

*    *    *

በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት ።

ማቴ. ፲፯ ፡ ፭ ።

የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ ። ከገናናው ክብር ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎ አልና ።

፪ ጴጥ. ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

*    *    *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ፡ «እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ ? » ብሎ በጠየቀ ጊዜ ጴጥሮስ ምን ብሎ መለሰለት ?

፪ ፡ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ስለምን ነገር ይነጋገሩ ነበር ?

፫ ፡ እግዚአብሔር አብ ከብሩህ ደመና በተናገረ ጊዜ ምን አለ ?

ጸሎት ፡ የመቅደሳችን ሥፍራ ከጥንት ጀምሮ ከፍ ያለ የክብር ዙፋን ነው ። . . . . አቤቱ ፡ ፈውሰኝ እኔም እፈወሳለሁ ፡ አድነኝ እኔም እድናለሁ ፡ አንተ ምስጋናዬ ነህና ።

ኤር. ፲፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ።



ምዕራፍ ፴፭ ።

## ጌታችን ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ።

ከሉቃ. ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

### ፩ ፡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና ።

ሉቃ. ፱ ፡ ፶፩ ፡ ፶፯ - ፷፪ ።

የሕማማቱና ወደ አብ የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና ። ከደቀ መዛሙርቱም ጋር በመንገድ ሲሄድ አንድ ሰው ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ» አለው ። ኢየሱስም ፡ «ለቀበሮች ጉድጓድ ፡ ለሰማይም ወፎች መሣፈሪያ አላቸው ፡ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም» አለው ።

ሌላውንም ፡ «ተከተለኝ» አለው ። እርሱ ግን ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ» አለ ። ኢየሱስም ፡ «ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው ፤ አንተስ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ » አለው ።

ደግሞ ሌላው ፡ «ጌታ ሆይ ፡ እከተልሃለሁ ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ከቤቴ ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ» አለ ። ኢየሱስ ግን ፡ «ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም» አለው ።

### ፪ ፡ ኢየሱስ ሰባ ሰዎችን በፊቱ ላከ ።

ሉቃ. ፲ ፡ ፩ - ፳፬ ።

ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎችን ሰባ ሾመ ፤ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ሥፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው ። አላቸውም ፡ «መከሩስ ብዙ ነው ፡ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው ፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት ። ሂዱ ፡ እነሆ እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ ። ወደ ምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ ያቀረቡላችሁን ብሉ ፡ በእርስዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው ። ነገር ግን ወደምትገቡባት ከተማ ሁሉ ባይቀበሉአችሁ ፡ ወደ አደባባይዋ ወጥታችሁ ፡ ከከተማችሁ የተጣበቀብንን ትቢያ እንኳን እናራግፍላችኋለን ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ወደ እናንተ እንደ ቀረበች ይህን ዕወቁ በሉ ። እላችኋለሁ ፡ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ይቀልላታል ። የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል ፡ እናንተንም ያልሰማ እኔን አይሰማም ፡ እኔንም እምቢ ያለ የላከኝን እምቢ አለ ።»

ሰባውም በደስታ ተመልሰው ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል» አሉት ። እርሱም ፡ «ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ ። እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ ፡ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ ፡ የሚጐዳችሁም ምንም የለም ። ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ፡ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ» አላቸው ።

በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና ፡ «የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ ፡ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ ፡ አዎን አባት ሆይ ፡ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና» አለ ።

ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው ፡ «የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው ። እላችኋለሁና ፡ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም ፤ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወደው አልሰሙም» አለ ።

### ፫ ፡ ኢየሱስ አሥር ለምጻሞችን ፈወሰ ።

ሉቃ. ፲፯ ፡ ፲፩ - ፲፱ ፤ ዘሌዋ. ፲፫ ፡ ፩ - ፫ ፡ ፵፭ ፡ ፵፮ ፤ ዘሌዋ. ፲፬ ፡ ፩ - ፴፪ ፤ ከሉቃ. ፭ ፡ ፲፪ - ፲፬ ጋር ይነጻጸር ።

ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በገሊላና በሰማርያ መካከል አለፈ ። ወደ አንዲት መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙ አሥር ለምጻሞች ዐውቀውት በታላቅ ቃል እየጮኹ ፡ «ኢየሱስ ሆይ ፡ አቤቱ ፡ ማረን» አሉ ።

በሩቅ ቆመው የጮኹበት ምክንያትም፡ በሙሴ ሕግ ፡ «የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀደደ ይሁን ፡ ራሱም የተገለጠ ይሁን ፡ ከንፈሩንም ይሸፍን ፤ ርኵስ ርኵስ ነኝ ይበልም ። ደዌው ባለበት ዘመንም ሁሉ ርኵስ ይሆናል ፤ እርሱ ርኵስ ነው ፤ ብቻውንም ይቀመጣል ፤ መኖሪያውም ከሠፈር ውጭ ይሆናል» ተብሎ ስለ ነበር ነው ። ከለምጽ ደዌው ቢድን ግን ፡ በመንጻቱ ቀን ወደ ቤቱ ሳይመለስ ወደ ካህኑ እንዲሄድ ፡ ካህኑም መርምሮ ደዌው እንደ ጠፋ ሲያረጋግጥ ፡ የዳነው ሰውዬ ለመንጻቱ የታዘዘውን መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት ። አስቀድሞ ለምጻሙን ሰው :- ርኵስ ነህ ብሎ ከሕዝቡ መካከል ለይቶት የነበረ ካህኑ ነውና በሚድንበትም ጊዜ ካህኑ በሕዝቡ ማኅበር እንዲገባ ከለምጹ ርኵሰት መንጻቱን አስታውቆ ያውጅለት ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ የመንጻት ሕግ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ብዙ ጊዜ የተፈጸመ አይመስልም ፤ ለዚያ በሽታ መድኃኒት የለውም ነበርና ። አሁን ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስ



www.ethiopianorthodox.org

ቶስ መልካም እያደረገ ከሥፍራ ወደ
ሥፍራ መዘዋወር ከጀመረ ወዲህ ፡ ከለ
ምጽ እየነጹ ወደ እነርሱ በሚመጡ ተፈ
የሾች ብዛት ካህናት አይደነቁ ይሆንን ?
ይህ የለምጻሞች መንጻት ፡ ክርስቶስ የተባ
ሰው በእውነት እንደ መጣ ለካህናትና ለሌ
ሞችም ሁሉ ምስክር ሆኖላቸው ነበር ።
ፈውስን የሚፈልጉ እነዚህ አሥር ለም
ሞችም ፡ «ማረን» እያሉ ሲጮኹ ኢየ
ሱስ መለሰ ፡ «ሂዱ ፡ ራሳችሁን ለካህናት
ሳዩ» አላቸው ። እነሆም ሲሄዱ ነጹ ።
ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ
በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ
ተመለሰ ፡ እያመሰገነውም በእግሩ ላይ በግ
ምባሩ ወደቀ ፡ እርሱም ሳምራዊ ነበረ ።
ኢየሱስም ፡ «የነጹ አሥር አልነበሩምን ?
ጠኙስ ወዴት አሉ ? ከዚህ ከልዩ ወገን
ቀር እግዚአብሔርን ሊያከብር የተመለሰ
ልተገኘምን ? » አለ ። ሳምራዊውንም ፡
«ተነሣና ሂድ ፡ እምነትህ አድኖሃል»
አለው ።

፬ ፡ ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ ።

ማቴ. ፲፱ ፡ ፩ ፡ ፲፫ - ፲፭ ፡ ማር. ፲ ፡ ፲፫ - ፲፮ ፡
ሉቃ. ፲፰ ፡ ፲፭ - ፲፯ ።

በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ይሁዳ ዳርቻ መጣ ። በዚያም ሳለ እጁን እንዲጭንባቸውና እን ዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ ፡ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠፁአ ቸው ። ኢየሱስ ግን አይቶ ተቈጣና ፡ «ሕፃ ናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ ፡ አትከ ልክሉአቸው ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና ። እውነት እላች ኋለሁ ፡ እንደ ሕፃን የእግዚአብሔርን መን ግሥት የማይቀበል ከቶ አይገባባትም» አላቸው ። አቀፋቸውም ፡ እጁንም ጭኖ ባረካቸው ።

* * *

ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብ ሔር መንግሥት የተገባ አይደለም ። ሉቃ. ፱ ፡ ፷፪ ።

ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአ ቸውም ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና ። ሉቃ. ፲፰ ፡ ፲፮ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ጌታ ሰባውን ሾሞ የላካቸው ምን እንዲያደርጉ ነበረ ?
፪ ፡ ከተፈወሱ ለምጻሞች መካከል ለምስጋና የተመለሰውን ጌታ ምን አለው ?
፫ ፡ ስለ ሕፃናትስ ምን ተናገረ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች ፡
እኔንም ቀኝህ ተቀበለችኝ ።
አቤቱ ፡ መንገድህን አመልክተኝ ፡
ፍለጋህንም አስተምረኝ ።

መዝ. ፷፪ (፷፫) ፡ ፰ ፡ ፳፬ (፳፭) ፡ ፬ ።





ምዕራፍ ፳፯ ።

## ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው ።

ዮሐ. ፱ ።

፩ ፡ የዕውሩ ማየት ።

ዮሐ. ፱ ፡ ፩ - ፯ ።

ኢየሱስ በአንድ የሰንበት ቀን በኢየሩሳ ሌም ሳለ ፡ ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነን ሰው አየ ። ደቀ መዛሙርቱም ፡ «መምህር ሆይ ፡ ይህ ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢ አት የሠራ ማን ነው ? እርሱ ወይስ ወላ ጆቹ ? » ብለው ጠየቁት ። ኢየሱስም ፡ «የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት ስለ ሠሩ አይደለም ። ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ፡ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች ። በዓ ለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሎ ወደ መሬት እትፍ አለ ፡ በምራቁም ጭቃ አድ ርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀብቶ ፡ «ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ» አለው ። ሄዶም ታጠበ ፡ እያየም መጣ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ የዕውሩና የፈሪሳውያን ክርክር ።

ዮሐ. ፱ ፣ ፰ - ፴፬ ።

ጐረቤቶቹም ዕውሩ ድኖ እያየ ሲመጣ ተመልክተው ፡ «ይህ ተቀምጦ ይለምን የነበረ አይደለምን ? » አሉ ። ሌሎችም ፡ «እርሱ ነው» አሉ ፤ ሌሎች ደግሞ ፡ «አይደለም ፡ እርሱን ይመስላል እንጂ» አሉ ። እርሱ ግን ፡ «እኔ ነኝ» አለ ። እነርሱም ፡ « ታዲያ ዓይኖችህ እንዴት በሩልህ ? » አሉት ። እርሱም መልሶ ፡ «ኢየሱስ የሚባለው ሰው ጭቃ አድርጎ ዓይኖቼን ቀባና፡ ሂደህ ታጠብ አለኝ ፡ ሂጄ ታጥቤም አየሁ» አለ ።

እነርሱም ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት ፤ ፈሪሳውያንም ደግሞ እንዴት እንዳየ እንደገና ጠየቁት ። እርሱም ፡ «ጭቃ በዓይኖቼ አኖረ ፡ ታጠብሁም አየሁም» አላቸው ። ከፈሪሳውያንም አንዳንዶች ፡ «ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም» አሉ ። ሌሎች ግን ፡ «ኃጢአተኛ ሰው እንደ እነዚህ ያሉ ምልክቶች ሊያደርግ እንዴት ይችላል ? » አሉ ። በመካከላቸውም ክሆነ መለያየት የተነሣ ፡ «አንተ ዓይኖችህን ስላበራልህ ስለ እርሱ ምን ትላለህ ?» አሉት ። እርሱም ፡ «ነቢይ ነው» አለ ።

እነርሱም ወላጆቹን ጠርተው ፡ «እናንተ ፡ ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን ? ታዲያ አሁን እንዴት ያያል ? » ብለው ጠየቁአቸው ። ወላጆቹም ፡ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ ለኢየሱስ የሚመሰክር ቢኖር የአይሁድ ሽማግሌዎች ከምኵራብ እንደሚያወጡት መወሰናቸውን ዐውቀው መልስ ሊሰጡ በመፍራት ፡ «ይህ ልጃችን እንደሆነ ፡ ዕውርም ሆኖ እንደ ተወለደ እናውቃለን ፤ አሁን ግን እንዴት እንዳየ አናውቅም ፤ ሙሉ ሰው ነውና እርሱን ጠይቁት» አሉ ።

ስለዚህ ሰውየውን ራሱን ሁለተኛ ጠርተው ፡ «እግዚአብሔርን አክብር ፤ ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እናውቃለን» አሉት ። እርሱ ግን ፡ «ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም ፤ የማውቀው አንድ ነገር አለ ፡ ይኸውም ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንደማይ ነው» አለ ። ደግመውም ፡ «እንዴት አድርጎ ዓይኖችህን አበራልህ ? » አሉት ። እርሱም መልሶ ፡ «አስቀድሜ ነገርኋችሁ አልሰማችሁም ፤ ስለምን ደግሞ ልትሰሙ ትወዳላችሁ ? እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትወዳላችሁን ?» አላቸው ። ተሳድበውም ፡ «አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ ፤ እኛ ግን የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን ፤ እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እናውቃለን ፤ ይህ ሰው ግን ከወዴት እንደሆነ አናውቅም» አሉት። ሰውየውም መልሶ ፡ «ከወዴት እንደሆነ እናንተ አለማወቃችሁ ይህ ድንቅ ነገር ነው ፤ ዳሩ ግን ዓይኖቼን አበራ ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሔር ይሰማዋል እንጂ ኃጢአተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን ። ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንዳበራ ፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም ፤ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ኑሮ ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር» አላቸው ። መልሰውም ፡ «አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ ፡ አንተም እኛን ታስተምረናለህን ? » በማለት አውግዘው ከምኵራብ አወጡት ።

፫ ፤ የዕውሩ ማመን ።

ዮሐ. ፱ ፣ ፴፭ - ፴፰ ።

ኢየሱስም ሰውየውን ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ ። ባገኘውም ጊዜ ፡ «አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን ? » አለው ። እርሱም መልሶ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ በእርሱ እምን ዘንድ ማን ነው ? » አለ ። ኢየሱስም ፡ «አይተኸዋልም ፡ ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው» አለው ። እርሱም፡ «ጌታ ሆይ አምናለሁ» አለ ፤ ሰገደለትም ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፡ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ።

ዮሐ. ፰ ፣ ፲፪ ።

ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ ።

፩ ጴጥ. ፬ ፣ ፲፬ ።

* * *


ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተው ምን በማድረግ ነው ?
፪ ፡ የሰውየው ወላጆች ለአይሁድ እንዳይመልሱ ስለምን ፈሩ ?
፫ ፡ ሰውየውን ወደ ውጭ እንዳወጡት በሰማ ጊዜ ኢየሱስ ምን አደረገ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ አንተ አምላኬ እንደሆንህ እነሆ ዐወቅሁ ።
በእግዚአብሔር ታመንሁ ፡ አልፈራም ፤ ሰው ምን ያደርገኛል ?
አቤቱ ፡ የምስጋና ስእለት የምሰጥህ ከእኔ ዘንድ ነው፤
ነፍሴን ከሞት ፡ እግሮቼን ከመውደቅ አድነሃልና ፡
በሕያዋን ብርሃን እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ዘንድ ።

መዝ. ፶፭ (፶፮) ፣ ፱ ፣ ፲፩ - ፲፫ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፯ ።

## የእግዚአብሔር መንጋና እረኛው ።

ዮሐ. ፲ ።

### ፩ ፡ ኢየሱስ የበጎቹ በርና እረኛ ነው ።

ዮሐ. ፱ ፡ ፴፰ - ፲ ፡ ፳፩ ።

ውር የነበረው ሰውዬ ፡ «አምናለሁ» ለው ጊዜ ኢየሱስ ለሚቃወሙት ፈሪሳ ውያን ፡ ከነቢያት መጻሕፍት በመጥቀስ ርሱ ራሱ ተስፋ የተሰጠበት የእግዚአብ ሔር ሕዝብ እረኛ ፡ በጎቹ የሚገቡበትም ር መሆኑን በምሳሌ እንዲህ ሲል ተና ረ ፡-

«እውነት እውነት እላችኋለሁ ፡ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው ፤ በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው ። ለእ ርሱ በረኛው ይከፍትለታል ፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል ፡ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል ። የራሱ ንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል ፡ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከ ተሉታል ፤ ሌላውን ግን ይሸሹታል እንጂ አይከተሉትም ፡ የሌሎችን ድምፅ አያው ቁምና ።» ይህን ምሳሌ ሲነግራቸው ግን ፡ ከበጎቹ አልነበሩምና አላስተዋሉም ።

ኢየሱስም ደግሞ አላቸው ፤ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ፡ እኔ የበጎች በር ነኝ ። ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴ ዎች ናቸው ፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸ ውም ። በሩ እኔ ነኝ ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ፡ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪ ያም ያገኛል ። ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም ፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸ ውም መጣሁ ። መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፤ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ይሰ ጣል ።

«እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያል ሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል ፤ ተኵላም ይነጥቃቸ ዋል ፡ በጎቹንም ይበትናቸዋል ። ሞያተኛ ስለሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተ ኛው ይሸሻል ። መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፤ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደ ማውቀው የራሴን በጎች ዐውቃለሁ ፡ የራ ሴም በጎች ያውቁኛል ፤ ነፍሴንም ስለ በጎቹ እሰጣለሁ ።

«ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ፡ ድምፄንም ይሰማሉ ፡ አንድ መንጋም ይሆ ናሉ ፡ እረኛውም አንድ ።

«ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እሰጣለ ሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል ። እኔ በፈቃዴ እሰጣታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳ ትም ። ልሰጣት ሥልጣን አለኝ ፡ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ፤ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ ።»

ኢየሱስ ፡ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» ብሎ በምሳሌ ሲናገር ይሰሙት የነበሩት አይሁድ ፡ «ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስ ራኤል እረኞች ወዮላቸው ! » በማለት በነ ቢዩ ሕዝቅኤል ልሳን እግዚአብሔር የተና ገረውን የወቀሳ ቃልና እውነተኛ እረኛን ከዳዊት ቤት ለማስነሣት የሰጠውን ተስፋ አላስታወሱ ይሆንን ? ከኢየሱስ ቃል የተ ነሣ በመካከላቸው መለያየት ሆነ ። ከእነር ሱም ብዙዎች ፡ «ጋኔን አለበት ፡ አብዶ አል» አሉ ። ሌሎችም ፡ «ይህ ጋኔን ያለ በት ሰው ቃል አይደለም ፤ ጋኔን የዕውሮ ችን ዓይኖች ሊያበራ ይችላልን ? » አሉ ።

(ኤር. ፳፫ ፡ ፩ - ፮ ፡ ሕዝ. ፴፬ ።)

### ፪ ፡ ኢየሱስ የበጎቹ ታዳጊ ነው ።

ዮሐ. ፲ ፡ ፳፪ - ፵፪ ።

ከዚህም በኋላ በሌላ ጊዜ ኢየሱስ በሰሎ ሞን ደጅ መመላለሻ ሲመላለስ ፡ ካላመኑ በት አይሁድ የሆኑ ከብበው ፡ «እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቈየናለህ ? አንተ ክርስ ቶስ እንደሆንህ ገልጠህ ንገረን» አሉት ። ኢየሱስም መልሶ ፡ «ነገርኋችሁ አታምኑ ምም ፤ እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል ፤ እናንተ ግን እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም ። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ ፡ እኔም ዐውቃቸዋለሁ ይከተሉኛማል ፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ፡ ለዘላለምም አይጠፉም ፡ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም ። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል ፡ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም ። እኔና አብ አንድ ነን» አላቸው ።

ኢየሱስም ፡ «እኔና አብ አንድ ነን» ባለ ጊዜ አይሁድ ፡ «አንተ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ በማድረግህ ትሳደባለህ» ብለው ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ ። እርሱ ግን ከእጃቸው ወጥቶ ፡ ዮሐንስ በመጀመ ሪያ ያጠምቅበት ወደ ነበረው ሥፍራ ሄደ።



www.ethiopianorthodox.org

ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው ፡ «ዮሐንስ አንድ ምልክት ስንኳ አላደረገም ፤ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ» አሉ ። በዚያም ብዙዎች በእርሱ አመኑ ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፤ በሩ እኔ ነኝ ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ፤ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል ። ዮሐ. ፲ ፡ ፱ ።

መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፤ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎች ይሰጣል ።

ዮሐ. ፲ ፡ ፲፩ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ወደ እግዚአብሔር መንጋ የሚያገባ በር ማን ነው ?

፪ ፡ ጌታችን ፡ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» ሲል ለበጎቹ ምን እንደሚያደርግ አስረዳ ?

፫ ፡ አይሁድ ኢየሱስን ሊወግሩት ለምን አሰቡ ?

ጸሎት ፡ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ፤ የሚያሳጣኝም የለም ። . . .
በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ
አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉውን አልፈራም ፤
በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል ። . . .
ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል ፤
በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ ።

መዝ. ፳፪ (፳፫) ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፮ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፰ ።

## አልዓዛርና እኅቶቹ ።

ዮሐ. ፲፩ ።

### ፩ ፡ የአልዓዛር መታመምና ሞት ።

ዮሐ. ፲፩ ፡ ፩ - ፲፮ ።

ከኢየሩሳሌም ውጭ ከደብረ ዘይት ግርጌ በሚገኝ ቢታንያ በተባለው መንደር ፡ ኢየሱስን የሚወዱ ማርታና ማርያም የተባሉ እኅትማማች ፡ አልዓዛር ከሚባል ወንድማቸው ጋር ይኖሩ ነበር ። በዚህም ወራት አልዓዛር ታምሞ ነበርና እኅቶቹ ፡ ጌታ ሆይ ፡ እነሆ የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ ኢየሱስ ላኩ ። እርሱም በሰማ ጊዜ ፡ «ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ እንዲከብር ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም» ብሎ በነበረበት ሥፍራ ገና ሁለት ቀን ዋለ ።

ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ፡ «ወደ ይሁዳ እንሂድ» አላቸው ። እነርሱም ፡ «መምህር ሆይ ፡ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር ፤ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን ? » አሉት ። ኢየሱስ ግን ፡ ጊዜው ከመድረሱ በፊት ምንም እን ደማይደርስበት ዐውቆ ፡ «ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን ? በቀን የሚመላ ለስ አይሰናከልም» ካለ በኋላ ፡ «ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል ፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ» አላቸው ።

ደቀ መዛሙርቱም ፡ ስለ እንቅልፍ መተ ኛት የተናገረ መስሎአቸው ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ተኝቶስ እንደሆነ ይድናል» አሉት ። በዚ ያን ጊዜ ኢየሱስ በግልጥ ፡ «አልዓዛር ሞተ ፤ እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል ፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ» አላቸው ። ቶማስም ጓደኞቹ ለሆኑ ደቀ መዛሙርት ፡ «ከእርሱ ጋር እን ሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ» አለ ።

፪ ፤ የእኅቶቹ ኀዘን ።

ዮሐ. ፲፩ ፡ ፲፯ - ፴፯ ።

ኢየሱስ ወደ ቢታንያ በመጣ ጊዜ አልዓ ዛር ሞቶ በመቃብር አራት ቀን ሆኖት ነበር ። ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማ ቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማርታና ወደ ማርያም ከኢየሩሳሌም መጥተው ነበር ።

ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች ፤ ስትገናኘውም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ በዚህስ ኖረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር ፤ አሁንም ከእግዚአብ ሔር የምትለምነውን ሁሉ እርሱ እንዲሰ ጥህ ዐውቃለሁ» አለችው ። ኢየሱስም ፡ «ወንድምሽ ይነሣል» አላት ። ማርታም ፡ «በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንደሚ ነሣ ዐውቃለሁ» አለችው ። ኢየሱስም ፡ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ፤ የሚያምን ብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ። ይህን ታምኚያለሽን ? » አላት ። እርስዋም ፡ «አዎን ጌታ ሆይ ፡ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ» አለችው ።

ይህንም ብላ ሄደች ፡ እኅትዋንም ማርያ ምን በሥውር ጠርታ ፡ «መምህር መጥቶ አል ይጠራሻል» አለቻት ። ማርያምም ፈጥና ተነሣች ፤ ማርታ ወደ ተቀበለችበት ሥፍራም መጣች ። እርስዋን ሲያጽናኑ የነበሩትም ፡ ወደ መቃብር የምትሄድ መስሎአቸው ተከተሉአት ።

ማርያምም ኢየሱስን ባየች ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አንተ በዚህ ኖረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር» አለችው ። ኢየሱስም ፡ የእርስዋንና ከእር ስዋ ጋር የነበሩትን ልቅሶ አይቶ በመን ፈሱ አዘነ ፤ እጅግም ተጨንቆ ፡ «ወዴት አኖራችሁት ? » አለ ። እነርሱም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ መጥተህ እይ» አሉት ። ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ ። አይሁድም ተመልክ ተው ፡ «እንዴት ይወደው እንደ ነበር እዩ» አሉ ። አንዳንዶቻቸውም ፡ «ይህ የዕ ውሩን ዓይኖች ያበራ ይህን ደግሞ እንዳይ ሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን ? » አሉ ።

፫ ፡ የአልዓዛር መነሣት ።

ዮሐ. ፲፩ ፡ ፴፰ - ፶፬ ፡ ፶፯ ።

ኢየሱስም በኀዘን ታውኮ ወደ መቃብር መጣ ፤ መቃብሩም የድንጋይ መዝጊያ የነ በረበት ዋሻ ነበረ ። ኢየሱስም ፡ «ድንጋ ዩን አንሡ» አለ ። የሞተውም እኅት ማርታ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል» አለችው ። ኢየሱስም ፡ «ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን ? » አላት ። ድንጋዩንም አነሡት ።

ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ ፡ «አባት ሆይ ፡ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃ ለሁ ። ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ ዐወ ቅሁ ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገ ርሁ» አለ ። ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ ፡ «አልዓዛር ሆይ ፡ ወደ ውጭ ና» ብሎ ጮኸ ። የሞተውም ፡ እጆቹና እግሮቹ በመ ግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበረ ። ኢየሱስም ፡ «ፍቱትና ይሂድ» አላቸው ።

ይህን ካዩት አይሁድም ብዙዎች በእ ርሱ አመኑ ። አንዳንዶች ግን ወደ ፈሪሳው ያን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ተናገሩ ። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም እንዲ ገድሉት ከተማከሩ በኋላ ፡ እርሱን ለመ ያዝ ፡ ያለበትን ሥፍራ የሚያውቅ ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘዙ ። ኢየ ሱስ ግን ከቢታንያ ተነሥቶ ኤፍሬም ወደ ምትባል ከተማ ሄዶ በዚያ ከደቀ መዛሙ ርቱ ጋር ተቀመጠ ።

*   *   *

ኢየሱስ አለ ፤ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ፡ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤ ሕያው የሆነም የሚያም ንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ። ዮሐ. ፲፩ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ።

ሞት ሆይ ፡ መውጊያህ የት አለ ? ሲኦል ሆይ ፡ ድል መንሣ ትህ የት አለ ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው ፡ የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው ፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ።

፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፭ - ፶፯ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ አልዓዛር በታመመ ጊዜ እኅቶቹ ምን አደረጉ ?
፪ ፤ ኢየሱስ ስለ አልዓዛር መታመም በሰማ ጊዜ ምን አለ ?
፫ ፤ ማርታ ፡ «በመጨረሻው ቀን ወንድሜ እንደሚነሣ ዐውቃለሁ» ባለች ጊዜ ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላት ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ አንተ ጌታዬ ነህ አልሁ ፡
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም ። . . .
የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ ፤
ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ ፤
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ ።

መዝ. ፲፭ (፲፮) ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፳፱ ።

## የአይሁድ ፋሲካ እንደ ቀረበ ።

ከሉቃ. ፲፱ ፤ ከዮሐ. ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፩ ፤ ስለ አንድ መኰንን የኢየሱስ ምሳሌ።

ዮሐ. ፲፩ ፡ ፶፭ - ፶፯ ፤ ሉቃ. ፲፱ ፡ ፩ ፡ ፲፩ - ፳፯ ።

የአይሁድ ፋሲካ ቀርቦ ነበርና ከየሥፍራው ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡ ሰዎች ኢየሱስን ይፈልጉ ነበር ። ባላገኙትም ጊዜ ፡ ሽማግሌዎቻቸው ሊይዙት መፈለጋቸውን ሰምተው እርስ በርሳቸው ፡ «ምን ይመስላችኋል ? ወደ በዓሉ አይመጣ ይሆንን ?» ይባባሉ ነበር ። እንዲሁ እርስ በርሳቸው ስለ እርሱ ሲጠያየቁ ፡ ኢየሱስ ፡ ከፋሲካ በፊት በኢየሩሳሌም መገኘት ነበረበትና ካለበት ሥፍራ ተነሥቶ በኢያሪኮና በቢታንያ በኩል በሚያልፍ መንገድ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዝ ነበር ።

ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ፈጥኖ የሚገለጥ እንደ መሰላቸው ያውቅ ነበርና ኢየሱስ ፡ ወዲያውኑ የክብሩ ተካፋዮች ሳይሆኑ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ አገልጋዮቹ በታማኝነት ሊያገለግሉት እንደሚገባቸው የሚያሳይ ምሳሌን እንዲህ ሲል ተናገረ ፡-

«አንድ መኰንን ለራሱ መንግሥትን ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ለመሄድ ሲነሣ ፡ አሥር ባሪያዎችን ጠርቶ አሥር ምናን* ሰጥቶ ፡ «እስክመጣ ድረስ ነግዱ» አላቸው ። የአገሩ ሰዎች ግን ይጠሉት ነበርና ፡ «ይህ በላያችን ሊነግሥ አንወድም» ሲሉ በኋላው መልእክተኞችን ላኩ ።

«መንግሥትን ይዞ በተመለሰ ጊዜ ገንዘብ የሰጣቸውን ባሪያዎች ነግደው ምን ያህል እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ እንዲጠሩለት አዘዘ ። የፊተኛውም ደርሶ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ » አለው ። እርሱም ፡ «መልካም ፡ አንተ በጎ ባሪያ ፡ በጥቂት የታመንህ ስለሆንህ በአሥር ከተሞች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ» አለው ። ሁለተኛውም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ምናንህ አምስት ምናን አተረፈ » አለው ። ይህንም ደግሞ ፡ «አንተም በአምስት ከተሞች ላይ ሁን» አለው ።

«ሌላውም መጥቶ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ በጨርቅ ጠቅልዬ የጠበቅኋት ምናንህ እነኋት ፤ ፈርቻለሁና ፡ ጨካኝ ሰው ስለሆንህ ፤ ያላኖርኸውን ትወስዳለህ ፡ ያልዘራኸውንም ታጭዳለህ » አለው ። ጌታውም ፡ «አንተ ክፉ ባሪያ ፡ አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ ። እኔ ያላኖርሁትን የምወስድና ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንሁ ዐወቅህ ፤ ምነው ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ያልሰጠኸው ? እኔም መጥቼ ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር» አለው ። በዚያም ቆመው የነበሩትን ፡ «ምናኑን ውሰዱበት ፡ አሥሩ ምናን ላለውም ስጡት» አላቸው ። እነርሱም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አሥር ምናን አለው» አሉት ። እርሱም ፡ «እላችኋለሁ ፡ ላለው ሁሉ ይሰጠዋል ፡ ከሌለው ግን ያው ያለው ስንኳ ይወሰድበታል ። ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው » አላቸው ።

፪ ፤ በቢታንያ ለኢየሱስ ያደረጉለት እራት ።

ዮሐ. ፲፪ ፡ ፩ - ፰ ፤ ማር. ፲፬ ፡ ፫ - ፱ ፤ ማቴ. ፳፮ ፡ ፮ - ፲፫ ፤ ሉቃ. ፲ ፡ ፴፰ - ፵፪ ።

ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ ። በዚያም እራት አደረጉለት ፤ ማርታም ታገለግል ነበር ፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ ።

ከዚህ በፊት መጀመሪያ ጊዜ በቤትዋ ስትቀበለው ማርታ ስታገለግል እኅትዋ ማርያም ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች ። ማርታም ቀርባ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አያገድህምን ? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት» ብላ ነበር ። ኢየሱስም ፡ «ማርታ ማርታ ፡ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ ፡ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው ፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ፡ ከእርስዋም አይወሰድባትም» በማለት መልሶላት ነበር ።

አሁንም ኢየሱስ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ማርያም ፡ ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ መጣች ፤ ብልቃጡንም ሰብራ በራሱ ላይ አፈሰሰችው ፡ እግሩንም ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች ፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ ።

ከደቀ መዛሙርትም አንዳንዶች ፡ «ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድር ነው ?» አሉ ። አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የአስቆሮቱ ይሁዳም ፡ «ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር* ተሽጦ ለድኆች ያልተሰጠ ስለምን ነው ?» አለ ። ይህንም የተናገረው ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድኆች አዝኖላቸው አይደለም ፤ የገንዘብ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለነበር ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስም ፡ «ተዉዋት ፤ ስለምን ታደክሙአታላችሁ ? መልካም ሥራ ሠርታልኛለች ። ድኆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና በማናቸውም በወደዳችሁት ጊዜ መልካም ልታደርጉላቸው ትችላላችሁ ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም። የተቻላትን አደረገች ፤ አስቀድማ ለመቃብሬ ሥጋዬን ቀባችው ። እውነት እላችኋለሁ ፡ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት በማናቸውም ሥፍራ ፡ እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ ሊሆን ይነገራል» አለ ።

* * *

ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው ፡ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው ። እንግዲያስ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ ፡ እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል ? በሌላ ሰው ገንዘብም ካልታመናችሁ ፡ የእናንተን ማን ይሰጣችኋል ? ሉቃ. ፲፮ ፡ ፲ - ፲፪ ።

በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ ።
፩ ዮሐ. ፫ ፡ ፲፰ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ ደቀ መዛሙርት ምን በማሰብ ተሳስተው ነበር ?
፪ ፡ ወዲያውኑ የክብሩ ተካፋዮች እንደማይሆኑ ምን ምሳሌ በመናገር አስረዳቸው ?
፫ ፡ የቢታንያዪቱ ማርያም ምን «መልካም ዕድል» መረጠች ?
፬ ፡ ምንስ «መልካም ሥራ» ለጌታዋ ሠራችለት ?

ጸሎት ፡ እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት ፡ እርስዋንም እሻለሁ ፡
በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ ፡
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ ፡
መቅደሱንም እመለከት ዘንድ ። መዝ. ፳፯ (፳፮) ፡ ፬ ።

* አንድ ምናን $፶ ያህል ነበረ ።
* አንድ ዲናር ፶ ሳንቲም ያህል ነበረ ።





ምዕራፍ ፴ ።

## ካህናት ላቀረቡት ጥያቄ የጌታችን መልስ ።

ማቴ. ፳፩ ።

### ፩ ፡ ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አነጻ ።

ዮሐ. ፲፪ ፡ ፲፪ - ፲፭ ፤ ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።

በማግሥቱም ፡ ወደ በዓሉ መጥተው የነበሩት ሕዝብ ፡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመጣ በሰሙ ጊዜ ፡ የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡና ፡ «ሆሣዕና ፡ በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው» እያሉ ጮኹ ። እርሱም በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ፡ በአገልግሎቱም መጀመሪያ እንዳደረገ ነጋዴዎችን በማውጣት ቤተ መቅደስን ካነጻ በኋላ ወደ ቢታንያ ተመልሶ በዚያ አደረ ።

### ፪ ፡ ኢየሱስ በለሲቱን ረገመ ።

ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፰ - ፳፪ ፤ ማር. ፲፩ ፡ ፳፩ - ፳፮ ።

በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ ። ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ ፤ ነገር ግን ከቅጠል ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና ፡ «ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ» አላት ። በለሲቱም ያን ጊዜውን ደረቀች ። ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተደነቁ ። ኢየሱስም ፡ «እውነት እላችኋለሁ ፡ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም ፡ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም ፡ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ ፡- ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት

www.ethiopianorthodox.org

ይሆናል ፤ አምናችሁም በጸሎት የምትለ ምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ ። ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ ፤ በሰማያት ያለው አባታ ችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላ ችሁ ፤ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት» አላቸው ።

፫ ፤ የካህናት አለቆች ስለ ሥልጣኑ ጠየ ቁት ።

ማቴ. ፳፩ ፤ ፳፫ - ፳፯ ፤ ማር. ፲፩ ፤ [illegible]
ሉቃ. [illegible] - ፰ ፤ ፰ ።

ወደ ቤተ መቅደስም ገብቶ ሲያስተምር ፤ ሕዝብ ልብ በሙሉ ተንጠልጥሎ ሲሰ ሙት ሳለ ፤ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀርበው ፤ «በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ ?» አሉት ። ኢየሱ ስም መልሶ ፤ «እኔ ደግሞ አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ ፤ እናንተም ያችን ብትነ ግሩኝ እኔ ደግሞ እነዚህን በምን ሥልጣን እንዳደርግ እነግራችኋለሁ ፤ የዮሐንስ ጥም ቀት ከወዴት ነበረች ? ከሰማይን ወይስ ከሰው ?» አላቸው ።

እነርሱም ፤ «ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» ሲል ዮሐንስ ለኢየሱስ መስክሮለት የነበረውን ምስክርነት ተቀብለው ቢሆኑ ኖሮ የኢየሱስ ሥልጣን ከማን እንደሆነ ሊጠይቁ ባልደፈሩም ነበር ። ካለመቀበላ ቸው የተነሣ ግን ኢየሱስ ባቀረበላቸው ጥያቄ ግራ ገባቸው ፤ እርስ በርሳቸውም ፤ «ከሰማይ ብንል ፤ እንኪያስ ስለምን አላመ ናችሁበትም ? ይለናል ፤ ከሰው ብንል ግን፤ ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ ያዩታልና ሕዝቡን እንፈራለን» አሉ ።

ለኢየሱስም መልሰው ፤ «አናውቅም» አሉት ። እርሱም ደግሞ ፤ «እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ አልነግራች ሁም» ብሎ አለማመናቸውን የሚገልጡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተናገረባቸው ።

፬ ፤ የሁለት ልጆች ምሳሌ ።

ማቴ. ፳፩ ፤ ፳፰ - ፴፪ ።

እንዲህም አላቸው ፤ «ምን ይመስላች ኋል ? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት ፤ ወደ አንደኛው ቀርቦ ፤ «ልጄ ሆይ ፤ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ» አለው ። እርሱም መልሶ ፤ «አልወድም» አለ ፤ ኋላ ግን ተጸጸተና ሄደ ። ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው ፤ እርሱም መልሶ ፤ «እሺ ጌታዬ» አለ ፤ ነገር ግን አልሄደም ። ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገ ማን ነው ?» አላቸው ።

እነርሱም ፤ «ፊተኛው» አሉት ። እር ሱም ፤ «እውነት እላችኋለሁ ፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሙአችኋል ። ዮሐንስ በጽ ድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና አላመና ችሁበትም ፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት ፤ እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ በኋላ ንስሐ አልገባች ሁም» አላቸው ።

፭ ፤ የግፈኞች ገበሬዎች ምሳሌ* ።

ማቴ. ፳፩ ፤ ፴፫ - ፵፮ ፤ ማር. ፲፪ ፤ ፩ - ፲፪ ፤
ሉቃ. ፳ ፤ ፱ - ፲፱ ።

«ሌላ ምሳሌ ስሙ ። የወይን አትክልት የተ ከለ ባለቤት ሰው ነበረ ፤ ቅጥርም ቀጠረለት መጥመቂያም ማሰለት ግንብንም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ ።

«የሚያፈራበትም ጊዜ ሲቀርብ ፤ ፍሬ ውን እንዲቀበሉ ባሪያዎቹን ወደ ገበሬ ዎች ላከ ። ገበሬዎቹም ባሪያዎቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት አንዱንም ገደሉት ሌላ ውንም ወገሩት ። ደግሞ ከፊተኞች የሚ በዙ ሌሎች ባሪያዎችን ላከ ፤ እንዲሁም አደረጉባቸው ።

«በኋላ ግን ፤ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከ ። ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ



እርስ በርሳቸው ፤ «ወራሹ ይህ ነው ፤ ኑ እንግደለውና ርስቱን እናግኝ» ተባባሉ ። ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደ ሉት ። እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ በሚመጣ ጊዜ በእነዚህ ገበሬዎች ምን ያደ ርግባቸዋል ?»

የሰሙትም መልሰው ፤ «ክፉዎችን በክፉ ያጠፋቸዋል ፤ የወይኑንም አትክ ልት ፤ ፍሬውን በየጊዜው ለሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል» አሉት ።

ኢየሱስም ፤ «ግንበኞች የናቁት ድን ጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁምን ? ስለ ዚህ እላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግ ሥት ከእናንተ ትወሰዳለች ፤ ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች» አላቸው ።

የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ምሳ ሌዎቹን ሰምተው ስለ እነርሱ እንደ ተና ገረ አስተዋሉ ፤ ሊይዙትም ሲፈልጉ ሳሉ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስላዩት ፈሩአቸው ።

* * *

እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይ ወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ። ልጁ ያለው ሕይወት አለው ፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም ።

ዮሐ. ፭ ፤ ፲፩ ፤ ፲፪ ።

በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፤ በማያምን ግን በአ ንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶ በታል ።

ዮሐ. ፫ ፤ ፲፰ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ «ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ ?» ብለው በጠየቁት ጊዜ ኢየሱስ ምን በመጠየቅ መለሰላቸው ?
፪ ፤ ጌታ በምን ምሳሌዎች የካህናት አለቆችን አለማመንና አለመታ ዘዝ አሳየ ?
፫ ፤ «ወራሹ ይህ ነው ፤ ኑ እንግደለው» የሚለው የምሳሌው ቃል ስለ ማን ይናገራል ?

ጸሎት ፤ ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን ፤ መን ግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድን ሆን ላደረገ ፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን ፤ አሜን ።

ራእይ ፩ ፤ ፭ ፤ ፮ ።

* በኢሳ. ፭ ፤ ፩ - ፯ የሚገኘውን ምሳሌ ለሚያውቁ ሁሉ የዚህ የጌታችን ምሳሌ ትርጉም ግልጽ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፴፩ ።

# ኢየሱስ የሚፈታተኑትን መልስ አሳጣቸው ።

ማቴ. ፳፪ ፣ ፲፭ - ፳፫ ፣ ፴፱ ።

## ፩ ፣ ስለ ግብር መገበር ።

ማቴ. ፳፪ ፣ ፲፭ - ፳፪ ፣ ሉቃ. ፳ ፣ ፳ - ፳፮ ።

የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ እጃቸውን ሊጭኑበት ስለ ፈሩ ፣ ጻድቃን መስለው በቃሉ የሚያጠምዱትን ሸማቂዎች ሰደዱበት ። እነርሱም ፣ «መምህር ሆይ ፣ እውነተኛ እንደ ሆንህ በእውነትም የእግዚአብሔርን መንገድ እንደምታስተምር እናውቃለን ፤ እንግዲህ ምን ይመስልሃል ? ለቈሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም ? » አሉት ። ከአይሁድ ብዙዎች ፣ እኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነንና ለቈሣር ግብር መስጠት የተገባ አይደለም ይሉ ነበርና ለዚህ ጥያቄ ፣ ተፈቅዶአል ብሎ በአጭሩ ቢመልስ በሕዝብ ዘንድ የሚያስጠላ ክርክርን የሚያገኙበት ይመስላቸው ነበር ። አልተፈቀደም ቢል ደግሞ ፣ በሮም መንግሥት ባለ ሥልጣን ዘንድ እንዲከሱት ይጠባበቁ ነበር ።

ኢየሱስም ክፋታቸውን ዐውቆ ፣ «እናንተ ግብዞች ፣ ስለምን ትፈትኑኛላችሁ ? የግብሩን ገንዘብ አሳዩኝ» አለ ። እነርሱም ዲናር አመጡለት ። እርሱም ፣ «ይህች መልክና ጽሕፈቲቱስ የማን ናት ? » አላቸው ። መልሰውም ፣ «የቈሣር ነው» አሉት ። በዚያን ጊዜም ፣ «እንኪያስ ፣ የቈሣርን ለቈሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ» አላቸው ።

እነርሱም ሰምተው ተደነቁ ፤ በሕዝቡም ፊት በቃሉ ሊያጠምዱት አልቻሉምና ትተውት ሄዱ ።

## ፪ ፣ ስለ ትንሣኤ ሙታን ።

ማቴ. ፳፪ ፣ ፳፫ - ፴፫ ፣ ሉቃ. ፳ ፣ ፳፯ - ፴፱ ፣
ዘዳግ. ፳፭ ፣ ፭ ፣ ፮ ፣ ዘጸ. ፫ ፣ ፮ ።

በዚያን ቀን ፣ ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ደግሞ ወደ ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት ፤ «መምህር ሆይ ፣ ሙሴ ፣ አንድ ሰው ሳይወልድ ሲሞት ፣ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለምዋች ወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ጻፈልን ። እንግዲያስ ሰባት ወንድማማች ነበሩ ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ፤ ሁለተኛውም አገባት ፣ ሦስተኛውም ፣ እንዲሁም ሰባቱ አገቡአትና ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ ። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች ። እንግዲህ ሰባቱ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች ?»

ኢየሱስም ግብዝነታቸውን ምንም ቢያውቅ ፣ ከጠየቁት በላይ ስለሚመጣው ስለ ትንሣኤ ኑሮ አስተምሮ ፣ እነርሱ የጠቀሱአቸውን የሙሴን መጻሕፍት ባለማስተዋላቸው እንዲህ ብሎ ገሠፃቸው ፤ «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ ። በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም ። ሙታን እንዲነሡ ግን ሙሴ ደግሞ በቊጥቋጦው ዘንድ ፣ ጌታን የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ በማለቱ አስታወቀ ። ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ስለ ሆኑ ፣ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም ።»

ሕዝቡም ይህን ሰምተው ተገረሙ ፤ ከጸሐፊዎችም አንዳንዶች ፣ «መምህር ሆይ ፣ መልካም ተናገርህ» አሉት ።

## ፫ ፣ ስለ ታላቂቱ ትእዛዝ ።

ማቴ. ፳፪ ፣ ፴፬ - ፵ ፣ ማር. ፲፪ ፣ ፳፰ - ፴፬ ።

ፈሪሳውያንም ፣ ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ ። ከእነርሱም አንድ ሕግ ዐዋቂ እንዲፈትነው ላኩ ። እርሱም ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ፣ «መምህር ሆይ ፣ ከሕግ ማናቸዪቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት ? » ብሎ ጠየቀው ። ኢየሱስም መልሶ ፣ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ ። ታላቂቱና ፊተኛዪቱ ትእዛዝ ይህች ናት ። ሁለተኛዪቱም ይህችን ትመስላለች ፣ እርስዋም ፣ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት ። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተንጠልጥለዋል» አለው ።

## ፬ ፣ የኢየሱስ ጥያቄ ።

ማቴ. ፳፪ ፣ ፵፩ - ፵፮ ።

ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ ፣ «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል ? የማንስ ልጅ ነው ?» ብሎ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፣ «የዳዊት ልጅ ነው» አሉት ። መልሶም ፣ «እንኪያስ ዳዊት ፦ ጌታ ጌታዬን ፣ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል ፣ እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል ? ዳዊትስ ፣ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል ?» አላቸው ።

ከእነርሱም አንድ ቃል ስንኳ ይመልስለት ዘንድ የተቻለው አልነበረም ፤ ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደ ፊት ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም ።



www.ethiopianorthodox.org

፰ ፡ የመሰናበቻ ንግግሩ በቤተ መቅደስ ።

ማቴ. ፳፫ ፡ ፩ - ፴፱ ።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው ፤ «ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል ። ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም ፤ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ ።

«እናንተ ግብዞች ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን ፡ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ ፤ እናንተ አትገቡም ፡ የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ ። እናንተ እባቦች ፡ የእፉኝት ልጆች ፡ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ ? ስለዚህ ፡ እነሆ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጸሐፊዎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ ፤ ከእነርሱም ትገድላላችሁ ፡ ትሰቅሉማላችሁ ፡ ከእነርሱም በምኵራባችሁ ትገርፋላችሁ ፡ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ ።

«ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ፡ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር ፡ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ ፤ አልወደዳችሁምም ። እነሆ ፡ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል ። እላችኋለሁና ፡ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም ።»

* * *

የቄሣርን ለቄሣር ፡ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ ።

ማቴ. ፳፪ ፡ ፳፩ ።

ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ ። ታላቂቱና ፊተኛዪቱ ትእዛዝ ይህች ናት ። ሁለተኛዪቱም ይህችን ትመስላለች ፡ እርስዋም ፡ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት ። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተንጠልጥለዋል ።

ማቴ. ፳፪ ፡ ፴፯ - ፵ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ግብር መክፈል የተገባ ነውን ?
፪ ፡ ታላቂቱና ፊተኛዪቱ ትእዛዝ የትኛዪቱ ናት ?
፫ ፡ ጌታ ከቤተ መቅደስ ሳይወጣ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ያለውን ፍቅር በምን ምሳሌ ገለጠ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው ፤
ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ ።
ከትእዛዝህ የተነሣ አስተዋልሁ ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ጠላሁ ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፡ ፩፻፫ ፡ ፩፻፬ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፴፪ ።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አዲስ ሥርዓት ሰጠ ።

ከማር. ፲፬ ፤ ከሉቃ. ፳፪ ፤ ከዮሐ. ፲፫ - ፲፯ ።

፩ ፤ ኢየሱስ ከሐዋርያት ጋር ፋሲካን በላ ።

ማር. ፲፬ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ - ፳፭ ፤ ዘጸ. ፲፪ ፡ ፲፬ ፡ ፶፪ ፤ ፳፬ ፡ ፰ ፤
፩ ቆሮ. ፲፩ ፡ ፳፫ - ፳፮ ፤ ፭ ፡ ፯ ።

የአይሁድ ፋሲካ በደረሰ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ የፋሲካን እራት ሊበላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ ። የእስራኤል ሕዝብ ይህን በዓል ከጥንት ጀምረው ያከበሩት ቀዋሚ በሆነ ምክንያት ነበር ። በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር አምላክ ፡ በበግ ደም መረጩት አባቶቻቸውን ከመቅሠፍት አድኖ ከግብፅ ባርነት ያወጣበት ዕለት እንዳይረሳ ፤ «ይህ ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ» ሲል የበግ ሥጋን ባልቦካ ቂጣ እንዲበሉ በማዘዝ የልጅ ልጆቻቸው የሚጠብቁት ሥርዓት አድርጎ ሰጥቶ ነበር ።

ይህም በየዓመቱ እየታሰበ እንደ ሥነ ሥርዓቱ ሲከበር ፡ የእግዚአብሔር በግ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ከኃ

ጢአት መቅሠፍት ከሰይጣንም ባርነት
ሊያድን ደሙን የሚያፈስስበት የመሰቀሉ
ጊዜ ደረሰ ። እርሱ ፋሲካችን ሆኖ እንዲ
ታረድ የተገባው ጊዜ ፤ እርሱን ለመግለጥ
ምሳሌ የሆኑት ጠቦቶች በሚታረዱበት
በእስራኤል ዓመት በዓል ጊዜ ነበረ ።

ኢየሱስ ጊዜው እንደ ደረሰ ዐውቆ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት ሲበላ ፡
ያን የዱሮ ሥርዓት አስቀርቶ አዲሱን ሥር
ዓት በመተካት ፤ እንጀራን አንሥቶ አመሰ
ገነ ፤ ቈርሶም ፤ «እንካችሁ ፤ ይህ ሥጋዬ
ነው» አለ ። እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ
አመሰገነና ሰጣቸው ፤ ሁሉም ከእርሱ
ጠጡ ። እርሱም ፤ «ይህ ስለ ብዙዎች የሚ
ፈስስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው» አላቸው ።

፱ ፡ ኢየሱስ የሐዋርያትን እግር አጥቦ
አዲስ ትእዛዝ ሰጣቸው ።

ዮሐ. ፲፫ ፡ ፩ - ፲፯ ፡ ፴፫ - ፴፭ ፡ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፳፬ - ፳፯ ።

ኢየሱስ ፡ ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድ
በት ሰዓት እንደ ደረሰ ዐውቆ ፡ በዚህ ዓለም
ያሉትን የወደዳቸውን ወገኖቹን እስከ
መጨረሻ ወደዳቸው ። እራትም ሲበሉ
ዲያብሎስ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳ
ልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ ፡ ኢየ
ሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ዐውቆ
ከእራት ተነሣ ፡ ልብሱንም አኖረ ፡ ማበ
ሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ ፤ በኋላም በመ
ታጠቢያው ውኃ ጨመረ ፡ የደቀ መዛሙ
ርቱንም እግር እያጠበ በታጠቀበት ማበሻ
ጨርቅ ያብስ ጀመር ።

ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ ፤ እርሱም፡
«ጌታ ሆይ ፡ አንተ የእኔን እግር ታጥባለ
ህን ? » አለው ። ኢየሱስም መልሶ ፡ «እኔ
የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም ፡
በኋላ ግን ታስተውለዋለህ» አለው ። ጴጥ
ሮስም ፡ «የእኔን እግር ለዘላለም አታጥ
ብም» አለው ። ኢየሱስም ፡ «ካላጠብሁህ
ከእኔ ጋር ዕድል የለህም» ብሎ መለሰለት።
ስምዖን ጴጥሮስም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ እጄንና
ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደ
ለም» አለው ። ኢየሱስም ፡ «የታጠበ እግ
ሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገ
ውም ፤ ሁለንተናው ንጹሕ ነውና ፤ እናን
ተም ንጹሐን ናችሁ ፡ ነገር ግን ሁላችሁ
አይደላችሁም» አለው ። አሳልፎ የሚሰጠ
ውን ያውቅ ነበርና ፡ «ሁላችሁ ንጹሐን
አይደላችሁም» አለ ።

እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አን
ሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ ፡ እንዲህም አላ
ቸው ፤ «ያደረግሁላችሁን ታስተውላላች
ሁን ? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላ
ችሁ ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ ።
እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራ
ችሁን ካጠብሁ ፡ እናንተ ደግሞ እርስ በር
ሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገ
ባችኋል ። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እና
ንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻች
ኋለሁና ። እውነት እውነት እላችኋለሁ ፡
ባሪያ ከጌታው ፡ መልእክተኛም ከላከው
አይበልጥም ። ይህን ብታውቁ ብታደርጉ
ትም ብፁዓን ናችሁ ። . . . ልጆች ሆይ ፡
ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ። እንደ
ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳ
ችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣ
ችኋለሁ ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራ
ችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች
በዚህ ያውቃሉ ።»

፲ ፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አጽናና ።

ሉቃ. ፳፪ ፡ ፴፩ - ፴፬ ፤ ማር. ፲፬ ፡ ፴፩ ፡
ዮሐ. ፲፫ ፡ ፴፫ ፡ ፴፯ ፤ ፲፬ ፤ ፩ - ፲፩ ፡ ፴፫ ።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለስምዖን ጴጥሮስ ፡
«ስምዖን ስምዖን ሆይ ፡ እነሆ ሰይጣን
እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ ፤ እኔ
ግን ፡ እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማ



www.ethiopianorthodox.org

ለድሁ ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድ
ሞችህን አጽና» አለው ።

እርሱም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ወደ ወኅኒም
ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋ
ጀሁ ነኝ» አለ ። ኢየሱስ ግን ፡ «ጴጥሮስ
ሆይ እልሃለሁ ፡ እንዳታውቀኝ ሦስት ጊዜ
እስክትክደኝ ድረስ ዛሬ ዶሮ አይጮኽም»
አለው ። እርሱም ቃሉን አበርትቶ ፡ «ከአ
ንተ ጋር የምሞት እንኳ ብሆን ከቶ አልክ
ድህም» አለ ። ሁሉም ደግሞ እንዲሁ
አሉ ።

ኢየሱስ ፡ «ልጆች ሆይ ፡ ገና ጥቂት ጊዜ
ከእናንተ ጋር ነኝ» ሲላቸው ኀዘን በልባ
ቸው ሞላና ጴጥሮስ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ወዴት
ትሄዳለህ ? » አለው ። ኢየሱስም ፡ «ልባ
ችሁ አይታወክ ፤ በእግዚአብሔር እመኑ ፡
በእኔም ደግሞ እመኑ ። በአባቴ ቤት ብዙ
መኖሪያ አለ ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋ
ችሁ ነበር ፤ ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ
እሄዳለሁና ፤ ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ ፡
እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ
ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳች
ኋለሁ ። ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ ፡
መንገዱንም ታውቃላችሁ» አለ ።

ቶማስም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ ወደምትሄድ
በት አናውቅም ፤ እንዴትስ መንገዱን
እናውቃለን ? » አለው ። ኢየሱስ ፡ «እኔ
መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ፤ በእኔ
በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ። እኔንስ
ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ
ነበር ። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላ
ችሁ አይታችሁትማል» አለ ።

ደግሞም እንዲህ አላቸው ፤ «ሰላምን
እተውላችኋለሁ ፡ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ፤
እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደ
ለም ። . . . . እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እና
ንተ አልመረጣችሁኝም ፤ አብም በስሜ
የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ፡ ልት
ሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችሁም ሊኖር
ሾምኋችሁ ። እርስ በርሳችሁ እንድትዋ
ደዱ ይህን አዛችኋለሁ ። . . . ዓለም ቢጠ
ላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ
ዕወቁ ። . . . ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የም
ልክላችሁ አጽናኝ ፡ እርሱም ከአብ የሚ
ወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ፡
እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል ፤ እናንተም
ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና
ትመሰክራላችሁ ። . . . በእኔ ሳላችሁ
ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋ
ለሁ ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ፤
ነገር ግን አይዞአችሁ ፤ እኔ ዓለምን አሸን
ፌዋለሁ ።»

፲፩ ፤ ኢየሱስ ስለ ራሱና የእርሱ ስለሚሆ
ኑት ጸለየ ።

ዮሐ. ፲፯ ፡ ፩ - ፳፮ ።

ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖ
ቹን አነሣና እንዲህ አለ ፤ «አባት ሆይ ፡
ሰዓቱ ደርሶአል ፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ ፡
በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠ
ኸው ፡ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይ
ወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብ
ረው ። . . . እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ
ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ ፤ አሁንም
አባት ሆይ ፡ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ
ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ
አክብረኝ ። . . . . .

«ቅዱስ አባት ሆይ ፡ እነዚህን የሰጠኸ
ኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ
ጠብቃቸው ። . . . ከክፉ እንድትጠብቃ
ቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አል
ለምንም ። . . . . አባት ሆይ ፡ ዓለም ሳይ
ፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን
እንዲያዩ ፡ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነ
ርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳ
ለሁ ። ጻድቅ አባት ሆይ ፡ ዓለም አላወቀ

ሆም እኔ ግን ዐወቅሁህ ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ ዐወቁ ፤ እኔንም የወደድህ ባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእ ነርሱ ፤ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታው ቃቸውማለሁ ።»

*      *      *

ኢየሱስ አለ ፤ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ። ዮሐ. ፲፬ ፣ ፮ ።

በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው ? የተቀመጠው አይደለምን ? እኔ ግን በመካከላችሁ እን ደሚያገለግል ነኝ ። ሉቃ. ፳፪ ፣ ፳፯ ።

በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ ። ዮሐ. ፲፮ ፣ ፴፫ ።

*      *      *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ አዲስ ሥርዓትን የሰጠ በምን ጊዜ ነበር ?
፪ ፤ አንዱ አንዱን እንዲያገለግል ጌታ ምን ምሳሌ ሰጥቶናል ?
፫ ፤ የሰጠንስ አዲስ ትእዛዝ ምንድር ነው ?
፬ ፤ ጌታ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ምን ብሎ ጸለየ ?

ጸሎት ፤ የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ ፤ መን ፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ ። ፩ ተሰ. ፭ ፣ ፳፫ ።





ምዕራፍ ፴፫ ።

## ጌታችን የተያዘባት ሌሊት ።

ማቴ. ፳፮ ፤ ማር. ፲፬ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፤ ዮሐ. ፲፰ ።

### ፩ ፤ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ ።

ማቴ. ፳፮ ፣ ፴ ፣ ፴፮ - ፵፮ ፤ ማር. ፲፬ ፣ ፴፪ - ፵፪ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፣ ፴፱ - ፵፮ ፤ ዮሐ. ፲፰ ፣ ፩ ፡ ፪ ።

መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ኢየሱስና አሥራ አንድ ደቀ መዛሙርቱ ፤ እራት ከበሉበት አዳራሽ ተነሥተው ጌቴሴማኒ ወደሚ ባል የአትክልት ሥፍራ ሄዱ ። የካህናት አለቆች በጌቴሴማኒ እንዲያስይዙት ሊያ ማክር የይሁዳን ተለይቶ መሄድም ኢየሱስ ዐወቀ ።

ወደ ጌቴሴማኒም ሲደርሱ ደቀ መዛሙ ርቱን ፤ «በዚህ ተቀመጡ» ብሎ ጴጥሮስ ንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ወሰደ ፤ እያዘነና እየተከዘም ፤ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች ፤ በዚህ ቈዩ ትጉም» አላ ቸው ።

ከእነርሱም ጥቂት እልፍ ብሎ በምድር ወድቆ ፤ «አባት ሆይ ፤ ሁሉ ይቻልሃል ፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደም



www.ethiopianorthodox.org

ወድ አይሁን» አለ ። ወደ እነርሱም ተመለሰ ፡ ተኝተውም አገኛቸው ፤ ጴጥሮስንም ፡ «ስምዖን ሆይ ፡ ተኝተሃልን ? አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጋ አልቻልህምን ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ፡ ጸልዩም ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ፡ ሥጋ ግን ደካማ ነው» አለ ።

ደግሞ ሄደና ፡ «አባቴ ሆይ ፡ ሳልጠጣት ይህች ጽዋ ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ ፈቃድህ ትሁን» አለ ። እንደገናም ቢመለስ ፡ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው ፤ የሚመልሱለትንም አላወቁም ። ደግሞም ትቶአቸው ሄደ ፡ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ ። ከዚያ ወዲያም ወደ እነርሱ መጥቶ፡ «እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም ፤ እነሆ ሰዓቲቱ ደረሰች ፤ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦ አል» አላቸው ።

፪ ፡ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ተያዘ ።

የሐ. ፲፰ ፡ ፫ - ፲፬ ፤ ማቴ. ፳፮ ፡ ፵፯ - ፶፮ ፤ ማር. ፲፬ ፡ ፵፫ - ፶፫ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፵፯ - ፶፬ ።

ይህንም ገና ሲናገር ፡ ሰይፍና ጐመድ የያዙ ጭፍሮችን ፡ ችቦና ፋናም የያዙ የካህናት አለቆችና የፈሪሳውያን ሎሌዎችን እየመራ ይሁዳ መጣ ፤ እንደ ሰጣቸውም ምልክት ቀርቦ ጌታውን ሳመ ። ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ ዐውቆ ወደ እነርሱ ቀረበና ፡ «ማንን ትፈልጋላችሁ ?» ቢላቸው ፡ «የናዝሬቱን ኢየሱስን» በማለት መለሱለት ። ኢየሱስም ፡ «እኔ ነኝ» አላቸው ፤ እነርሱም ወደ ኋላ አፈግፍገው ወደቁ ። ደግሞም ፡ «ማንን ትፈልጋላችሁ ?» ብሎ ጠየቃቸው ፤ እንደገናም ፡ «የናዝሬቱን ኢየሱስን» አሉ ። እርሱም ፡ «እኔ ነኝ አልኋችሁ ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ» አለ ።

ስምዖን ጴጥሮስም የያዘውን ሰይፍ መዝዞ የሊቀ ካህናቱን ሎሌ ቀኝ ጆሮ ቈረጠ ፤ የሎሌውም ስም ማልኮስ ይባል ነበር ። ኢየሱስም ጴጥሮስን ፡ «ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው ፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን ? » ብሎ የሎሌውን ጆሮ ዳሰሰና ፈወሰ ። በዚያን ጊዜም ኢየሱስን ይዘው አሠሩት ፤ የሞትም ፍርድ ሲፈርዱበት የሚጠባበቁት ተሰብስበውበት ወደ ነበር ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ቤት ወሰዱት ።

፫ ፡ ጴጥሮስ ጌታን ካደ ።

የሐ. ፲፰ ፡ ፲፭ - ፲፰ ፡ ፳፭ - ፳፯ ፤ ማቴ. ፳፮ ፡ ፶፰ ፡ ፷፱ - ፸፭ ፤ ማር. ፲፬ ፡ ፶፬ ፡ ፷፮ - ፸፪ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፶፬ - ፷፪ ።

ኢየሱስ በጌቴሴማኒ በተያዘ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ትተውት ሸሹ ። ዮሐንስ ግን ኢየሱስን ተከተለ ፤ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበረና ከኢየሱስ ጋር ወደ ግቢው ገባ ። ጴጥሮስም ከሩቅ ተከተለ ፡ ከበር ውጭም ቆሞ ስለ ነበር ዮሐንስ ለበረኛዩቱ ነግሮ አስገባው ፤ በረኛዩቱም ገረድ ጴጥሮስን ፡ «አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን ? » አለችው ። እርሱም ፡ «አይደለሁም» አለ ።

ሌሊቱ ብርድ ስለ ነበረ ሎሌዎች አንድደውት የፈመ እሳት በግቢው መካከል ነበረ ። ጴጥሮስም የነገሩን ፍጻሜ ያይ ዘንድ ከሎሌዎች ጋር ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሌሎች ሰዎች አስተውለውት ፡ «አንተ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ አይደለህምን ? » አሉት ። እርሱም ፡ «አይደለሁም» ብሎ በሁሉ ፊት ካደ ። ከሊቀ ካህናቱ ሎሌዎች ጆሮው የተቈረጠው ዘመድ የሆነ አንድ ሌላ ደግሞ ፡ «በአትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አይቼህ አልነበርሁምን ? » አለው ። ሌሎ



ችም ፡ «አነጋገርህ ያስታውቃልና በእውነት አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ» አሉት ። በዚያን ጊዜም ፡ «ሰውየውን አላውቅም» ብሎ ይረግምና ይምል ጀመር ።

ወዲያውም ዶሮ ጮኸ ። ዶሮም በጮኸ ጊዜ ኢየሱስ ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተ ። ጴጥሮስም ፡ ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ እንዳለው የጌታ ቃል ትዝ አለው ፤ ወደ ውጭም ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ ።

*        *        *

ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ፡ ጸልዩም ። ማር. ፲፬ ፡ ፴፰ ።

ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጐሰሙ ብትታገሡ ፡ ምን ክብር አለበት ? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ ፡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል ። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና ።

፩ ጴጥ. ፪ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

*        *        *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ በጌቴሴማኒ ኢየሱስ ምን ብሎ ጸለየ ?
፪ ፤ ጴጥሮስ የማልኮስን ጆሮ በቈረጠ ጊዜ ኢየሱስ ምን አለው ?
፫ ፤ ዶሮ በጮኸ ጊዜ ጴጥሮስ ምን አደረገ ?

ጸሎት ፤ አባቴ ፡ አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን ። ማቴ. ፳፮ ፡ ፴፱ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፴፩ ።

## የጌታችን ስቅለትና ትንሣኤ ።

ከማቴ. ፳፯ ፤ ከዮሐ. ፲፱ ፤ ከሉቃ. ፳፬ ።

### ፩ ፤ ዕለተ ስቅለት ።

ማቴ. ፳፯ ፥ ፩ - ፲ ፤
የሐዋ. ፩ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ፥ ዮሐ. ፲፱ ፥ ፴፬ - ፴፯ ።

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ ፤ ለገዢው ለጴንጤናዊው ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት ።

በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ ፤ የሰጡትን ሠላሳውን ብርም ለካህናት አለቆች መልሶ ፤ «ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ» አለ ። እነርሱ ግን ፥ «እኛስ ምን አግዶን ? » ባሉት ጊዜ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ጥሎ ወደ ሸክላ ሠሪው መሬት ሄደ ፤ ታንቆም በግምባሩ ወደቀ ፥ ሞተም ። የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው ፥ «የደም ዋጋ ነውና በመባ ሣጥን ልንጨምረው አይገባንም» ብለው ከተመካከሩ በኋላ ያን የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት ።

ዮሐንስ የተባለው ደቀ መዝሙርም እስከ ጎልጎታ ድረስ ጌታችንን ተከትሎ በመስቀል አጠገብ ሲቆም ፥ ኢየሱስ ነፍሱን ከሰጠ በኋላ ከጭፍራዎቹ አንዱ ጎኑን በጦር እንደ ወጋው ፥ ነገር ግን ከአጥንቶቹ አንዱ እንዳልተሰበረ አየ ። በየዓመቱ በፋሲካ በዓል ስለሚታረድም በግ ፥ «ከእርሱ አጥንት አይሰበርም» ተብሎ እንደ ተጻፈ ከትንሣኤ በኋላ ትዝ አለው ። ደግሞም ፥ «የወጉትን ያዩታል» ሲል የተናገረውን የነቢዩ ዘካርያስን ትንቢት አሰበ ። የሚያነቡትም ያምኑ ዘንድ ያየውንና ያረጋገጠውን መስክሮ ጻፈ ።



### ፪ ፤ ዕለተ ትንሣኤ ።

ሉቃ. ፳፬ ፥ ፩ - ፶፫ ።

ሞቶም በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከገሊላ ከተከተሉት ሴቶች አንዳንዶቹ ፥ ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ወደ መቃብር ማልደው ቢመጡ መነሣቱን ተረዱ ። ከመቃብሩም ተመልሰው ለአሥራ አንዱና ለሌሎች መነሣቱን አወሩ ፤ ነገራቸውም እንደ ቅዠት መስሎ ስለ ታያቸው አላመኑአቸውም ።

እነሆ በዚያ ቀን ከእነርሱ ሁለት ሰዎች ከኢየሩሳሌም ውጭ ወዳለው ኤማሁስ ወደሚሉት መንደር ሲሄዱ ስለዚህ ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር ።

ሲነጋገሩና እየተመራመሩም ሲሄዱ ሳሉ ኢየሱስ ራሱ ወደ እነርሱ ቀርቦ አብሯቸው ይሄድ ጀመር ፤ ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይኖቻቸው ተከልለው ነበር ። እርሱም ፥ «እያዘናችሁ ስትሄዱ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩት ይህ ነገር ምንድር ነው ? » አላቸው ። ከሁለቱም አንዱ ቀለዮጳ የተባለው መልሶ ፥ «አንተ ብቻ እንግዳ ነህን ? በዚህስ ወራት በኢየሩሳሌም የሆነውን አታውቅምን ? » አለው ። መልሶም ፥ «እርሱ ምንድር ነው ? » አላቸው ።

እነርሱም ፥ «በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ የነበረውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ፥ የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ለሞት ፍርድ አሳልፈው መስጠታቸውና መስቀላቸው ነው ። እኛ ግን እስራኤልን እንዲያድን ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር ፤ ከዚህም ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው ። ደግሞም ሴቶ
ከእኛ ወደ መቃብሩ ማልደው ሄደው ነ
ርና ተመልሰው ፥ ሕያው ነው የሚሉ መ
እክትን አየን ሲሉ አስገረሙን ። ከእኛ
ጋር ከነበሩት ወደ መቃብሩ ቢሄዱ ሴቶች
እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙ ፤ እርሱን ግን
አላዩትም» አሉት ።

እርሱም ፥ «እናንተ የማታስተውሉ ፥ ነቢ
ያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማ
መን የዘገየ ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀ
በል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገ
ባው የለምን ? » አላቸው ። ከሙሴና ከነቢ
ያትም ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በብሉይ
ኪዳን መጻሕፍት የተጻፈውን ተረጐመላ
ቸው ።

ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ ፤ እርሱም አልፎ የሚሄድ መስሎአቸው ፥ «ቀኑ መሽቶ ፀሐይ ገብቶአልና ከእኛ ጋር እደር» እያሉ ግድ አሉት ፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ ። ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ያዘ ፥ ባረከውም ቈርሶም ሰጣቸው ። ዓይኖቻቸውም ተከፈቱና ዐወቁት ፤ ያን ጊዜም ከእነርሱ ተሠወረ ።

እርስ በርሳቸውም ፥ «በመንገድ ሲናገረንና መጻሕፍትንም ሲተረጕምልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን ? » ተባባሉ ። በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ፤ አሥራ አንዱንና ከእነርሱ ጋር የነበሩትንም ፥ «ጌታ በእውነት ተነሥቶአል ፥ ለስምዖንም ታይቶአል» እያሉ በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው ። ቀለዮጳና ጓደኛውም በመንገድ የሆነላቸውን ፥ እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸው ተረኩ ።

ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ ፥ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው ። ከፍርሃትና ከደስታም የተነሣ

www.ethiopianorthodox.org

ሲደነቁ ሳሉ ፡ «እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ» አለ ፤ ተዘጋጅቶ ከነበረው ምግብም ተቀብሎ በፊታቸው በላ ።

ከዚህም በኋላ ፡ «ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው» አላቸው ። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው ። አላቸውም ፡ «ክርስቶስ መከራን ይቀበላል ፡ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል ፡ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል ። እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ ።»

* * *

ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ፡ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ ። ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ፡ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ፡ ከሙታን ባስነሣው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ ። ፩ ጴጥ. ፩ ፡ ፲፰ - ፳፩ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በኢየሱስ መስቀል አጠገብ የቆመ ማን ነበረ ? ምንስ አየ ?

፪ ፡ ወደ ኤማሁስ ይሄዱ የነበሩ ሰዎች በምን ምክንያት ያዝኑ ነበር ?

፫ ፡ ኢየሱስ ራሱን ሳይገልጥላቸው በፊት ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት በመጥቀስ ምንን ያስረዳቸው ነበር ?

ጸሎት ፡ የታረደው በግ ኃይልና ባለጸግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል ። ታርደሃልና ፡ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተሃልና ። አሜን ። ራእይ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።





ምዕራፍ ፴፫ ።

## በገሊላ ባሕር ዳር ።

ዮሐ. ፳፩ ።

፩ ፡ ጌታችን ያስገኘው የዓሣ ብዛት ።

ዮሐ. ፳፩ ፡ ፩ - ፲፫ ።

ሐዋርያት በገሊላ አገር ከጌታ ጋር እንዲገናኙ ተቃጥረው ስለ ነበር ከትንሣኤ በኋላ ወደ ገሊላ ሄዱ ። ከእነርሱም አንዳንዶች በባሕር ዳር ሆነው ጊዜው መሸት ሲል ስምዖን ጴጥሮስ ፡ «ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ» አላቸው ። እነርሱም ከእርሱ ጋር ወደ ጀልባ ገቡ ፤ በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም ።

በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ ፤ እነርሱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም ። ኢየሱስም ፡ «ልጆች ሆይ ፡ አንዳች የሚበላ አላችሁን ? » አላቸው ። እነርሱም ፡ «የለንም» ብለው መለሱለት ።

እርሱም ፡ «መረቡን በጀልባዪቱ በስተቀኝ ጣሉ ፡ ታገኙማላችሁ» አላቸው ። እንደ ቃሉም አደረጉ ፤ በዚያን ጊዜም ከዓሣው ብዛት የተነሣ መረቡን ሊጐትቱ አቃታቸው ። ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን ፡ «ጌታ ነው እኮ» አለው ። ስምዖን ጴጥሮስም ጌታ መሆኑን ባስተዋለ ጊዜ ልብሱን ታጥቆ ወደ ኢየሱስ ለመድረስ ወደ ባሕር ተወረወረ ። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ዓሣ የሞላበትን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ጌታችን ያዘጋጀላቸው ምሳ ።

ዮሐ. ፳፩ ፡ ፱ - ፲፬ ።

ወደ ምድርም በደረሱ ጊዜ ፍም ፡ ዓሣም በላዩ ሆኖ ፡ እንጀራም ተዘጋጅቶ አገኙ ። ኢየሱስም ፡ «አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ» አላቸው ። ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባዪቱ ገብቶ በብዙ ታላላቅ ዓሦች ተሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ ።

ኢየሱስም ፡ «ኑ ፡ ምሳ ብሉ» አላቸው ። እርሱም ራሱ እንጀራን አንሥቶ ሰጣቸው ፡ እንዲሁም ዓሣውን ።

፫ ፡ የስምዖን ጴጥሮስ መጽናት ።

ዮሐ. ፳፩ ፡ ፲፭ - ፳፭ ።

ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን ፡ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፡ ትወደኛለህን ? » አለው ። እርሱም ፡ «አዎን ጌታ ሆይ ፡ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው ። ኢየሱስም ፡ «የበግ ግልገሎቼን አሰማራ» አለው ።

ሁለተኛም ፡ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፡ ትወደኛለህን ? » አለው ። እርሱም ፡ «አዎን ጌታ ሆይ ፡ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው ። ኢየሱስም ፡ «ጠቦቶቼን ጠብቅ» አለው ።

ሦስተኛም ፡ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፡ ትወደኛለህን ? » አለው ። ሦስተኛ ጊዜ ፡ ትወደኛለህን ? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አንተ ሁሉን ታውቃለህ ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ » አለው ። ኢየሱስም ፡ «በጎቼን አሰማራ ። እውነት እውነት እልሃለሁ ፡ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር ፤ በሸመገልህ ጊዜ ግን እጆችህን ትዘረጋለህ ፡ ሌላውም ያስታጥቅሃል ፡ ወደማትወደውም ይወስድሃል» አለው ። ይህን ያለውም በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ነው ። ይህንም ብሎ ፡ «ተከተለኝ» አለው ።

* * *

እኛ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ዐውቀናል አምነን ማል ። . . . እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን ።

፩ ዮሐ. ፬ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ።

በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ ።

ቈላ. ፬ ፡ ፲፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ አሁን በዚህ ጊዜ ያጠመዱት የዓሣ ብዛት ፡ ምን ሌላ ጊዜን ያሳሰባቸው ይመስላችኋል ? (ሉቃ. ፭ ፡ ፩ - ፲፩ ።)

፪ ፤ ከሙታን የተነሣው ጌታ ፡ ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ ያደሩትን ደቀ መዛሙርት ምን በማድረግ አገለገላቸው ?

፫ ፤ ለስምዖን ጴጥሮስስ ምን በማለት የአገልግሎት አደራ ሰጠው ?

ጸሎት ፤ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደደን በጸጋም የዘላለምን መጽናናት በጎንም ተስፋ የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን ልባችሁን ያጽናኑት በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ ያጽኑአችሁ ።

፪ ተሰ. ፪ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።





ምዕራፍ ፴፯ ።

## የቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና አጠባበቅ ።

ከሐዋ. ፪ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፰ ።

፩ ፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ።

የሐዋ. ፪ ፡ ፵፩ - ፵፯ ፤ ፬ ፡ ፬ ፡ ፴፪ - ፴፯ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ ካረገ በኋላ የጰንጠቆስጤ ቀን በደረሰ ጊዜ ፡ መቶ ሃያ በሚያህሉ ደቀ መዛሙርት ላይ መንፈስ ቅዱስ መጣ ። በዚያን ዕለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የተጠመቁት ሦስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች ተጨምረውላቸው ፤ በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት እየተጉ በደስታና በጥሩ ልብ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሲኖሩ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው ። ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር ፤ ባመኑትም ሁሉ ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው ። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር ።

ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው ፤ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ፡ ይህ የእኔ ገን



www.ethiopianorthodox.org

ዘብ ነው የሚል አንድ ስንኳ አልነበረም ። ከእነርሱም ችግረኛ አልተገኘም ፤ ቤትም ርስትም ያላቸው እየሸጡ ዋጋውን ያመጡ፡ በሐዋርያት እግር አጠገብም ያኖሩ ነበር ፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያን ዳንዱ ያካፍሉት ነበር ።

እንደዚሁም ካደረጉት ዮሴፍ የሚሉት ትውልዱ ከቆጵሮስ የነበረ አንድ ሌዋዊ ነበረ ። በሐዋርያትም ዘንድ በርናባስ ይባል ነበር ፡ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ማለት ነው ። እርሱም እርሻውን ሸጠ ገንዘቡን በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረ።

፪ ፤ የሐናንያና የሰጲራ ግብዝነት ።

የሐዋ. ፭ ፡ ፩ - ፲፩ ።

ሐናንያ የተባለ ሰውም ፡ የበርናባስንና የብዙ ሌሎችን አደራረግ በመመልከት ፡ ከሚስቱ ከሰጲራ ጋር ተመካክሮ መሬት ሸጠ ። ነገር ግን የመሬቱ ሙሉ ዋጋ እንደ ሆነ በማስመሰል የሸያጩን እኩሌታ አም ጥቶ በሐዋርያት እግር አኖረ ።

ጴጥሮስም ፡ «ሐናንያ ሆይ ፡ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስ ቶር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን ? ከሸጥኸ ውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን ? ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ ? ለእ ግዚአብሔር እንጂ ለሰው አልዋሸህም» አለው ። ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ፡ ሞተም ። በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ ። ጐበዞችም ተነሥ ተው ከፈኑት ፡ አውጥተውም ቀበሩት ።

ከሦስት ሰዓት በኋላም ሚስቱ ሰጲራ የሆነውን ሳታውቅ ገባች ። ጴጥሮስም መልሶ ፡ «እስቲ ንገሪኝ ፤ መሬታችሁን ይህን ለሚያህል ሸጣችሁትን ?» አላት ። ርስዋም ፡ «አዎን ፡ ይህን ለሚያህል ው» አለች ።

ጴጥሮስም ፡ «የጌታን መንፈስ ትፈታ ተኑ ዘንድ ስለምን ተስማማችሁ ? እነሆ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው ፡ አንቺንም ያወጡሻል» አላት ። ያን ጊዜም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ፡ ሞተችም ፤ ጐበ ዞችም ሲገቡ ሞታ አገኙአት ፡ አውጥተ ውም በባልዋ አጠገብ ቀበሩአት ። በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ ። ሕዝቡም ያከብሩ አቸው ነበር ፤ እውነተኛ ካልሆነ አንድ ስንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር አልነበ ረም ። ከፊትም ይልቅ ብዙ ወንዶችና ሴቶች እያመኑ ለጌታ ይጨመሩ ነበር ። በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር ።

፫ ፤ የሰማርያ ቤተ ክርስቲያን ።

የሐዋ. ፰ ፡ ፬ - ፲፫ ።

ከዚህም በኋላ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን በሰበከላቸው ጊዜ ሕዝቡ በደስታ ሰሙ ። በክርስቶስም ስም ያደረገ ትን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙዎች አምነው ተጠመቁ ። በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ ።

እስከዚህ ድረስ ግን መላው የከተማ ሰዎች ፡ ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ሲሞን የተባለውን ጠንቋይ ያከ ብሩ ፡ በጥንቆላ ሥራውም እየተገረሙ ያደምጡት ነበር ። የወንጌል ቃል ደርሶላ ቸው እየተጠመቁ ወደ ክርስቶስ አሁን ዘወር ሲሉ ግን ፤ ሲሞን ራሱ ደግሞ የሚደ ረገውን ምልክት ባየ ጊዜ አምኖ ተጠ መቀ ።

፬ ፤ የጠንቋዩ ሲሞን ክፉ አሳብ ።

የሐዋ. ፰ ፡ ፲፬ - ፳፭ ።

በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማ ርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው ። እነርሱም በወረዱ ጊዜ መን ፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ እየጸለዩ እጃቸ ውን ጫኑባቸው ።

ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መን ፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ፤ ገንዘብ አመጣላቸውና ፡ «እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ» አለ ። ጴጥሮስ ግን ፡ «የእግዚአብሔርን ስጦታ በገን ዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ ። ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም ። እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ ፤ ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን ፤ በመራራ መርዝና በዓመፅ እሥ ራት እንዳለህ አይሃለሁና» አለው ። ሲሞ ንም መልሶ ፡ «ካላችሁት አንዳች እንዳይ ደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ» አላቸው ።

እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተ ናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ፤ በሳምራውያን በብዙ መንደሮችም ወንጌ ልን ሰበኩ ።

* * *

አትሳቱ ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም ። ሰው የሚዘራ ውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና ።

ገላ. ፮ ፡ ፯ ።

እናንተ ኃጢአተኞች ፡ እጆቻችሁን አንጹ ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ፡ ልባችሁን አጥሩ ።

ያዕ. ፬ ፡ ፰ ።

ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ ፡ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ ፤ . . . . እንደ ብርሃን ልጆችም ተመላለሱ ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ ።

ኤፌ. ፭ ፡ ፰ - ፲፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ በርናባስ ማን ነበረ ? ምንስ አደረገ ?
፪ ፤ ሐናንያና ሰጲራ ምን ክፋት አደረጉ ?
፫ ፤ ሲሞንስ ማን ነበረ ? ምንስ ክፉ ነገር አሰበ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ መርምረኝ ፡ ልቤንም ዕወቅ ፤
ፈትነኝ መንገዴንም ዕወቅ ፤
በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ ፤
የዘላለምንም መንገድ ምራኝ ።

መዝ. ፩፻፴፰ (፩፻፴፱) ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፴፯ ።

# የእስጢፋኖስ ምስክርነትና ሞት ።

የሐዋ. ፮ ፡ ፩ - ፰ ፡ ፩ ።

፩ ፡ የእስጢፋኖስ አገልግሎት ።

የሐዋ. ፮ ፡ ፩ - ፯ ።

በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ነዋሪ በሆኑት አይ ሁዳውያን መካከል በግሪክና በልዩ ልዩ ውጭ አገሮች ተወልደው የመጡት አይሁ ዳውያን ይገኙ ነበር ። ከሁለቱም ወገን ደቀ መዛሙርት ቍጥር እየበዛ ሄደ ። ነገር ግን ከውጭ አገር መጥተው ደቀ መዛ ሙርት የሆኑት ፡ «በየቀኑ በሚታደል የተ ራድኦ አገልግሎት መበለቶቻችንን ቸል ይሉአቸዋላችሁ» ብለው በይሁዳውያን ደቀ መዛሙርት ወገኖቻቸው ላይ ያንጐራ ጕሩ ጀመር ።

ሐዋርያትም ደቀ መዛሙርትን ሁሉ ሰብስበው ፡ «የእግዚአብሔርን ቃል ትተን እንዲህ ባለ አገልግሎት እንድንውል የሚ ገባ ነገር አይደለም ። ወንድሞች ሆይ ፡ በመልካም የተመሰከረላቸውን ፡ መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ፤ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን ። እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን» አሉ ።

ይህም ቃል በማኅበሩ ሁሉ ፊት ተወ ደደ ፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበ ትን ሰው እስጢፋኖስን ፡ ከእርሱም ጋር ሌሎችን ስድስት ሰዎች መርጠው በሐዋር ያት ፊት አቆሙአቸው ፤ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው ።



፪ ፡ የእስጢፋኖስ መከሰስ ።

የሐዋ. ፮ ፡ ፰ - ፲፭ ።

እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክ ትን ያደርግ ነበር ። የነጻ ወጪዎች ከተባለ ችው ምኵራብም ከቀሬናና ከእስክንድር ያም ፡ ከኪልቅያና ከእስያም ከነበሩት አን ዳንዶቹ ተነሥተው ይከራከሩት ነበር ፤ ነገር ግን እርሱ ይናገርበት የነበረውን ጥበ ብና መንፈስ ሊቃወሙ አልቻሉም ።

በዚያን ጊዜም ፡ «ይህ ሰው በሙሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲና ገር ሰምተነዋል» የሚሉ ሰዎችን አስነሥ ተው ሕዝቡን አናደዱ ። ቀርበውም ያዙ ትና ወደ ሸንጎው አምጥተው ፡ «ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ሥፍራ ፡ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ከመናገር አይተውም ፤ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ሥፍራ ያፈር ሰዋል ፡ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋል» የሚሉ የሐ ሰት ምስክሮችን አቆሙ ። በሸንጎውም የተ ቀመጡት ሁሉ ትኵር ብለው ሲመለከቱት ፊቱ እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ታያቸው ።

፫ ፡ የእስጢፋኖስ ንግግር ።

የሐዋ. ፯ ፡ ፩ - ፶፫ ።

ሊቀ ካህናቱም ፡ «ይህ ነገር እንዲህ ነውን ? » አለው ። እስጢፋኖስም እንዲህ አለ ፡-

«ወንድሞችና አባቶች ሆይ ፡ ስሙ ። የክ ብር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም ታየና «ከአገርህ ወጥተህ ወደማሳይህ ምድር ና» አለው ። እግዚአብሔርም ፡ «ዘርህ በሌላ አገር መጻተኞች ይሆናሉ ፡ ከአራት መቶ ዓመትም በኋላ ይወጣሉ» አለው ። አብር ሃምም ይስሐቅን ፡ ይስሐቅም ያዕቆብን ፡ ያዕቆብም አሥራ ሁለቱን የአባቶችን አለ ቆች ወለደ ።

«የአባቶች አለቆችም በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት ፤ እግዚአብሔርም ከእ ርሱ ጋር ነበረ ፡ ከመከራውም ሁሉ አወ ጣው ፤ ፈርዖንም በግብፅ ላይ ቢትወደድ አድርጎ ሾመው ። አባቶቻችንም ምግብን ባላገኙ ጊዜ ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሰደዳቸው ፤ በሁለተኛውም ጊዜ ዮሴፍ አባቱንና ቤተ ዘመዱን ሁሉ ልኮ አስጠራ ።

«እግዚአብሔርም ለአብርሃም የማለ ለት የተስፋው ዘመን ሲቀርብ ሙሴ ተወ ለደ ፤ የፈርዖን ልጅም አነሣችው ፡ ልጅም እንዲሆናት አሳደገችው ። እርሱም ፵ርባ ዓመት ሲሞላው ወንድሞቹን ጐበኘ ፤ እነ ርሱ ግን እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እን ደሚሰጣቸው አላስተዋሉምና ከእነርሱ አንዱ ፡ «በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድ ትሆን የሾመህ ማን ነው ?» ብሎ ገፋው ። ከዚያም ከ፵ርባ ዓመት በኋላ ፡ «ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው ? » ብለው የካዱትን ይህን ሙሴን በቍጥቋ ጦው በታየው መልአክ እግዚአብሔር ሹምና ቤዛ አድርጎ ላከው ። ይህ ሰው ድን ቅና ምልክት እያደረገ ከግብፅ አውጥቶ ፵ርባ ዓመት መራቸው ፡ እንዲሰጠንም ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ ። አባቶ ቻችን ግን ሊታዘዙት አልወደዱም ፤ ነገር ግን ገፉት ፡ በልባቸውም ወደ ግብፅ ተመ ለሱ ፤ ለጣዖትም መሥዋዕት አቀረቡ ።

«እግዚአብሔርም ሙሴን ተናግሮ እን ዳዘዘውና እንዳሳየው ምሳሌ የተሠራች የምስክር ድንኳን ከአባቶቻችን ዘንድ በም ድረ በዳ ነበረች ፤ በኢያሱም ጊዜ የነበሩ አባቶቻችን በተራ ተቀብለው ወደ ተሰጠ ቻቸው ምድር አገቡአት ፤ እስከ ዳዊት ዘመንም ድረስ ኖረች ።

«ዳዊትም ለእግዚአብሔር ማደሪያን ለመሥራት ለመነ ፤ ቤት የሠራለት ግን ሰሎሞን ነበረ ። ነገር ግን ፡ ሰማይ ዙፋኔ



www.ethiopianorthodox.org

ነው ፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት ፤ የምትሠሩልኝ ቤት እንዴት ያለ ነው ? ይላል ጌታ ሲል ፤ ነቢዩ እንደ ተናገረ ፤ ልዑል የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም ።

«እናንተ አንገተ ደንዳኖች ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ። ከነቢያትስ አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን ነው ? የጻድቁን ፤ የክርስቶስን መምጣት አስቀድሞ የተናገሩትንም ገደሉ ፤ እናንተም አሁን እርሱን አሳልፋችሁ ሰጣችሁት ገደላችሁትም ።»

፡ የእስጢፋኖስ ሞት ።

የሐዋ. ፯ ፡ ፶፬ - ፰ ፡ ፩ ።

ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቈጡ ፤ ጥርሳቸውንም አፋጩበት ። እርሱም ፤ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት ፤ የእግዚአብሔርን ክብር ፤ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና ፤ «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ» አለ ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፈኑ ፤ ወደ እርሱም ሮጡ ፤ ከከተማም ወደ ውጭ አውጥተው ወገሩት ። የሚወግሩት ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል * በሚሉት ጐበዝ እግር [illegible]

እስጢፋኖስም ፤ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፤ ነፍሴን ተቀበል» ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር ። ተንበርክኮም ፤ «ጌታ ሆይ ፤ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው» ብሎ ከጮኸ በኋላ አንቀላፋ ።

በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ ፤ ከሐዋርያትም በቀር ሁሉ ተበተኑ ።

*    *    *

እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን ፤ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ ።

ራእይ ፪ ፡ ፲ ።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ ፤ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ ።

፩ ጴጥ. ፬ ፡ ፲፱ ።

*    *    *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የእስጢፋኖስ ተቃዋሚዎች በእርሱ ላይ ምንና ምን ክስ አቀረቡ ?
፪ ፤ እስጢፋኖስስ መልስ ሲሰጥ ፤ አባቶቻቸው ዮሴፍን እንደ ሸጡ ፤ ለሙሴም እንዳልታዘዙ ስለምን ያሳስባቸው ነበር ?
፫ ፤ በሞተስ ጊዜ ምን ብሎ ጸለየ ? ይህስ ጸሎት የማንን ጸሎት ያሳስባል ?

ጸሎት ፤ በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ ።
የእውነት አምላክ አቤቱ ፤ ተቤዠተኸኛል ።

መዝ. ፴ (፴፩) ፡ ፭ ።

* ፩ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ፴፱ አሳዳጅ የነበረው ሳውል ደቀ መዝሙር እንደሆነ ይነግራል ።




www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፴፰ ።

# የወንጌል ትምህርት በአረማውያን ።

ከሐዋ. ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።





፩ ፤ የጴጥሮስ ወደ ኢዮጴ መጠራት ።

የሐዋ. ፱ ፡ ፴፪ ፡ ፴፮ - ፵፫ ።

ጴጥሮስ በየሥፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደሚኖሩ ቅዱሳን ደግሞ ወረደ ። በዚያም ሳለ ፤ መልካም ነገር የሞላባት የምትመጸውትም ፤ ጣቢታ የሚሉአት ደቀ መዝሙር ፤ ቅርብ በሆነች በኢዮጴ ከተማ ሞተች ። በዚያም ያሉ ደቀ መዛሙርት ልከው ፤ ሳይዘገይ እንዲመጣላቸው ጴጥሮስን ለመኑት ። ወደዚያም በደረሰ ጊዜ በድንዋ ወደሚገኝበት ሰገነት አወጡት ፤ መበለቶችም ሁሉ እያለቀሱ በበጎነት ያደረገችላቸውን ልብሶች አሳዩት ።

ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አስወጥቶ ተንበረከከና ጸለየ ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ ፤ «ጣቢታ ሆይ ፤ ተነሺ» በማለት እጅዋን ያዘና አስነሣት ። ይህንም ከሰሙት ብዙዎች በጌታ አመኑ ። ጴጥሮስም ፤ ስምዖን ከሚሉት ከአንድ ቍርበት ፋቂ ጋር አያሌ ቀን ተቀመጠ ።

፪ ፤ የጴጥሮስ ወደ ቂሣርያ መጠራት ።

የሐዋ. ፲ ፡ ፩ - ፳፫ ።

በቂሣርያ የሮም ጦር ሠራዊት መቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ ። እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ ሰው ነበረ ።

አንድ ዕለትም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ አየ ፤ ደነገጠም ። መልአኩም ፤ «ቆርኔሌዎስ ሆይ ፤ ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ ። እርሱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት ተቀምጦአል ፤ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል» ብሎ ሄደ ። ቆርኔሌዎስም በመልአክ የተነገረውን ከገለጠላቸው

በኋላ ሦስት ሰዎችን ወደ ኢዮጴ ላከ ።

በነጋውም ወደ ከተማ ሲቀርቡ ፡ ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት እንዲጸልይ ወደ ቤቱ ጣራ ወጣ ። ተርቦም ሊበላ ወደደ ፡ ሲያዘጋጁለት ሳለም ተመሰጠ ፡ በራእይም ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ ። በዚያውም አራዊት ፡ በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት ። «ጴጥሮስ ሆይ ፡ ተነሣና አርደህ ብላ» የሚልም ድምፅ መጣለት ። ጴጥሮስ ግን ፡ «ጌታ ሆይ ፡ አይሆንም ፤ አንዳች ርኵስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና» አለ ። ደግሞም ፡ «እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው» የሚል ድምፅ መጣለት ። ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ ፤ ከዚያም በኋላ ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ ።

ጴጥሮስም ስላየው ራእይ ፡ ምን ይሆን ? ብሎ በልቡ ሲያመነታ ፡ እነሆ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ደርሰው ፡ «ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ አለን ? » ብለው ጠየቁ ። መንፈስ ቅዱስም ጴጥሮስን ፡ «ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል ፤ ተነሥተህ ውረድ ፤ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ» አለው ። ጴጥሮስም ወረደ ፡ ነገሩንም ሰማ ፤ በማግሥቱም ተነሥቶ ከሰዎቹ ጋር ሄደ ። በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ ።

## ፫ ፡ የአሕዛብ ሰዎች መጠመቅ ።

የሐዋ. ፲ ፥ ፳፬ - ፵፰ ።

በነጋውም ወደ ቂሣርያ ገቡ ፤ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና ወዳጆቹን ሰብስቦ ይጠባበቃቸው ነበር ። ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ በፊቱ ወደቀና ሰገደለት ። ጴጥሮስ ግን ፡ «ተነሣ ፤ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ» ብሎ አስነሣውና ገባ ፤ ለተሰበሰቡትም ሰዎች ፡ «አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይገናኝና ይገባ ዘንድ እንዳልተፈቀደ ታውቃላችሁ ። ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኵስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ ፤ ስለዚህም ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ ፤ ታድያ በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ ?» አላቸው ።

ቆርኔሌዎስም ስለ መልአኩ ቃልና በምን ምክንያት እንዳስጠራው ከገለጠ በኋላ ፡ «[illegible] ዘንድ የታዘዝኸውን ሁሉ እንድንሰማ አሁን በእግዚአብሔር ፊት በዚህ አለን» አለው ።

ጴጥሮስም ፡ «እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ ። የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህን ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ ። ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ ፤ እኛም የናዝሬቱ ኢየሱስ በአይሁድ አገር ላደረገው ሁሉ ምስክሮች ነን ። እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት ፤ እግዚአብሔር ግን በሦስተኛው ቀን አስነሣው ። እርሱም ፡ ለሕዝብ እንድንሰብክና ፡ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደሆነ እንድንመሰክር አዘዘን ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአትን ሥርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» አላቸው ።

ጴጥሮስ ገና ይህን ሲናገር ሳለ ፡ ቃሉን በሰሙት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ፤ በሌላ ቋንቋም እየተናገሩ እግዚአብሔርን አከበሩ ። ከተገረዙት ወገን ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ሰዎችም ባልተገረዙት ሰዎች ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ ። በዚያንም ጊዜ ጴጥሮስ ፡ «እነዚህ እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ሊከለክላቸው የሚችል ማን ነው ? » አለ ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው ።

## ፬ ፡ ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ጥምቀት መስማማት ።

የሐዋ. ፲፩ ፥ ፩ - ፲፰ ።

ጴጥሮስም ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ ሐዋርያትና ሌሎች ወንድሞች ከእርሱ ጋር ሲከራከሩ ፡ «ወዳልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህ » አሉት ። ጴጥሮስ ግ
ከመጀመሪያ ጀምሮ በተራ ነገሩን ሁሉ
ሲገልጥ ፡ «እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ ላመንነው ለእኛ እንደ ሰጠን ያን
ስጦታ ለእነርሱ ከሰጠ ፡ እግዚአብሔርን
ለመከልከል የምችል እኔ ማን ነኝ ?» አላ
ቸው ። እነርሱም ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ፡ «እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው» እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ ።

* * *

ኢየሱስ አለ ፤ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ፡ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ። ማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱ ፡ ፳ ።

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል ። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ፡ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ፡ ወንድም ሴትም የለም ፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና ። ገላ. ፫ ፥ ፳፮ - ፳፰ ።

* * *

ጥያቄ፡ ፩ ፡ ቆርኔሌዎስ በራእይ ምን አየ ? ምንስ ትእዛዝ ተሰጠው ?
፪ ፡ ጴጥሮስ ምን ራእይ አየ ? ከራእዩስ ምን ተማረ ?
፫ ፡ ቆርኔሌዎስና ወዳጆቹ ቃሉን ሲሰሙ ምን ተደረገ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ አሕዛብ ያመስግኑህ ፡
አሕዛብ ሁሉ ያመስግኑህ ። . . .
እግዚአብሔር ይባርከናል ፡
የምድርም ዳርቻ ሁሉ ይፈሩታል ።
መዝ. ፷፯ (፷፮) ፥ ፭ ፡ ፯ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፴፱ ።

# የአንጾኪያና የኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናት ።

የሐዋ. ፲፩ ፡ ፲፱ - ፲፪ ፡ ፳፭ ።

## ፩ ፤ በአንጾኪያም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች ።

የሐዋ. ፲፩ ፡ ፲፱ - ፴ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ።

በእስጢፋኖስ ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት ፤ ቃሉን ለአይሁድ ብቻ እየመሰከሩ እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ ። ከእነርሱ የሆኑ የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች ግን ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል ለግሪክ ሰዎች ሰበኩ ። የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረች ፤ ከግሪኮችም እጅግ ብዙዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ ።

በአንጾኪያ ብዙ ግሪኮች ቃሉን ተቀብለው በክርስቶስ እንዳመኑ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በተወራ ጊዜ በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላኩ ። እርሱም በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጸጋ አይቶ ደስ አለው ፤ በጌታ ጸንተው እንዲኖሩ የሙሉ ልባቸው ፈቃድ እንዲሆን ሁሉንም መከራቸው ፤ ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበርና ። ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ ።

በርናባስም ይህን ባየ ጊዜ ፡ ከአሳዳጅነት ወደ ክርስቶስ ተመልሶ ከደማስቆና



ከኢየሩሳሌም ወደ ጠርሴስ የተሰደደውን ሳውልን ለመፈለግ ሄደ ። ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው ፤ አንድ ዓመትም ሙሉ በቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ ብዙ ሕዝብን አስተማሩ ። ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ ክርስቲያን የተባሉ በአንጾኪያ ነበረ ።

በዚያን ጊዜ አጋቦስ የተባለው ነቢይ ፡ ታላቅ ራብ እንደሚሆን በመንፈስ አመለከተ ። የአንጾኪያ ደቀ መዛሙርትም ፡ እንደ ችሎታ እንደ ችሎታቸው አዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ሊልኩ ወሰኑ ። እንዲሁም አድርገው በበርናባስና በሳውል እጅ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሰደዱት ።

## ፪ ፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ጸናች።

የሐዋ. ፲፪ ፡ ፩ - ፳፭ ።

በዚያን ዘመን ሄሮድስ የተባለ ፡ የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ በኢየሩሳሌም ነግሦ ነበር ። እርሱም ቤተ ክርስቲያንን ለመቃወም ወዶ ፤ የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደለ ። ይህም አይሁድን ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጴጥሮስን ደግሞ አስያዘና ወደ ወኅኒ አስገባው ። ጊዜውም የፋሲካ ወራት ነበረና በዓሉ ካለፈ በኋላ ወደ ሕዝብ ሊያወጣው አስቦ ፡ በጥብቅ እንዲጠብቁት ለአራት ክፍል ጭፍራ አሳልፎ ሰጠው ። እንዲህ ባለ ሁኔታም ጴጥሮስ ሲጠበቅ በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር ።

ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታሥሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር ፤ ጠባቂዎችም በወኅኒው ደጅ ሆነው ይጠብቁ ነበር ።

እነሆም የጌታ መልአክ ቀረበ ፤ በወኅኒው ውስጥም ብርሃን በራ ። መልአኩም ጴጥሮስን ነክቶ አነቃውና ፡ «ፈጥነህ ተነሣ» አለው ። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ ። መልአኩም ፡ «ታጠቅና ጫማህን አስገባ» አለው ፤ እንዲሁም አድርጎ መልአኩን ተከተለ ። ይህንም ሲያደርግ ራእይን የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ እውነት መሆኑን አላወቀም ። የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ከሚያወጣው ከብረቱ መዝጊያ ደረሱ ፤ መዝጊያውም ዐውቆ ተከፈተላቸው ፤ ወጥተውም ጥቂት እንደ ሄዱ መልአኩ ከእርሱ ተለየ ። ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ ፡ «ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንዳዳነኝ አሁን በእውነት ዐወቅሁ» አለ ።

ይህንም እንዳስተዋለ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ፡ ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ ። የደጁንም መዝጊያ ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የሚሉአት አንዲት ገረድ ልትሰማ ቀረበች ። የጴጥሮስንም ድምፅ ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ደጁን ሳትከፍት ወደ ቤት ተመልሳ ፡ «ጴጥሮስ በደጅ ቆሞአል» ብላ አወራች ። እነርሱም ፡ «አብደሻል» አሉአት ። ጴጥሮስ ግን ማንኳኳቱን ደጋገመ ፤ ከፍተውም አዩትና ተገረሙ ። እርሱም ዝም እንዲሉ በእጁ በመጥቀስ ጌታ ከወኅኒ እንዴት እንዳወጣው ተርኮ ፡ «ይህን ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሩ» አላቸው ። ከዚያም ወጥቶ ወደ ሌላ ሥፍራ ሄደ ።

በነጋም ጊዜ ጭፍራዎች ከእንቅልፍ ሲነቁ ፡ «ጴጥሮስን ምን አግኝቶት ይሆን ?» ብለው ታወኩ ። ሄሮድስም አስፈልጎ ባጣው ጊዜ ጠባቂዎቹን መረመረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዲገድሉአቸውም አዘዘ ። ከይሁዳም ተነሥቶ ወደ ቂሣርያ ሄደ ።

ከሲዶና ሰዎችም ጋር ተጣልቶ ነበር ፤ እነርሱም ፤ አገራቸው ከሄሮድስ አገር ምግብ ያገኝ ነበርና ወደ እርሱ መጥተው ዕርቅ ለመኑ ። እንዲገናኙ በተቀጠሩበት ቀንም ሄሮድስ ልብሰ መንግሥቱን ለበሰና በዙፋን ተቀምጦ ተናገራቸው ። ሕዝቡም፡ «ይህ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው እንጂ የሰው አይደለም» ብለው ጮኹ ። እርሱም ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው ፤ በትልም ተበልቶ ሞተ ። የእግዚአብሔርም ቃል ያድግና ይበዛ ነበር ። በርናባስና ሳውልም አገልግሎታቸውን በፈጸሙ ጊዜ ፤ ማርቆስን ከእነርሱ ጋር ይዘው ወደ አንጾኪያ ተመለሱ ።

* * *

በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ ። ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን ።

ኤፌ. ፬ ፣ ፬ - ፯ ።

ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል ፤ ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር ።

፩ ጴጥ. ፬ ፣ ፲፭ ፣ ፲፮ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ የተላከ ማን ነበረ ? በዚያስ እንዲረዳው ማንን አመጣ ?

፪ ፤ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስለ ጌታው መጀመሪያ የሞተ ማን ነበረ ?

፫ ፤ ጴጥሮስ በወኅኒ ሲጠበቅ ሳለ በቤተ ክርስቲያን ምን ይደረግ ነበር ? (የሐዋ. ፲፪ ፣ ፳ ።)

ጸሎት ፤ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፤ የእግዚአብሔርም ፍቅር ፤ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን ። አሜን ። ፪ ቆሮ. ፲፫ ፣ ፲፬ ።





ምዕራፍ ፵ ።

## ጀግናው ጌዴዎን ።

መሳ. ፮ - ፰ ።

(ከም. ፲፫ የሚከተል ነው ።)

### ፩ ፤ የመሳፍንት ዘመን ።

መሳ. ፪ ፣ ፩ - ፲፱ ።

ከኢያሱ ጋር የነበሩ ሽማግሌዎች ከሞቱ በኋላ እስራኤል በኣሊም የተባሉትን የከነዓንን አማልክት ተከተሉ ፤ አመለኳቸውም ። እግዚአብሔርም ፤ «እኔ ከእናንተ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳን ለዘላለም አላፈርስም ፤ እናንተም መሠዊያቸውን አፍርሱ እንጂ በዚህች ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አታድርጉ አልሁ ። እናንተ ግን አልሰማችሁም ፤ ስለዚህም የቀሩት ሕዝቦች ያስጨንቋችኋል» አላቸው ። ከዚያም ወዲያ ጠላቶቻቸውን ሊቋቋሙ አልቻሉም ፤ እጅግም ተጨነቁ ። እግዚአብሔርም በመጨነቃቸው አዝኖ መሳፍንትን እያስነሣ በእያንዳንዱ መስፍን ዘመን ከጠላቶቻቸው እጅ ያድናቸው ነበር ። መስፍኑ ሲሞት ግን ሌሎችን አማልክት ሊከተሉ ወዲያውኑ ይመለሱ ነበር ። ካስጨነቋቸው ጠላቶች አንዱ ምድያም ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ከምድያም እንዲያድናቸው ያስነሣው መስፍን ጌዴዎን ነበረ ።

### ፪ ፤ የጌዴዎን መጠራት ።

መሳ. ፮ ፣ ፩ - ፴፪ ።

የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ ፤ እግዚአብሔርም በምድያም እጅ ሰባት ዓመት አሳልፎ ሰጣቸው ። በየዓመቱም እስራኤል ዘር በዘሩ ጊዜ ምድ



www.ethiopianorthodox.org

ያማውያንና ረዳቶቻቸው በብዛት እንደ አንበጣ ሆነው ግመሎቻቸውንና ድንኳኖ ቻቸውን ይዘው ይመጡና የእህላቸውን ቡቃያ ያጠፉባቸው ነበር ። ከዚህም የተ ነሣ እስራኤላውያን እጅግ ተጠቁ ፤ በተራ ራም ላይ ጕድጓድና ዋሻ እያበጁ ይሸሸጉ ነበር ። ጭንቀታቸውም ስለ በዛ ወደ እግ ዚአብሔር ጮኹ ።

በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ከምናሴ ነገድ ለሆነ ለኢዮአስ በሆ ነችው ዛፍ ሥር ተቀመጠ ፤ የኢዮአስም ልጅ ጌዴዎን ከምድያማውያን ለመሸሸግ በወይን መጥመቂያው ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር ።

የእግዚአብሔርም መልአክ ለእርሱ ተገ ልጦ ፡ «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው ፡ እግዚአ ብሔር ከአንተ ጋር ነው» አለው ። ጌዴዎ ንም ፡ «ጌታዬ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን ? አባቶቻችንስ ፡ ከግብፅ አውጥቶናል ብለው ይነግሩን የነበረ ተአምራቱ ወዴት አለ ?» አለው ። እግዚአብሔርም ፡ «በዚህ ኊልበትህ ሂድ ፡ ከምድያምም እጅ እስራ ኤልን አድን ፤ እነሆ ልኬሃለሁ» አለው ።

ጌዴዎንም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ እስራኤልን በምን አድናለሁ ? ወገኔ ከምናሴ ነገድ ሁሉ ይልቅ የተጠቃ ነው ፤ እኔም በአባቴ ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ» አለው ። እግዚአ ብሔርም ፡ «በእርግጥ ከአንተ ጋር እሆና ለሁ ፤ ምድያምንም እንደ አንድ ሰው ትመ ታለህ» አለው ። ጌዴዎንም ሄዶ ለእግዚአ ብሔር መልአክ ቍርባንን አመጣ ፤ የእግ ዚአብሔርም መልአክ ፡ «በዚህ ድንጋይ ላይ አኑር» አለና እጁን ዘርግቶ በያዘው በትር ጫፍ ቍርባኑን አስነካ ። እሳትም ከድንጋዩ ውስጥ ወጥቶ ቍርባኑን በላ ። የእግዚአብሔርም መልአክ ከዓይኑ ተሠ ወረ ። ጌዴዎንም ፡ «የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና ወዮልኝ» ብሎ እጅግ ፈራ ፡ እግዚአብሔርም ፡ «ሰላም ለአንተ ይሁን ፤ አትፍራ አትሞ ትም» አለው ። ጌዴዎንም ለእግዚአብ ሔር መሠዊያ ሠርቶ ስሙን ፡ «እግዚአብ ሔር ሰላም» ብሎ ጠራው ።

በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎ ንን ፡ «የአባትህ የሆነውን የበኣልን መሠ ዊያ አፍርስ ፤ በዚያም ኮረብታ ላይ ለአም ላክህ ለእግዚአብሔር መሠዊያን አሳም ረህ ሥራ ፡ የአባትህ የሆነውንም ሁለተኛ ውን የሰባት ዓመት በሬ ውሰድና የሚቃ ጠል መሥዋዕት አድርገህ ሠዋ» አለው ። ጌዴዎንም የአባቱን ቤተ ሰዎችና የከተማ ውን ሰዎች ስለ ፈራ ይህን በቀን ማድረግ አልቻለም ፡ ነገር ግን በሌሊት አደረገው ።

በማግሥቱም የከተማው ሰዎች ተነሥ ተው እነሆ ፡ የበኣል መሠዊያ ፈርሶ ፡ በተ ሠራውም መሠዊያ ላይ ሁለተኛው በሬ ተሠውቶ አገኙት ። ነገሩንም በመረመሩ ጊዜ ፡ «ይህን ነገር ያደረገ ጌዴዎን ነው» አሉ ። የጌዴዎንንም አባት ኢዮአስን ፡ «የበኣልን መሠዊያ አፍርሶአልና እንዲ ሞት ልጅህን አውጣ» አሉት ። ኢዮአ ስም ፡ «ለበኣል ትምዋገቱለታላችሁን ? ወይስ እርሱን ታድናላችሁን ? እርሱ አም ላክ ከሆነ መሠዊያውን ካፈረሰው ጋር ለራሱ ይምዋገት» አላቸው ። በዚያም ቀን ጌዴዎንን ይሩበኣል ብሎ ጠራው ፤ ትርጓ ሜውም በኣል ይምዋገት ማለት ነው ።

## ፫ ፡ የጌዴዎን ጭፍራ ።

መሳ. ፮ ፡ ፴፫ - ፯ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ።

ምድያማውያንም መጥተው በኢይዝራ ኤል ሸለቆ ሠፈሩ ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በጌዴዎን አደረበት ፡ ጌዴዎ ንም ቀንደ መለከቱን ነፋ ፤ ወደ ምናሴና ወደ አሴርም ወደ ዛብሎንና ወደ ንፍታሌ ምም ላከ ፤ ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰልፈኞችም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ ።

ጌዴዎንም እግዚአብሔርን ፡ «እንደ ተናገርህ እስራኤልን በእኔ እጅ ታድን እን ደሆነ ፡ እነሆ ፡ በአውድማው ላይ የተባ ዘተ የበግ ጠጕር አኖራለሁ ፤ በጠጕሩ ብቻ ጠል ሆኖ ምድሩ ሁሉ ደረቅ ቢሆን እንደ ተናገርህ እስራኤልን በእኔ እጅ እን ድታድናቸው ዐውቃለሁ» አለ ። በነጋ ውም ማልዶ ተነሣ ፡ ጠጕሩንም ጨመ ቀው ፡ ከጠጕሩም የተጨመቀው ጠል ቆሬ ሙሉ ውኃ ሆነ ። ጌዴዎንም እግዚአብሔ ርን ፡ «እኔ ይህን አንድ ጊዜ ስናገር አትቈ ጣኝ ፤ አሁንም ጠጕሩ ብቻ ደረቅ ሆኖ በም ድሩ ሁሉ ጠል ይሁን» አለው ። እግዚአብ ሔርም በዚያ ሌሊት እንዲሁ አደረገ ፡ ጠጕሩ ብቻ ደረቅ ሆኖ በምድሩ ሁሉ ጠል ነበረ ።

እግዚአብሔርም ፡ «ከአንተ ጋር ያለው ሕዝብ በዝቶአል ፤ ስለዚህ እስራኤል ፡ እጄ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይብኝ ምድያ ምን በእጃቸው አሳልፌ አልሰጥም ። አሁ ንም ፡- የፈራ የደነገጠም ተነሥቶ ይመለስ ብለህ አውጅ» አለው ። ከሕዝቡም ሃያ ሁለት ሺህ ተመለሱ ።

እግዚአብሔርም ጌዴዎንን ፡ «ሕዝቡ ገና ብዙ ነው ፤ ወደ ውኃ አውርዳቸው ፡ በዚያም እፈትናቸዋለሁ» አለው ። ጌዴዎ ንም ወደ ውኃ አወረዳቸው ። እግዚአብሔ ርም ፡ «ውሻ እንደሚጠጣ ውኃ በምላሱ የሚጠጣውን ሁሉ ፡ እርሱን ለብቻው አድ ርገው ፤ እንዲሁም ሊጠጣ በጕልበቱ የሚ ንበረከከውን ሁሉ ለብቻው አድርገው» አለው ። በቍጥርም የበዛው እየተንበረከከ ጐንበስ ብሎ ሲጠጣ ፡ በእጃቸው እየጨ ለፉ ውኃ የጠጡት ቍጥር ሦስት መቶ ብ[...] ነበረ ። እግዚአብሔርም ጌዴዎንን ፡ «በ[...] ጃቸው ውኃ በጠጡት በሦስት መቶ[...] ሰዎች አድናችኋለሁ ፤ የቀሩትም ወደ ሥ[...] ራቸው ይመለሱ» አለው ። ጌዴዎንም እ[...] ርሱን ሁሉ አሰናብቶ ሦስቱን መቶ ብ[...] በእርሱ ዘንድ አስቀረ ፤ የምድያምም ሠፈ[...] ከበታቹ በሸለቆው ዳር ነበረ ፤ ግመሎቻ[...] ውም በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ የማይቈ[...] ጠሩ ነበሩ ።

## ፬ ፡ የጌዴዎን ድል ።

መሳ. ፯ ፡ ፱ - ፳፭ ፡ ፰ ፡ ፬ ፡ ፲ - ፲፱ ፡ ፳፰[...]

በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ፡ «በእጅ[...] አሳልፌ ሰጥቻቸዋለሁና ተነሥተህ ወ[...] ጠላት ሠፈር ውረድ ። የፈራህ እንደሆነ[...] ሎሌህ ፉራ ከአንተ ጋር ይሂድ ፡ የሚናገሩ[...] ትንም ትሰማለህ ፤ እጅህም ትበረታለች» አለው ። እርሱና ፉራም ወረዱ ፤ በደረሱም ጊዜ አንድ ሰው ሕልሙን ለባልንጀራው ሲያጫውት ፡ «እነሆ ሕልም አለምሁ ፤ እነ[...] ሆም አንዲት የገብስ እንጐቻ ወደ እኛ ሠፈር ተንከባልላ ወረደች ፡ ወደ ድንኳ ኑም ደርሳ እስኪወድቅ ድረስ መታችው ፡ ገለበጠችውም» ይል ነበር ። ባልንጀራ ውም መልሶ ፡ «ይህ ነገር ከእስራኤል ሰው ከኢዮአስ ልጅ ከጌዴዎን ሰይፍ በቀር ሌላ አይደለም ፤ እግዚአብሔርም ምድያምንና ሠራዊቱን ሁሉ በእጁ አሳልፎ ሰጥቶ አል» አለው ።

ጌዴዎንም ሕልሙንና ትርጓሜውን በሰማ ጊዜ ሰገደ ። ወደ እስራኤል ሠፈርም ተመልሶ ፡ «እግዚአብሔር ምድያምን በእ ጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአልና ተነሡ !» አለ። ሦስቱንም መቶ ሰዎች በሦስት ወገን ከፈ ላቸው ፤ በሁሉም እጅ ቀንደ መለከትና ባዶ ማሰሮ ፡ በማሰሮውም ውስጥ ችቦ ሰጠ ። እርሱም ፡ «እኔን ተመልከቱ ፤ ወደ


www.ethiopianorthodox.org

ሠፈሩ ዳርቻ በደረስሁ ጊዜ ፡ እኔ ከእኔም
ጋር ያሉት ሁሉ ቀንደ መለከት ስንነፋ ፡
እናንተ ደግሞ በሠፈሩ ዙሪያ ሁሉ ቀንደ
መለከታችሁን እየነፋችሁ ፦ ለእግዚአብ
ሔርና ለጌዴዎን እያላችሁ ጩኹ» አላ
ቸው ።

ይህን ካለ በኋላም ከመቶ ሰዎች ጋር
ወደ ጠላት ሠፈር ዳርቻ በሌሊት መጣ ፡
ቀንደ መለከቶችንም ነፉ ፡ በእጆቻቸው
የዙአቸውንም ማሰሮች ሰባበሩ ። ሦስ
ቱም ወገኖች ቀንደ መለከታቸውን ነፉ ፡
ማሰሮችንም ሰባበሩ ፡ በግራ እጃቸውም
ችቦችን ፡ በቀኝ እጃቸውም ቀንደ መለከቶ
ችን ይዘው እየነፉ ፡ «የእግዚአብሔርና
የጌዴዎን ሰይፍ» ብለው ጮኹ ። ሁሉም
በየቦታቸው በሠፈሩ ዙሪያ ቆሙ ፡ የምድያ
ምም ሠራዊት ሁሉ ደንግጠው ሮጡ ፡ እየ
ጮኹም በሰይፍም እርስ በርሳቸው እየተ
መታቱ ወደ ዮርዳኖስ በሚያስሄደው መን
ገድ ሸሹ ። የእስራኤልም ሰዎች ከንፍታሌ
ምና ከአሴር ከምናሴም ሁሉ ተሰብስበው
ምድያምን አሳደዱ ። የኤፍሬም ሰዎችም
ተሰብስበው በዮርዳኖስ ምድያማውያንን
ተገናኙ ፡ መኳንንቶቻቸውንም ገደሉ ። ጌዴ
ዎንና ሦስቱ መቶ ሰዎችም ምንም ቢደ
ክሙ እስከ ዮርዳኖስ ማዶ እያሳደዱ ሁለ
ቱን የምድያምን ነገሥታት ይዘው ገደሉ
አቸው ። ምድያምም በእስራኤል ፊት ተዋ
ረደ ፤ በጌዴዎንም ዕድሜ ምድሪቱ ዐርባ
ዓመት ዐረፈች ።

* * *

በብዙ ወይም በጥቂት ማዳን እግዚአብሔርን አያስቸግረ
ውም ።

፩ ሳሙ. ፲፬ ፡ ፮ ።

እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር
መረጠ ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለ
ምን ደካማ ነገር መረጠ ፡ . . . ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአ
ብሔር ፊት እንዳይመካ ።

፩ ቆሮ. ፩ ፡ ፳፯ - ፳፱ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ እስራኤላውያን በጭንቀት የወደቁ በምን ምክንያት ነበረ ?
፪ ፡ ጌዴዎን በተጠራ ጊዜ ምን ያደርግ ነበር ?
፫ ፡ ከጌዴዎን ጋር ለሰልፍ የሄዱ ስንት ነበሩ ? በእጃቸውስ ምን
ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም ፤
. . . በአንተ ታምነናልና . . . . እርዳን ።

፪ ዜና. ፲፬ ፡ ፲፩ ።



ምዕራፍ ፴፩ ።

# ኃያሉ ሶምሶን ።

መሳ. ፲፫ - ፲፮ ።



## ፩ ፤ የሶምሶን ልደት ።

መሳ. ፲፫ ፡ ፩ - ፳፭ ።

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት
እንደገና ክፉ ሥራ ሠሩ ፤ እግዚአብሔርም
በፍልስጥኤማውያን እጅ አሰልፎ ሰጣ
ቸው ።

ከዳን ወገን የሆነ ማኑሄ የሚባል የጾርዓ
ሰው ነበረ ፤ ሚስቱም መካን ነበረች ፡
ልጅም አልነበራትም ። የእግዚአብሔርም
መልአክ ለሴቲቱ ተገለጠ ፡ «እነሆ ወንድ
ልጅ ትወልጃለሽ ። ልጁም ለእግዚአብ
ሔር የተለየ ናዝራዊ* ይሆናልና በራሱ
ላይ ምላጭ አይድረስበት ፡ እርሱም እስራ
ኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን
ይጀምራል» አላት ።

ሴቲቱም ወደ ባልዋ መጥታ ሁሉን ነገ
ረችው ። ማኑሄም ፡ «ጌታ ሆይ ፡ የላክኸው
የእግዚአብሔር ሰው ፡ እባክህ እንደገና
ይምጣልን» ብሎ ለመነ ። የእግዚአብሔ
ርም መልአክ እንደገና ወደ ሴቲቱ መጣ ።
እርስዋም ሩጣ ለባልዋ ተናገረችና አስከት
ላው መጣች ። እርሱም ፡ «ከዚህች ሴት
ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህን ? » አለው ፤
እርሱም ፡ «እኔ ነኝ» አለ ። ማኑሄም ፡ «ነገ
ርህ በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን
ነው ? » አለው ። የእግዚአብሔርም መል
አክ ፡ «ስሜ ድንቅ ነውና ለምን ትጠይቃ
ለህ ? » ብሎ መለሰ ፡ ተአምራትንም አድ
ርጎ ፡ ማኑሄና ሚስቱ ባቀረቡት በመሥዋ
ዕቱ ነበልባል ውስጥ ዐረገ ። እነርሱም በግ
ምባራቸው ተደፉ ።

ማኑሄም ሚስቱን ፡ «እግዚአብሔርን
አይተናልና እንሞታለን» አላት ። እርስ
ዋም ፡ «እግዚአብሔርስ ሊገድለን ቢወድ
ኖሮ እንዲህ ያለ ነገር ባላስታወቀንም
ነበር» አለችው ። በጊዜውም ልጅ ወለ
ደች ፡ ሶምሶንም ብላ ጠራችው ። ልጁም
አደገ ፡ እግዚአብሔርም ባረከው ፤ የእግዚ
አብሔርም መንፈስ በዳን ሠፈር ውስጥ
ሊያነቃቃው ጀመረ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ ፡ የሶምሶን ኃይል ።

መሳ. ፲፬ ፥ ፩ - ፲፮ ፥ ፫ ።

በዚያን ዘመን ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል ላይ ይገዙ ነበርና እስራኤል ሁሉ ይፈሩአቸው ነበር ። ሶምሶን ግን አንዲት ፍልስጥኤማዊት አግብቶ ከከተማዋ ሰዎች ጋር በመጣላት ብዙዎችን ገደለ ፡ ተመልሶም በአንድ ዋሻ ውስጥ ተሸሽጎ ተቀመጠ ።

በዚያን ጊዜ ፍልስጥኤማውያን በይሁዳ ወዳለው ወደ ሌሒ ወጥተው ሠፈሩ ፡ ለይሁዳ ሰዎችም ፡ «ሶምሶንን ልናሥር ፡ እንዳደረገብንም ልናደርግበት መጥተናል» አሉ ። ከይሁዳም ሰዎች ሦስት ሺህ ወደ ሶምሶን ሄደው ፡ «ገዦቻችን ፍልስጥኤማውያን እንደሆኑ አታውቅምን ? ያደረግህብን ይህ ምንድር ነው ? አሥረን በእጃቸው እንሰጥሃለን» አሉት ። በሁለትም አዲስ ገመድ አሥረው አወጡት ።

ወደ ሌሒ ባመጡትም ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እልል እያሉ ተገናኙት ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በኃይል ወረደበት ፤ ክንዱም የታሠረበት ገመድ በእሳት እንደ ተበላ ፈትል ሆነ ፡ ከእጁም ወደቀ ። አዲስ የአህያ መንጋጋም አገኘ ፡ በእርሱም አንድ ሺህ ሰው ገደለ ። ከዚህም በኋላ እጅግ ተጠምቶ ፡ «አንተ ይህችን ማዳን በባሪያህ እጅ ሰጥተሃል ፤ አሁንም በጥም እሞታለሁ» ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ። እግዚአብሔርም በሌሒ ያለውን ዐዘቅት ሰነጠቀ ፡ ከእርሱም ውኃ ወጣ ፤ ሶምሶንም ጠጣ ፡ ተጠናከረም ። ያንንም ቦታ ዓይን ሀቆሬ ብሎ ጠራው ፤ ይህም ማለት ፡ የጮኸው ሰው ምንጭ ማለት ነው ።

ሶምሶንም ወደ ፍልስጥኤማውያን አገር ወደ ጋዛ ሄደ ፤ በዚያም ጋለሞታ ሴት አይቶ ወደ እርስዋ ገባ ። የጋዛ ሰዎችም ወደ ከተማ እንደ ገባ ሰምተው ፡ ማለዳ ሲወጣ እንገድለዋለን በማለት በከተማዪቱ በር ሌሊቱን ሁሉ ሸመቁበት ። ሶምሶንም በእኩለ ሌሊት ተነሥቶ የከተማዪቱን በር መዝጊያ ያዘ ፡ ነቅሎም በትከሻው ላይ አድርጎ በኬብሮን ፊት ወዳለው ተራራ ራስ ላይ ወጣ ፡ በዚያም ጣለው ።

## ፫ ፡ የሶምሶን [illegible] ድቀት ።

መሳ. ፲፮ ፥ ፬ - [illegible]

ከዚህም በኋላ ደግሞ [illegible] ሴትን ወደደ ። የፍልስጥኤማውያንም መኳንንት ወደ እርስዋ መጥተው ፡ «እርሱን ሸንግለሽ በእርሱ ያለ ታላቅ ኃይል በምን እንደ ሆነ ፡ የምናሸንፈውም በምን እንደሆነ ዕወቂ ፡ እያንዳንዳችንም ሺህ አንድ መቶ ብር እንሰጥሻለን» አሉአት ።

ደሊላም ሶምሶንን ፡ «ታላቅ ኃይልህ በምን እንደሆነ ፡ የምትታሠርበትስ ምን እንደሆነ እባክህ ንገረኝ» አለችው ። እርሱም ፡ «በሰባት ባልደረቀ በእርጥብ ጠፍር ቢያሥሩኝ እደክማለሁ» አላት ። ደሊላም በሰባት እርጥብ ጠፍር አሠረችው ፤ በጓዳም ውስጥ ሰዎች ተደብቀው ነበር ። እርስዋም ፡ «ሶምሶን ሆይ ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ» አለችው ። እርሱም ጠፍሩን በጣጠሰው ።

ደሊላም ፡ «አታለልኸኝ» በማለት ብትወቅሰውና ብትጠይቀው ፡ እንደገና ደግሞ ሁለት ጊዜ በሐሰት አታለላት ። ደሊላም ፡ «እወድሻለሁ እንዴት ትለኛለህ ? » ብላ ዕለት ዕለት ነዘነዘችው ፤ ነፍሱም ተጨነቀች ። መልሶም ፡ «ለእግዚአብሔር የተለየሁ ነኝና ከቶ በራሴ ላይ ምላጭ አልደረሰም » ብሎ የልቡን ገለጠላት ። ከዚህም በኋላ በጕልበትዋ ላይ አስተኝታ የተጐነጐነ ጠጕሩን አስላጨችው ፡ እንደገናም ፡ «ሶምሶን ሆይ ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ» አለችው ። ከእንቅልፉም ነቅቶ ፡ እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው ሳያውቅ ፤ እንደ ሌላ ጊዜ ሁሉ አደርጋለሁ ብሎ ተነሣ ። ነገር ግን ፍልስጥኤማውያን ይዘው ዓይኖቹን አወጡ ፤ ወደ ጋዛም አምጥተው አሠሩት ፤ በግዞትም ሆኖ እህል ይፈጭ ነበር ። የተላጨውም ጠጕሩ ሊያድግ ጀመረ ።

## ፬ ፡ የሶምሶን ሞት ።

መሳ. ፲፮ ፥ ፳፫ - ፴፩ ።

የፍልስጥኤማውያን መኳንንትም በሶምሶን መታሠር ደስ ብሎአቸው ለአምላካቸው ለዳጎን መሥዋዕትን ሊሠዉ ተሰበሰቡ ። ሕዝቡም ሁሉ ፡ «አምላካችን ዳጎን ጠላታችንን በእጃችን አሳልፎ ሰጠን» እያሉ አምላካቸውን አመሰገኑ ። ልባቸውም ደስ ባለው ጊዜ ፡ «በፊታችን እንዲጫወት ሶምሶንን ጥሩት» አሉ ። ሶምሶንንም አስመጡት ፡ በፊታቸውም ተጫወተ ፡ ተዘባበቱበትም ።

ሶምሶንም እጁን የያዘውን ብላቴና ፡ «ቤቱን የደገፉትን ምሰሶች እጠጋባቸው ዘንድ አስይዘኝ» አለው ። በዚያም ቤት ሰዎች ሞልተውበት ነበር ፤ በሰገነቱም ላይ ሲጫወት ይመለከቱት የነበሩ ሦስት ሺህ ያህሉ ነበሩ ። ሶምሶንም ፡ «እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አስበኝ ፡ አበርታኝም» ብሎ እግዚአብሔርን ጠራ ። አንዱንም ምሰሶ በቀኝ እጁ ፡ አንዱንም በግራ እጁ ይዞ በሙሉ ኃይሉ ገፋቸው ። ቤቱም በውስጡ በነበሩት መኳንንትና ሕዝብ ላይ ወደቀ ፤ በሞቱም የገደላቸው በሕይወት ሳለ ከገደላቸው በዙ ። በእስራኤል ላይ ሃያ ዓመት ከፈረደ በኋላ በዚህ ጊዜ ሞተ ፡ ቤተሰቦቹም ወርደው አመጡት ፡ በአባቱም መቃብር ቀበሩት ።

* * *

ልጄ ሆይ ፡ ልብህን ስጠኝ ፤
ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ ።
ጋለሞታ ሴት የጠለቀች ዐዘቅት ናትና ፡
ሌላዪቱም ሴት የጠበበች ጕድጓድ ናትና ።
እንደ ሌባ ታደባለች ፡
ወስላቶችንም በሰው ልጆች መካከል ታበዛለች ።

ምሳሌ ፳፫ ፥ ፳፮ - ፳፰ ።

እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ስትሆኑ እርሱ ከእናንተ ጋር ነው ፤ ብትፈልጉትም ይገኝላችኋል ፤ ብትተዉት ግን ይተዋችኋል ።

፪ ዜና. ፲፭ ፥ ፪ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ስለምትወልደው ልጅ ለማኑሄ ሚስት ምን ተባለ ?
፪ ፤ ለሶምሶን የተሰጠው ኃይል ምን በማድረጉ ታየ ?
፫ ፤ ወደ ውድቀት የደረሰውስ ከምን ኃጢአት ራሱን ባለመጠበቁ ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ እንዳላፍር ልቤ በሥርዓትህ የቀና ይሁን ።

መዝ. ፩፻፲፰ (፩፻፲፱) ፥ ፹ ።

* ናዝራዊ ተብሎ ለእግዚአብሔር ስለ ተለየ ሰው የምናነበው በዘኍ. ም. ፮ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፵፪ ።

# ሞዓባዊት ሩት ።

## መጽሐፈ ሩት ።

### ፥ ኑኃሚንና ምራትዋ ሩት ።

ሩት ፩ ፥ ፩ - ፳፪ ።

ሳፍንት በእስራኤል ይፈርዱበት በነበ
ው በዚያ ክፉ ዘመን በአገሩ ላይ ራብ
ነ ። አቤሜሌክ የተባለውም ቤተልሔ
ዊ ሚስቱን ኑኃሚንንና ሁለት ልጆቹን
ዞ ወደ ሞዓብ ሄደ በዚያም ተቀመጠ ።
ዚያም ሳሉ አቤሜሌክ ሞተ ። መሐሎንና
ሌዎን የተባሉ ልጆቹም ከሞዓባውያን
ዮች ሩትና ዖርፋ የተባሉትን አገቡ ።
ጆችንም ሳይወልዱ እንደ አባታቸው
ዚያው አገር ሞቱ ። ኑኃሚንም ሁለት
ጆችዋንና ባልዋን አጥታ በኀዘን ስት
ር ሳለ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንጀራ
ዶ ሰጠ ሰማችና ወደ ቤተልሔም ለመ
ለስ ከምራቶችዋ ጋር ተነሣች ።

መንገድም ሲጀምሩ ፡ «ልጆቼ ሆይ ፡ ወደ እናቶቻችሁ ተመለሱ ፤ እግዚአብሔር በየባላችሁ ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ» ብላ ሳመቻቸው ። ዖርፋም በብዙ እንባ ከእርስዋ ተመለሰች ፤ ሩት ግን ተጠግታ ፡ «ወደ ምትሄጅበት እሄዳለሁና ፡ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ አታስቸግሪኝ ። ሕዝብሽ ሕዝቤ ፡ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል ፡ ከሞትም በቀር አንቺንና እኔን አንዳች አይለየን» አለቻት ። ኑኃሚንም ፡ ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቈረጠች ባየች ጊዜ ከማባበሏ ዝም አለች ፤ ይዛትም ሄደች ።

የገብስ መከር በሚታጨድበት ወራትም ወደ ቤተልሔም ደረሱ ። የከተማዪቱም ሰዎች ፡ «ይህች ኑኃሚን ናትን ? » እያሉ ተንጫጩ ። ነገር ግን ኑኃሚን ማለት ደስታ ማለት ስለሆነ ፡ «ሁሉን የሚችል አምላክ አስጨንቆኝ መርሮኛልና ማራ በሉኝ እንጂ ኑኃሚን አትበሉኝ» በማለት የደረሰባትን ኀዘን ገለጠች ። (ማራ ማለትም መራራ ማለት ነው ።)

### ፪ ፥ ቤተልሔማዊው ቦዔዝ ።

ሩት ፪ ፥ ፩ - ፳፫ ፤ ዘሌዋ. ፲፱ ፥ ፱ ፡ ፲ ።

ኑኃሚን የባልዋን ርስት መሸጥ ግድ እስከሚሆንባት ደኀይታ ነበር ። ሞዓባዊት ሩትም ፡ «እህል እንድቃርም ወደ እርሻ ልሂድ» ብላ ሄደች ፤ እንደ አጋጣሚም የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረ ወደ ቦዔዝ እርሻ ገብታ አጫጆችን በመከተል ቃረመች ። ቦዔዝም ኃያል ሰው ነበረ ።

እነሆም ቦዔዝ አጫጆቹን ሊጐበኝ መጣና ፡ «እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» አላቸው ። የአጫጆቹንም አዛዥ ፡ «ይህች ቆንጆ የማን ናት ?» ብሎ ጠየቀ ። እርሱም ፡ «ከኑኃሚን ጋር ከሞዓብ የመጣች ናት ፤ እርሷም ፡ እንድቃርም እባክህ ፍቀድልኝ አለችኝ ፤ ከማለዳም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አላረፈችም» አለው ።

ቦዔዝም ሩትን ፡ «ልጄ ሆይ ፡ ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ ፡ ነገር ግን ገረዶቼን ተጠጊ ። እንዳያስቸግሩሽም ጐበዛዝትን አዝዣለሁ ፤ በተጠማሽም ጊዜ ወደ ማድጋው ሄደሽ እነርሱ ከቀዱት ውኃ ጠጪ» አላት ። በግምባርዋም ተደፍታ ፡ «እኔን እንድትቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ ? እንግዳ አይደለሁምን ? » አለችው ።

ቦዔዝም ፡ «ባልሽ ከሞተ በኋላ አባትሽንና እናትሽን የተወለድሽባትንም ምድር ትተሽ ቀድሞ ወደማታውቂው ሕዝብ እንደ መጣሽና ለአማትሽ ያደረግሽውን ነገር ሁሉ ሰምቻለሁ ። እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ ፤ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን» አላት ። እርስዋም ፡ «ጌታዬ ሆይ ፡ ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ ሳልሆን አጽናንተኸኛልና በዓይንህ ሞገስ ላግኝ» አለችው ።

በምሳም ጊዜ ቦዔዝ ፡ «ቅረቢና ብዪ» ብሎ ከተጠበሰ እሸት ሰጣት ፤ በልታም ጠገበች ፡ አተረፈችም ። ደግሞም ልትቃርም በተነሣች ጊዜ ቦዔዝ አጫጆቹን ፡ «በነዶው መካከል ትቃርም ፡ አታሳፍሩአት ፤ ከነዶውም ተዉላት ፡ አትውቀሱአትም» ብሎ አዘዛቸው ። እንዲሁ እስከ ማታ ድረስ ቃረመች ፤ የቃረመችውንም ወቃች ፤ ተሸክማም ወደ አማትዋ ገባች ። አማትዋም የቃረመችውን ፡ ከምሳም ያተረፈችውን አይታ ቦዔዝ ያደረገላትን ሁሉ በሰማች ጊዜ ፡ «ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ ያልተወምና በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን ። ይህ ሰው የቅርብ ዘመዳችን ነውና እንደ ሕጉ ቃል ርስታችንን ሊገዙልን ከሚችሉት አንዱ ነው» አለቻት ። ሩትም የገብሱና የስንዴው መከር እስኪጨረስ ድረስ የቦዔዝን ገረዶች እየተጠጋች ቃረመች ።

### ፫ ፥ ቦዔዝ ሩትን አገባ ።

ሩት ፫ ፥ ፩ - ፬ ፥ ፳፪ ።

እንደ ሙሴ ሕግ ኑኃሚን የምትሸጠውን ርስት የሚገዛው ቅርብ ዘመድ የምዋቹን ሚስት ሩትን ደግሞ ለማግባት ይገባው ነበር* ። ኑኃሚን ይህን ሁሉ ለሩት አስታውቃ ፡ የመከር ወራት ሳያልቅ ወደ ቦዔዝ ላከቻት ። ቦዔዝም ፡ «ልጄ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ ፤ ባለጠጋም ድኃም ብለሽ ጐበዛዝትን አልተከተልሽምና ከበፊቱ ይልቅ አሁን ቸርነት አድርገ



www.ethiopianorthodox.org

ሻል ። አሁንም አትፍሪ ፡ የአገሬ ሕዝብ ሁሉ ምግባረ መልካም ሴት መሆንሽን ያውቃሉና ያልሽውን ነገር ሁሉ አደርግል ሻለሁ ። ይሁን እንጂ ከእኔ የቀረበ ዘመድ አለና ዋርሳሽ ሊሆን ይወድ ይሆናል ፡ ባይ ወድ ግን እኔ ዋርሳ እሆንሻለሁ» አላት ።

ሩትም ወደ ኑኃሚን ተመልሳ የቦዔዝን ቃል ሁሉ አጫወተቻት ። እርስዋም ፡ «ልጄ ሆይ ፡ ሰውየው ይህን ነገር ዛሬ እስ ኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስ ኪታወቅ ድረስ ዝም በዪ» አለቻት ። ቦዔ ዝም የቅርብ ዘመዳቸው አለመቻሉን አረ ጋግጦ ፡ የሚገባውን ሁሉ በምስክሮች ፊት በመፈጸም ሩትን አገባት ።

ሩትም ለቦዔዝ ወንድ ልጅ ወለደችለት። ጐረቤቶችም ኑኃሚንን ፡ «ዛሬ ወራሽ ልጅ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ ፤ ስሙም በእስራኤል ይጠራ ። ከሰባትም ወንዶች ልጆች ይልቅ ለአንቺ ከምት ሻል ከምትወድሽ ምራት ተወልዶአልና ሰውነትሽን ያሳድሰዋል ፡ በእርጅናሽም ይመግብሻል» አሉአት ። ኑኃሚን ሕፃኑን ወስዳ አቀፈችው ፡ ሞግዚትም ሆነችው ። ጐረቤቶችዋም ፡ «ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት» እያሉ ስሙን ኢዮቤድ ብለው ሰየሙ ። እርሱም የእሴይ አባት ነው ፤ እሴይም የዳዊት አባት ነው ።

(ማቴ. ፩፡፭፡፮ ።)

* * *

ጌታ ለዘላለም አይጥልም ፤
ቢያሳዝንም እንደ ምሕረቱ ብዛት ይራራል ፤
የሰውን ልጆች ከልቡ አያስጨንቅም ፡ አያሳዝንምም ።

ሰቆቃ. ፫፡፴፩ - ፴፫ ።

እግዚአብሔር ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት ።

፩ ጴጥ. ፭፡፯ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ሩት ከጣዖታት ወደ እግዚአብሔር መመለስዋን በምን አሳየች ?
፪ ፡ ቦዔዝ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው መሆኑን በምን አሳየ ?
፫ ፡ «ኑኃሚን አትበሉኝ» ያለችው የባልቴቲቱ ኀዘን በምን ተለ ወጠ ?

ጸሎት ፡ አቤቱ ፡ ምሕረትህን እንዴት አበዛህ !
የሰው ልጆች በክንፎችህ ጥላ ይታመናሉ ። . . .
ምሕረትህን በሚያውቁህ ላይ ፡
ጽድቅህንም ልባቸው በቀና ላይ ዘርጋ ።

መዝ. ፴፭ (፴፮) ፡ ፯ ፡ ፲ ።

ለእስራኤል የተሰጡ እነዚህ ሕግጋት ተጽፈው የሚገኙ በዘሌዋ. ፳፭ ፡ ፳፭ - ፳፰ና በዘዳግ. ፳፭ ፡ ፭ - ፲ ነው ።





ምዕራፍ ፴፫ ።

## የሳሙኤል ልደትና መጠራት ።

፩ ሳሙ. ፩ - ፫ ።

### ፩ ፤ የሐና ጸሎት ።

፩ ሳሙ. ፩ ፡ ፩ - ፲፱ ፤ ፩ ዜና. ፮ ፡ ፲፮ ፡ ፳፱ ፡ ፳፮ - ፳፰ ።

በኤፍሬም አገር የሚኖር ሕልቃና የተባለ ሌዋዊ ከሁለት ሚስቶቹ ጋር በየዓመቱ ለእግዚአብሔር እንዲሠዋ ፡ መቅደሱ ወደ ነበረበት ወደ ሴሎ ይሄድ ነበር ። ፍናና የተባለችው ሚስቱም የልጆች እናት ስት ሆን ሐና የተባለችው ግን መካን ነበረች ። መሥዋዕት በሚሠዋበትም ቀን ሕልቃና እድል ፈንታቸውን ለቤተሰቦቹ ሲያድል ፡ ይወዳት ስለነበር ለሐና ሁለት እጥፍ እድል ፈንታ ሰጣት ። ፍናና ግን ሐናን ልጅ ባለመውለድዋ እያበሳጨች አንዳች መቅመስ እስኪሳናት ድረስ ታስለቅሳት ነበር ። ሕልቃናም ሐናን ፡ «ለምን ታለቅ ሻለሽ ? ለምንስ አትቀምሺም ? እኔስ ከአ ሥር ልጆች አልሻልሽምን ?» አላት ።

ሐናም ተነሣች ፡ በእግዚአብሔርም ፊት ልትጸልይ ወደ መቅደስ ሄደች ። ተመ ርራም ነበርና በጽኑ ልቅሶ ስትጸልይ ፡ «አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ ፡ ለባሪያህ ወንድ ልጅ ብትሰጥ ፡ ዕድሜውን ሁሉ ለአንተ እሰጠዋለሁ ፡ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም» ብላ ተሳለች ።

ድምፅዋን ሳታሰማም ጸሎትዋን በእግዚ አብሔር ፊት ስታስረዝም ካህኑ ዔሊ እንደ ሰከረች ቈጥሮ ገሠፃት ። እርስዋ ግን ፡ «ጌታ ሆይ አይደለም ፤ እኔስ ልብዋ ያዘነባት ሴት ነኝ ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ » አለችው ። ዔሊም ፡ «በደኅና ሂጂ ፡ የእስራኤልም አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ» ብሎ መለሰላት ። ሐናም መንገድዋን ሄደች ፡ በላችም ፤ ከዚያም ወዲያ ፊትዋ



www.ethiopianorthodox.org

ኀዘንተኛ መስሎ አልታየም ። ማልደውም ተነሥተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

## ፪ ፤ የሳሙኤል ልደትና እድገት ።

፩ ሳሙ. ፩ ፣ ፲፱ - ፪ ፣ ፴፮ ፤ ዘሌዋ. ፲፯ ፣ ፮ ።

እግዚአብሔርም ሐናን አሰባት ፤ ፀንሳም ወንድ ልጅ ወለደች ። «ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ» ስትልም ሳሙኤል ብላ ጠራችው ።

የዓመቱን መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ሴሎ የሚወጡበትም ቀን ሲደርስ ሐና ባልዋን ፡ «ሕፃኑ ጡት እስኪተው ድረስ አልወጣም ፤ ከዚያም በኋላ በእግዚአብሔር ፊት እንዲታይ ፡ ሁልጊዜም በዚያ እንዲሆን ይገባው እሄዳለሁ» አለችው ። ልጅዋንም እያጠባች በቤትዋ ተቀመጠች ። ጡት በተወ ጊዜ ግን ለመሥዋዕት ወይፈኑን ይዛ ወደ እግዚአብሔር ቤት አመጣችው ። ሕልቃናና ሐናም ሕፃኑን ወደ ዔሊ አቀረቡት ፤ እርስዋም ፡ «ጌታዬ ሆይ ፡ ወደ እግዚአብሔር ለመጸለይ በዚህ ቆማ የነበረች ሴት እኔ ነኝ ። ስለዚህ ሕፃን ጸለይሁ ፤ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ሰጥቶኛል ፤ እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ» አለች ። ስትጸልይም ፡ «ልቤ በእግዚአብሔር ጸና ፤ በማዳንህ ደስ ብሎኛል» በማለት እግዚአብሔርን አመስግና ከባልዋ ጋር ወደ ቤትዋ ተመለሰች ።

በየዓመቱም ከባልዋ ጋር ስትወጣ ለሳሙኤል የሠራችለትን ታናሽ መደረቢያ ታመጣለት ነበር ። እግዚአብሔርም አሰባት ፤ ሦስት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ልጆችም ወለደች ። ብላቴናው ሳሙኤልም በእግዚአብሔር ፊት አደገ ።

ካህኑ ዔሊም ሸመገለ ፤ አፍኒንና ፊንሐስ የተባሉ ልጆቹም እግዚአብሔርን የማያውቁ ለሆዳቸው ብቻ የሚያስቡ ምናምንቴዎች ስለ ነበሩ መሥዋዕትን ከሚያቀርቡ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር እንዲቃጠል የታዘዘውን ስብ በግድ ይወስዱ ነበር ። ከዚህም የተነሣ ሰዎች የእግዚአብሔርን መሥዋዕት ይንቁ ነበርና የጐበዛዝት ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ሆነ ። ዔሊም በሥራቸው አዝኖ ገሠፃቸው ፤ በክፋታቸው እንደ ጸኑ ባየ ጊዜ ግን ተዋቸው ፤ የእግዚአብሔርንም ቤት ሲያረክሱ አልከለከላቸውም ።

የእግዚአብሔርም ሰው ወደ ዔሊ መጥቶ ፡ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ መሥዋዕቴን ስለ ምን ረገጣችሁ ? እንድትወፍሩም መጀመሪያ በመብላታችሁ ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ ? ስለዚህም ከቤትህ የሚወለዱ ገና በጐልማሳነት ይሞታሉ ፤ ሁለቱም ልጆችህ አፍኒንና ፊንሐስ በአንድ ቀን ይሞታሉ ። ያከበሩኝን አከብራለሁና የናቁኝም ይናቃሉና» አለው ። ይህም ሁሉ ሲሆን ብላቴናው ሳሙኤል እያደገ ፡ በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስ እያገኘ ሄደ ።

## ፫ ፤ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራ ።

፩ ሳሙ. ፫ ፣ ፩ - ፳፩ ።

በዚያ ክፉ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ ፤ ራእይም አይገለጥም ነበር ። ብላቴናውም ሳሙኤል በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ሲያገለግል ገና እግዚአብሔርን አላወቀም ነበር ።

የዔሊም ዓይኖች መፍዘዝ ከጀመሩ በኋላ በአንድ ሌሊት የእግዚአብሔር መብራት ገና ሳይጠፋ ዔሊና ሳሙኤል በየሥፍራቸው ተኝተው ሳሉ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠርቶ ፡ «ሳሙኤል ሆይ» አለው ። እርሱም ተነሣ ፡ ወደ ዔሊም ሮጦ ፡ «እነሆኝ የጠራኸኝ» አለው ። ዔሊም ፡ «አልጠራሁህም ፡ ተመልሰህ ተኛ» አለው ። ሄዶም ተኛ ።



እግዚአብሔርም ደግሞ ፤ «ሳሙኤል ሆይ» ብሎ ጠራው ። ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደና ፡ «እነሆኝ የጠራኸኝ» አለ ። እርሱም ፡ «ልጄ ሆይ ፡ አልጠራሁህም ፤ ተመልሰህ ተኛ» ብሎ መለሰ ። ሄዶም ተኛ ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ሦስተኛ ጊዜ ጠራው ። እርሱም ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደና ፤ «እነሆኝ የጠራኸኝ» አለ ። ዔሊም ብላቴናውን የጠራው እግዚአብሔር መሆኑን አስተውሎ ፡ «ሄደህ ተኛ ፤ ቢጠራህም ፡- አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው» አለው ። ሳሙኤልም ሄዶ በሥፍራው ተኛ ።

እግዚአብሔርም እንደ ቀድሞው ፡ «ሳሙኤል ሳሙኤል» ብሎ ጠራው ። ሳሙኤልም ፡ «ባሪያህ ይሰማልና ተናገር» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «እነሆ በዔሊ ቤት ላይ የተናገርሁትን የምፈጽምበት ቀን ይመጣል ፤ ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ ዐውቆ አልከለከላቸውምና የቤቱ ኃጢአት እንዳይሠረይለት በዔሊ ቤት ምያለሁ» አለው ።

ሳሙኤልም እስኪነጋ ድረስ ተኛ ፤ ማልዶም ተነሣ ፡ የእግዚአብሔርንም ቤት ደጃፍ ከፈተ ። ነገሩንም ለዔሊ ሊናገር ፈራ ። ዔሊም ሳሙኤልን ጠርቶ ፡ «ልጄ ሆይ ፤ እግዚአብሔር የነገረህን ነገር ከእኔ አትሸሽግ» አለው ። ሳሙኤልም ነገሩን ሁሉ ነገረው ፤ ዔሊም ፡ «እርሱ እግዚአብሔር ነው ፤ ደስ ያሰኘውን ያድርግ» አለ ።

ሳሙኤልም አደገ ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ ፤ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር ። እግዚአብሔርም ደግሞ በሴሎ ተገለጠ ፤ በቃሉም ለሳሙኤል ይገለጥ ነበር ፤ የሳሙኤልም ቃል ለእስራኤል ሁሉ ደረሰ ።

* * *

ያከበሩኝን አከብራለሁ ፡ የናቁኝም ይናቃሉ ።

፩ ሳሙ. ፪ ፣ ፴ ።

ሕግን የሚጠብቅ አስተዋይ ልጅ ነው ፤
ምናምንቴዎችን የሚከተል ግን አባቱን ያሳፍራል ።

ምሳሌ ፳፰ ፣ ፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የሳሙኤል ወላጆች እነማን ነበሩ ? እናቱስ ምን ብላ ጸለየች ?
፪ ፤ የዔሊ ልጆች እነማን ነበሩ ? ምንስ ክፉ ነገር ያደርጉ ነበር ?
፫ ፤ ሳሙኤል ፣ እግዚአብሔር እንደጠራው ባስተዋለ ጊዜ ምን ብሎ መለሰለት ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር ።

፩ ሳሙ. ፫ ፣ ፱ ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፵፩ ።

## የእግዚአብሔር ታቦት መማረክና መመለስ ።

፩ ሳሙ. ፬ - ፯ ።

### ፩ ፡ የታቦት መማረክ ።

፩ ሳሙ. ፬ ፡ ፩ - ፳፪ ፡ መዝ. ፸፯ (፸፰) ፡ ፶፯ - ፷፬ ፡ ኤር. ፯ ፡ ፲፪ ።

ዔሊ በእስራኤል ላይ ዐርባ ዓመት ከፈረደ በኋላ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሊዋጉ ወጡ ፤ ነገር ግን በፍልስጥኤማውያን ተመቱ ። የእስራኤል ሽማግሌዎችም ፡ «ዛሬ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለምን መታን ? በመካከላችን እንዲሄድ ፡ ከጠላቶቻችንም እጅ እንዲያድነን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እናምጣ» አሉ ። ሕዝቡም ወደ ሴሎ ልከው ፤ የሠራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት አመጡ ። ሁለቱም የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር መጡ ።

የቃል ኪዳኑ ታቦትም ወደ ሰልፈኞች ሠፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ ። ፍልስጥኤማውያንም የሰሙትን የእልልታ ድምፅ ምክንያት ባስተዋሉ ጊዜ ፈርተው ፡ «ወዮልን ! እነዚህ አማልክት ግብፃውያንን በመቅሠፍት የመቱ ናቸው ። እናንተ ፍልስጥኤማውያን ሆይ ፤ ጐብዙ ፡ ተዋጉም» አሉ ። ፍልስጥኤማውያንም ተዋጉ ፤ እስራኤልም ሸሹ ፡ ሠላሳ ሺህም እግረኞች ሞቱ ። የእግዚአብሔርም ታቦት ተማረከች ፤ አፍኒንና ፊንሐስም ሞቱ ።

የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ የነበረ ካህኑ ዔሊም ፡ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ልቡ ተናውጦ በሴሎ መንገድ ዳር በወንበር ላይ ተቀምጦ የሰልፉን ሁኔታ ለመስማት ይጠባበቅ ነበር ። እነሆም ፡ በራሱ ላይ ትቢያ የነሰነሰ ሰው ከሰልፍ እየበረረ ወደ ሴሎ ገብቶ ባወራ ጊዜ ከተማዪቱ ተጯጯኸች ። ዔሊም ፡ «ይህ ጩኸት ምንድር ነው ?» አለ ። ሰውዬውም ፈጥኖ መጣና ፡ «ዛሬ ከሰልፍ ኰበለልሁ ፤ በእስራኤል ታላቅ ግድያ ሆኖአል ፡ ሁለቱም ልጆችህ ሞተዋል ፤ የእግዚአብሔርም ታቦት ተማርካለች» አለው ። ዔሊም ስለ እግዚአብሔር ታቦት በሰማ ጊዜ ከወንበር ወደቀ ፤ አንገቱም ተሰበረና ሞተ ።

የፊንሐስ ሚስት ልትወልድ ጊዜዋ ቀርቦ ነበር ። የእግዚአብሔር ታቦት እንደ ተማረከች ፡ አማትዋና ባልዋም እንደ ሞቱ በሰማች ጊዜ ምጥ ያዛትና ወለደች ። በዙሪያ የነበሩት ሴቶችም ፡ «አትፍሪ ፡ ወንድ ልጅ ወልደሻል» አሉአት ። እርስዋ ግን ፡ «የእግዚአብሔር ታቦት ተማርካለችና ክብር ከእስራኤል ለቀቀ» ስትል ሕፃንዋን ኢካቦድ ብላ ሰይማው ሞተች ። «ኢካቦድ» ማለት «ክብር የት ነው ? » ማለት ነው ።

### ፪ ፡ ታቦት በፍልስጥኤም አገር ።

፩ ሳሙ. ፭ ፡ ፩ - ፲፪ ።

ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ በአዛጦን ከተማ ወደ ነበረው ወደ ጣዖታቸው ወደ ዳጎን ቤትም አገቡት ፤ በዳጎንም አጠገብ አኖሩት ። በማግሥቱም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግምባሩ ወድቆ ተገኘ ። ሰዎችም ዳጎንን አንሥተው አቆሙት ። በነጋውም ማለዱ ፤ እነሆም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ ወድቆ ራሱና እጆቹ ተቈርጠው ደረቱ ብቻ ቀርቶ ነበር።

የእግዚአብሔርም እጅ በአዛጦን ሰዎች ላይ ከበደች ፡ አጠፋቻቸውም ፤ በእባጭም መታቻቸው ። እነርሱም ፡ «የእስራኤል አምላክ ታቦት በእኛ ዘንድ አይቀመጥ» ብለው የአገሩን አለቆች ፡ «በእስራኤል አምላክ ታቦት ምን እናድርግ ?» አሉ ። አለቆቹም፡ «ወደ ጌት ይዙር» ብለው መለሱ ። ወደ ጌትም ተሸከሙት ፤ በከተማዪቱም ላይ ታላቅ ድንጋጤና መቅሠፍት ሆነ ። ከአንዱ ከተማም ወደ ሌላው ሲወስዱ ሕዝቡ እጅግ ደንግጠው ይጮኹ ነበር ፤ በየደረሰበትም የእባጭና የሞት ድንጋጤ ሆነ አይጦችም አገሩን አጠፉ ። የፍልስጥኤማውያንም ዋይታ እስከ ሰማይ ወጣ ።

### ፫ ፡ የታቦት መመለስ ።

፩ ሳሙ. ፮ ፡ ፩ - ፯ ፡ ፪

የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤም አገር ሰባት ወር ከቈየች በኋላ ሕዝቡ ካህናትንና ምዋርተኞችን ጠርተው ፡ «የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ሥፍራዋ በምን እንስደዳት ?» አሉ ። እነርሱም ፡ «ለእስራኤል አምላክ ክብርን ስጡ ፤ ለበደል መሥዋዕትም እንደ ፍልስጥኤማውያን አለቆች ቍጥር አምስት የወርቅ እባጮች ፡ አምስትም የወርቅ አይጦች አቅርቡ ። አንዲት ሰረገላም ሠርታችሁ ቀንበር ያልተጫነባቸውን ሁለት የሚያጠቡ ላሞችን ጥመዱ ፤ እንቦሶቻቸውንም ለይታችሁ ወደ ቤት መልሱአቸው ። የእግዚአብሔርንም ታቦት ወስዳችሁ በሰረገላው ላይ አኑሩት ፤ የበደል መሥዋዕትንም በሣጥን ውስጥ አድርጋችሁ በታቦቲቱ አጠገብ አኑሩት ፤ እንዲሄድም አድርጉት ። ተመልከቱም ፤ በድንበሩም መንገድ ወደ ቤትሳሚስ ቢወጣ ይህን ክፉ ነገር ያደረገብን እግዚአብሔር ነው ፡ በዚያ ባይወጣ ግን የእርሱ እጅ እንዳልመታን ፡ የደረሰብንም እንዲያው እንደ መጣብን እናውቃለን» ብለው መለሱላቸው ።

ሰዎቹም እንዲሁ አደረጉ ፡ የሚያጠቡትንም ሁለቱን ላሞች በሰረገላ ጠመዱአቸው ፤ እንቦሶቻቸውንም ከቤት ውስጥ ዘጉአቸው ። ላሞቹም እምቧ እያሉ ወደ ቤትሳሚስ በሚወስደው መንገድ አቅንተው ሄዱ ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላሉም ። ሰረገላውም ወደ ቤትሳሚሳዊው ወደ ኢያሱ እርሻ መጣ ። ታቦቲቱንም የተ



www.ethiopianorthodox.org

ብኋት ሰዎች የሰረገላውን እንጨት ፈል
ነው ላሞቹን ለእግዚአብሔር ለሚቃጠል
ሥዋዕት አቀረቡ ። አምስቱ የፍልስጥ
ማውያን አለቆችም ይህን አይተው ወደ
ገራቸው ተመለሱ ። የቂርያትይዓሪም
ዎችም ታቦቲቱን ወስደው አሚናዳብ
ደ ተባለው ሰው ቤት አጋቡአት ፤ ሃያ
መትም በዚያ ተቀመጠች ።

፤ የእስራኤል ንስሐና ድል ።

፩ ሳሙ. ፯ ፣ ፫ - ፲፮ ።

ሙኤልም የእስራኤልን ቤት ሁሉ ፤
ሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር ከተ
ለሳችሁ እንግዶችን አማልክት ከመካከ
ችሁ አርቁ ፤ ልባችሁንም ወደ እግዚአብ
ር አቅኑ ፤ እርሱንም አምልኩ ፤ ከፍልስ
ኤማውያንም እጅ ያድናችኋል» ብሎ
ናገራቸው ። የእስራኤልም ሰዎች በአ
ና አስታሮት የተባሉትን አማልክት አር
ው እግዚአብሔርን ብቻ አመለኩ ።

ሳሙኤልም እስራኤልን ሁሉ ወደ ምጽጳ ሰብስቦ ስለ እነርሱ ጸለየ ። እነርሱም ፤ «እግዚአብሔርን በድለናል» ብለው ጾሙ ። ፍልስጥኤማውያንም መሰብሰባቸውን በሰሙ ጊዜ ወጡባቸው ። እስራኤልም ሳሙኤልን ፤ «ወደ እግዚአብሔር ትጸልይልን ዘንድ አትታክት» አሉት ። ሳሙኤልም መሥዋዕትን አቅርቦ ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም ገው ፤ በፍልስጥኤማውያን ላይ ታላቅ ነጐድጓድ አንጐደጐደ ፤ አስደነገጣቸውም ፤ በእስራኤልም ፊት ድል ተመቱ ። ሳሙኤልም ድንጋይን ወስዶ አቆመና ፤ «እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል» ሲል አቤንኤዘር ብሎ ጠራው ። አቤንኤዘር ማለት የመ ት ድንጋይ ማለት ነው ። ፍልስጥኤማውያንም በሳሙኤል ዕድሜ ሁሉ ተዋርደው ቀሩ ። ሳሙኤልም ዕድሜውን ሙሉ በእስራኤል ላይ ፈረደ ።

*　　*　　*

ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል ፤ በከንፈሮቹም ያከብረኛል ፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው ። ኢሳ. ፳፱ ፣ ፲፫ ።

ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ ፤ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ ፤ ክፉ ማድረግን ተዉ ፤ መልካም መሥራትንም ተማሩ ። ኢሳ. ፩ ፣ ፲፮ ።

*　　*　　*

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ታቦት የተማረከች በምን ምክንያት ነበረ ?
፪ ፤ እግዚአብሔር ኃይሉን ለፍልስጥኤማውያን በምን አሳየ ?
፫ ፤ ሳሙኤል ሕዝቡን ወደ ምጽጳ የሰበሰባቸው ለምን ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ አምላካችን ሆይ ፤ ከአንተ በቀር ሌሎች ጌቶች ገዝተውናል ፤ ነገር ግን በአንተ ብቻ ስምህን እናስባለን ። ኢሳ. ፳፮ ፣ ፲፫ ።





ምዕራፍ ፵፫ ።

## ሳኦል ተቀብቶ ነገሠ ።

፩ ሳሙ. ፰ - ፲፪ ።

፩ ፤ እስራኤል ንጉሥን ፈለገ ።

፩ ሳሙ. ፰ ፣ ፩ - ፳፪ ።

ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን ፈራጆች አደረጋቸው ። እነርሱ ግን በአባታቸው መንገድ አልሄዱም ፤ የግል ጥቅማቸውንም ስለ ወደዱ ጉቦ እየተቀበሉ በቅንነት የማይፈርዱ ሆኑ ።

የእስራኤል ሽማግሌዎችም ወደ ሳሙኤል ተሰብስበው ፤ «አንተ ሸምግለሃል ፤ አሁንም እንደ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ንጉሥ አድርግልን» አሉት ። ይህ ነገራቸው ግን ሳሙኤልን አሳዘነው ፤ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ ። እግዚአብሔርም ፤ «በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ ስማቸው ፤ ንጉሥም አንግሥላቸው» አለው ።

፪ ፤ ሳኦል ነገሠ ። ፩ ሳሙ. ፱ ፣ ፩ - ፲ ፣ ፳፯ ።

ስሙ ቂስ የተባለ አንድ ጽኑዕ ኃያል ብንያማዊ ሰው ነበረ ፤ ለእርሱም ሳኦል የሚባል ልጅ ነበረው ፤ በእስራኤልም ዘንድ ከሳኦል ይልቅ መልከኛ የሆነ ሰው አልነበረም ፤ እርሱም ከትከሻው በላይ ከሕዝብ ሁሉ ይልቅ ዘለግ ያለ ነበረ ። አንድ ቀንም የቂስ አህዮች ጠፉ ፤ ቂስም ልጁን ሳኦልን ፤ «ከብላቴኖቹ አንዱን ይዘህ ተነሣ ፤ አህዮችንም ለመፈለግ ሂድ» አለው ። ከአንድ ብላቴናም ጋር ሄደ ።

ብዙ መንገድም ከተጓዙ በኋላ ሳኦል ብላቴናውን ፤ «አባቴ ስለ አህዮች ማሰብ ትቶ ስለ እኛ እንዳይጨነቅ እንመለስ» አለው ። እርሱም ፤ «እነሆ አንድ የከበረ የእግዚአብሔር ሰው በዚች ከተማ አለ ፤ ምናልባት የምንሄድበትን መንገድ ይነግረናል» አለው ። ሳኦልም ፤ «የተናገርኸው ነገር መልካም ነው» አለው ። ሁለቱም ወደ ከተማዪቱ በገቡ ጊዜ እነሆ ፤ መሥዋዕትን ለመሠዋትና ከተጠሩት ጋር ለመብላት የመጣው ነቢዩ ሳሙኤል ተገናኛቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ቀን በፊት እግዚአብሔር ሳሙ
ኤን ፡ «ነገ በዚህች ሰዓት ከብንያም አገር
ድ ሰው እሰድልሃለሁ ፡ ለሕዝቤ ለእስ
ኤል አለቃ እንዲሆን ትቀባዋለህ ፤ ከፍ
ጥኤማውያንም እጅ ሕዝቤን ያድናል»
ም ገልጦለት ነበር ። ሳሙኤልም ሳአ
ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ፡ «ያ የነገር
ሰው እነሆ» አለው ። ሳሙኤልም ሳአ
፡ «ዛሬ ከእኔ ጋር ትበላለህ ፡ ነገም አሰ
ትሃለሁ ፤ በልብህም ያለውን ሁሉ እነ
ሃለሁ ። ከሦስት ቀንም በፊት የጠፉ
ዮችህ ተገኝተዋልና ልብህን አትጣል
ው ። የእስራኤል ምኞት ለማን ነው ?
ንተና ለአባትህ ቤት አይደለምን ? »
ው ። ሳኦልም መልሶ ፡ «እኔ ከእስራ
ነገዶች ከሚያንስ ወገን የሆንሁ ብን
ዊ አይደለሁምን ? እንዲህስ ያለውን
ን ነገርኸኝ ?» አለ ።

ሳሙኤልም ሳኦልንና ብላቴናውን
ዶ ወደ አዳራሽ አገባቸው ፤ ከመርፈቂ
ም በከፍተኛው ቦታ አስቀመጣቸውና
ጥ ቤት ዘንድ አቈይቶ የነበረውን
ል ፈንታ አስመጥቶ ፡ «ሕዝቡን ከጠ
ጀምሮ ለአንተ ተጠብቆአልና እነሆ
» አለው ። ሳኦልም ከሳሙኤል ጋር
ት አደረ ። ማለዳውም ተነሡ ፡ ወደ
ም ወጡ ። ሳሙኤልም ሳኦልን ፡ «ብላ
ውን ወደ ፊታችን እንዲያልፍ እዘ
» አለው ። ሳሙኤልም የዘይቱን
ሌ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ ዘይትን አፈ
፡ ሳመውና ፡ «በርስቱ በእስራኤል ላይ
ቃ እንድትሆን እግዚአብሔር ቀብቶ
፤ ከጠላቶቻቸውም እጅ ታድናቸዋ
» አለው ።

ሙኤልም ሕዝቡን ሁሉ ወደ እግዚአ
ሔር ወደ ምጽጳ ጠራ ፤ ሳኦልንም አቅ
፡ «ከሕዝቡ ሁሉ እርሱን የሚመስል

እንደሌለ እግዚአብሔር የመረጠውን ታያ ላችሁን ? » አላቸው ። ሕዝቡም ሁሉ ፡ «ንጉሥ ሕያው ይሁን» እያሉ እልልታ አደረጉ ። ሳሙኤልም የመንግሥቱን ወግ ነግሮ በመጽሐፍ ጻፈው* ። ሳኦልም ወደ ቤቱ ወደ ጊብዓ ሄደ ፤ እግዚአብሔር ልባቸውን የነካ ኃያላንም ከእርሱ ጋር ሄዱ ። ምናምንቴዎች ሰዎች ግን ፡ «ይህ ሰው እንዴት ያድነናል ?» ብለው ናቁት ፡ እጅ መንሻም አላመጡለትም ።

፫ ፤ በሳኦል ብርታት መንግሥቱ ጸናች ።

፩ ሳሙ. ፲፩ ፡ ፩ - ፲፭ ።

ከዚህም በኋላ ናዖስ የተባለው የአሞን ንጉሥ የእስራኤልን ድንበር አልፎ በኢያቢስ ገለዓድ ሠፈረ ። የኢያቢስም ሰዎች ፡ «ቃል ኪዳን አድርግልን ፡ እንገዛልሃለንም» አሉት ። ናዖስም ፡ «ቀኝ ዓይናችሁን ሁሉ በማውጣት ቃል ኪዳን አደርግላችኋለሁ ፤ በእስራኤልም ሁሉ ላይ ስድብ አደርጋለሁ» በማለት መልእክተኞችን ወደ እስራኤል እንዲልኩ ሰባት ቀን ፈቀደላቸው ።

መልእክተኞቹም ወደ ጊብዓ መጥተው ለሳኦል ሲነግሩ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደ ፡ ቍጣውም እጅግ ነደደ ። እስራኤልንም ሁሉ አስከ ትሎ ወጣ ፤ ወገግም ባለ ጊዜ ወደ ሠፈሩ ገብተው እስከ ቀትር ድረስ አሞናውያንን መቱ ፡ በተኑአቸውም ።

ሕዝቡም ሳሙኤልን ፡ «ሳኦል አይንገሥብን ያሉትን እንግደላቸው» አሉት ። ሳኦልም ፡ «ዛሬ እግዚአብሔር ለእስራኤል ማዳን አድርጎአልና ዛሬ አንድ ሰው አይሞትም» አለ ። ሳሙኤልም ሕዝቡን ወደ ጌልገላ ሰበሰበ ፤ በዚያም ሳኦልን በእግዚአብሔር ፊት አነገሡት ። በእግዚአብሔርም ፊት መሥዋዕትን አቀረቡ ፤ ሳኦልና እስራኤልም ሁሉ ታላቅ ደስታ አደረጉ ።



www.ethiopianorthodox.org

፬ ፡ የሳሙኤል ንግግር ። ፩ ሳሙ. ፲፪ ፡ ፩ - ፳፭ ።

ሳሙኤልም ለእስራኤል ሁሉ ፡ «የነገራችሁኝን ሁሉ ሰምቼ ንጉሥ አንግሼላችኋለሁ ። እነሆም ንጉሡ በፊታችሁ ይሄዳል፤ እኔም ሸምግያለሁ ፡ ከሕፃንነቴም ጀምሬ እስከ ዛሬ ድረስ በፊታችሁ ሄድሁ ። እነሆኝ ፡ በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባውም ፊት መስክሩብኝ ፤ በማን ላይ ግፍ አደረግሁ ? ዓይኖቼንስ ለማሳወር ከማን እጅ ጉቦ ተቀበልሁ ?» አለ ። እነርሱም ፡ «አልሸነገልኸንም ፡ ግፍም አላደረግህብንም» ብለው መሰከሩለት ።

እርሱም ቀጥሎ ፡ «ለእናንተና ለአባቶቻችሁ እግዚአብሔር ስላደረገው ጽድቅ ሁሉ በእርሱ ፊት እምዋገታችሁ ዘንድ በዚህ ቁሙ ። አምላካችሁ እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ሆኖ ሳለ ፦ እንዲህ አይሁን ፡ ነገር ግን ንጉሥ ይንገሥልን አላችሁኝ ። አሁንም ቁሙ ፡ ተመልከቱም ፡ የስንዴ መከር ዛሬ አይደለምን ? ንጉሥ በመለመናችሁ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ክፋት እንዳደረጋችሁ ዕወቁ» ሲል ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ፤ እግዚአብሔርም ነጐድጓድና ዝናብ ላከ ፤ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርንና ሳሙኤልን እጅግ ፈሩ ። ሳሙኤልንም ፡ «ንጉሥ በመለመናችን በድለናልና እንዳንሞት ጸልይልን» አሉት ። ሳሙኤልም ፡ «አትፍሩ ፡ መልካሙን መንገድ አስተምራችኋለሁ ፡ ስለ እናንተም መጸለይን አልተውም ። ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ ፡ በፍጹም ልባችሁም በእውነት አምልኩት» አላቸው ።

* * *

የወለደህን አምላክ ተውህ ፡
ያሳደገህን እግዚአብሔርን ረሳህ ።

ዘዳግ. ፴፪ ፡ ፲፰ ።

ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ ፡ ያደረገላችሁንም ታላቅ ነገር አይታችኋልና በፍጹም ልባችሁ በእውነት አምልኩት ።

፩ ሳሙ. ፲፪ ፡ ፳፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ሕዝቡ ምን ብለው ለመኑት ?
፪ ፤ ሳኦል ከየትኛው ነገድ ነበረ ? ከሕዝቡስ ሁሉ በምን በለጠ ?
፫ ፤ በመከር ጊዜ እንዲዘንብ ሳሙኤል ለምን ጸለየ ?

ጸሎት ፤ አምላኬ ፡ ከታናሽነቴ ጀምረህ አስተማርኸኝ . . .
ለሚመጣ ትውልድም ሁሉ ክንድህን
ኃይልህንም ጽድቅህንም እስክነግር ድረስ
አቤቱ ፡ አትተወኝ ። መዝ. ፸ (፸፩) ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

* ዘዳግ. ፲፯ ፡ ፲፬ - ፳ ።



ምዕራፍ ፵፯ ።

## የዳዊት መመረጥ ።

፩ ሳሙ. ፲፫ - ፲፯ ።

### ፩ ፡ የሳኡል አለመታዘዝ ።

፩ ሳሙ. ፲፫ ፡ ፩ - ፲፭ ፡ ፴፭ ።

ፍልስጥኤማውያን እንደገና በእስራኤል ላይ በርትተው ነበርና ሳኡል ሊዋጋቸው ተነሥቶ ሕዝቡን ወደ ጌልገላ ሰበሰበ ። ፍልስጥኤማውያንም ብዙ ሺህ ሰረገሎችና ፈረሰኞች ፡ ታላቅ ሕዝብም ሆነው ተሰበሰቡ ፡ በማክማስም ሠፈሩ ። የእስራኤል ሰዎችም ተጨንቀው በዋሻና በጉድጓድ ይሸሸጉ ፡ ወደ ዮርዳኖስ ማዶም ይሸሹ ጀመር ። ወደ ሳኡል ከተሰበሰቡት ብዙዎች ተመልሰው ይበታተኑ ጀመር ።

ሳሙኤል ወደ ጌልገላ መጥቶ በመሥዋዕት ከእግዚአብሔር ሞገስ እንዲለምን ቀን ቀጥሮ ነበርና ሳኡል ሳሙኤልን በመጠባበቅ ተጨነቀ ። እንደ ቀጠሮው ጊዜ ሰባት ቀን ከቈየ በኋላ ፡ ፍልስጥኤማውያን አሁን ይወርዱብኛልና ከዚህ ይበልጥ መጠባበቅ አልችልም ብሎ ሳኡል ራሱ እጅግ ደፍሮ መሥዋዕትን ማሳረግ ጀመረ። ከሚያቀርባቸውም መሥዋዕቶች አንዱን እንደ ፈጸመ ወዲያውኑ ሳሙኤል መጣና ፡ «ያደረግኸው ምንድር ነው ? » አለው ። ሳኡልም ፡ «ሕዝቡ ከእኔ ተለይተው እንደ ተበታተኑ አየሁ ፡ ፍልስጥኤማውያንም አሁን ይወርዱብኛል አልሁ ፤ ስለዚህም ሳልታገሥ መሥዋዕትን አሳረግሁ» አለ ። ሳሙኤልም ፡ «አላበጀህም ፡ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና መንግሥትህ አይጸናም ። እግዚአብሔርም እንደ ልቡ የሆነ ሰው መርጦአል ፤ በሕዝቡም ላይ አለቃ እንዲሆን አዝዞታል» አለው ።

ከፍልስጥኤማውያን ሠፈር ማራኪዎች እየወጡ ይዘርፉ ነበር ፤ የሚቃወማቸውም አልነበረም ። ሳኡል ከነሰዎቹ ወደ ብንያም ጊብዓ ወጥቶ ሠፈረ ። አንድ ቀንም የሳኡል ልጅ ዮናታን ጋሻ ጃግሬውን ፡ «በብዙ ወይም በጥቂት ማዳን እግዚአብሔርን አያስቸግረውም» ብሎ ወደ ፍልስጥኤማውያን ተሻግሮ በሰይፍ መታቸው ፡ አስደነገጣቸውም ። ሳኡልና ሰዎቹም ይህን ባዩ ጊዜ ገሥግሠው ተከተሉ ፤ ታላቅም ድል አደረጉ ። ሕዝቡም ፡ «ዛሬ ዮናታን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎአል ፤ በእስራኤልም ዘንድ ታላቅ መድኃኒት አደረገ» አሉ ።

ከዚህም በኋላ ሳሙኤል ሳኡልን ፡ «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፦ ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ እስራኤልን እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ * ይላልና ሄደህ አማሌቅን ከነእንስሶቻቸው ፈጽመህ አጥፋ ፡ አትማራቸውም» አለው ። ሳኡልም ሕዝቡን አስከትሎ ሄደ ፤ በታላቅ መምታትም መቱአቸው ፡ ገደሉአቸውም ። ነገር ግን ለአማሌቅ ንጉሥና ምርጥ ምርጥ ለሆኑት እንስሶች ራሩላቸው ።

እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ፡ «ሳኡል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና ስላነገሥሁት ተፀፀትሁ» አለ ። ሳሙኤልም አዝኖ ሳኡልን ሊገናኘው መጣ ፤ ሳኡልም ፡ «የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጸምሁ» አለው ። ሳሙኤልም ፡ «ይህ በጆሮዬ የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት ምንድር ነው ?» አለ ። ሳኡልም ፡ «ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ይሠዉአቸው ዘንድ አምጥተዋቸዋል» አለ ። ሳሙኤልም ፡ «በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን ? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት ፡ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል ። የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ» አለው ። ከዚህም በኋላ ሳሙኤል እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ሳኡልን ለማየት ዳግመኛ አልሄደም ፡ ለሳኡልም አለቀሰ ።

### ፪ ፡ የዳዊት መቀባት ።

፩ ሳሙ. ፲፮ ፡ ፩ - ፲፫ ።

እግዚአብሔር ሳሙኤልን ፡ «ለናቅሁት ለሳኡል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው ? በቀንድህ ዘይትን ሞልተህ ሂድ ፡ በልጆቹ መካከልም ንጉሥ አዘጋጅቻለሁና ወደ እሴይ ወደ ቤተልሔም እልክሃለሁ» አለው ። ሳሙኤልም ፡ «እንዴት እሄዳለሁ ? ሳኡል ቢሰማ ይገድለኛል» አለ ። እግዚአብሔርም ፡ «አንዲት ጊደር ይዘህ ሂድና ፦ ለእግዚአብሔር ልሠዋ መጣሁ በል ። እሴይንም ወደ መሥዋዕቱ ጥራው ፡ የምታደርገውንም አስታውቅሃለሁ» አለው ።

ሳሙኤልም ጊደር ይዞ ወደ ቤተልሔም መጣ ። የከተማዪቱ ሽማግሌዎችም ፡ «የመጣኸው ለደኅንነት ነውን ? » ሲሉ እየተንቀጠቀጡ ሊገናኙት መጡ ። እርሱም ፡ «ለእግዚአብሔር ልሠዋ መጣሁ ፤ እናንተም ከእኔ ጋር ኑ» ብሎ እሴይንና ልጆቹን ወደ መሥዋዕቱ ጠራ ።

በመጡም ጊዜ ሳሙኤል የእሴይን ታላቅ ልጅ ኤልያብን ተመልክቶ ፡ «በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው» አለ ። እግዚአብሔር ግን ፡ «ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ ፤ ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት ፡ ሰው ፊትን ያያል ፡ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል» አለው ።

እሴይም አሚናዳብን ጠርቶ በሳሙኤል ፊት አሳለፈው ፤ እርሱም ፡ «ይህን ደግሞ እግዚአብሔር አልመረጠውም» አለ ። እሴይም ሣማን አሳለፈ ፡ ከእርሱም በኋላ ከልጆቹ አራት ሌሎችን ጠርቶ በሳሙኤል


www.ethiopianorthodox.org

ፊት ተራ በተራ አሳለፋቸው ። ሳሙኤ ልም እሴይን ፡ «እግዚአብሔር እነዚህን አልመረጠም ፤ የቀረ ሌላ ልጅ አለህን ?» አለው ። እሴይም ፡ «ታናሹ ገና ቀርቶ አል ፤ እነሆም በጎችን ይጠብቃል» አለ ። ሳሙኤልም ፡ «እርሱ እስኪመጣ ድረስ አንቀመጥምና ልከህ አስመጣው» አለው። ልኮም አስመጣው ፤ እርሱም ቀይ ፡ ዓይ ኑም የተዋበ ፡ መልኩም ያማረ ነበረ ። እግ ዚአብሔርም ፡ «ይህ ነውና ተነሥተህ ቅባው» አለ ። ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው ። የእ ግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያ ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ ።

፪ ፡ የሳአልና የዳዊት መገናኘት ።

፩ ሳሙ. ፲፮ ፣ ፲፬ - ፳፫ ።

እግዚአብሔርም መንፈስ ከሳአል ራቀ ፡ ክፉም መንፈስ አሠቃየው ። ባሪያዎቹም ፡ «ንጉሥ ሆይ ፡ በገና የሚመታ ሰው እንፈ ልግ ፤ በፊትህም ሆኖ በሚመታ ጊዜ ደኅና ትሆናለህ» አሉት ። ሳአልም ፡ «ፈልጋችሁ አምጡልኝ» አላቸው ። ከብላቴናዎቹም አንዱ መልሶ ፡ «እነሆ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ የቤተልሔማዊውን የእሴ ይን ልጅ አይቻለሁ ፡ እርሱም ጽኑዕ ኃያል ነው ፡ በነገርም ብልህ ፡ መልኩም ያማረ ነው ፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው» አለ ።

ሳአልም ወደ እሴይ ልኮ ፡ «ከበጎች ጋር ያለውን ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ» አለ ። እሴይም እንጀራንና ወይን ጠጅን አዘ ጋጀ ፡ አህያውንም ጫነ ፡ ከፍየሎቹም ጠቦ ቱን መርጦ በዳዊት እጅ ላከ ። ዳዊትም ወደ ሳአል መጣ ፡ በፊቱም ቆመ ፡ ሳአልም እጅግ ወደደው ፡ ጋሻ ጃግሬውም አደረ ገው ። ክፉም መንፈስ በመጣበት ጊዜ ዳዊት በገና እየመታ ደስ ያሰኘው ያሳርፈ ውም ነበር ።

* * *

እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት ፡ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል ። ፩ ሳሙ. ፲፭ ፣ ፳፪ ።

ሰው ፊትን ያያል ፡ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል ። ፩ ሳሙ. ፲፮ ፣ ፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የሳአል መንግሥት ያልጸናበት በምን ምክንያት ነው ?
፪ ፤ «እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነ ሰው መርጦአል» የተባለ ስለ ማን ነው ?
፫ ፤ ሳአል ዳዊትን ያስመጣው ምን እንዲያደርግለት ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ረድኤቴ መድኃኒቴም ፡
የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ
በፊትህ ያማረ ይሁን ። መዝ. ፲፰ (፲፱) ፣ ፲፬ ።

* ዘጸ. ፲፯ ፡ ፰ - ፲፯ ።





ምዕራፍ ፵፯ ።

## ዳዊትና ጎልያድ ።

፩ ሳሙ. ፲፯ ፡ ፩ - ፲፰ ፡ ፭ ።

፩ ፤ የጎልያድ ተግዳሮት ።

፩ ሳሙ. ፲፯ ፣ ፩ - ፲፩ ።

ፍልስጥኤማውያን ጭፍሮቻቸውን በይ ሁዳ ባለው በሰኰት አከማችተው ለሰልፍ ተዘጋጁ ። ሳአልና የእስራኤል ሰዎችም ሊገናኙአቸው ወጡ ። ፍልስጥኤማውያ ንም በአንድ ወገን በተራራ ላይ ተሰለፉ ፤ እስራኤላውያንም በሌላ ወገን በተራራ ላይ ተሰለፉ ፡ በመካከላቸውም ሸለቆ ነበረ ።

ከጠላትም ሠፈር የጌት ሰው ጎልያድ ወጥቶ በእስራኤል ሰዎች ፊት ቆመ ። ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ ዝነኛ ጀግና ነበረ ። እርሱም የነሐስ ቍር ፡ ጥሩርና ገምባሌም ለብሶ ነበር ፤ የጦሩም የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ ነበረ ፤ ጋሻ ጃግሬውም በፊቱ ይሄድ ነበር ። ድምፁ ንም ከፍ አድርጎ ፡ «ለእናንተ አንድ ሰው ምረጡ ፡ ወደ እኔም ይውረድ ፤ ከእኔም ጋር ሊዋጋ ቢችል ቢገድለኝም ባሪያዎች እንሆ



www.ethiopianorthodox.org

ቸኋለን ፡ እኔ ባሸንፈው ግን ብገድለ
ም እናንተ ባሪያዎች ትሆኑናላችሁ»
እስራኤላውያንን ተገዳደረ ። ሳኦልና
ራኤልም ሁሉ የጀግናውን ቃል በሰሙ
እጅግ ፈሩ ፤ ደነገጡም ። ጎልያድም
ትና ማታ እስከ ዐርባ ቀን ድረስ እየ
ይገዳደር ነበር ።

የዳዊት ዝግጅት ።

፩ ሳሙ. ፲፯ ፣ ፲፪ - ፶ ።

ቱ የእሴይ ታላላቅ ልጆች ሳኦልን ተከ
ው ከሰልፉ ነበሩ ። ዳዊት ግን ከሳኦል
ልሶ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር ።
ይም ዳዊትን ፡ «ከዚህ እሸትና እንጀራ
ንድሞችህ ፡ ይህንም አይብ ለሻለቃው
ርስና የወንድሞችህን ደኅንነት ጠይቅ፤
አቸውንም አምጣልኝ» ብሎ ላከው ።
ዊትም ማልዶ ተነሣ ፤ በጎቹንም ለጠ
ትቶ ሄደ ። በደረሰም ጊዜ በዕቃ ጠባ
እጅ ዕቃውን አኑሮ ወደ ሠራዊቱ
፤ የወንድሞቹንም ደኅንነት ጠየቀ ።
ርሱም ጋር ሲነጋገር እነሆ ጎልያድ
ት ሠፈር ወጥቶ ፡ «ዛሬ የእስራኤልን
ራዎች ተገዳደርኋቸው ፡ እንዋጋ
አንድ ሰው ስጡኝ» ብሎ ጮኸ ።
ራኤል ሰዎችም ከእርሱ ሸሹ ፤ እርስ
ቸውም ፡ «ይህን ሰው አያችሁትን ?
ን የሚገድል ቢኖር ንጉሡ እጅግ አበ
ልጁን ይድርለታል ፡ የአባቱንም
ግብር ነጻ ያወጣል» ተባባሉ ። ዳዊ
በአጠገቡ ለነበሩት ፡ «ከእስራኤል
ፎትን ለሚያርቅ ሰው ምን ይደረግለ
የሕያው አምላክን ጭፍራዎች የሚ
ይህ ፍልስጥኤማዊ ማን ነው ? »

ቅ ወንድሙ ኤልያብም ሰማው ፤
መንፈስም ፡ «ለምን ወደዚህ ወረ
እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ

በዳ ለማን ተውሃቸው ? እኔ ኵራትህንና የልብህን ክፋት ዐውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል» አለው ። ዳዊትም ፡ «እኔ ምን አደረግሁ ? ይህ ታላቅ ነገር አይደለምን ?» ብሎ ከእርሱ ዘወር አለና ንግግሩን ቀጠለ ።

የተናገረውንም ቃል የሰሙ ሰዎች ለሳኦል ተናገሩ ፤ ሳኦልም አስጠራው ። ዳዊትም ሳኦልን ፡ «ስለ እርሱ የማንም ሰው ልብ አይውደቅ ፤ እኔ ባሪያህ ሄጄ ያንን ፍልስጥኤማዊ እወጋዋለሁ» አለው ። ሳኦልም ፡ «አንተ ገና ብላቴና ነህ ፡ እርሱም ከብላቴንነቱ ጀምሮ ጦረኛ ነው» አለው ። ዳዊትም መልሶ ፡ «እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር ፡ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር ። በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር ፡ ከአፉም አስጥለው ነበር ፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይገፍ እመታውና እገድለው ነበር ። እኔ ባሪያህ አንበሳና ድብ መታሁ ፤ ይህም ፍልስጥኤማዊ የሕያው አምላክን ጭፍራዎች ተገዳድሮአልና ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሆናል» አለ ።

ሳኦልም የራሱን የጦር ልብስ በዳዊት ላይ አደረገ ፤ ዳዊትም የሳኦልን ሰይፍ ታጠቀ ፤ ገና አልፈተነውምና መሄድ ሞከረ ። ዳዊትም ሳኦልን ፡ «እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም» ብሎ አወለቀ ። በትሩንም ይዞ ሄደ ከወንዝም አምስት ድብልብል ድንጋዮችን መረጠ በኮረጆውም ከተታቸው ፤ ወንጭፍም በእጁ ነበረ ፤ ወደ ጎልያድም ቀረበ ።

፫ ፤ የእስራኤል ድል ።

፩ ሳሙ. ፲፯ ፣ ፵፩ - ፶፫ ፤ ፲፰ ፣ ፩ - ፭ ።

ጎልያድም ዳዊትን ትዥር ብሎ አየው ፤ ቀይ ብላቴናም መልኩም ያማረ ነበረና በንቀት አነጋገር ፡ «በትር ይዘህ የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝን ? ወደ እኔ ና ፤ ሥጋህንም ለሰማይ አሞራዎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ» ብሎ በአምላኮቹ ስም ረገመው ። ዳዊትም መልሶ ፡ «አንተ ሰይፍና ጦር ይዘህ ትመጣብኛለህ ፤ እኔ ግን ፡ ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል አምላክ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ ። እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል ፤ ራስህንም ከአንተ አነሣዋለሁ ፤ የፍልስጥኤማውያንንም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ አሞራዎችና ለምድር አራዊት ዛሬ እሰጣለሁ ። ይኸውም ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ እንድታውቅ ፤ በዚህ የተሰበሰበውም ሁሉ እግዚአብሔር የሚያድን በሰይፍና በጦር እንዳይደለ እንዲያውቅ ነው ። ሰልፉ የእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል» አለው ።

ጎልያድም ተነሥቶ ዳዊትን ሊገናኘው ቀረበ ፤ ዳዊትም ወደ እርሱ ሲሮጥ እጁን ወደ ኮረጆው አግብቶ አንድ ድንጋይ ወሰደ ፡ ወነጨፈውም ። ድንጋዩም በጎልያድ ግምባር ተቀረቀረ ፡ እርሱም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ ። ዳዊትም ሮጦ በጎልያድ ላይ ቆመ ፤ ሰይፉንም ወስዶ አንገቱን ቈረጠ ። ፍልስጥኤማውያንም ጀግናቸው እንደ ሞተ ባዩ ጊዜ ሸሹ ። የእስራኤል ሰዎችም ተነሥተው እልል አሉ ፡ አሳደዱአቸውም ። በዚያም ቀን ትልቅ ድል አገኙ ።

ሳኦልም ዳዊትን በጦረኞች ላይ ሾመው ። የሳኦል ልጅ የዮናታን ነፍስም በዳዊት ነፍስ ታሠረች ፤ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ስለ ወደደው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ፤ ልብሱንና ሰይፉንም ቀስቱንና መታጠቂያውንም ፡ የለበሰውንም ካባ ሳይቀር ለዳዊት ሸለመው ።

* * *

እነዚያ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ ፤
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ
እንላለን ።

መዝ. ፲፱ (፳) ፣ ፯ ።

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል ?

ሮሜ ፰ ፣ ፴፩ ።

* * *


ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ጎልያድ ማን ነበረ ? ለእስራኤል ሰዎችስ ምን አለ ?
፪ ፤ ዳዊት ጎልያድን ያልፈራ በምን ምክንያት ነበረ ?
፫ ፤ ዳዊት ጎልያድን የገደለ በምን ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ የሚያምኑህን ከሚቃወሙ በቀኝህ
የምታድናቸው ፤
ቸርነትህን ድንቅ አድርገህ ግለጠው ።

መዝ. ፲፮ (፲፯) ፣ ፯ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፶፰

# የዳዊት መሳደድ ።

፩ ሳሙ. ፲፰ ፣ ፯ - ፳፯ ፣ ፯

## ፩ ፣ ሳኦል በዳዊት ቀናበት ።

፩ ሳሙ. ፲፰ ፣ ፯ - ፳ ፣ ፵፪ ።

ዳዊት ጎልያድን ገድሎ ከሳኦልና ከእስራ
ኤል ሠራዊት ጋር በድል ክብር ሲመለስ ፣
ነየከተማው የወጡ ሴቶች ከበሮና አታሞ
እየመቱ ንጉሡን ሲቀበሉ ፣ «ሳኦል ሺህ
ዳዊትምእልፍገደለ»እያሉይዘፍኑነበር ።
ሳኦልም በልቡ ፣ «ለዳዊት እልፍ ፣ ለእኔ
ግን ሺህ ብቻ ሰጡኝ ፤ ከመንግሥት በቀር
ምን ቀረበት ? » ብሎ ሊቀና ጀመረ ።

በነጋውም ዳዊት በሳኦል ፊት በገና
ሲመታ የሳኦል ምቀኝነት ገነፈለ ፤ ከግን
ቱም ጋር አጣብቄ እመታዋለሁ ብሎ የያዘ
ውን ጦር ወረወረ ። ዳዊት ግን ከፊቱ
ዘወር በማለት ሁለት ጊዜ ዳነ ። እግዚ
አብሔርም ከዳዊት ጋር ስለ ነበረ ሳኦል
ፈራው ፤ ዳዊትም በአካሄዱ ሁሉ አስተ
ውሎ ያደርግ ነበር ፣ እስራኤልም ሁሉ ወደ
ዱት ።

ሳኦልም ጎልያድን ለሚገድለው ሰው
የሰጠውን ተስፋ በማሰብ ዳዊትን ፣ «ታላ
ቂቱ ልጄ ሜሮብ እነኋት» አለው ፤ ሠርጉ
ሲደርስ ግን ለሌላ ሰው ዳራት ። ይሁን
እንጂ የሳኦል ታናሽ ልጁ ሜልኮል ዳዊ
ትን ወደደች ። ሳኦልም ይህን በሰማ ጊዜ
ዳዊትን በፍልስጥኤማውያን እጅ ይጥ
ለው ዘንድ አስቦ በማጫ ምትክ ከፍልስጥ
ኤማውያን መቶ ሰዎች እንዲገድል ነገ



ረው ። ዳዊት ግን ግዳዩን አከናውኖ ሜል
ኮልን ለማግባት በቃ ፤ ስሙም በእስራኤል
ሁሉ ከበረ ።

ይሁን እንጂ ዳዊት አማቱ ሳኦል ካልገደ
ለው እንደማያርፍ ተረድቶ ኰበለለ ፤ ነገር
ግን እንደ ነፍሱ ከሚወደው ከዮናታን ጋር
በድብቅ ሊመካከር ተመለሰ ። ዮናታንም
የአባቱን የሳኦልን አሳብ ካረጋገጠ በኋላ
ከዳዊት ጋር ወደ ተቃጠረበት ሜዳ ሊያሰ
ናብተው ወጣ ። እየተላቀሱም ተሳሳሙ ።
[illegible]ቱንም ዳዊት እጅግ አለቀሰ ። ዮናታ
ንም ፣ «በደኅና ሂድ ፤ እነሆ እኛ ሁለታ
ችን ፦ በእኔና በአንተ በዘሬና በዘርህ መካ
ከል ለዘላለም እግዚአብሔር ይሁን ብለን
በእግዚአብሔር ፊት ተማምለናል »
አለው ። ዳዊትም ተነሥቶ ሄደ ፤ ዮናታ
ንም ወደ ከተማ ገባ ።

## ፪ ፣ ዳዊት ከሳኦል ፊት ሸሸ ።

፩ ሳሙ. ፳፩ ፣ ፩ - ፳፪ ፣ ፪ ፤ ዘጸ. ፳፭ ፣ ፴ ።

ዳዊት በሸሸ ጊዜ ካህናት ወደሚኖሩበት
ከተማ ወደ ኖብ መጣ ። መሸሹንም ሳይገ
ልጥ ካህኑን አቢሜሌክን ፣ «አምስት እን
ጀራ በእጄ ስጠኝ» አለው ። ካህኑም
መልሶ ፣ «የተቀደሰ እንጀራ እንጂ ሁሉ
የሚበላው እንጀራ የለኝም» ብሎ ከእግዚ
አብሔር ፊት ከተነሣው ከተቀደሰ እንጀራ
ሰጠው ።

ዳዊትም አቢሜሌክን ፣ «የንጉሥ ጉዳይ
ስላስቸኰለኝ ሰይፌን አላመጣሁምና በአ
ንተ ዘንድ ጦር ወይም ሰይፍ አለን ? »
አለው ። ካህኑም ፣ «የገደልኸው የጎልያድ
ሰይፍ አለ» ብሎ ለዳዊት ሰጠው ። ዳዊት
ግን ለባኦል እረኞች አለቃ የሆነውን ኤዶ
ማዊውን ዶይቅን አይቶ ፣ ለሳኦል ይነግ
ራል ብሎ በማሰብ ፈራ ፤ ከዚያም ተነሥቶ
የእስራኤልን ድንበር ተሻግሮ ወደ ፍልስ
ጥኤም አገር ፣ አንኩስ ወደ ተባለው ወደ
ጌት ንጉሥ ሸሸ ። ጌትም ጎልያድ የኖረበት
ከተማ ነበረ ።

የአንኩስ ባሪያዎችም ፣ «ሳኦል ሺህ
ዳዊትም እልፍ ገደለ ብለው ሴቶች በዘፈን
ያወደሱት ይህ የአገሩ ንጉሥ አይደለ
ምን ? » አሉት ። ዳዊትም ይህን ቃል
በልቡ አኖረ ፣ እጅግም ፈራ ፤ በፊታቸ
ውም አእምሮውን ለወጠ ፤ በያዙትም ጊዜ
እንደ እብድ ሆኖ በበሩ መድረክ ላይ
ተንፈራፈረ ፣ ልጋጉም በጢሙ ላይ ይወ
ርድ ነበር ። አንኩስም ባሪያዎቹን ፣
«በፊቴ ያብድ ዘንድ ይህን ያመጣችሁት
እብድ ጠፍቶብኝ ነውን ? እንዲህ ያለውስ
ወደ ቤቴ ይገባልን ?» ብሎ አስወጣው ።
ዳዊትም በይሁዳ ወዳለው ዓዶላም ወደ
ተባለው ዋሻ ሄዶ ተሸሸገ ። ከጌት ሰዎ
ችም እጅ ያዳነውን አምላክ እንዲህ ብሎ
አመሰገነ ፦

«እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከ
ዋለሁ ፣
ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው ። . . .
ይህ ችግረኛ ጮኸ ፣ እግዚአብሔርም
ሰማው ፤
ከመከራውም ሁሉ አዳነው ።»

መዝ. ፴፫ (፴፬) ።*

በይሁዳ ምድረ በዳ እንደ ተሸሸገ በተሰማ
ጊዜ የተጨነቀ የተከፋም ሁሉ ወደ እርሱ
ይሄድ ጀመር ፣ ብዙዎችም ሆኑ ፤ ዳዊትም
በላያቸው አለቃ ሆነ ።

## ፫ ፣ ሳኦል በቍጣ ዳዊትን አሳደደ ።

፩ ሳሙ. ፳፪ ፣ ፮ - ፳፫ ፤ ፳፫ ፣ ፲፬ - ፳፱ ።

ሳኦል በዳዊት ማምለጥ ተቈጥቶ ባሪያዎ
ቹን በመውቀስ ፣ «ልጄ ከእሴይ ልጅ ጋር
ሲማማልና እንዲዶልትብኝ ሲያነሣሣው
ማንም ለእኔ አዝኖ አላስታወቀኝም» አላ
ቸው ። ኤዶማዊው ዶይቅም በኖብ ስላ
የው ነገር ነገረው ። ሳኦልም እጅግ ተቈ



www.ethiopianorthodox.org

ጥቶ አቢሜሌክን ብቻ ሳይሆን ከነቤተሰቦቻቸው ሰማንያ አራት ካህናትን ጭምር አስገደለ ። ከአቢሜሌክ ልጆች አብያታር የተባለው ግን አምልጦ ወደ ዳዊት ሸሸ ። ዳዊትም ፡ «ነፍሴን የሚፈልግ የአንተን ነፍስ ይፈልጋልና በእኔ ዘንድ ተጠብቀህ ትኖራለህና አትፍራ» አለው ።

ዳዊትም በዚፍ ምድረ በዳ ባለው በተራራማው ሥፍራ ተቀመጠ ፤ ሳኦልም ሁል ጊዜ ይፈልገው ነበር ፡ እግዚአብሔር ግን በእጁ አሳልፎ አልሰጠውም ።

ዳዊትም በጥሻው ውስጥ ሳለ ዮናታን አገኘውና ፡ «አንተ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆናለህ ፡ እኔም ከአንተ በታች ሁለተኛ እሆናለሁ» ብሎ እጁን በእግዚአብሔር ካጸና በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

የዚፍ ሰዎችም ወደ ሳኦል መጥተው ፡ «ዳዊት በእኛ ዘንድ ተሸሽጎ የለምን ? አሁንም ንጉሥ ሆይ ፡ ነፍስህ እንደ ወደደች ውረድ ፤ እርሱን አሳልፈን ልንሰጥህ እኛ አለን» አሉት ። ሳኦልም እነርሱን አመስግኖ ከራሱ ሰዎች ጋር ሄደ ፤ ዳዊትንም በምድረ በዳ አሳደደው ። ሳኦልም በአንድ ተራራ ጐን ሲሄድ ፡ ዳዊትና ሰዎቹም በዚያው ተራራ በሌላ ጐን ይሄዱ ነበር ። ሳኦልና ሰዎቹም ዳዊትንና ሰዎቹን ለመያዝ ሲከብብዋቸው መልእክተኛ ወደ ሳኦል ደርሶ ፡ «ፍልስጥኤማውያን አገሩን ወርረውታልና ፈጥነህ ና» አለው ። ሳኦልም ዳዊትን ማሳደድ ትቶ ተመለሰ ። የዚያም ሥፍራ ስም የማምለጥ ዓለት ተባለ ።

፲ ፤ ዳዊት የሳኦልን ነፍስ አከበረ ።

፩ ሳሙ. ፳፮ ፡ ፩ - ፳፯ ፡ ፯ ፤ ፲፬ ፡ ፱ ።

የዚፍ ሰዎችም ሁለተኛ ወደ ሳኦል መጥተው ዳዊት ዳግመኛ እንደ ተሸሸገ ገለጡለት ። ሳኦልም ሦስት ሺህ ሰዎች አስከትሎ ሄደ ፤ በዚፍም ምድረ በዳ ሠፈረ ። ዳዊትም ሰላዮችን ልኮ ሳኦል የሠፈረበትን ሥፍራ በተረዳ ጊዜ ፡ አቢሳ የተባለውን የእኅቱን የጽሩያን ልጅ ይዞ በሌሊት ወደ ሠፈሩ ገባና በጭፍሮቹ መካከል ወደ ተኛው ወደ ሳኦል መጣ ፤ የሳኦልም ጦር በራስጌው ተተክሎ ነበር ።

አቢሳም ዳዊትን ፡ «ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል ፤ አሁንም ከምድር ጋር በጦር ላጣብቀው» አለው ። ዳዊትም አቢሳን ፡ «እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንጹሕ አይሆንምና አትግደለው ፤ ነገር ግን በራሱ አጠገብ ያለውን ጦርና የውኃውን መንቀል ያዝና እንሂድ» አለው ። ማንም ሳያይ ሳይሰማም ያንን ይዘው ሄዱ ፤ ከባድ የሆነ እንቅልፍ ከእግዚአብሔር ወድቆባቸው ነበርና የነቃ አልነበረም ።

ዳዊትም ከሠፈሩ ፊት ለፊት በሚገኘው ተራራ ላይ ቆሞ የሳኦል የአጎቱ ልጅና የሠራዊቱ አለቃ የሆነውን አብኔርን በመጥራት ፡ «አብኔር ሆይ ፡ አንተ ጐልማሳ አይደለህምን ? ጌታህን ንጉሡን ለመግደል አንድ ሰው ገብቶ ነበርና ጌታህን ንጉሡን የማትጠብቅ ስለምን ነው ? የንጉሡ ጦርና የውኃው መንቀል ዬት እንደሆነ ተመልከት» አለው ።

ሳኦልም ፡ «ልጄ ዳዊት ሆይ ፡ ይህ ድምፅህ ነውን ? » አለው ። ዳዊትም ፡ «ጌታዬ ንጉሥ ሆይ ፡ ድምፄ ነው ። ጌታዬ ባሪያውን ስለምን ያሳድዳል ? ምንስ ክፋት ተገኘብኝ ?» አለው ። ሳኦልም ፡ «በድያለሁ ልጄ ሆይ ዳዊት ፡ ዛሬ ነፍሴ በዓይንህ ፊት ከብራለችና ተመለስ ፤ እነሆ ስንፍና አድርጌአለሁ ፡ እጅግ ብዙም ስቻለሁ» አለ ። ዳዊትም መልሶ ፡ «የንጉሥ ጦር እነሆ ፤ ከብላቴኖችም አንድ ይምጣና ይውሰዳት ። ነፍስህም ዛሬ በዓይኔ ፊት እንደ ከበረች እንዲሁ ነፍሴ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ትከበር ፤ ከመከራም ሁሉ ያድነኝ» አለ ። ዳዊትም መንገዱን ሄደ ፤ ሳኦልም ወደ ሥፍራው ተመለሰ ።

ዳዊት ግን በልቡ ፡ አንድ ቀን በሳኦል እጅ እጠፋለሁ ፤ ወደ ፍልስጥኤም አገር ከመሸሽ በቀር የሚሻለኝ የለም ብሎ በማሰብ ከሰዎቹ ጋር ወደ ጌት ንጉሥ ሄደ ። የጌት ንጉሥ አንኩስም በደኅና ተቀብሎ ጺቅላግ በተባለች ከተማ እንዲኖር ፈቀደለት ።



* * *

ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ። ተወዳጆች ሆይ ፤ ራሳችሁ አትበቀሉ ፡ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ ፤ በቀል የእኔ ነው ፡ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና ።

ሮሜ ፲፪ ፡ ፲፯ - ፲፱ ።

እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም ፤
ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ ።

መዝ. ፴፫ (፴፬) ፡ ፬ ። *

* * *


ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሳኦል ይወደው የነበረውን ዳዊትን የጠላውና ያሳደደው በምን ምክንያት ነበረ ?
፪ ፤ በሳኦልና በልጁ በዮናታን መካከል ምን ልዩነት ይታያል ?
፫ ፤ ዳዊት ሳኦልን ለመግደል አለማሰቡን በምን አሳየ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ለኃይልህ እቀኛለሁ ፤
በምሕረትህም ማልዶ ደስ ይለኛል ፤
በመከራዬ ቀን መጠጊያዬና አምባዬ ሆነኸኛልና ።
ረዳት ሆይ ፡ ለአንተ ለአምላኬ እዘምራለሁ ፤
አንተ አምላኬ ፡ መጠጊያዬ ምሕረቴም ነህና ።

መዝ. ፶፰ (፶፱) ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። *

* የመዝሙሩን አርእስት ይመልከቱ ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፵፱ ።

# የዳዊት መንግሥት ።

፩ ሳሙ. ፳፰ ፡ ፫ - ፪ ሳሙ. ፱ ፡ ፲፫ ።

## የሳኦል ሞትና የዳዊት መንገሥ ።

፩ ሳሙ. ፳፰ ፡ ፫ - ፳፭ ፡ ፴፩ ፡ ፩ - ፪ ሳሙ. ፭ ፡ ፲ ፡ ፩ ዜና ፡ ፲ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ለስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ሊዋጉ ... ። ሳኦልም እግዚአብሔርን ቢጠይቅ ...ልስ ባላገኘ ጊዜ ኃጢአትን በኃጢአት ... ጨምሮ ሞቶ የነበረውን ሳሙኤልን ...ጠየቅ ፡ መናፍስትን ወደምትጠራ ... በድብቅ ሄደ ። ሳሙኤልም ፡ «እግዚ...ብሔር ከራቀህ ለምን ትጠይቀኛለህ ? ... አንተና ልጆችህ ከእኔ ጋር ትሆናላ...» አለው ። ሳኦልም እጅግ ፈራ ፡ በቁ... ሙሉም በምድር ላይ ወደቀ ።

... በማግሥቱም ሰልፍ ሆነ ፤ የእስራኤ...ም ሰዎች ከጠላት ሸሽተው በጊልቦዓ ...ራ ላይ ተወግተው ወደቁ ። ፍልስጥኤ...ውያንም ዮናታንንና ሁለት ወንድሞቹን ገደሉ ፤ ሳኦልም ተስፋ ቈርጦ በገዛ ሰይፉ ላይ ወደቀ ፡ ሞተም ።

በሦስተኛውም ቀን አንድ አማሌቃዊ ወደ ዳዊት መጥቶ ፡ «ሕዝቡ ከሰልፍ ሸሽተው ወደቁ ፤ ሳኦልና ዮናታን ደግሞ ሞተዋል» አለው ። የሚሸለምም መስሎት በገዛ እጁ ሳኦልን እንደ ገደለ ተናግሮ ከሳኦል የወሰደውን ዘውድ ለዳዊት ሰጠው ። ዳዊትና ሰዎቹም ልብሳቸውን ቀደው አለቀሱ ፤ ጾሙም ። በመሸም ጊዜ ዳዊት ወሬኛውን አማሌቃዊ ፡ «እግዚአብሔር የቀባውን ለመግደል ለምን አልፈራህም ? » ብሎ አስገደለው ። ዳዊትም ስለ ሳኦልና ስለ ዮናታን ይህን የኀዘን ቅኔ ተቀኘ ፦

« የእስራኤል ክብር በኮረብቶች ላይ ተወግቶ
ሞተ ፤
ኃያላን እንዴት ወደቁ ! . . . .
ሳኦልና ዮናታን የተዋደዱና የተስማሙ ነበሩ ፤
በሕይወታቸውና በሞታቸው አልተለያዩም ። . . .
ወንድሜ ዮናታን ሆይ ፡ እኔ ስለ አንተ እጨ
ነቃለሁ ፤
በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበረ ፤
ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበረ ።
ኃያላን እንዴት ወደቁ !
የሰልፍም ዕቃ እንዴት ጠፋ ! »

ከዚህም በኋላ ዳዊት በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ኬብሮን ወጣ ፤ የይሁዳም ሰዎች መጥተው በይሁዳ ላይ እንዲነግሥ ቀቡት ። የሳኦል ሠራዊት አለቃ አብኔርም የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን ወደ መሃናይም ወስዶ በቀሩት የእስራኤል ነገዶች ላይ አነገሠው ። በሳኦል ቤትና በዳዊት ቤት መካከል ብዙ ዘመን ጦርነት ሆነ ፤ የዳዊትም ቤት እየበረታ ፡ የሳኦል ቤት ግን እየደከመ የሚሄድ ሆነ ። ኢያቡስቴም ከሞተ በኋላ የእስራኤል ነገድ ሁሉ ወደ ኬብሮን መጥተው በላያቸው እንዲነግሥ ዳዊትን ቀቡት ።

ንጉሡና ሰዎቹም በአገሩ ውስጥ ከተቀመጡት ከኢያቡሳውያን እጅ ኢየሩሳሌምንና አምባዪቱን ጽዮንን ያዙ ። ዳዊትም ጽዮንን የዳዊት ከተማ ብሎ ጠራት ፤ ዙሪያዋንም ቀጠራት ። ዳዊትም እየበረታ ሄደ ፤ የሠራዊትም አምላክ ከእርሱ ጋር ነበረ ። ዳዊትም በኬብሮን መንገሥ በጀመረ ጊዜ ሠላሳ ዓመት ሆኖት ነበር ፤ በኬብሮንም ሰባት ዓመት ከመንፈቅ ፡ በኢየሩሳሌምም ሠላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ ።

## ፪ ፡ ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ጽዮን አገባ ።

፪ ሳሙ. ፮ ፡ ፩ - ፲፱ ፡ ፩ ዜና. ፲፫ ፡ ፩ - ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፩ - ፲፯ ፡ ፫ ፡ ዘኍ. ፯ ፡ ፱ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ።

ዳዊት ሠላሳ ሺህ ሰው ሰብስቦ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ጽዮን ሊያወጣ ሄደ ። ነገር ግን እንደ ሙሴ ትእዛዝ ሳይሆን ፡ ማለት ሌዋውያን በትከሻቸው ላይ ሳይሸከሙአት ፡ ፍልስጥኤማውያን አድርገው እንደ ነበር በበሬዎች በሚጐተት በአዲስ ሰረገላ ላይ ጫኑአት ። የአሚናዳብ ልጆችም ዖዛና አሒዮ አዲሱን ሰረገላ ይነዱ ነበር ። ዳዊትና ሕዝቡም በቅኔና በበገና ፡ በከበሮና በጽናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ያሸበሽቡ ነበር ።

ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ፋነኑ ፤ ዖዛም እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ ፤ ስለ ድፍረቱም ተቀሥፎ ወዲያው ሞተ ። ዳዊትም አዘነ ፤ የእግዚአብሔርንም ታቦት ቅርብ በሆነ በአቢዳራ ቤት እስከ ሦስት ወር ድረስ አቈያት ። ከዚያ በኋላ ግን በሌዋውያን ትከሻ አሸክሞ እርሱና የእስራኤል ቤት ሁሉ በሆታና በሽብሸባ ፡ ቀንደ መለከትንም በመንፋት ወደ ጽዮን አመጧት ። ዳዊት ራሱም በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት እያሸበሸበ በጽዮን ወደ ተከለላት ድንኳን አገቡአት ። ዳዊትም መሥዋዕትን አሳረገ ፡ ሕዝቡንም በእግዚአብሔር ስም መርቆ ለእያንዳንዱ እንጀራና የሥጋ ቍራጭ የዘቢብ ጥፍጥፍም አከፋፈለ ።

## ፫ ፡ ዳዊት ቤተ መቅደስን ሊሠራ ወደደ ።

፪ ሳሙ. ፯ ፡ ፩ - ፳፱ ፡ ፩ ዜና. ፲፯ ፡ ፩ - ፳፯ ።

ንጉሡም ነቢዩ ናታንን ፡ «እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ ፡ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጃች ውስጥ እንደ ተቀመጠች እይ» አለው ። ናታንም ፡ ንጉሡ ቤተ መቅደስን ለመሥራት ማሰቡን አስተውሎ ፡ «በልብህ ያለውን ሁሉ አድርግ» አለው ።

በዚያ ሌሊት ግን እግዚአብሔር ናታንን ፡ «ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ ትለዋለህ ፦ አንተ ቤት አትሠራልኝም ፤ መንጋውን ስትከተል በሕዝቤ ላይ አለቃ እንድ



www.ethiopianorthodox.org

ትሆን ወሰድሁህ ፤ በምድርም ላይ እንዳሉ እንደ ታላላቆቹ ስም ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ ፤ ከጠላቶችህም አሳርፍሃለሁ ። እግዚአብሔርም ደግሞ ፦ እኔ ቤት እሠራልሃለሁ ብሎ ይነግርሃል ። ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ዘርህን አስነሣለሁ ፤ እርሱም ለስሜ ቤት ይሠራል ። ክፉም ቢያደርግ ቀጥቼ እገሥጸዋለሁ ፤ ምሕረቴን ግን ከሳኦል እንዳራቅሁ ከእርሱ አላርቅም ። ቤትህና ዙፋንህም በፊቴ ለዘላለም ይጸናል» አለው ። ዳዊትም ይህን የተስፋ ቃል በሰማ ጊዜ ፤ «አቤቱ አምላክ ሆይ ፤ ለባሪያህና ለቤቱ የተናገርኸውን ለዘላለም አጽናው ፤ እንደ ተናገርህም አድርግ» ብሎ አመሰገነ ።

## ፬ ፤ ዳዊት ለዮናታን የማለውን አሰበ ።

፪ ሳሙ. ፱ ፣ ፩ - ፲፫ ፤ ፱ ፣ ፩ ።

ዳዊት በሄደበት ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ድል ይሰጠው ነበርና በዙሪያው ያሉትን አገሮች አስገብሮ ታላቅ ስም በማግኘት ዝነኛ ንጉሥ ሆነ ።

ዳዊትም ፤ «ስለ ዮናታን የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳደርግለት ከሳኦል ቤት አንድ ሰው ቀርቶአልን ? » አለ ። ከሳኦል ቤት የነበረ ሲባ የተባለ ባሪያም ተጠርቶ ዳዊትን ፤ «እግሩ ሽባ የሆነ አንድ የዮናታን ልጅ አለ» አለው ። ንጉሡም ልኮ ሜምፊቦስቴ የተባለውን የዮናታን ልጅ አስመጥቶ ፤ «ስለ አባትህ ቸርነት አደርግልሃለሁና አትፍራ ፤ የአባትህንም የሳኦልን መሬት ሁሉ እመልስልሃለሁ ፤ አንተም ሁል ጊዜ ከገበታዬ እንጀራ ትበላለህ» አለው ። እርሱም ፤ «የሞተ ውሻ ወደምመስል ወደ እኔ የተመለከትህ እኔ ምንድርነኝ ? » ብሎ እጅ ነሣ ።

ንጉሡም ሲባን ፤ «ለሳኦል የነበረውን ሁሉ ለጌታህ ልጅ ሰጥቻለሁና እረስለት» አለው ። ሜምፊቦስቴም ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ከዳዊት ገበታ እየበላ በኢየሩሳሌም ተቀመጠ ፤ ሁለት እግሩም ሽባ ነበረ ።

* * *

ጠላትህ ቢወድቅ ደስ አይበልህ ፤
በመሰናከሉም ልብህ ሐሴት አያድርግ ።

ምሳሌ ፳፬ ፣ ፲፯ ።

እግዚአብሔር ፈራጅ ነው ፤
ይህን ያዋርዳል ፤ ይህንም ያከብራል ።

መዝ. ፸፬ (፸፭) ፣ ፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዳዊት መናገሻ ከተማው እንድትሆን ምን ሥፍራ መረጠ ?
፪ ፤ ቤተ መቅደስን ሊሠራ ሲወድ እግዚአብሔር ምን አለው ?
፫ ፤ ከዮናታን ጋር ያደረገውን ኪዳን ሲያስብ ምን አደረገ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፤ እንደ ቃልህ ፤
ለባሪያህ መልካም አደረግህ ።
በትእዛዛትህ ታምኛለሁና ፤
መልካምን ምክርና እውቀትን አስተምረኝ ።

መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፣ ፷፭ ፤ ፷፮ ።



www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፶ ።

# የዳዊት ኃጢአትና ንስሐ ።

፪ ሳሙ. ፲ - ፲፪ ።

## ፩ ፤ ዳዊትና ቤርሳቤህ ።

፪ ሳሙ. ፲ ፣ ፩ - ፲፩ ፣ ፭ ፤ ፳፫ ፣ ፴ ፣ ፴፱ ።

ናዖስ የተባለ የአሞን ንጉሥ በሞተ ጊዜ ዳዊት ፤ ናዖስ ያደረገለትን ወረታ በማሰብ በፈንታው የነገሠ ልጁን ሐኖንን ሊያጽናናው ሰዎቹን ላከ ። ሐኖንና የአሞን ሰዎች ግን ፤ አገሪቱን ለመሰለል እንጂ ለማጽናናት አልተላኩም ሲሉ የዳዊትን መልእክተኞች አሳፍረው በመስደዳቸው እስራኤልን አስቈጡ ፤ ሶርያውያንንና ሌሎችንም ቀጥረው ሊዋጉአቸው ተሰናዱ ። ዳዊትም እስራኤልን ሁሉ ሰብስቦ ወጣ ፤ ድልም በማድረግ የአሞንን ረዳቶች ሁሉ አባርሮ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ።

ነገሥታት ወደ ሰልፍ የሚወጡበት ጊዜ እንደገና ሲደርስም ዳዊት የአሞንን ከተማ ረባትን እንዲወጉአት የሠራዊቱን አለቃ ኢዮአብን ከነሠራዊቱ ልኮ እርሱ ራሱ በኢየሩሳሌም ቀረ ።

አንድ ዕለትም ወደ ማታ ጊዜ ከምንጣፉ ተነሣ ፤ በሰገነቱም ላይ ሲመላለስ ሳለ አንዲት ሴት ስትታጠብ አየ ፤ ሴቲቱም መልከ መልካም ነበረች ። ስለ እርስዋ ሲጠይቅም ፤ ከኃያላኖቹ የአንዱ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ መሆንዋን ተረዳ ። ልኮም አስመጣት ፤ ከእርስዋም ጋር ተኛ ፤ ወደ ቤትዋም ተመለሰች ። ሴቲቱም ፀነሰች ፤ ለዳዊትም ፤ አርግገፀአለሁ ብላ ላከችበት ።

## ፪ ፤ ዳዊትና ኦርዮ ።

፪ ሳሙ. ፲፩ ፣ ፮ - ፳፯ ።

ዳዊትም ፤ ኬጢያዊውን ኦርዮን ስደድልኝ ሲል ወደ ኢዮአብ ላከ ። ኦርዮም መጣ ፤ ዳዊትም የሕዝቡና የሰልፉ ሁኔታ እንዴት እንደ ሆነ ብሎ ጠይቆ ሲያበቃ ፤ «ወደ ቤትህ ሂድ» አለው ። ኦርዮ ግን በንጉሥ ቤት ደጅ ከባሪያዎች ጋር ተኛ ። ዳዊት ፤

ኦርዮ ወደ ቤቱ እንዳልሄደ በሰማ ጊዜ ፡
ከመንገድ የመጣህ አይደለምን ? ስለምን
ወደ ቤትህ አልወረድህም ?» አለው ። ኦር
ዮም ፡ «ጌታዬ ኢዮአብና የጌታዬ ባሪያ
ዎች በሜዳ ሠፍረዋል ፤ እኔ ልበላና
ልጠጣ ከሚስቴም ጋር ልተኛ እሄዳለ
ሁን ?» ብሎ መለሰለት ። ዳዊትም ፡ «ዛሬ
ደግሞ በዚህ ተቀመጥ» ብሎ በፊቱ እንዲ
በላና እንዲጠጣ ጠራው ፡ አሰከረውም ።
ኦርዮ ግን ከጌታው ባሪያዎች ጋር አደረ
እንጂ ወደ ቤቱ አልሄደም ።

በነጋም ጊዜ ዳዊት ለኢዮአብ ፡ «ኦር
ዮን ጽኑ ሰልፍ ባለበት ሥፍራ አቁሙት ፡
ተመትቶም እንዲሞት ከኋላው ሽሹ»
ብሎ ጻፈ ፤ ደብዳቤውንም በኦርዮ እጅ
ላከ ። ኢዮአብም እንደ ታዘዘ አደረገ ፤ ኦር
ዮም ተመትቶ ሞተ ።

የኦርዮም ሚስት ባልዋ እንደ ሞተ በሰ
ማች ጊዜ አለቀሰች ። የልቅሶዋም ወራት
ሲፈጸም ዳዊት ወደ ቤቱ አስመጣት ፤
ሚስትም ሆነችው ፡ ወንድ ልጅም ወለደ
ችለት ። አድራጎቱ ግን በእግዚአብሔር
ፊት ክፉ ነበረ ።

### ፱ ፡ ዳዊትና ናታን ።

፪ ሳሙ. ፲፪ ፡ ፩ - ፲፭ ።

እግዚአብሔር ነቢዩን ናታንን ወደ ዳዊት
ላከ ፤ ናታንም ዳዊትን ፡ «በአንድ ከተማ
አንዱ ባለጠጋ አንዱም ድኃ የሆኑ ሁለት
ሰዎች ነበሩ ። ባለጠጋውም ብዙ በግና
ላም ነበረው ። ለድኃው ግን አንዲት
ታናሽ በግ ብቻ ነበረችው ፤ እንጀራውንም
ትበላ ፡ ከዋንጫውም ትጠጣ ነበር ፡ እንደ
ልጁም ነበረች ። ወደ ባለጠጋውም እን
ግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ሳይወስድ
የዚያን ድኃ ሰው በግ ወስዶ ለመጣው እን
ግዳ አዘጋጀ» አለው ።

ዳዊትም በዚያ ሰው እጅግ ተቈጥቶ ፡
«ይህን ያደረገ ሰው ሞት ይገባዋል ፤ ባለ
መራራት ይህን አድርጎአልና ስለ አንዲቱ
በግ አራት ይመልስ» አለው ። ናታንም
ዳዊትን ፡ «ያ ሰው አንተ ነህ ። እግዚአብ
ሔር እንዲህ ይላል ፡ ንጉሥ ልትሆን ቀባ
ሁህ ፤ ያለህንም ሁሉ ሰጠሁህ ፤ ይህም
አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምር
ልህ ነበር ። ስለምን የእግዚአብሔርን ነገር
አቃለልህ ? ኦርዮን በሰይፍ መትተሃል
ሚስቱንም ሚስትህ እንድትሆን ወስደ
ሃል ። ስለዚህም ለዘላለም ከቤትህ ሰይፍ
አይርቅም» አለው ። ዳዊትም ናታንን ፡
«እግዚአብሔርን በድያለሁ » አለው ።
ናታንም ዳዊትን ፡ «እግዚአብሔር ደግሞ
ኃጢአትህን አርቆልሃል ፤ አትሞትም ።
ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላ
ቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃ
ልና የተወለደልህ ሕፃን ይሞታል» ብሎ
ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

### ፲ ፡ የሕፃኑ ሞት ።

፪ ሳሙ. ፲፪ ፡ ፲፭ - ፳፭ ።

እግዚአብሔርም የኦርዮ ሚስት ለዳዊት
የወለደችውን ሕፃን በሕመም መታው ።
ዳዊትም ስለ ሕፃኑ እግዚአብሔርን ለመነ፡
ጾመም ፤ በመሬትም ላይ ተኛ ። የቤቱ
ሽማግሌዎችም ከመሬት ሊያነሡት መጡ፡
እርሱ ግን እምቢ አለ ።

በሰባተኛውም ቀን ሕፃኑ ሞተ ። የዳዊ
ትም ባሪያዎች ፡ «ብንነግረው እንዴት
ይሆን ? በነፍሱ ክፉ ያደርጋል» ብለው
ሕፃኑ እንደ ሞተ ይነግሩት ዘንድ ፈሩ ።
ዳዊትም ባሪያዎቹ በሹክሹክታ ሲነጋገሩ
ባየ ጊዜ ፡ «ሕፃኑ ሞቶአልን ? » አላቸው ።
እነርሱም ፡ «ሞቶአል» አሉት ። ዳዊትም
ተነሥቶ ታጠበ ፡ ልብሱንም ለወጠ ፡ ወደ
እግዚአብሔርም ቤት ገብቶ ከሰገደ በኋላ
ወደ ቤቱ መጥቶ ፡ «እንጀራ አምጡልኝ»



አለ ፤ ተቀምጦም በላ ።

ባሪያዎቹም ፡ «ይህ ያደረግኸው ምን
ድር ነው ? በሕይወት ሳለ ስለ ሕፃኑ አለቀ
ስህ ፤ ከሞተ በኋላ ግን ተነሥተህ እንጀራ
በላህ» አሉት ። እርሱም ፡ «ሕፃኑ ሕያው
ሳለ ፡ እግዚአብሔር ይምርልኝ እንደሆነ
ማን ያውቃል ? ብዬ ጾምሁ ። አሁን ግን
ሞቶአል ፤ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን ?
እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ
እኔ አይመለስም» አለ ።

ዳዊትም ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽና
ናት ፤ እርስዋም ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች
ለት ፤ ስሙንም ሰሎሞን ብሎ ጠራው ።
እግዚአብሔርም ወደደው ፤ በናታንም ተና
ግሮ ስሙን ይዲድያ ብሎ ጠራው ። ይዲ
ድያ ማለትም እግዚአብሔር የወደደው
ማለት ነው ።

### ፲፩ ፡ የዳዊት የንስሐ ጸሎት ።

መዝ. ፶ (፶፩) ።

ስላደረገው ክፋት ናታን ከተናገረው በኋላ
ዳዊት እንዲህ ሲል ጸለየ ፡-

« አቤቱ ፤ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ ፤
እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን
ደምስስ ።
ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ፡
ከኃጢአቴም አንጻኝ ፤
እኔ መተላለፌን ዐውቃለሁና
ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና ። . . .
የማዳንህን ደስታ ስጠኝ ፡
በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ ።
ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተም
ራለሁ ፡
ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለ
ሳሉ ።»

* * *

እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ ።

፩ ቆሮ. ፲ ፡ ፲፪ ።

የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው ፤
የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር
አይንቅም ።

መዝ. ፶ (፶፩) ፡ ፲፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዳዊት ከዐሥርቱ ቃላት የትኛዎቹን ተላለፈ ?
፪ ፤ «እግዚአብሔርን በድያለሁ» ብሎ ንስሐ ሲገባ ምን መልስ ተሰ
ጠው ?
፫ ፤ ኃጢአቱ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚያስከትል ተነገረው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ፡
ከኃጢአቴም አንጻኝ ፤
እኔ መተላለፌን ዐውቃለሁና
ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና ።

መዝ. ፶ (፶፩) ፡ ፪ ፡ ፫ ።

www.ethiopianorthodox.org



ምዕራፍ ፺፩ ።

## …አቤሴሎም ዓመፅ ።

፪ ሳሙ. ፲፫ - ፲፱ ።

### …የዳዊት ልጆች ።

፪ ሳሙ. ፫ ፡ ፪ - ፭ ፤ ፭ ፡ ፲፫ - ፲፮ ፤ ፲፫ ፡ ፩ - ፲፱ ፡ ፴፫ ።

…ት ብዙ ሚስቶችና ልጆች ነበሩት ።
…ሞን በፊት ተወልደው በታሪካቸው
…ወቁት ፤ በኵር የሆነ አምኖን ፤ ሦስ
… ልጁም አቤሴሎም ፤ የተዋበች እኅ
… ትዕማር ፤ አዶንያስም ነበሩ ። አም
… ትዕማርን አስገድዶ ስላስነወራት
…ት ልጅ ወንድምዋን አቤሴሎምን
…ን ፤ አቤሴሎምም አስገድሎት ሸሸ ፤
… ሦስት ዓመትም ድረስ ከእናቱ አባት
…ር ንጉሥ ጋር ተቀመጠ ። ዳዊትም
…እርሱ እንዲሄድ እጅግ ናፈቀ ፤ ይሁን
… ወደ ኢየሩሳሌም ከመለሰው በኋላ
… እስከ ሁለት ዓመት ድረስ አልተ
…ውም ። ከዚያ በኋላ ግን ተቀብሎ
…ት ። በእስራኤል ሁሉ ዘንድ እንደ
…ሎም በውበቱ የተመሰገነ ሰው አል
…ም ።

### ፪ ፡ የአቤሴሎም ሴራ ።

፪ ሳሙ. ፲፭ ፡ ፩ - ፲፯ ፡ ፳፱ ።

ከዚህም በኋላ አቤሴሎም በአባቱ ላይ አሲሮ የእስራኤላውያንን ልብ ሰረቀ ። ሁሉን ካዘጋጀ በኋላም ወደ ኬብሮን ሄዶ ወደ እያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ፤ «የቀንደ መለከት ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ፦ አቤሴሎም ነገሠ በሉ» የሚሉ መልእክተኞችን ሰደደ ። ሴራውም ጽኑ ሆነ ፤ ሕዝቡም እየበዛለት ሄደ ። አቤሴሎምም ጠቢብ የሆነውን የአባቱን የዳዊትን አማካሪ ፤ የቤርሳቤህን አያት አኪጦፌልን አማካሪው እንዲሆን አስጠራው ።

ዳዊትም ፤ የእስራኤል ሰዎች ልብ ከአቤሴሎም ጋር እንደሆነ በሰማ ጊዜ ባሪያዎቹን ፤ «ተነሡ እንሽሽ ፤ መጥቶም እንዳይዘን ፤ ከተማዪቱንም በሰይፍ እንዳይመታ እንሂድ» አላቸው ። እነርሱም ፤ «እነሆ ጌታችን ንጉሡ የመረጠውን ሁሉ እኛ ባሪያዎችህ እሺ ብለን እናደርጋለን» አሉት ። ንጉሡም ከባሪያዎቹ ፤ ከሕዝቡና ከምርጥ ጭፍሮቹ ጋር ከኢየሩሳሌም ወጣ ። የጌት ሰው ኢታይም ከነሰዎቹ ዳዊትን ተከትሎ ሄደ ።

ካህናቱ ሳዶቅና አብያታርም ደግሞ የቃል ኪዳን ታቦት ከተሸከሙ ሌዋውያን ጋር ወጡ ። ንጉሡም ሳዶቅን ፤ «የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማ መልስ ፤ በእግዚአብሔር ዓይን ሞገስ አግኝቼ እንደሆንሁ ይመልሰኛል ፤ አልወድህም ቢለኝ ግን ፤ እነሆኝ ፤ ደስ የሚያሰኘውን ያድርግብኝ» አለው ።

ዳዊትም ተከናንቦ ያለ ጫማ እያለቀሰ የደብረ ዘይትን ዐቀበት ወጣ ፤ ሕዝቡም ተከናንበው እያለቀሱ ወጡ ። ዳዊትም አኪጦፌል ከአቤሴሎም ጋር ያሴረበት መሆኑን በሰማ ጊዜ ፤ «አቤቱ ፤ የአኪጦፌልን ምክር ስንፍና አድርገህ እንድትለውጥ እለምንሃለሁ» ብሎ ጸለየ ። ወደ ተራራውም ራስ በደረሰ ጊዜ የዳዊት ወዳጅ አርካዊው ኩሲ በራሱ ላይ ትቢያ ነስንሶ ሊገናኘው መጣ ። ዳዊትም ፤ «ወደ አቤሴሎም ሄደህ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ አድርግልኝ ፤ የምትሰማውንም ነገር ሁሉ ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር ንገራቸው ፤ በልጆቻቸውም እጅ ይላኩልኝ» ሲል ላከው ። ኩሲም ከአቤሴሎም ጋር ለመገናኘት ሄደ ።

አቤሴሎምም ወደ ኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ አኪጦፌልን ፤ «ምን እናድርግ ? » ሲል ጠየቀው ። አኪጦፌልም ፤ «ሳንዘገይ አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች መርጠን አባትህን እንከተል ፤ ደክሞ ሳለም እንውደቅበት» ብሎ መለሰለት ። የዳዊት ወዳጅ ኩሲ ግን ፤ «ግልገሎችዋ በተነጠቁ ጊዜ ድብ መራራ እንደ ሆነች አባትህና ሰዎቹ መራርና ኃያላን መሆናቸውን አስብ ፤ ምክሬንስ ከሰማህ ፤ ከእስራኤል ሁሉ ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሆነ ጭፍራ ይሰብሰብ፤ አንተም በመካከላቸው ሆነህ ወደ ሰልፍ ውጣ» በማለት እንዲዘገይ አደረገው ። አኪጦፌልም ምክሩ ተቀባይነት እንዳላገኘ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ሄደ ፤ በገዛ እጁም ታንቆ ሞተ ።

ዳዊትና ሰዎቹም ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ መሃናይም መጡ ። እስራኤልና አቤሴሎምም ዮርዳኖስን ተሻግረው በገለዓድ ምድር ሠፈሩ ።

### ፫ ፡ የአቤሴሎም ሞት ።

፪ ሳሙ. ፲፰ ፡ ፩ - ፲፱ ፡ ፲፭ ።

ዳዊትም ሰዎቹን ቈጠረ ፤ ለሰልፍም አዘጋጅቶ ፤ «እኔ ደግሞ ከእናንተ ጋር እወጣለሁ» አላቸው ። እነርሱ ግን ፤ «አንተ ለብቻህ ከእኛ ከአሥሩ ሺህ ይልቅ ትበልጣለህና አትወጣም ፤ በከተማ ተቀምጠህ ብትረዳን ይሻላል» አሉ ። ንጉሡም ፤ «መልካም የሚመስላችሁን አደርጋለሁ» አለ ። በበሩም አጠገብ ቆሞ ሰልፈኞቹን ባስወጣ ጊዜ ፤ የጦር አዛዦቹን ኢዮአብንና አቢሳን ኢታይንም ፤ «ለብላቴናው ለአቤሴሎም ስለ እኔ ራሩለት» ብሎ አዘዘ ፤ ሕዝቡም ሁሉ የንጉሡን ትእዛዝ ሰሙ ።

በዚያውም ቀን ታላቅ ውጊያ ሆነ ፤ የአቤሴሎም ተከታዮችም በዳዊት ሰዎች ተመቱ ፤ ብዙዎችም ሞቱ ። አቤሴሎምም በበቅሎ ተቀምጦ ብዙ ቅርንጫፍ ባለበት ዛፍ በታች ሲሄድ ራሱ በዛፉ ተያዘ ፤ በቅሎውም ሾልኮ ሲሄድ እርሱ ከዛፉ ተንጠልጥሎ ቀረ ። ሁኔታውንም ያየው ሰው ለኢዮአብ ነገረው ። ኢዮአብም ጦሮች ይዞ መጣ ፤ እርሱና ጋሻ ጃግሬዎቹም አቤሴሎምን ገደሉት ።

የሳዶቅ ልጅ አኪማአስም ኢዮአብን ፤ «እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንደ ተበቀለ



www.ethiopianorthodox.org

ለት ሮጬ ለንጉሥ የምሥራች ልንገር» አለ ። ኢዮአብም ፡ «የንጉሡ ልጅ ሞቶአልና ዛሬ አትናገርም» ብሎ ኵሲን ፡ «ሂድ ፤ ያየኸውንም ለንጉሡ ንገር» አለው ። ኵሲም እጅ ነሥቶ ከሮጠ በኋላ አኪማአስ ደግሞ ፡ «እኔስ ብሮጥ ምን ይገዳል ?» ብሎ ከኵሲ በኋላ ሮጠ ፡ ቀደመውም ።

ዳዊትም በሁለት የከተማ በር መካከል ተቀምጦ ነበር ፤ ዘበኛውም ወደ በሩ ሰገነት ወጣና ፡ «ብቻውን የሚሮጥ ሰው አያለሁ» ብሎ ለንጉሡ ጮኸ ። ቀጥሎም ፡ «ሌላ ሰው አየሁ ፤ የፊተኛውም ሩጫ የአኪማአስን ሩጫ ይመስላል» አለ ። ንጉሡም ፡ «እርሱ መልካም ሰው ነውና መልካም ወሬ ያመጣል» አለ ።

አኪማአስም ድምፁን ከፍ አድርጎ ንጉሡን ፡ «ሁሉ ደኅና ሆኖአል» አለ ። ንጉሡም ፡ «ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና ነውን ? » አለ ። አኪማአስም ፡ «ትልቅ ሽብር አይቻለሁ ፤ ምን እንደሆነ ግን አላውቅም» ብሎ መለሰለት ። በዚያን ጊዜም ኵሲ ከኋላው ደረሰ ። ንጉሡም ፡ «ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና ነውን ?» አለው ። ኵሲም ፡ «የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶች ሁሉ እንደዚያ ብላቴና ይሁኑ» ብሎ መለሰለት ። ንጉሡም እጅግ አዘነ ፤ በበሩም ላይ ወዳለው ቤት ወጥቶ አለቀሰ ፡ ሲሄድም ፡ «ልጄ አቤሴሎም ፤ ልጄ ፤ ልጄ አቤሴሎም ሆይ ፡ በአንተ ፈንታ ሞቼ ኖሮ ቢሆን ፡ ልጄ አቤሴሎም ፡ ልጄ ሆይ» ይል ነበር ።

ከዚህም በኋላ የእስራኤል ሰዎች ፡ «የቀባነው አቤሴሎም ሞቶአል ፤ እንግዲህ ንጉሡን ለመመለስ ስለምን ዝም ትላላችሁ?» ሲሉ የይሁዳ ሰዎች ዳዊትን ለመቀበል መጡ ፤ ወደ ኢየሩሳሌምም መለሱት ።

* * *

በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቻለሁና እስኪሟገትልኝ ድረስ ፡ ፍርድንም ለእኔ እስኪያደርግ ድረስ ቍጣውን እታገሣለሁ ። ወደ ብርሃን ያወጣኛል ፡ ጽድቁንም አያለሁ ።

ሚክ. ፯ ፡ ፱ ።

ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና ይነሣማል ፡
ኀጥኣን ግን በክፉ ላይ ይወድቃሉ ።

ምሳሌ ፳፬ ፡ ፲፮ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ዳዊት ከኢየሩሳሌም በሸሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን ታቦት ያወጣለትን ካህን ምን አለው ?

፪ ፡ ለአቤሴሎም ምክር የሰጡት ማንና ማን ነበሩ ? ምክራቸውስ ምን የሚል ነበረ ?

፫ ፡ ዳዊት የጦር አለቆቹን ስለ አቤሴሎም ምን አዝዞ ነበር ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ቅጣኝ ፤ ነገር ግን እንዳታዋርደኝ በመጠን ይሁን እንጂ በቍጣ አይሁን ። ኤር. ፲ ፡ ፳፬ ።





ምዕራፍ ፶፪ ።

## የሰሎሞን መንግሥት ።

፩ ነገ. ፩ - ፲ ።

፩ ፤ የሰሎሞን ጥበብና ታላቅነት ።

፩ ነገ. ፩ ፡ ፩ - ፱ ፡ ፴፬ ፤ ፪ ዜና. ፪ ፡ ፩ - ፲፫ ።

ዳዊት በሸመገለ ጊዜ ልጁ አዶንያስ ንጉሥ ሊሆን አሴረበት ፤ ዳዊት ግን ፡ «በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር እንደ ማልሁ ሰሎሞን ይነግሣል» ብሎ ሰሎሞንን አነገሠ ። ዳዊትም ሞተ ፡ ተቀበረም ፡ ሰሎሞንም በአባቱ ዙፋን ተቀመጠ ፡ መንግሥቱም እጅግ ጸና ።

ሰሎሞንም የመገናኛ ድንኳን ወደ ነበረበት ወደ ገባዖን ሄዶ በነሐስ መሠዊያው ላይ ብዙ መሥዋዕትን አቀረበ ። ሌሊትም በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ተገለጠለትና ፡ «ምን እንድሰጥህ ለምነኝ» አለው ። ሰሎሞንም ፡ «አቤቱ አምላክ ሆይ ፣ እኔ ባሪያህ መውጫዬንና መግቢያየን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ሆኜ ሊቈጠር በማይቻል በታላቅ ሕዝብህ መካከል ነኝ ። ስለዚህ በሕዝብህ ላይ መፍረድ እንዲችል መልካሙንና ክፉውንም እንዲለይ ለባሪያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው» ብሎ ለመነ ። እግዚአብሔርም መልሶ ፡ «ፍርድን እንድትለይ ማስተዋልን ለመንህ እንጂ ታላቅነትን ለራስህ አልለመንህምና እንደ ቃልህ አድርጌልሃለሁ ። ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ፡ ከአንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ ። ደግሞም ያልለመንኸውን ባለጠግነትንና ክብርን ሰጥቼሃለሁ ። አባትህ ዳዊት በመንገዴ እንደ ሄደ የሄድህም እንደሆነ ዕድሜህን አረዝመዋለሁ» አለው ። ሰሎሞንም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ። በቃል ኪዳን ታቦት ፊት ቆሞም መሥዋዕትን አቀረበ ፤ ለባሪያዎቹም ሁሉ ግብዣ አደረገ ።

በዚያን ጊዜም ሁለት ጋለሞቶች ወደ ንጉሡ ቀረቡ ። አንደኛዪቱም ፣ «ጌታዬ ሆይ ፣ ይህች ሴት በሌሊት በሕፃንዋ ላይ ስለ ተኛችበት ሙቶ አገኘችው ። እንቅልፍም ጥሎኝ ሳለ የሞተ ሕፃንዋን በእኔ



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ አድርጋ የእኔን ሕፃን ወሰደች ።
ልጄን አጠባ ዘንድ ስነሣም ፣ እነሆ ሞቶ
ል ፤ በብርሃን ሳየው ግን የወለድሁት
ልጄ አልነበረም» አለችው ። ሁለተኛዪቱ
ን ፡ «አንቺ እንደምትዪው አይደለም ፡
ደኅነኛው የእኔ ነው» አለች ።

ንጉሡም ፡ «ሰይፍ አምጡልኝ ፡ ደኅነ
ውንም ሕፃን ከሁለት ክፈሉና ግማሽ
ግማሽ አካፍሉአቸው» አለ ። የደኅነኛው
ናትም ስለ ልጅዋ ተቸግራ ፣ «ጌታዩ
ይ ፡ ለእርስዋ ይሰጥ እንጂ አይገደል»
ለች ። ሌላዪቱ ግን ፣ «ይከፈል እንጂ
ኔም ለአንቺም አይሁን» አለች ። ንጉ
ም ለሕፃኑ የራራችውን ተመልክቶ ፣
ይህችኛዪቱ እናቱ ናትና ደኅነኛውን
ፃን ስጡአት» አለ ። ይህም ፍርድ በእስ
ኤል ሁሉ ተሰማ ፤ ሕዝቡም የእግዚአብ
ር ጥበብ እንደ ነበረበት አይተው ን
ን ፈሩ ። ሰሎሞንም ከኤፍራጥስ ጀምሮ
ከ ግብፅ ዳርቻ ድረስ በመንግሥታት
ላይ ነገሠ ። ስለ ጥበቡም የሰሙ ነገ
ታት ወደ እርሱ ይመጡ ነበር ። ሰሎሞ
ሦስት ሺህ ምሳሌዎች ተናገረ ፡ መኃ
ም ሺህ አምስት ነበረ ።

ሰሎሞን ቤተ መቅደስን አሠራ ።

፩ ነገ. ፭ ፣ ፩-፰ ፣ ፳፮ ፤ ፪ ዜና ፪ ፣ ፩-፯ ፣ ፲ ።

ሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤት ለመሥ
አሰቦ ፣ የአባቱ ወዳጅ ወደ ነበረው
ጢሮስ ንጉሥ ወደ ኪራም ሲልክ ፣
ግዚአብሔር ለአባቴ ለዳዊት ፡ በአ
ፈንታ በዙፋንህ ላይ የማስቀምጠው
ህ ለስሜ ቤት ይሠራል ብሎ እንደ ነገ
፣ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም ቤት
ሥራት አስቤአለሁ ። አሁንም ፣ የም
ው ቤት እጅግ ታላቅና ድንቅ ይሆና
በዙ የዝግባና የጥድ እንጨት ፣ ብልሃ
ችንም ሠራተኞች ላክልኝ» አለው ።

ኪራምም የፈለገውን ሁሉ አደረገለት ። ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ቤት መሠረት የሚሆኑትን ምርጥ ምርጥ የሆኑ ድንጋዮችን አስጠረበ ።

በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ሰሎሞን ፣ አባቱ ዳዊት ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበለው ምሳሌ ፣ አዘጋጅቶ ለትም በነበረው ሥፍራ በሞሪያ ተራራ የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመረ ። በሰባት ዓመትም ውስጥ ሠራው ። አባቱም ዳዊት የቀደሰውን የብርና የወርቅ ዕቃ ሁሉ አገባ ። ሰሎሞንም ቤቱን በወርቅ አስለብጦ በዕንቍ አስጌጠው ። በመቅደስም ውስጥ የሚቆሙትን የወርቅ መሠዊያንና የወርቅ ገበታን ፣ አሥር የወርቅ መቅረዞችንም አሠራ ። በአደባባዩም የሚቆመውን አንድ ታላቅ የነሐስ መሠዊያን ፣ የነሐስ ኵሬንና አሥር የነሐስ መታጠቢያ ሰኖችንም አሠራ ። ስለ ቤተ መቅደሱ አሠራርና ውበት መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ያስረዳል ።

ሰሎሞንም የቃል ኪዳኑን ታቦት ከጽዮን አስመጣ ፤ ካህናቱም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አደረጉት ። ከመቅደስም በወጡ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ሞላው ። ሰሎሞንም ከሕዝቡ ፊት ቆሞ ፤ «በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን ? እነሆ ፡ ሰማይና ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ፡ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ ? ነገር ግን አቤቱ ፣ ባሪያህና ሕዝብህ ወደዚህ ሥፍራ የሚጸልዩትን ልመና ስማ ፤ በማደሪያህ በሰማይ ስማ ፤ ሰምተህም ይቅር በል» ብሎ ጸለየ ። ሕዝቡንም ባረከ ፡ መሥዋዕትንም ሠውቶ የእግዚአብሔርን ቤት ቀደሰ ። እስራኤልም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ቀን በዓል አደረጉ ።



፫ ፡ የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት መጣች ።

፩ ነገ. ፲ ፣ ፩-፲፫ ፣ ፳፫ ፣ ፳፱ ፣
፱ ፣ ፳፭ ፤ ፪ ዜና ፱ ፣ ፩-፲፪ ።

የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ ተጓዘች ። በግመሎችም ላይ ሽቱና ወርቅ የከበረም ዕንቍ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ገባች ። ወደ ሰሎሞንም በደረሰች ጊዜ በልብዋ ያለውን ሁሉ አጫወተችው ። ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ ፈታላት ። የሳባም ንግሥት ጥበቡንና ክብሩን ባየች ጊዜ አደነቀች ፡ ነፍስም አልቀረላትም ፤ እርስዋም ፣ «በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው ። እኔም መጥቼ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበር ፤ እነሆም ፡ እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር ። በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ሰዎችህ ምስጉኖች ናቸው ፤ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን» ብላ እጅግ ብዙ ወርቅና ሽቱ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው ፤ እርስዋ እንደ ሰጠችው ያለ የሽቱ ብዛትም ከዚያ ወዲያ አልመጣም ።

ንጉሡም ሰሎሞን በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ ፣ የወደደችውን ሁሉ ፣ ከእርሱም የለመነችውን ሁሉ ጨመረላት ። እርስዋም ተመልሳ ከባሪያዎችዋ ጋር ወደ ምድርዋ ሄደች ።

ሰሎሞንም በባለጠግነትና በጥበብ ከምድር ነገሥታት ሁሉ በለጠ ። በዘመኑም ሁሉ እስራኤል ሁሉ እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ተዘልሎ ይቀመጥ ነበር ። ምድርም ሁሉ ጥበቡን ይሰማ ዘንድ የሰሎሞንን ፊት ይመኝ ነበር ።

* * *

ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል !
ማስተዋልንም ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው ።

ምሳሌ ፲፮ ፣ ፲፮ ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፤
ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው ። ምሳሌ ፱ ፣ ፲ ።

* * *

ጥያቄ ፡ ፩ ፡ ሰሎሞን ከእግዚአብሔር ምን ለመነ ?
፪ ፡ ቤተ መቅደስን ካሠራ በኋላስ ምን ብሎ ጸለየ ?
፫ ፡ ለሳባ ንግሥትስ ምን ሰጣት ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ለባሪያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው ።

፩ ነገ. ፫ ፣ ፱ ።



www.ethiopianorthodox.org